አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ  መርሐ ግብር

# የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና


በ

ሠመረ ተስፋጋብር



መስከረም 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒትስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ  መርሐ ግብር

# የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና

በ

ሠመረ ተስፋጋብር

በአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

አማካሪ

አየለ ፍቅሬ (ዶ.ር)

መስከረም 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒትስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና

በ

ሠመረ ተስፋጋብር

መስከረም 2010 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ---------------------------------- | ---------------------------------- |

| የፈታኝ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ---------------------------------- | ---------------------------------- |
| ------------------------------------ | ---------------------------------- |

# ምስጋና

በመጀመርያ ደረጃ ጥናቱን ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ፅሑፌን በተደጋጋሚ በማረም እና ተስተካክሎ እንዲቀርብ ገንቢ አስተያየትና ምክራቸውን ላካፈሉኝ አማካሪ ዶ.ር አየለ ፍቅሬ ከልብ አመሰግናለሁኝ፡፡

የምርምር ጽሑፌን አንብበው ክፍተቶቹን ነቅሰው በማውጣት፣ የሚነበቡ ተጨማሪ ቴክስቶችን በመስጠት እና በመጠቆም ይህንን ጥናት በአዲስ መልኩ እንድሰራው እና የበለጠ እንድማርበት ዕድል ለፈጠሩልኝ መምህሬ አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)ን ለቀና ትብብራቸው እና አባታዊ ምክራቸው እጅግ በጣም አመሰግናለሁ!!

ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በመስክ ተገኝቼ በምሰበስብበት ወቅት ከስራ እና ከስብሰባ የተረፋቸውን ጊዜ በመስጠት፣ ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ ከመረጃ አቀባዮች ጋር በማስተዋወቅ እና በማስተርጎም ሌት ተቀን ከጎኔ ሳይለዩ ቀና ትብብር ያደረጉልኝን የታሕታይ አድያቦ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሐላፊ እንዲሁም የኩናማ ብሔረሰብ ተወካይ የሆኑትን አቶ ብርሃነ ኬኞ ምን ብዬ እንደማመሰግናቸው አላውቅም እና እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

ከመስክ የሰበሰብኩትን የኩናምኛ መረጃ ወደ ፅሑፍ በመቀየር፣ከዚያም ወደ ትግርኛ በመተርጎም እና ኮምፒውተር ላይ ያስፈርኩትን ፅሑፍ በማረም መልካም ውለታ ለዋሉልኝ የኩናማ ብሔረሰብ ተወላጆች መምህር አበዶም ገብረዮሐንስ፣ መምህር አሽብር ጃምቦ እና መምህርት አስመረት ሰሎሞን ከልብ አመሰግናለሁኝ፡፡

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ላይ ታች በምልበት ወቅት ስለኩናማ ብሔረሰብ የሚያውቁትን በማካፈል እና መፃሕፍት በማዋስ ለተባበሩኝ አቶ ሃፍታይ ገብረእግዚአብሔር እና አቶ ተኽላይ ጉዑሽ፤ እንዲሁም የሚችሉትን ሁሉ በማድረግ ድጋፋቸውን ላልተለየኝ አቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ፣ አቶ ሃይለ ገዛኢ እና አቶ ንጉሰ ሊላይ ከልብ አመሰግናለሁ፤ ሁሌም አከብራችዋለሁኝ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ላይ ሲሆን፤ ተረቶችን በመሰብሰብ እና በመመደብ የይዘት ትንተና አካሂዷል፡፡ ዓላማውም በኩናማ ብሔረሰብ የሚተረቱ ተረቶችን በመሰብሰብ ምደባ ማካሄድ እና የይዘት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ ተረቶቹ የተሰበሰቡት ከብሔረሰቡ መረጃ አቀባዮች ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይት ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ 78ቱ ተረቶች በአካባቢያዊ እና ምሁራን በተከተሉት መንገድ፤ እንዲሁም በይዘት የተመደቡ ሲሆን ከነዚህ መካከል 42 ተረቶች በማሳያነት ተተንትነዋል፡፡

በጥናቱ እንደተደረሰበት ተረቶቹ በአካባቢያዊ መጠሪያቸው “ሳማ ኬካ” እና “ኔላ ሳማ” ተብለው ይታወቃሉ፡፡ “ሳማ ኬካ” ተብለው የሚታወቁ ተረቶች በብሔረሰቡ ዘንድ እውነት ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ሲሆኑ፤ ስለብሔረሰቡ አመጣጥ፣ ብሔረሰቡ ስላካሄዳቸው ጦርነቶች፣ ስለ ቦታ እና ጎሳ ስያሜዎች፣ ስለ ኬት መጣና የጎሳ መሪዎች ጀግንነት የሚተርኩ ናቸው፡፡ “ኔላ ሳማ” በመባል የሚታወቁት ደግሞ ፈጠራዊ መሆናቸውን የሚታመንባቸው ሲሆኑ፤ አእምሮን እያዝናኑ ስነምግባር እና ብልሕነትን የሚያስተምሩ፣ የብሔረሰቡን ባህል፣ ልማድ እና አኗኗር ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ተረቶቹ ምሁራን ከተከተሉት የአመዳደብ ስልት አንፃር ሲታዩ ደግሞ ሌጀንድ፣ ገላጭና ፉቡላ ናቸው፡፡

ተረቶቹ በይዘታቸው በአምስት ዋና ዋና ምድቦች የተከፈሉ ሲሆን እነሱም የት መጣነትን የሚያሳዩ፣ ብልህነት፣ መጥፎ ባህርያትን፣ ጓደኝነት እና ጥንካሬን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ተረቶች ስነ ምግባራዊ ስብከቶች እና ማህበራዊ ህይወትን ለመምራት የሚበጁ የህይወት ፍልስፍናዎች የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ እኩይ የሚባሉ ተግባራትን በመኮነን እንዳይስፋፉ የሚገታባቸው፣ መልካም የሚባሉትን ደግሞ በመደገፍ ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማድረግ ታሪክ እና ባህል የሚተከልባቸው መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ የብሔረሰቡ ባህል የማስቀጠል እና የመተርጎም ጥቅም ያላቸው፣ የብሔሰቡ አባላት ለሚያነሱዋቸው ፍልስፍናዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ምላሽ የሚሰጥባቸው መሆናቸው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

በመጨረሻም ጥናቱ ተረቶቹ የብሔረሰቡን ታሪክ እና ባህል ለመረዳት ያላቸውን ሚና የላቀ ሆኖ በመገኘቱ ተጠናክረው የሚቀጥሉበት እና ተሰንደው የሚቀረሱበት ሁኔታ ቢመቻች ሲል እንደ ይሁንታ አቅርቧል፡፡

## ማውጫ


**አርእስት** **ገፅ**

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

ምዕራፍ አንድ ........ 1

1. መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.2. የጥናቱ ዓላማ ........ 2

1.3. የምርምር ጥያቄዎች ........ 3

1.4. የጥናቱ ፋይዳዎች ........ 3

1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 3

1.6. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 4

1.7. የጥናቱ ዘዴ ........ 5

1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ........ 5

1.7.2. የናሙና አመራረጥ ........ 6

1.7.3. የጥናቱ አተናተን ዘዴ ........ 6

1.8. የመስክ ስራ ........ 7

1.8.1. ከመስክ በፊት ........ 7

1.8.2. በመስክ ላይ ........ 8

1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 11

1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 11

1.9.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 12

ምዕራፍ ሁለት ........ 13

2.ክለሳ ድርሳን ........ 13

2.1.ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ........ 13

2.1.1.የተረት ምንነት ........ 13

2.1.2. የተረት ምደባ ........ 15

2.1.3. ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ........ 18

2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 21

2.2.1 በተረት ላይ የተደረጉ ቀደምት ማሚያ ጥናቶች ........ 21

2.2.2. በኩናማ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ቀደምት ፎክሎራዊ ጥናቶች ...... 26
ምዕራፍ ሶስት ........ 29
3. የኩናማ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራ ........ 29
3.1. የኩናማ ብሄረሰብ አመጣጥ ታሪክ........ 29
3.2. የኩናማ ብሄረሰብ ቋንቋ እና እምነት ........ 31
3.3. መልክዓ ምድር፣ የአየር ንብረት እና ስነ ህዝብ ........ 33
3.4. ኢኮኖሚ........ 35
3.5. የኩናማዎች የስም አወጣጥ ስርዓት ........ 35
ምዕራፍ አራት........ 39
4.የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና........ 39
4.1. የተረት ምደባ ........ 39
4.1.1 ከአካባቢያ ምደባ አንፃር ........ 39
ሀ. ሳማ ኬካ ........ 39
ለ. ኔላ ሳማ ........ 41
4.1.2. ምሁራን ከተከተሉት የምደባ ስልት አንፃር ........ 44
ሀ. ሌጀንድ ........ 44
ለ. ገላጭ ተረቶች ........ 45
ሐ. ፋቡላ ........ 46
4.2. የይዘት ትንተና........ 48
4.2.1. የት መጣንነት የሚያሳዩ ........ 49
4.2.2. ብልህነትን የሚመለከቱ ........ .51
4.2.3. መጥፎ ባህርያትን የሚመለከቱ ........ 54
4.2..4. ጓደኝነትን የሚመለከቱ ........ 58
4.2.5. ጥንካሬ እና ሙሉ ጤንነትን የሚመለከቱ ........ 60
ምዕራፍ አምስት ........ 63
5.ማጠቃለያና ይሁንታ........ 63
5.1. ማጠቃለያ ........ 63
5.2. ይሁንታዎች ........ 64
ዋቢ ጽሁፎች ........ 65
የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር........ 69

አባሪ 1. ከኩናምኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ተረቶች ............................. 1
አባሪ 2. በኩናምኛ ቋንቋ የተሰበሰቡ ተረቶች ..................................................... 53
አባሪ 3.  ለቃል አቀባዮች የቀረቡ የቃል ጥያቄዎች .......................................... 101
አባሪ 4. የቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ተርጓሚዎች ፎቶ ግራፎች .......................... 102

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ተረት የመተረት ጥበብ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ የፈጠራ ውጤት እንደሆነ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልፃሉ (Thompson, 1946 እና Fischer, 1963)። ይህን ሐሳብ በተረት ላይ ጥናት በማድረግ ቀዳሚ የሆነውን (Thompson, 1946:3) *"When we confine our view to our own world, we see that for at least three or four thousand years, and doubtless for ages before, the art of the story-teller has been cultivated in every society."* በማለት ገልፆታል። ተረት የሰው ልጅ የሚኖርበትን ዓለም፣ የራሱን ማንነትና አሉኝ የሚላቸውን ማህበራዊ እሴቶች ለመረዳት እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማለት የሚፈጥረው ከትውልድ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ የስነቃል ዘውግ ነው።

እንደ Thompson እና Leach አገላለፅ ተረቶች አለማቀፋዊ ባህሪ ያላቸው የስነ ቃል ዘውጎች ናቸው። የአተራረክ ስልቱ እና የሚተረክበትን አጋጣሚ እንደየ ባህሉ የሚለያይ ቢሆንም ተረት የሌለው ማሕበረሰብ የለም (Leach 1949፡ 409፤ Thompson, 1946:4)። በየተኛውም ማህበረሰብ ማለት ይቻላል ተረት ለመተረት እና ለመስማት የማይጓጓ ሰው አይኖርም። ተረት ከስነ ቃል ቅርፃች መካከል በዝርው ከሚቀርቡት መካከል የሚመደብ ሲሆን በውስጡም ለተዝናኖት ከሚቀርቡ ድራማዊ ባህርይ ካላቸው ተራ ተረቶች እስከ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች የሚስተናገዱበት ውስብስብ ሚቶሎጂያዊ ጉዳይ የሚያጠቃልል ነው (Fischer, 1963፡263)። ተረት በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊተረት ይችላል። ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማርና ለማዝናናት፣ የተጣሉትን ለማስታረቅ፣ ሀዘንተኞችን ለማጽናናት ወዘተ. እንደየዐውዱ አመቺነት ይተረታል።

ተረትን ከየአቅጣጫው በመሰብሰብ የማሳተም እና ትንተና የማድረግ ስራ ይበልጥ ትኩረት ያገኘው በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው (Thompson, 1946፤ Fischer, 1963)። የፎክሎር፣ የስነ ልቦና፣ የስነ ልሳን እንዲሁም የፖሎቲካ ምሁራን በተለያዩ የዓለማችን ስፍራዎች የሚተረቱ ተረቶች በመሰብሰብ ፋይዳቸውን፣ ቅርጻቸውን ተስተላልፎአቸውን… በተመለከተ ጥናት አድርገዋል።

በተረቶች ውስጥ የአንድ ማህበረሰብ ታሪክ፣ አኗኗር፣ የዓለም አመለካከት፣ የህይወት ፍልስፍና ወዘተ. ይንፀባረቃል። በዚህም ተረቶች በመሰብሰብ በንድፈ ሐሳብ ቃኝቶ ምደባ እና

የይዘት ትንተና ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህንን እንደመነሻነት በመያዝ ይህ ጥናት የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶችን በመሰብሰብ ምደባ እና የይዘት ትንተና ላይ ትኩረት አድርጎ የቀረበ ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኮርሶች በምማርበት ወቅት የኮርስ ማሚያ ወረቀቶችን ለመሥራት የተለያዩ የኤም.ኤ. እና የቢ.ኤ. መመረቂያ ጥናቶችን ቅኝት አድርጌ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ከሚገኙ በርካታ ብሔረሰቦች መካከል የተወሰኑት ፎክሎራቸው በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር አጥኚዎች ለመዳሰስ ተሞክሯዋል፡፡ ሆኖም የኩናማ ብሔረሰብ ባህል በተመለከተ ሃፍታይ (2003) እና ኒቆዲሞስ (1973) በስተቀር ሌላ የተደረገ ጥናት አላገኘሁም፡፡ ስለሆነም የዚህን ብሔረሰብ ባህል ያልተጠና በመሆኑ ለጥናት አነሳስቶኛል፡፡

በመጀመርያ ዲግሪ ተመርቄ እንደወጣሁ በላዕላይ አዲያቦ ወረዳ በመምህርነት ለሁለት ዓመታት ሠርቻለሁኝ፡፡ እዚያ በምኖርበት እና በማስተምርበት ወቅት ከአካባቢው ትንሽ ርቀት ላይ ስለሚገኘው የኩናማ ብሔረሰብ ባህል በተመለከተ ብዙ ነገር እሰማ ነበር፡፡ የሰርግ ሥርዓታቸው፣ ባህላዊ አስተዳደራቸው፣ ተረት እና ምሳሌያዊ አነጋገራቸው፣ የወሊድ ሥነ ሥርዓታቸው፣ የባህላዊ መድኃኒት እውቀታቸው … ካደግኩበት አካባቢ እና ባህል ለየት ያለ እና ትኩረት የሚስብ ነበር የሆነብኝ፡፡ በዚህም መሠረት ስለ ጥናት ርእስ እና አካባቢ ሳሰላስል የዚህ ብሔረሰብ ባህላዊ ሃብት ከሆኑት አንዱ ተረትን መረጥኩኝ፡፡ ተረትን በመሰብሰብ ለመመደብ እና የይዘት ትንተና ለማድረግ ተነሳሳሁኝ፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በትግራይ ክልል ከሚገኙ ሦስት ብሔረሰቦች መካከል አንዱ በሆነው በኩናማ ብሔረሰብ የሚተረቱ ተረቶች በመሰብሰብ መመደብ እና የይዘት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ

- ✓ ተረቶቹን በአካባቢያዊ ምደባ እና ምሁራን በተከተሉት የአከፋፈል ስልት መሰረት ለይቶ መግለጽ
- ✓ በተረቶቹ ውስጥ የተስተማሰሉ ዓበይት ሰብአዊ ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ በተመረጡ ተረቶች ምሳሌነት ተንትኖ ማሳየት
- ✓ ከተረቶቹ የይዘት ትንተና በመነሳት ወደፊት ምን ሊደረግ እንደሚገባ ማመላከት

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በአካባቢያዊ መለያቸው እና ከሚያነሱዋቸው ሰብአዊ ጣጣዎች አንጻር ምን ምን ይመስላሉ? በተረቶቹ ተስተማስለው የቀረቡ ጉዳዮችስ? እና የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በአሁኑ ጊዜ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ፋይዳዎች

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ ከዚህ የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡

- አንድ ህዝብ በየዘመናቱ ያካበተውን እውቀት እና የህይወት ገጠመኝ በስነ ቃሎቹ ይቀርሳል፡፡ ስለሆነም የተጠኚው ብሔረሰብ እምነት፣ ዝንባሌ እና ባህል በማወቅ መልኩ ያለውን የእውቀት ክፍተት ይሞላል፤
- የኩናማ ብሔረሰብ ቃላዊ ሃብት የሆኑት ተረቶች ከዚህ በፊት ያልተጠኑ በመሆናቸው ወደ አካዳሚ በማምጣት ለጥናትና ለምርምር እንዲውሉ ያደርጋል፡፡
- በኩናምኛ ቋንቋ ለሚዘጋጁ የመማርያ እና ማስተማርያ መጻህፍት ዝግጅት ለሚያደርጉ አካላት እንዲሁም በብሔረሰቡ ልማት እና እድገት ላይ ተሳትፎ ማድረግ ለሚፈልጉ አካላት /ተቋማት/ እንደ ግብአት ይሆናል፤
- ተረቶቹን ሰንዶ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ይጠቅማል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ኩናማ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ የሚገኝ ብሔረሰብ ነው፡፡ ይህ ጥናት ትኩረት ያደርገው በኢትዮጵያ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን እና ሰሜን ምዕራብ በታሕታይ አዲያቦ በሚገኙት የብሔረሰቡ አባላት ላይ ብቻ ነው፡፡ በተለይ (ሽምብሊና፣ መዳበ፣ ገዛ አዱራ፣ ገዛ መቐር፣ ዕርዲ ወያነ፣ ዒላ ኩናማ፣ ዓዲ ጎሹ እና አደባይ) በሚባሉ ቀበሌዎች የሚገኙ የኩናማ አባላት ሚተርቷቸው ተረቶች ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ነው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች የተመረጡት በኢላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ነው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች የመረጥኩበት ምክንያት ብዛት ያላቸው የብሔረሰቡ ኣባላት የሰፈሩባቸው እና ከድንበር የራቁ ስፍራዎች በመሆናቸው ለደህንነት የተመቹ ስለሆኑ ነው፡፡ ከርእሰ ጉዳይ አንጻር ደግሞ ይህ ጥናት የተረት ጥናት አካል በሆኑት የተረት ምደባ እና የይዘት ትንተና ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የመጀመርያው ምዕራፍ የጥናቱን አጠቃላይ ንድፍ ይይዛል፡፡ በውስጡም የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ፋይዳዎች፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን እና መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች፣ ከመስክ በፊት እና በመስክ ላይ የተከናወኑ ተግባራት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች የያዘ ነው፡፡

ምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳናት የቀረበበት ነው፡፡ ጥናቱን ለማከናወን የሚረዳ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ የቀረበበት ነው፤ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የተዳሰሱበት ነው፡፡ ምዕራፍ ሶስት ለጥናት የተመረጠውን የኩናማ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ በውስጡም ስለብሔረሰቡ አመጣጥ ታሪክ፣ ቋንቋና እምነት፣ መልከዓ ምድር፣ የአየር ንብረትና ስነ ህዝብ፣ ኢኮኖሚ እና የስም አወጣጥ ስርዓት የሚመለከቱ መረጃዎችን አካቷል፡፡

ምዕራፍ አራት ከመስክ የተሰበሰቡት ተረቶችን ምደባ፣ እንዲሁም የይዘት ትንተና ይዟል፡፡ ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች የቀረበበት ነው፡፡ በመጨረሻም ዋቢ መፃሕፍትና የተጠቀሱ ጥናታዊ ፅሑፎች ይገኙበታል፡፡

በአባሪ አንድ የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር፣ በአባሪ ሁለት የተሰበሰቡትን 78 ተረቶች በአማርኛ ትርጉማቸው፣ በአባሪ ሶስት ደግሞ በተተረቱበት ኩናምኛ ቋንቋ ቀርቧል፡፡ በአባሪ አራት ለቃል አቀባዮች የቀረቡ የቃል ጥያቄዎች፣ በአባሪ አምስት ደግሞ የቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ተርጓሚዎች ፎቶ ግራፎች ቀርቧል፡፡

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴ

### 1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የጥናቱ ዓላማዎች ለማሳካት እና የምርምር ጥያቄዎቹን ለመመለስ ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሚያለሁ፡፡ በካልአይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የታተሙ እና ያልታተሙ ጽሑፎች ከቤተ መጻሕፍት እና ከኢንተርኔት የሰበሰብኩ ሲሆን፤ እንዲሁም "አንድ አጥኚ ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት ስለሚያጠናው አካባቢ እና ህዝብ በቤተ መጻሕፍት ጥልቅ ንባብ ማድረግ አለበት" በማለት (Donald, 1972: 407) እንደሚመክሩት የኩናማ ብሔረሰብ ሚኖርበት አካባቢ፣ ስለ ህዝቡ ታሪክ፣ ስለ ባህላዊ አስተዳደር እና ሽምግልና ሥርዓት ወዘተ. የተጻፉ ጹሑፎች ተመልክቻለሁ፡፡ በቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ለዚህ ጥናት ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች ለመሰብሰብ በዋናነት ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ተጠቅሚያለሁ፡፡

በመስክ ላይ ተገኝቶ የሚደረግ የስነ ቃል አሰባሰብ ተግባር በሶስት መንገዶች ሊከወን እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ (Goldstien, 1964 እና ፈቃደ፣ 1991)፡፡ እነዚህ ዘዴዎች ተፈጥሮአዊ መቼት፣ አርቴፊሻል መቼት እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት ናቸው፡፡ እኔም ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ባደርግበት ወቅት ተረቶችን በተፈጥሮአዊ አውዳቸውን ሲተረቱ ካጋጠመኝ ለመሰብሰብ፣ ሳይመች ሲቀር ግን አርቴፊሻል መቼትን ተጠቅሜ ለመሰብሰብ አቅጄ ነበር የሄድኩት፡፡ ነገር ግን ተረት በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች እንደየአስላጊነቱ የሚተረት በመሆኑ በእያንዳንዱ አጋጣሚ ላይ ተገኝቶ የተረትን ክዋኔ ለመመልከት ሰፊ ጊዜ እና ገንዘብ ይጠይቃል፡፡ በአጋጣሚዎች ላይ ተገኝቶ የተረት ክዋኔን ለመመልከት ሲታቀድም ተረት መተረት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ ሳይተረትም ይቀራል፡፡ እነዚህ እና ሌሎች ጉዳዮችን ተረትን በተፈጥሮአዊ መቼትም ሆነ በቅንብር ተፈጥሮአዊ ለመሰብሰብ አዳጋች ያደርጉታል፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ደግሞ ተረቶቹን መመደብ እና ይዘታቸውን መተንተን በመሆኑ ፈቃደ (1991፣123) "በአርቴፊሻል መቼት ተመራማሪው አንድን ስነ ቃል ከዐውዱ ውጪ ማንኛውም አቀባይ በተገኘበት ጊዜና ቦታ ሊሰበስብ ይችላል" በማለት እንደገለጸው ተረቶቹ በአርቲፊሻል መቼት ነው የሰበሰብኩት፡፡

አርቴፊሻል መቼትን በመጠቀም ተረት በመተረት ችሎታቸው እና በአፈ ታሪክ እውቀታቸው ከታወቁ የብሔረሰቡ አባላት ጋር ጥልቅ ቃለ መጠይቅ በማካሄድ መረጃዎችን ተሰብስበዋል፡፡

ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ መረጃ አቀባዮቼ ተረት ሲተሩትልኝ እያዳመጥኩኝ እና “ኤ” በማለት እየተሳተፍኩ የምልከታ ዘዴን ተጠቅሜ ተረቶችን ሰብስቤያለሁ፡፡ ሌላው የተጠቀምኩት መረጃ የመሰብሰብያ ዘዴ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ባደረኩት ቃለ ምልልስ ግልፅ ያልሆኑልኝን መረጃዎች ለማጣራት እና ተጨማሪ ማብራርያ አልያም እርማት ለማግኘት በማሰብ ሁለት ሴቶች ያካተተ ስድስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት እንዲወያዩ አድርጌያለሁ፡፡ በዚህም የቡድኑ አባላት የነበሩኝን ጥያቄዎች በመመለስ እና እርስ በራሳቸው በመደማመጥ እና በመከራከር ትክክለኛ መረጃ እንድይዝ እገዛ አድርገውልኛል፡፡ እነዚህን ዘዴዎች ተጠቅሜ ማስታወሻ እየያዝኩ እና እየተከታተልኩ የመስክ ቆይታየን በፈቀደልኝ መጠን መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡

### 1.7.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ይህ ጥናት ኢላማ ተኮር (Purposive sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተከተለ ነው፡፡ ኢላማ ተኮር የተመረጠበት ምክንያት በጥናቱ ወሰን እንደተገለጸው በተጠቀሱ ቦታዎች በቂ መረጃ ሰጪዎችን ማግኘት ስለሚቻል ነው፡፡ አንድ የመስክ ተመራማሪ በቂ መረጃዎችን በምን ሁኔታ እና ከማን ማግኘት እንደሚችል አላማ ይዞ መውጣት እንዳለበት፣ (Purposive sampling) መጠቀም ደግሞ አላማውን ከግብ ለማድረስ እንደሚረዳው (Kumar, 1991: 62) ይገልጻል፡፡ በዚህ መሠረትም የኩናማ ብሔረሰብ በብዛት የሚገኙባቸው እና ለደህንነት አመቺ የሆኑትን ቀበሌዎች የመረጥኩ ሲሆን፤ የመረጃ ሰጪዎችን ናሙና አመራረጥ በተመለከተ እንዲሁ መረጃ በመስጠት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ይረዳሉ ብዬ ያመንኩባቸውን 31 ሰዎች በመምረጥ አሳትፌያለሁኝ፡፡ በማህበረሰቡ ተረት በመተረት የሚታወቁትና አፈ ታሪክ ያውቃሉ የተባሉትን ሰዎች በማፈላለግ 78 ተረቶች ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በዚህ ጥናት ጾታ በተመለከተ ከሁለቱንም ጾታዎች መረጃ ተሰብበዋል፡፡

### 1.7.3. የጥናቱ አተናተን ዘዴ

አንድ የፎክሎር ተመራማሪ በመስክ ተገኝቶ ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች ከሰበሰበ በኃላ ጥናቱን ለማስኬድ የሚበጅ የቴዎሪ ማእቀፍ መምረጥ ይኖርበታል፡፡ ምርጫውም ምክንያታዊ እና ቴክስቶቹን በሚገባ ለመተንተን የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡ የኔ ጥናት ትኩረት ያደረገው በቃላዊ የፎክሎር ዘውግ የሚመደበው ተረት ላይ በመሆኑ እንደ መታገዢያ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional Appraoch) ነው የተጠቀምኩት፡፡ ቆየት ብዬ በንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ስር ለማሳየት እንደምሞክረው ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ቃላዊ ሃብቶችን

ለመመርመር ከሚያስችሉ ዓበይት የፎክሎር ጽንሰ ሐሳቦች አንዱ ነው፡፡ ተረቶቹ ለብሔረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት እና ለመተንተን ቅርበት አለው ብዬ ስለማምን እንደ ዋና የመተንተኛ መሳርያ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

## 1.8. የመስክ ስራ

ይህ ክፍል ጥናቱን ለማካሄድ ከመስክ በፊትና በመስክ ላይ የተከናወኑ ተግባራት የቀረበበት ነው፡፡

### 1.8.1. ከመስክ በፊት

"የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና" በሚል ያቀረብኩትን የጥናት ርእስ በትምህርት ክፍሉ ተቀባይነት አግኝቶ እንድሰራበት ከተነገረኝ ቀን ጀምሮ ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት በቤተ መጻህፍት ውስጥ ከኔ የጥናት ርእስ ተዛማጅነት ያላቸውን ካልአይ የመረጃ ምንጮችን አንብቤ መረጃ ይዣለሁ፡፡ የጥናቴ ዓላማ ያሳካሉ ያልኩዋቸውን በጥናቱ ሂደት ይመለሳሉ ብዬ ያሰብኩዋቸውን የምርምር ጥያቄዎችን አዘጋጀሁ፡፡ ከዚያም በመስክ ተገኝቼ ለጥናቴ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን ተረቶች እንዴትና በምን ሁኔታ እንደምሰበስብ እቅድ አወጣሁ፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ ተረቶችን ለመሰብሰብ ያስችላሉ ያልኩዋቸው ጥያቄዎችን አዘጋጅቼ ለመረጃ አቀባዮቼ ዓላማዬን እንዴት ማስረዳት እንዳለብኝ እና በምን ሁኔታ ብቀርባቸው የተሻለ መረጃ ሊሰጡኝ እንደሚችሉም በማሰብ በቂ ዝግጅት አደረኩኝ፡፡

በመስክ ተገኝቼ መረጃ ለመሰብሰብ ያስቹልኛል ያልኩዋቸውን መረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመጠቀም በቪድዮ ከሜራ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በመቅረጸ ድምፅና በማስታወሻ ደብተር የመሳሰሉ መሳርያዎችን የታገዘ መረጃ ለመሰብሰብ ቅድመ ዝግጅት አደረኩ፡፡

የመስክ ቦታውን በተመለከተ ምንም እንኳ ከዚህ በፊት እስከ ሽራሮ ያለውን የማውቀው እና ሁኔታውን በተመለከተ የተወሰነ ግንዛቤ የነበረኝ ቢሆንም የአካባቢው ተወላጆች እና ከዚህ በፊት በኩናማ ብሔረሰብ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎችን አፈላልጌ በማነጋገር የማርፍበትን ቦታ፣ የትራንስፖርት አማራጭ፣ ጤና ጣብያ ያለበት አካባቢ፣ በቦታው ማድረግ ያለብኝ አንዳንድ ጥንቃቄዎች ወዘተ. በተመለከተ የተወሰነ ምስል በመያዝ የስነ ልቦና ዝግጅት አድርጌያለሁ፡፡ በመጨረሻም ሰኞ ጥር፣ 01/2009 ዓ.ም. ከትምህርት ክፍሉ የትብብር ደብዳቤ አፅፌያለሁ፡፡

### 1.8.2. በመስክ ላይ

ከአዲስ አበባ የኩናማ ብሔረሰብ ወደ ሚገኝበት ምዕራብ ትግራይ በቀጥታ ከመሄድ ይልቅ ወደ መቐለ በመሄድ የትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ድረስ በመሄድ ዓላማዬን አስረድቼ፣ እግረ መንገዴንም ስለኩናማ ብሄረሰብ ባህል በተመለከተ በቢሮው የተሰራ ነገር ይኖር እንደሆነ አጠያይቄ መሄድ ተገቢ ሆኖ ስለተሰማኝ ማክሰኞ ጥር 02/2009 ዓ.ም. ከጥዋቱ ሶስት ሰዓት ከአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ወደ መቐለ በአውሮፕላን ተጓዝኩኝ። መቐለ ደርሼ አረፍ ካልኩ በኃላ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ ወደ ትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሂጄ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በማሳየት የመጣሁበትን ዓላማ አስረዳሁኝ።

የኩናማ ብሔረሰብ ባህል ላይ መስራት የምፈልግ መሆኑን የሰሙት የቢሮው ሰራተኞች በደስታ ነበር የተቀበሉኝ። እነሱ በበኩላቸው "ተባበሩት" የሚል ደብዳቤ ፅፈው፣ ወደ ታሕታይ አድያቦ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ስልክ ደውለው አስተዋወቁኝ፤ እንዲሁም የአንዳንድ ያግዙሃል ብለው ያመኑባቸውን ሰዎችን አድራሻ እና ስልክ ቁጥር ሰጥተው ሰኙኝ።

ሐሙስ ጥር 04/2009 ዓ.ም. ከጥዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ከመቐለ አውቶቡስ ተራ በመነሳት ወደ ሽረ ተጓዝኩኝ። ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሲሆን ሽረ ደረሼ ምሳ በላሁኝና በሌላ ሚኒባስ ተሳፍሬ ወደ ሽራሮ ቀጠልኩኝ። ዓርብ ጥር 05/2009 ዓ.ም. ሽራሮ ከተማ ውስጥ ወደ ሚገኘው የታሕታይ አድያቦ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ፣ የትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆኔን የሚገልፁ መታወቂያዎችን በማሳየት አላማዬን አስረዳሁኝ። የእኔ መምጣት በቀን 02/05/2009 ዓ.ም. ከመቐለ ተደውሎ ተነግሮዋቸው ስለነበር በመልካም ገጽታ ተቀብለው አስተናገዱኝ።

ከቅዳሜ ጥር 06/2009 ዓ.ም እስከ ረቡዕ ጥር 10/2009 ዓ.ም. ባሉት አራት ቀናት አካባቢዎችን በመጎብኘት፣ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም ከመንግስትና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ ያገኘሁዋቸውን ሰነዶችና መጽሔቶች በማገላበጥ፣ አገሩን በማወቅ፣ እራሴን ከአየር ሁኔታው ጋር በማለማመድ እና መረጃ ሰጪዎችን በማጠያየቅ እና ቅድመ ዝግጅት በማድረግ አሳለፍኩኝ።

በስራ እና ስብሰባ መደራረብ ምክንያት ሳላገኛቸው የሰነበትኩትን የታሕታይ አድያቦ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሐላፊና የኩናማ ብሔረሰብ ተወካይ የሆኑት አቶ ብርሃነ ኬኖን ረቡዕ ጥር 10/2009 ዓ.ም. ከሰዓት ተገናኝተን ሻይ ቡና እያልን የተለያዩ መረጃዎችን ተለዋወጥን፡፡ ከዚያም የጥምቀት በዓል አከባበርን በኩናማዎች ዘንድ ምን እንደሚመስል ማየት እንደምፈልግ ስነግራቸው ሐሳቤን በደስታ ተቀበሉት፡፡ ካላቸው የስራ እና የስብሰባ ብዛት አንፃርም በዓሉ ከሳቸው ጋር መሆኔ ሰፊ ጊዜ ሊኖረን ስለሚያስችል እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅሜ ጥር 11/2009 ዓ.ም. ኩናማዎች የጥምቀት በዓልን በድምቀት ወደ ሚያከብሩበት ጣብያ ለምለም ከአቶ ብርሃነ ጋር በመሄድ ከበርካታ የብሔረሰቡ ተወላጆች፣ የጎሳ መሪዎች እና መረጃ አቀባዮች ጋር ተዋወኩኝ፡፡ አቶ ብርሃነ ደግሞ የመጣሁበትን አላማ በሚገባ በማብራራት የብሄረሰቡ አባላት የሚያውቁትን መረጃ እንዲሰጡኝ በር ከፈቱልኝ፡፡ በዚህም ከጥር 11-28/2009 ዓ.ም. ባሉት 18 ቀናት ውስጥ በቀበሌዎቹ ያለስጋት እየተዘዋወርኩኝና ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ቀጠሮ እየያዝኩኝ 48 የሚሆኑ ተረቶችን በምስል፣ በድምጽና በማስታወሻ ደብተር አስደግፌ ሰበሰብኩኝ፡፡

ቀን ቀን በድምጽ፣ በምስል እና በማስታወሻ ደብተር መዝግቤ የሰበሰብኩዋቸውን ተረቶች እና መረጃዎች ማታ ማታ ከአቶ ብርሃነ፣ ከመምህር አበዶም ገብረዮሐንስ እና ከመምህር አሸብር ጃምቦ ጋር በመሆን ከኩናምኛ ወደ ትግርኛ የመተርጎም ስራ አከናውኛለሁ፡፡ እነዚህ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በኩናምኛ የሰበሰብኩትን መረጃ በመተርጎም፣ በማመሳከር እና በቃል የተሰበሰበውን የኩናምኛ መረጃ ወደ ጽሁፍ በማስፈር፣ ኃላ ደግሞ በላፕቶፕ ኮምፒውተሬ ላይ ያሰፈርኩትን የኩናምኛ ጹሑፍ በማረም አግዘውኛል፡፡ ከአካባቢው ውጪ የሚኖር እና የሚረዳኝ የኩናምኛ ቋንቋ ተናጋሪ የማላገኝ በመሆኑ ደከመኝ ሳልል የቦታው ከፍተኛ ሙቀት ተቋቁሜ ቀን ከሌሊት ስርቼ መምጣት ግዴታ ነበር የሆነብኝ፡፡

ከጥር11- 28/2009 ዓ.ም. ባሉት ቀናት ውስጥ 48 ተረቶች ብቻ ነው መሰብሰብ የቻልኩት፡፡ ከእነዚህ ውስጥም በተደረገው የመተርጎም እና የማጣራት ስራ 43ቱ ብቻ ነበር የተረትን ባህሪ የሚያሟሉት፡፡ የቀሩት መረጃ ሰጪዎቹ ከጊዜ ብዛት እንዲሁም ተረቶቹ ከመርዘማቸው የተነሳ ታሪካቸው የተረሱ እና የተቆረጡ እና ድግግሞሽ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ምንም እንኳ መረጃ ለመሰብሰብ የሄድኩበት ወቅት ተማሪዎች እና መምህራን የሚያርፉበት፣ እንዲሁም እንደ ሰርግ የመሳሰሉ ህዝብ በብዛት የሚያሰባስቡ ማህበራዊ አጋጣሚዎች የሚደረጉበት በመሆኑ መረጃ አቀባዮች በቀላሉ ለማግኘት እችላለሁኝ በማለት ከግምት አስገብቼ አቅጄው የነበረ ቢሆንም በኩናማ ብሔረሰብ ሰርግ በብዛት በማጋጠሙ መረጃ

ሊሰጡኝ ቀጠሮ ያስያዙኝ መረጃ አቀባዮቼ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመንቀሳቀስ፣ የተወሰኑ መረጃ አቀባዮቼ ደግሞ በስብሰባ እና በስራ መደራረብ ምክንያት በተደጋጋሚ ያስያዙኝን ቀጠሮዎች በመሠረዛቸው ከዚህ በላይ መረጃ ለመሰብሰብም ሆነ የተተኳሪ ቡድን በመመስረት ግልጽ ያልሆኑልኝ መረጃዎችን ለማጣራት አልቻልኩም። ስለዚህ ሌላ መፍትሔ ማፈላለግ ነበረብኝ። ከዚያም ዓብይ ጾም ከገባ በኃላ ሰርግና መልሱ ገብ ስለሚል መረጃ አቀባዮቼን ተመልሼ እንደምምመጣ ነግሬያቸው በተቻለ መጠን የሚያውቁትን ተረት አስታውሰው እንዲጠብቁኝ ተነጋግረን በቀን 29/05/2009 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩኝ።

የሰበሰብኩዋቸውን ተረቶች እና መረጃዎች በአጠቃላይ የመስክ ቆይታየን በተመለከተ ከአማካሪዬ ጋር ተነጋገረንበት። በዚህም የሚቀሩኝ ነገሮች እንዳሉ በመጠቆም ተመልሼ በመሄድ ተጨማሪ መረጃ እንድሰበስብ፣ የቀሩትን መረጃዎችን እንዳሟላ መከሩኝ።

የሁለተኛውን ዙር የመስክ ስራ ለማከናወን የካቲት 14/2009 ዓ.ም፣ ከአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ወደ አክሱም በአውሮፕላን ተጓዝኩኝ። አመሻሽ ላይ ሽራሮ ገብቼ አደርኩና ከየካቲት 15-29/2009 ዓ.ም. ባሉት 15 ቀናት ውስጥ 39 ተረቶች ሰበሰብኩኝ። ከእነዚህ የተሰበሰቡ ተረቶች ደግሞ 35ቱ ብቻ ናቸው የተረትነት ባህሪ ያላቸው ሆነው የተገኙት።

በአጠቃላይ በሁለት ዙር የተደረገው ከመስክ መረጃ የመሰብሰብ ስራ ጥናቱ ለማካሄድ በተመረጡ ቀበሌዎች በመዘዋወር፣ መረጃ አቀባዮች በሰጡኝ ቀጠሮ መሠረት እየተገኘሁና ተጨማሪ ጥቆማዎችን እየተቀበልኩ 31 የኩናማ ብሔረሰብ ተወላጆችን በማነጋገር 78 ተረቶች ለመሰብሰብ ችያለሁኝ። በሁለተኛው ዙር ከሰበሰብኩዋቸው መረጃዎች አሻሚ ሆነው ያገኘሁዋቸውን በመለየት የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግ ትክክለኛነታቸውን አረጋግጫለሁ። በመጨረሻም የሰበሰብኩዋቸውን መረጃዎች ወደ ትግርኛ በመተርጎም፣ ተረቶቹ በተተረቱበት ኩናምኛ ቋንቋ ወደ ጽሁፍ በመገልበጥ ኮምፒውተር ላይ አስፍሬ፣ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በጽሁፍ ያሰፈርኩትን እንዲያርሙልኝ አድርጌ የመስክ ቆይታየን ጨርሼ ሐሙስ የካቲት 30/2009 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩኝ።

## 1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

### 1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ከመስክ ተገኝቼ ተረቶችና መረጃዎች ለመሰብሰብ በየቀበሌዎቹ በምዘዋወርበት ወቅት በርካታ ችግሮች ገጥመውኛል፡፡ ያጋጠሙኝን ችግሮች ሁሉ እዚህ ማስፈር ባልችልም ዋናዋናዎቹ ለመጥቀስ ያህል፤

- ✓ ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ቆላማ እና የሙቀት መጠኑ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ካደኩበት እና ከነበርኩበት አካባቢ በጣም የተለየ የአየር ፀባይ ያለው በመሆኑ እንደልቤ ተንቀሳቅሼ ስራየን በአግባቡ እንዳልሰራ እና እንዳልተኛ አድርጎኛል፡፡ በዚህም ጤናየ ላይ ጫና አሳድሮብኛል፡፡
- ✓ የኩናማ ብሔረሰብ አባላት በተወካያቸው አማካኝነት ካልተነገራቸው በስተቀር መረጃ በፍፁም አይሰጡም፡፡ የብሔረሰቡ አባላት መረጃ ለመስጠት ክፍት አይደሉም፡፡ በተወካያቸው አማካኝነት ቢነገራቸውም ለማውራት ፍቃደኞች አይደሉም፤ ሲጠየቁ ስለ ብሔረሰቡ ታሪክ ያውቃል ያሉትን ወይም የጎሳ መሪን ከመጠቆም የዘለለ መረጃ አይሰጡም፡፡ ይህንን በመስበር መረጃ ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡
- ✓ መረጃ አቀባዮቼ በተለያዩ ምክንያታት በቀጠሩኝ ቀንና ሰዓት አለመገኘት
- ✓ ከብዙ መግባባት እና መለማመድ በኃላ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ ለመነሳት፣ ድምጻቸውና ቪድዮ ለመቅረፅ ፍቃደኛ አለመሆን፤ ይህ ደግሞ ሙሉውን ተረት አድምጠው ለሚተረጉሙልኝ ሰዎች ለማስታወስ እና የተረቱን ፍሰት እንዳለ ለመከታተል ከባድ አድርጎታል፡፡
- ✓ አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ በእድሜ የገፉ ከመሆናቸው የተነሳ ድምጻቸውን ባለመሰማቱ ለሚተረጉሙልኝ እና ወደ ጽሑፍ ለሚቀይሩልኝ ሰዎች አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል፡፡
- ✓ ኩናምኛ እና አማርኛ አቀላጥፎ የሚናገር እንዲሁም የሚፅፍ ሰው ባለመገኘቱ ተረቶቹ ከተተረቱበት ኩናምኛ ቋንቋ መጀመርያ ወደ ትግርኛ፣ ከትግርኛ ደግሞ ወደ አማርኛ ነው የተተረጎሙት፡፡ ይህ ደግሞ እጅግ ከባድ እና አድካሚ በመሆኑ ሰፊ ግዜ ተሻምቶኛል፡፡
- ✓ ካረፍኩበት ሽራሮ ወደ የኩናማ ብሄረሰብ የሰፈረባቸው አካባቢዎች የሚያደርስ የትራንስፖርት አቅርቦት ባለ መኖሩ በእግር ከአንድ ሰዓት ተኩል እስከ ሁለት ሰዓት ያስኬዳል፡፡ ሙቀቱን ተቋቁሞ ወደ እነዚህ ቀበሌዎቹ በየቀኑ መመላለስ ከባድ ፈተና ነበር የሆነብኝ፡፡

### 1.9.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች

ከላይ ለተገለፁ ችግሮችን ለመፍታት የሚከተሉትን መፍትሔዎች ወስጃለሁ፡፡

- ✓ የአካባቢውን የአየር ፀባይ ለመልመድ ብቸገርም አለባበሴን በማስተካከል፣ ጃንጥላ እና ነጠላ ጫማ በመግዛት ፀሐይና ሙቀቱን ለመቋቋም ጥረት አድርጌያለሁ፡፡
- ✓ ከመረጃ አቀባዮቼ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ከአቶ ብርሃነ ኬኞ ጋር ወደ ቀበሌዎቹ በመሄድ እንዲያስተዋውቁኝ ማድረግ አማራጭ የሌለው መንገድ ነበር፡፡ በዚህም ከስራ ነፃ የሚሆኑበት ቀን እና አጋጣሚ እየጠበቅኩ፣ ለስራ እና ለስብሰባ ወደ ቀበሌዎቹ ሲንቀሳቀሱ አብሬያቸው በመሄድ ከብሄረሰቡ ጋር አስተዋውቀውኛል፡፡ በዚህም በቀላሉ ለመግባባትና መረጃ ለመሰበሰብ ችያለሁ፡፡
- ✓ መረጃ አቀባዮቼ በቀጠሮዋቸው ሳይገኙ ሲቀሩ በትእግስት በመጠበቅ፣ ሳይመች ሲቀር ደግሞ ቀን በመቀየር መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡
- ✓ ፎቶ ግራፍ ለመነሳትና ድምፃቸውን ለመቀረጽ ፍቃደኛ ያልሆኑትን መረጃ አቀባዮቼ ለማግባባት በፊት የቀረፅኩትን ደግሜ በማሰማት እና በማሳየት ፍቃደኛ ሆነው እንዲቀረፁ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ፍቃደኛ ያልሆኑትን ደግሞ ማስታወሻ ደብተርና እስክርቢቶን ተጠቅሜ ሰብስቤያለሁ፡፡ ከተቀረፁት ተረቶች መካከል ፍሰቱ እና ታሪኩ የተቋረጠ፣ የማይሰማ ድምፅ ሲያጋጥም በሌላ ቀን ሰዎቹን አግኝቼ ደግመው እንዲተርኩልኝ አድርጌያለሁ፡፡
- ✓ ኩናምኛ እና አማርኛ አቀላጥፎ የሚችል ሰው ባላገኝም የኩናምኛ ቋንቋ መምህራን የሆኑትን ሶስት መምህራን እንዲሁም አቶ ብርሃነ ኬኞን ተጠቅሜ ከኩናምኛ ወደ ትግርኛ የመተርጎም ስራውን አከናውኛለሁ፡፡ ከትግርኛ ወደ አማርኛ እራሴ በመተርጎም አሻሚ የሆነብኝን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ትግርኛ አማርኛ ተናጋሪ ጓደኞቼና የቀድሞ አስተማሪዎቼ እንዲያነቡት በማድረግ ችግሩን ለማቃለል ችያለሁ፡፡
- ✓ የትራንስፖርት ችግርን ለማቃለል አመቺ በሆኑ ቦታዎች ለሞተር ሳይክል እየከፈልኩ እንዲያመላልሱኝ በማድረግ፣ ሞተር ሳይክል የማይገቡትን ደግሞ በእግር በመመላለስ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

ይህ ምዕራፍ በሁለት ዓበይት ክፍሎች ተዋቅሮ የቀረበ ነው፡፡ የመጀመርያው ክፍል የተረት ምንነትና ምደባ በተመለከተ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የሚበጅበት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ከዚህ ቀድሞ በዚህ ርእስ ዙርያ ላይ የተሰሩ ተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ሲሆን በስሩም ሁለት ርእሰ ጉዳዮች አሉት፡፡ የመጀመርያው በ "ተረት" ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ ቀደምት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ቅኝት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለጥናት በተመረጠው የኩናማ ብሔረሰብ ላይ የተካሄዱ ፎክሎራዊ ጥናቶች የሚዳሰሱበት ነው፡፡

### 2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

#### 2.1.1.የተረት ምንነት

ተረትን እንዲህ ነው ብሎ ባጭሩ ከመበየን ይልቅ በውስጡ የሚካተቱን በመዘርዘር፣ ስለ ሙያው እና ባህሪው በመተንተን ለመግለጽ መሞከር የተሻለ ይመስለኛል፡፡ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራንም ይህንን ነው ያደረጉት ለምሳሌ (Thompson, 1946 እና Fischer, 1963)፡፡ ተረት ላይ ጥናት ካደረጉ ምሁራን በቀዳሚነት ስሙ የሚነሳው Thompson ተረትን እንደ ሚከተለው ይበይነዋል፡፡

> *Although the term "folktale" is often used in English to refer to the "household tale" or "fairy tale" it is also legitimately employed in a much broader senese to include all forms of prose narrative, written or oral which have came to be handed down through the years. In this usage the important fact is the traditional nature of the material (1946, 4).*

ምንም እንኳ ተረት ሲባል ዝም ብሎ ተራ ነገር ወይም ተጨባጭ ያልሆነ ነገር አድርጎ የማሰብ ሁኔታ ቢኖርም በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአጠቃቀም አድማሱን በማስፋት በዝርው መልክ የሚቀርቡ ሁሉንም ሃገረሰባዊ ትረካዎች ጥቅል መጠርያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በውስጡም ለተዝናኖት ከሚተረቱ ተራ ተረቶች እስከ እውነት ናቸው ተብለው የሚታመኑ ታሪካዊ ትረካዎች እና ሚቶች ያካትታል፡፡ ይህንን ሐሳብ (Fischer, 1963:273) እንደሚከተለው ያጠናክረዋል፡፡

*The term folktale is used broadly to refer to any traditional dramatic narrative of more or less fixed form, transmitted primarly in oral tradition. Myths, legends, fables, etc., are thus intended by the term.*

አንድ ማህበረሰብ ስለ ዓለም ያለው አመለካከት፣ በአካባቢው ስላለው ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ሁኔታ... በስነቃሉ አማካይነት ይቀረሳል። ማህበረሰቡ በውስጡ አሉኝ የሚላቸውን መልካም እሴቶች፣ ታሪክ፣ እምነት፣ ሞራል እና ስነ ምግባር በተረቶቹ አማካይነት አስተማስሎ በማቅረብ ልጆቹን ያስተምራል፤ ቀጣይነት እንዲኖራቸውንም ያደርጋል። ተረቶች እንደ የስነቃል ዘርፍነታቸው የአንድን ማህበረሰብ የዘመናት ታሪክ፣ አስተሳሰብ እና ገጠመኝ ከትውልድ ትውልድ ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ይህንን በሚመለከት ፈቃደ (1991፣13) “የዛሬው ትውልድ የቆመበትን መሠረት ለማወቅ (ዛሬ የራስ ብቻ ሳይሆን የትናንትም ውጤት ነውና) ትናንትን ማወቅም ዛሬን ለማወቅ እና የነገውንም መንገድ ለማቀድ ስለሚበጅ አፋዊ ኪነተ ቃል እና አፋዊ ታሪክ አንድን ህዝብ የማወቅያ እና የዚያንም ህዝብ መለወጫ መንገድ መፈለግያ መሳርያ ሊሆን ይችላል” በማለት ይገልጻል።

የተረት አቀራረብ በዝርው መልክ ሆኖ ከመደበኛ ንግግር የተለየ፣ ሳቢ እና አጓጉ ነው። Fischer በተረት የሚካተቱ ትረካዎች ድራማዊ ባህርይ ያላቸው፣ ገፀ ባህርያቱ አሸንፈው ለመውጣት ሲፍጨረጨሩ በሚያጋጥሙ መጠነኛ ግጭቶች ልብ የሚሰቅሉ እና የሚማርኩ መሆናቸው አብራርቷል (1963፣ 237)። ይህን ሓሳብ Thompson (1946:3) በበኩሉ “ተረት መስማት በሁሉንም አካባቢዎች አጓጉ  እና አስደሳች ነው፤ የፈለገውን ዓይነት ተረት ቢሆንም ሰዎች የመስማት ጉጉታቸውን ይረኩበታል” በማለት ገልፆታል። ፈቃደ ደግሞ “ተረት እድሜ፣ ጾታን፣ መደብን ሳይለይ ሰዎችን ሁሉ ይስባል። ... ፣ ተረት በተለያዩ ሰዎች የሚታሰብ፣ የሚፈለግ፣ የሚመረመር እንጂ ያለፈ፣ ያረጀ-ያፈጀ አይደለም”(1991፣53) ይላል።

የስነ ጽሑፋዊ መዝገበ ቃላት ተረትን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል። “ሀገረሰባዊ ተረቶች ዓለማቀፋዊ ክስተት ሆነው በቃል የሚተላለፉ፣ የደራሲዎቻቸው ማንነት የማይታወቅ፣ አጭር፣ ቁጥብ እና በቁም ነገር የተሞሉ ታሪኮች ናቸው። ሚቶችን፣ የልዕለ ጀግኖች አፈታሪክን፣ አስማቴ ተረቶችን፣ የመናፍስት ወዘተ. ታሪኮችን የሚይዙ ናቸው” (Gray፣ 1992፣ 121)። ይህ ወሰነ ትርጉም ቀደም ሲል በእነ Thompson የሰጡትን ሐሳብ የሚያጠናክር ነው። በተረት የሚካተቱ የስነቃል ዓይነቶችን በመዘርዘር ባህሪውን ለመግለፅ ጥረት አድርጓል።

የተረትን ተስተላልፎ በተመለከተ የሚሰነዘሩ ሐሳቦች አብዛኞቹ "ቃላዊ በሆነ መንገድ ነው" የሚል እምነት ያላቸው ሲሆን Thompson ግን ተረቶቹ ከየአቅጣጫው ተሰብስበው እና ታትመው በፅሑፍ መልክ የመገኘት እድል ስላላቸው በፅሑፍም ሊሆን ይችላል በማለት ያስረዳል (1964፣3)። ከአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ተረትን ሰብስቦ የማሳተም፣ የመተርጎም እና የማጥናት ስራ ብዙ የማህበረሰብ ሳይንስ ተማራማሪዎችን ትኩረት የሳበ በመሆኑ አንድ ተረት የሚተርት ሰው ተረቱን የግድ በቃል ሲተረት መስማት ላይጠበቅበት ይችላል። Fischer (1963:272) በበኩሉ ተስተላልፎው በዋናነት በቃል ቢሆንም በፅሑፍ የመተላለፍ ዕድል እንዳለውም ኣብራርቷል።

የፎክሎር መዝገበ ቃላት  በበኩሉ ተረትን እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> *ተረትን በቀጥታ ለመበየን ሙከራ ያደረገ የለም፤ ነገር ግን ተረት የሚለውን ቃል ለሁሉም ዓይነት ባህላዊ ትረካዎችን ጥቅል መጠርያ ተደርጎ ይወሰዳል። በውስጡም ከጥንታዊ የአኗኗር ዘዴ ያልራቁ ህዝቦች ከሚተርኩዋቸው የፈጠራ ሚቶች እስከ ውስብስብ የሆኑ ዘመናዊ ተረቶችን ያካትታል። በባህሪው ደግሞ  ባህላዊ ነው። ተስተላልፎው ከአንድ ሰው ወደ ሌላኛው ቃላዊ በሆነ መንገድ ነው። ሲተረክም ያስታወሱትን እንዳለ ሳይጨምሩ ሊሆን ይችላል፤ አልያም ደግሞ ተራቹ ጨምሮ ወይም ቀይሮ ሊተርተው ይችላል። ተረቶች አለም አቀፋዊ ባህሪ አላቸው። የትም ቦታ ያሉ ባህሎች እና ህዝቦች ተረት ይተርታሉ (Leach,1949: 408-409)።*

የተረት ምንነት በተመለከተ ከዚህ በላይ የተሰጡትን መነሻ በማድረግ ተረት በዝርው መልክ የሚቀርቡ ሃገረሰባዊ ትረካዎች ጥቅል መጠርያ ነው። በውስጡም አንድ ማሕበረሰብ ለመዝናናት፣ ለማስተማር፣ የዓለምን እንቆቅልሽ ለመፍታት ወዘተ. የሚተርካቸው ፈጠራዊ ባህርይ ያላቸው ሌጀንዶች፣ ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮች እና የመሳሰሉትን ያካትታል። በዚህ ጥናት የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ሲባል የኩናማ ብሔረሰብ ለዘመናት ሲተርካቸው የኖረ ከትውልድ ትውልድ ቃላዊ በሆነ መንገድ ሲተላለፉ የኖሩ ዝርው ትረካዎችን ይመለከታል።

### 2.1.2. የተረቶች ምደባ

> *Before it can become an object of serious and well-considered study, every branch of knowledge needs to be classified (Thompson,1946፡413).*

የአንድን ማህበረሰብ ወይም አካባቢ ተረቶችን ሰብስበን ለማጥናት በምንነሳበት ወቅት በመስክ ቆይታ ወይም በተለያዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን ተረቶች ምደባ ማካሄድ ተገቢ ነው፡፡ ምደባ ለጥናት አመቺነት በር ከመክፈቱም በላይ የስነቃል ዓይነቶችን በአግባቡ ለማወቅ ያግዛል፡፡ በተረት ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች የተሰበሰቡትን ተረቶች ምደባ ማካሄድ ወሳኝ መሆኑ ይመክራሉ *Thompson (1946፡413),* Fischer (1963:236), Finnegan (1970:327), Arewa (1980፣ VI), Okpewho (1992፡181) እና ፈቃደ (1991፣54)፡፡ ምሁራኑ እንደሚያስገነዝቡት በማንኛውም የእውቀት መስክ ለሚካሄድ ከፍ ያለና የተደራጀ ጥናት ምደባ እጅግ አስፈላጊና እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚታይ ተግባር ነው፡፡ ለጥናት የተመረጡ ተረቶች የተለያዩ መስፈርቶች በማበጀት መመደብ ተረቶቹን የበለጠ እንድንረዳ መንገድ ይከፍታል፡፡ ይህን ሓሳብ Fischer እንደሚከተለው አጠናክሮታል፡፡ "*The classification of folktale into types according to their social function, content, structure, typical audience, etc., is essential for a full understanding of them" (1963:236)፡፡*

ተመራማሪዎቹ የተረት ምደባ አስፈላጊ መሆኑ ቢያምኑም ታድያ ተረትን ለመመደብ የሚያስችል አንድ ወጥ የሆነ አመዳደብ ስልት አለመኖሩን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ Okpewho "የቃል ተረትን የመመደብ ጉዳይ የቆየ ችግር ነው" (1992፣181) ሲል Fischer ደግሞ አንድን ተረት ባለው ማህበራዊ ፋይዳ፣ መባያ ጉዳይ፣ ገፀ ባህሪ ወዘተ. መሠረት መመደብ አሻሚ አልያም ደግሞ ከጊዜ እና ቦታ አንፃር የተለያየ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ አሻሚ የሚሆንበት ምክንያት ሲያብራራም በአንድ አካባቢ የምናገኘው ተረት ለአንዳንድ ሰዎች ሚት ሲሆን ለሌሎች ደግሞ ዝም ብሎ ለመዝናኛ የሚቀርብ እንደሆነ፤ ጥብቅ የሆኑ ሚትዮሎጂያዊ ተረቶችም ለማሳቅ እና ለማዝናናት የሚቀርቡበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም አንድ ተረት በአንድ ምድብ ብቻ ተወስኖ የማይቀር በመሆኑ፣ በነዚህ እና ሌሎች ምክንያቶች ምደባው አስቸጋሪ ይሆናል በማለት አብራርቷል (1963፣236)፡፡

ከዚህ የተነሳም ተረት ላይ ጥናት ያደረጉ አጥኚዎች ተረቶቹን ለመመደብ የተከተሉት ስልት ስንመለከት አብዛኞቹ የየራሳቸው መንገድ ነው የተከተሉት፡፡ ተረቶችን ለመመደብ

የሚያስችል አንድ ወጥ ስልት ባለመኖሩ እና የአጥኚዎቹ ምርጫ እና እይታ ስለሚለያይ የየራሳቸውን ምክንያት በመስጠት ተረቶችን ለመመደብ ጥረት አድርገዋል፡፡ ከእነዚህ ዋና ዋናዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

በተረት ጥናት ቀዳሚ የሆነውን Thompson ተረቶቹን ምትሀታዊ ተረቶች (fairy tale)፣ በአንድ ቦታና ወቅት ተፈፅሟል ተብሎ የሚታመን እውነተኛ ፍፃሜ የያዙ ተረቶች (novella)፣ የጀግና ተረቶች (hero tale)፣ ጥንታዊ ሌጀንድ (sage) እና ገላጭ ተረቶ (explanatory tale) በማለት በአምስት መድቧቸዋል (1946፣7-10)፡፡ ተረቶቹን ለመመደብ የተገለገለበት መስፈርት የተረቶቹ ይዘት ነው፡፡

የሊምባ ተረቶች ላይ ጥናት ያደረገች Finnegan ተረትን ለመመደብ ለአካባቢያዊ አመዳደብን ቅድምያ መስጠት የተሻለ መሆኑን በመጠቆም በተረቶቹ ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህርያት እንደመስፈርት ተጠቅማ ምደባ አድርጋለች፡፡ በዚህም "ስለ ሰው የሚተርኩ፣ ስለ እንስሳ የሚተርኩ እና ስለ ኬት መጣ የሚተርኩ በማለት የሊምባ ተረቶች በሶስት ክፍሎች መድባቸዋለች (1970፣327)፡፡

በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ያሉትን የአርብቶ አደሮች ተረቶች ያጠናው Arewa ደግሞ ተረቶች መመደብ ያለባቸው በሚነገሩበት አካባቢ ያላቸው መጠርያ፣ እንዲሁም ቅርፃቸው ባካተተ መልኩ መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይህን ዘዴ ተከትሎም የሰበሰባቸውን ተረቶች "የኬት መጣ ተረቶች (Stories of Origin)፣ የእንስሳት ተረቶች (Animal tales)፣ ተራ ተረቶች (Ordinary tales) እና ቀመራዊ ተረቶች (Formula tales) በማለት በአራት መድቧቸዋል (1980፣VI)፡፡

Arewa ከሱ በፊት ተረት ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ተረትን ለመመደብ የተከተሉትን ዘዴ እና ያበረከቱት አስተዋፅኦም ዳስሰዋል፡፡ የተለያዩ ሐሳቦች ይዘው ተረትን ለመመደብ ከሞከሩ ምሁራን መካከል Bascom (1965)፣ Propp (1968)፣ Aarene (1910) እና Okpewho (1980) በዋናነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን አስረድቷል፡፡ ከነዚህ መካከል Bascom ህዝቡ ስለተረቶቹ ያለውን እምነት እና መቼቱን መሰረት አድርጎ ተረቶችን ሚት፣ አፈታሪክ እና የሀገረሰብ ተረት በማለት በሶስት እንደሚከፍላቸው ገልፅዋል፡፡

Okpewho (1992፣181-182) ደግሞ ተረቶችን በጥቅሉ ሌጀንድ (Legened)፣ ገላጭ ተረቶች (Explanatory tales) እና ፋቡላ (Fables) በሚል መመደብ የተሻለ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ከሱ በፊት በተረት ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ተረቶችን ለመመደብ

በውስጣቸው ባሉት ገፀ ባህርያት፣ ይዘታቸው፣ ባህርያቸው፣ የሚተረቱበት ዓውድ፣ ወቅት ወዘተ በመስፈርትነት መጠቀማቸው እና እሱ የተከተለው መንገድ የተሻለ እና አሻሚነትን ያስቀረ መሆኑ ያስረዳል፡፡

ምሁራኑ ተረቶችን ለመመደብ ከተከተሉዋቸው መንገዶች መረዳት እንደሚቻለው በየትኛውም ቦታ የሚገኙትን ተረቶች ሰብስቦ ለመመደብ የሚያስችል አንድ ወጥ የሆነ መንገድ አለመኖሩን ነው፡፡ እንደ ተመራማሪው ምርጫ የአከፋፈል ስልቱንም የተለያየ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ Thompson (1965)፣ Arewa (1980) እና Finnegan (1970፣327) እንደሚያስገነዝቡት የተሰበሰቡትን ተረቶች ምደባ በሚደረግበት ወቅት ለአካባቢያዊ ምደባ (Local classification) ቅድሚያ መስጠት ከችግሩ ማቃለያ ዘዴዎች እንደ አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እነዚህ ምሁራን ለአንድ አካባቢ ተረቶች የወጣውን መስፈርት ለሌላው አካባቢ መጠቀም ችግር ማስከተሉን በመረዳታቸው ተረቶቹ በአካባቢው ትውፊት ላይ ተመስርቶ መከፋፈል ይኖርባቸዋል በማለት መክረዋል፡፡ የተረቶቹ ባለቤቶች ተረቶቹንን ምን ብለው እንደሚጠሩዋቸው ማወቅ ለምናደርገው ምደባ የራሱ አበርክቶ እንዳለው እና ተረቶቹን የበለጠ እንድንረዳቸው የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥም ከመስክ የተሰበሰቡትን የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶችን ለመመደብ የተረቶቹን አካባቢያዊ ምደባ ቅድምያ የሚሰጠው ይሆናል፡፡ እንዲሁም ተረቶቹ በምሁራን የመመደብያ ስልት በመከተል ምን እንደሚመስሉ ለመግለጽ ጥረት ይደረጋል፡፡

### 2.1.3.ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ

> *Functionalism interprets folklore as on going process of expressing information and beliefs within folk groups through communicative means (Sim./ Stephens:174).*

የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ላይ የተመሠረተው ይህ ጥናት የተመሠረተበት የምርምር ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር ጥናት ከሚውሉ ዓበይት ንድፈ ሐሳቦች አንድ ሆኖ ከፎክሎር ዘውጎች በበለጠ ስነ ቃልን ለማጥናት በስፋት የሚያገለግል ነው (Sims, 2005: 175)፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የአንድን ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ቃላዊ ሃብቶች በመመርመር ተግባራቸውን የሚያሳይ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሐሳብ እንደ መታገኒያነት በመጠቀም ለጥናቱ የተመረጡትን የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ይዘታቸው ወይም ተግባራቸው በመፈከር እና በመተንተን ተረቶቹ ለብሄረሰቡ

አባላት ምን ፋይዳ አላቸው? ወይም ደግሞ ለምን ዓላማ ይተረታሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አደርጋለሁኝ፡፡

የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን መሠረት በማድረግ የተለያዩ የፎክሎር ሙሁራን በርካታ የፎክሎር ተግባራት ዘርዝረዋል፡፡ ከእነዚህ ሙሁራን ቀዳሚ የሆነው እና ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር ጥናት ያስተዋወቀው William R. Bascom (1954) ነው፡፡ Bascom በፎክሎር ጥናት የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ትኩረት የአንድ ማሕበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን አባላት በሚጋሩዋቸው እሴቶች እንዴት እንደሚግባቡ ላይ እንደሆነ በማስረዳት ፎክሎር ለተገልጋዮቹ አራት ዓበይት ተግባራት እንዳሉት ይገልፃል፡፡ እነሱም የማስተማር (Education)፣ የማምለጥ (to escape from the limitations of society)፣ የባህልን ጠቀሜታ ለመግለፅ (Validating culture)፣ እና የመግታት ወይም የመቆጣጠር ተግባር (maintain conformity to the accepted of behavior) ናቸው (1954፡ 343-346)፡፡

ፈቃደ ደግሞ የስነቃልን ተግባራት የመግለጥ ተግባር፣ የማጠናከር ተግባር፣ የማምለጫ ተግባር፣ የማስተማር ተግባር እና የመግታት-መቆጣጠር ተግባር በማለት በአምስት ዓበይት ክፍሎች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ገልፅዋል (1991፣17)፡፡ ተረትም የስነቃል ዘርፍ እንደ መሆኑ መጠን እነዚህን ተግባራት ከግብ ለማድረስ እንደሚችል ከዚህ አገላለፅ መረዳት ይቻላል፡፡

Bascom እንደሚለው ፎክሎር ለየተኛውም ቡድን በተለይ ደግሞ የፅሑፍ ክሂል ባልዳበረበት ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የማስተማር ተግባር እንዳለው፤ የፎክሎሩ ባለቤት የተለያዩ የስነቃል አይነቶች በመጠቀም የታዳጊ ህጻናትን አእምሮ በትምህርት ለማጎልበት፣ ወጣቶችን በስነ ምግባር ለማነፅ ያገለግላል፡፡ እንዲሁም የማህበረሰቡ ታሪክ፣ ባህል እና አስተሳሰብ ለአዲሱ ትውልድ ለማስረፅ ይጠቀምበታል (1954፡ 344-345)፡፡

ፈቃደ (1991፣20) ደግሞ ይህንን ሐሳብ "ስነቃሎች የአኗኗርን ሥርዓት፣ ስነ ምግባር እና ብልሃት ያስተምራሉ፡፡ የአነጋገር፣ የአካሄድ ሥርዓትን ያሳውቃሉ፡፡ በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የኅብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ፡፡ የልጆችና የወጣቶችን ባህርይ ገና ከለጋነታቸው ለመቅረፅም ያገለግላሉ" ሲል ገልፆታል፡፡ ተረት የአንድን ማህበረሰብ ወግና ልማድ ለማስተማር፣ ታሪክን ለማስተላለፍ ይተረታል፡፡ ጥላቻ እና ቂም ለማስረሳት፣ ሀዘንተኞችን ለማጽናናት፣ እርቀ ሰላም ለማውረድ ይተረታል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ፖሎቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖምያዊ አጋጣሚዎች ሂስ ለመስጠትም ይተረታል፡፡

በስነቃል ላይ ሰፊ ጥናት ያደረገች Finnegan የተረትን ጠቀሜታ በተመለከተ "… story of instance are told to educate and socialize children, or by drowing a moral, to warn people not to break the norms of the society" (1970: 330) በማለት ትገልፃለች::

ስነ ቃል የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን እሴቶችን፣ ስነ ምግባር እና የአኗኗር ዘይቤን ከማስተማርያነት በተጨማሪ የማህበረሰቡ እምነት እና አመለካከት እንዳይጣስ ለመቆጣጠርያነትም ያገለግላሉ፡፡ ማህበረሰቡ ከሚፈልገው እና ከሚፈቅደው ውጪ ለሚሄዱ እና ለሚያፈነግጡ ግለሰቦች ለመቆጣጠር እና ጫና ለማሳደር ይጠቅማል Bascom (1954፡346)፡፡ አንድ ማሕበረ ሰብ ለዘመናት ጠብቆ ያኖራቸውን እሴቶች ሳይጣሱ እና ሳይሸራረፉ እንዲቀጥሉ ይፈልጋል፡፡ እነዚህን የሚፈታተኑ እና ከሱ ከፍላጎቱ ውጪ ለሚንቀሳቀሱ ከተግባራቸው እንዲታረሙ "የአደብ ግዛ" ተረቶችን በመተረት፣ በስርዓተ ማህበሩ እንዲገለሉና እንዲጠየፉ በማድረግ በስነ ቃሉ አማካኝነት ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ በዚህም ስነ ቃልን ለመቆጣጠር ተግባር ይገለገልበታል፡፡

ሌላው የስነ ቃል ተግባር የማምለጥ ተግባር ነው፡፡ "አንድ ማሕበረሰብ ካሉት ወይም ከሚያጋጥሙት አጥሮች እና ክልከላዎች በቀልዶች አማካኝነት ያመልጣል" Bascom (1954: 343)፡፡ እንዲተገብረው የማይፈቀድለትን ተግባር ላይ በመቀልድ እና በማሾፍ ክልከላዎቹን በመጣስ እንደተፈፀሙ አስመስሎ በማቅረብ በሐሳቡ ያመልጣል፡፡ ይህን ሐሳብ ፈቃደ (1991፣18-20) የሰው ልጅ ከአድካሚው የህይወት ውጣ ውረድ፣ ከማያምንባቸው ደምቦች እና ክልከላዎች እንዲሁም ከተፈጥሮአዊ አጥር ስነ ቃልን ተጠቅሞ እንደሚያመልጥና በምናቡ አዲስ አለም ውስጥ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡

አንድ ማሕበረሰብ በህይወት ዘመኑ እና በረጅም ታሪኩ ያካበታቸውን፣ አሉኝ የሚላቸውን መልካም እሴቶች ተገቢነታቸው በመግለፅ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ሌላው የስነቃል ተግባር ነው፡፡ Bascom (1954: 344) እንደገለፀው ስነ ቃል የአንድ ማህበረሰብ ባህልን ጠቃሚነት በመግለጽ እና የባህላዊ ስርዓቶቹ ተገቢነትን የማረጋገጥ ተግባር እንዳለው ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ በተመለከተ ፈቃደ "ስነ ቃሎች አንድ ማህበረሰብ ከልደት እስከ ሞት የሚያከነውናቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነት እና ተገቢነት እያሳመኑ ክዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ" (1991፣18) በማለት ይገልጻል፡፡

Dorson (1972፡22) በበኩሉ "የአንድን ቡድን ስነ ቃል በተለይ ደግሞ በሐተታ ተፈጥሮ አማካይነት እምነቶች፣ ባህሎች እና ከበራዎችን የማጽናት ወይም የማጠናከር ተግባር አለው" በማለት ገልፅዋል፡፡

## 2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸውን ቀደምት የኤም.ኤ. ዲግሪ መሟያ ጥናቶች የሚዳሰስበት ነው፡፡

### 2.2.1. በተረት ላይ የተደረጉ ቀደምት ማሟያ ጥናቶች

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል ተረት ላይ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በተረት ላይ የቀረቡ የባችለር ዲግሪ ፅሑፎች በዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል እነዚህ ናቸው፡፡ እንግዳ ወልደሰማያት (1974)፣ ያዕቆብ ወልደማርያም (1974)፣ ዳሃብ ትኩእ (1974)፣አወቀ ዉቤ (1975)፣ ሙሉጌታ ነጋሳ (1976)፣ ጥሩነህ አበራ (1982)፣ አበበ ከበደ (1982)፣ ሰውነት መኮንን (1984)፣ ዘኒት አብዱረሺድ (1992)፣ ሙሉነህ ጉግሳ (1993)፣ ተስፋየ ሊሞሬ (1993)፣ እና ስሩር በድሩ (1995) በቅደም ተከተላቸው በጭላሎ፣ በከፋ፣ በትግራይ፣ በወላይታ፣ በጅባትና ማጫ፣ በኦሮሞ፣ በሰላሌ፣ በሞጣ፣ በሃረሪ፣ በክስታኔ፣ በሃድያ እና በስልጤ ናቸው፡፡ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ በተረት እና ቃላዊ ተረኮች ላይ የተሰሩ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡ ለማ ንጋቱ (1999)፣ ማንያለው አባተ (1999)፣ አማረ ሞላ (1999)፣ ምንዳ ገብሬ (2000)፣ ሞላ ጀምበሬ (2002) እና ከሁሉም በላይ (2004) በቅደም ተከተላቸው መሠረት በየም፣ በቤንች፣ በሻካቾ፣ በጌድኦ፣ በዓፋር እና በነገደ ወይጦ ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡

በውጭ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍልም ለአርትስ ባችለር ዲግሪ እና ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያነት ተረት ላይ የተሰሩ ጥናቶች አሉ፡፡ ጥናቶቹ በተካሄዱበት ዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል መሰረት አብዱል ቃዲር ሐጂ (1982)፣ መላክነህ መንግስቱ (1990)፣ ተስፋይ ገብረማርያም (1990)፣ ሳህሉ ኪዳኔ (1996)፣ ይሄነው ጀምበሬ (1996)፣ ባይለየኝ ጣሰው (1999)፣ አብርሃም አለሙ (2000) እና ብርሃኑ በቀለ (2008) በቅደም ተከተላቸው መሠረት በሶማሌ፣ በአገው፣ በጀብላዊ፣ በቦረና፣ በምእራብ ጎጃም፣ በአኝዋክ፣ በጅማ ኦሮሞ እና በምስራቅ ወለጋ ኦሮሞ ተረቶች ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡

ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ ከእኔ ጥናት ጋር የበለጠ ተቀራራቢ ናቸው ብዬ የመረጥኳቸው ስድስት የኤም.ኤ. ዲግሪ ጥናቶች ለመቃኘት ሞክሬያለሁ፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከ1999 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም. ባለው ዘመን ተሰርተው ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ናቸው፡፡ በተሰሩበት ዘመን ቅደም ተከተል እንደሚከተለው እንደሚከተለው የሚዳሰሱ ይሆናል፡፡

ለማ ንጋቱ "በየም ብሔረሰብ ፆታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት ምስል ትንተና" በሚል ርእስ በ1999 ዓ.ም. ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በየም ብሄረሰብ የሚተረኩ ፆታ ተኮር ተረቶችን ሰብስቦ በተረቶቹ ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ መተንተን ነው፡፡ ተረቶቹን በዘር መመደብ፣ ተረቶቹን ፆታዊ ምስልን የሚያንፀባርቁባቸው መንገዶች መለየት እና ፆታ ተኮር ተረቶችን ከነ አውዳቸው አደራጅቶ መሰነድ የሚሉ ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ እነዚህ አላማዎችን ለማሳካት ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ከ23 የብሄረሰቡ አባላት 104 ተረቶችን እንደሰበሰበ በመግለፅ፣ ከነዚህ ውስጥም ፆታዊ ምስል ጎልቶ ይታይባቸዋል ያላቸውን 66 ተረቶች መርጦ ትንተና አካሂዷል፡፡ በጥናቱ ግኝትም ተረቶቹ በብሄረሰቡ አጠራር "ቶቾ" እና "ኤሻ" ተብለው እንደሚጠሩ ገልጾዋል፡፡ "ቶቾ" የሚባሉት እውነት ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ሲሆኑ "ኤሻ" የሚባሉት ደግሞ የፈጠራ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው እንደ ሆኑ አጥኚው ገልፅዋል፡፡ ተረቶቹን ከአካባቢያዊ አመዳደብ ባሻገር አፈ ታሪክ፣ ሚታዊ አፈ ታሪክ እና ገላጭ ተረቶች በማለት ሊመደቡ እንደሚችሉ ገልፅዋል፡፡

የለማ ጥናት በዓላማው ላይ ጾታ ተኮር ተረቶችን ከነአውዳቸው በስርዓት አደራጅቶ እንደሚያሳይ ቢገልፅም ተረኮቹን በየተኛው አውድ እንደሰበሰባቸው አልጠቀመም፡፡ እንዲሁም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት እና አርተፍሻል መቼት ተጠቅሞ እንደሰበሰበ ቢገልፅም አፈፃፀሙ ምን እንደሚመስል ባለመጠቆሙ እንደ ድክመት ይታያል፡፡

የለማ ጥናት በግኝቱ እንደሚያሳየው በአፈ ታሪክ እና በገላጭ ተረቶች ላይ ወንዶች በአወንታዊ መንገድ ማለትም ንፁህ እና የበላይ፣ ሴቶች ደግሞ በአሉታዊ መንገድ ማለትም የጎደፉ እና የበታች ሆነው እንደተሳሉ ነው፡፡

"የቤንች ቃላዊ ዝርው ትረካ ዘሮች እና ማህበራዊ ፋይዳቸው" በሚል ርእስ በ1999 ዓ.ም. ማንያለው አባተ ያቀረበው ጥናት በተረት ላይ ከተሰሩ ጥናቶች ተጠቃሽ ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሰብስቦ ማህበራዊ ፋይዳቸው በተመለከተ ትንተና ማድረግ እና

በብሄረሰቡ ዘንድ ተለይተው ሚታወቁ ተረኮችን በመለየት ባህርያቸውን ማሳየት ነው፡፡ ማንያለው የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅ መሆናቸውን ገልፅዋል፡፡ እነዚህን ዘዴዎች ተጠቅሞ 97 ዝርው ተረኮችን ሰብስቧል፡፡

የተሰበሰቡትን ተረኮች ምደባ የተደረገባቸው ሲሆን፣ በአካባቢያዊ ምደባ "ቶስ" እና "ኤሽ" ተብለው እንደሚከፈሉ ገልፅዋል፡፡ "ቶስ" በመባል የሚታወቁት እውነት ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ሲሆኑ "ኤሽ" የሚባሉት ደግሞ የፈጠራ እንደሆኑት ገልፅዋል፡፡

የማንያለው ጥናት የቤንች ዝርው ተረኮች የማዝናናት እና የማስተማር፣ የብሄረሰቡን አመጣጥ ማሳየት፣ አንድ ግለሰብ ከአካባቢው ነዋሪ ጋራ አስማምቶ እንዴት መኖር እንዳለበት የማሳየት ፋይዳ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

አማረ ሞላ "የሻካቾ ብሄረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም. ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የሻካቾ ብሄረሰብ ተረቶችን በመሰብሰብ ቅርፅና ይዘታቸውን መተንተን ነው፡፡ የአላማው ተተግባሪነት በተመለከተ የሻካቾ ብሄረሰብ ተረቶች በአካባቢያዊ ምደባቸው "ኬሞ" እና "ኢንጌሞ" ተብለው እንደሚጠሩ፤ እንዲሁም ደግሞ አፈ ታሪክ፣ ገላጭ እና ፋቡላ በሚል ሊመደቡ እንደሚችሉ ጥናቱ ያሳያል፡፡ "ኬሞ" በመባል የሚታወቁት ተረቶች ስለ የብሄረሰቡ መሪዎች፣ የእምነት አባቶች የሚያትቱ እና አፈ ታሪክ ሊባሉ የሚችሉ ሲሆኑ "ኢንጌሞ" ደግሞ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ይዘት ያላቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ ትምህርታዊ ይዘት ያላቸው ተረቶች መሆናቸውን ገልፅዋል፡፡

የሻካቾ ብሄረሰብ ተረቶች የአከዋወን ስልት በተመለከተ በመግቢያው የሚከወኑ፣ በሂደት እና በአጨራረስ የሚከወኑ እና በመዝግያ የሚከወኑ በማለት አከዋወናቸውን አሳይቷል፡፡ በብሄረሰቡ ተረት በመተረት የሚተዳደር ሰው እንደሌለ፣ እንዲሁም ተረት ለመተረትና ለማዳመጥ የተለየ ቦታና ጊዜ እንደማይጠይቅ ጥናቱ ያመላክታል፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ መረጃ ለመሰብሰብ አርተፊሻል መቼትን እንደተጠቀመ ቢገልፅም በቃለ መጠይቅ ነው ወይስ በምልከታ፣ አልያም ደግሞ በሌላ መንገድ በጥናቱ ዘዴ ላይ የተገለፀ ነገር ባለመኖሩ እንደ የጥናቱ ክፍተት የሚታይ ነው፡፡ በአጠቃላይ 74 ተረቶችን ሰብስቦ በ50 ተረቶች ላይ የይዘት ትንተና አካሂዷል፡፡ ተረቶቹ ብልህነት፣ መጥፎ ባህርያት፣ ጓደኝነት… በሚል መድቦ

ተንትነዋል፡፡ በመጨረሻም የሻኪቾ ተረቶችን እንዳልተሰበሰቡ እና እንዳልተጠኑ የገለፀ ሲሆን የሰበሰባቸውን ተረቶች በሻክኛ ቋንቋ እና በአማርኛ ትርጉማቸው በአባሪነት አያይዟል፡፡

ምንዳ ገብሬ "የጌድኦ ልማዳዊ ስርዓትና ዝርው ቃል ተረኮች" በሚል ርእስ በ2000 ዓ.ም. ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የብሄረሰቡን ልማዳዊ ስርዓቶች እና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ያለውን ግንኙነት መርምሮ ማህበራዊ ግልጋሎታቸውና ምንነታቸው ማመልከት ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ የተሳትፎ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ የምንዳ ጥናት የምርምር ጥያቄዎቹ በግልፅ ያልተቀመጡ መሆናቸው ምናልባት እንደ ክፍተት የሚታይ ይመስለኛል፡፡

የአላማው ተተግባሪነት በተመለከተ ዝርው ቃል ተረኮቹን ሰብስቦ በአካባቢው ምደባ መሠረት "መማሳ" እና "ጢንጎ" የሚል መጠርያ እንዳላቸው ገልፅዋል፡፡ "መማሳ" ተብለው የሚታወቁ የቃል ተረኮች ሽማግሌዎች በእርቅ ስነ ስርዓት ላይ በአደባባይ የሚጠቀሙባቸው እና የሚተረኩበት ጊዜ ደግሞ ቀን ሲሆን፤ "ጢንጎ" የሚባሉት ደግሞ በማንኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች ሊተረኩ የሚችሉ እና እንደየ አስፈላጊነቱ አጋጣሚው ሊነገሩ የሚችሉ ተረኮች እንደሆኑ በጥናቱ አሳይቷል፡፡ አጥኚው 17 የ"መማሳ" እና 35 የ"ጢንጎ" ተረኮችን ሰብስቦ በተወሰኑት ላይ የይዘት ትንተና አካሂዷል፡፡ በዚህም የጌድኦ ቃል ተረኮችን ክዋኔውንና ማህበራዊ ግልጋሎቱን ገልፀዋል፡፡ አጥኚው ጥናቱን ሲያጠቃልል ዝርው ቃል ተረኮቹ በአሁኑ ጊዜ በዘመናዊ ትምህርትና በተለያዩ ሃይማኖቶች መስስፋፋት ምክንያት እየተረሱ እንደመጡ እና ጭራሹኑ ወደ ማይነገሩበት ደረጃ እንደደረሱ ማረጋገጡን ገልፅዋል፡፡

ሞላ ጀምበሬ "በአሳይታ ወረዳ የአፋር ብሔረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና" በሚል ርእስ በ2002 ዓ.ም. ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በዓፋር ክልል በአሳይታ ወረዳ የሚተረቱ ተረቶችን ሰብስቦ በማደራጀት በዓይነት እና በይዘት መመደብ እንዲሁም የይዘት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ ሞላ ቃለ መጠይቅን ተጠቅሞ 82 ተረቶችን የሰበሰበ ሲሆን ከነዚያ የተረትነትን ባህሪ የሚያሟሉ ያላቸውን 61 ተረቶችን በአይነት እና በይዘት መድቦ ትንተና አካሂዷል፡፡

የአፋር ብሄረሰብ ተረቶች የትኩረት አቅጣጫ አብዛኞቹ ብሄረሰቡ አለኝ ብሎ የሚመካባቸው እሴቶችን ወይም ምግባራትን ማሞገሻ እና ማጠናከርያ፣ ከማህበረሰቡ ባህል እና ፍላጎት የሚያፈነገጡትን ደግሞ የሚወገዙባቸው እና የሚቀጡባቸው ባጠቃላይ ተረቶቹ የስነ ምግባር ስብከቶች መሆናቸውን በጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡ ተረቶችን ሲመድብ ለአካባቢያዊ ምደባ

ቅድምያ መስጠቱን ገልፅዋል። በዚህ መሰረትም ተረቶቹ “ተርሄ ተረሄ” እና “ሃየየኑ” በሚል አካባቢያዊ መጠርያ እንደሚታወቁ ገልፅዋል። “ተርሄ ተርሄ” በመባል የሚታወቁት ተረቶች እውነት ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው እና ስለ ብሔረሰቡ የተለያዩ ባህላዊ እምነቶች፣ ስለ ብሄረሰቡ አመጣጥ፣ ብሔረሰቡ ስላካሄደው ጦርነት ወዘተ. የሚተርኩ መሆናቸውን ገልፅዋል። “ሃየየኑ” የሚባሉት ደግሞ የፈጠራ እንደሆኑ የሚታመንባቸውና እምነትን ከማስረገጥ እና ከማፅናት ይልቅ ማህበራዊ እውነታን ማፅደቅ፣ ስነ ምግባርን ማስተማር ላይ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውን አሳይቷል። ሙያዊ መደባ በሚል ንኡስ ርእስ ደግሞ የዓፋር ተረቶች የአፈታሪክ፣ ገላጭ እና ፋቡላ በማለት በሶስት መመደብ እንደሚቻል አሳይቷል።

ተረቶቹ የሚተረቱባቸውን አጋጣሚ በተመለከተ “ተርሄ ተርሄ” ብዙ ጊዜ ቀን ላይ ሽማግሌዎች በሚገናኙባቸው ማህባራዊ አጋጣሚዎች በአደባባይ ሲሆን አልፎ አልፎ ማታማታ አባቶች ልጆቻቸውን ታሪክ ለማስተማር ሊተርኩዋቸው እንደሚችሉ ገልፅዋል። የ“ተርሄ ተርሄ” አይነት ተረቶች ተራኪዎችም ሆኑ ተሳታፊዎች አዋቂ ወንዶች መሆናቸውን፤ ተራኪዎች ሲተርኩ ተረቱን ከማን እንደሰሙትም ጭምር እየገለፁ እንደሆነ አጥኚው ገልፅዋል። “ሃየየኑ” በመባል የሚታወቁት ተረቶች ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር፣ ስነ ምግባርን ለማስተማር እና ሰዎችን ለማዝናናት እንደሚተረኩ ገልፅዋል። በብሄረሰቡ ውስጥ ተረት በመተረት የሚተዳደሩ ሰዎች እንዳሉ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል።

“የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች” በሚል ርእስ ከሁሉም በላይ በ20004ዓ.ም. ጥናት አካሂዳለች። የጥናቷ ዋና አላማ የነገዴ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ለማህበረሰቡ አባላት ያላቸው ፋይዳ መመርመር የሚል ነው። ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመጠቀም 48 ተረኮችን ሰብስባለች። የተሰበሰቡትን ተረኮች ነገዴና ጡሊ (ቅምጫ እና ቅል)፣ ነገዴ እና ነብዩ ሙሴ (ሙሳ)፣ ነገዴ  እና ግብፅ፣ ነገዴ፣ ንግስተ ሳባና አፄ ፋሲል፣ ነገዴ  እና የአካባቢው የቦታ ስያሜዎች፣ ነገዴና ሼህ ሁሴን ጅብሪል… ወዘተ. በማለት መድባ ትንተና አካሂዳለች።

የከሁሉም ጥናት ላይ  እንደ ክፍተት የሚታየው የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት እና የምርምር ጥያቄዎቹን ለመመለስ ተረኮቹ በተፈጥሮአዊ እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት መሰበሰባቸውን ብትገልፅም አፈፃፀሙ ምን እንደሚመስል በጥናቱ ዘዴ አለመግለፅዋ ነው።

በአጠቃላይ የእኔ ጥናት ከላይ ከተዳሰሱት 6 ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡ ጥናቶች ጋር ሲነፃፀር ዝምድናም፣ ልዩነትም አለው። ዝምድናቸው የእኔ ጥናትም ሆነ የእነሱ ተረትን

ከመስክ በመሰብሰብ የይዘት ትንተና በማድረግ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ነው፡፡ ልዩነቱ ደግሞ ጥናቶቹ በተለያየ ባህል ያላቸው ብሄረሰቦች ላይ የተመሰረቱ መሆኑ፤ እንዲሁም የአላማ ልዩነት ስላላቸው ነው፡፡ ከእነዚህ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፎች ከእኔ ጥናት በተሻለ መልኩ የሚቀራረብ ጥናት የሞላ ጀምበሬ ነው፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ጥናቶች የይዘት ትንተና ሲያካሂዱ የነገረ ፆታ ላይ፣ አፈታሪክ እና ተረክ ላይ፣ የተረቶቹን የአከዋወን ስልት መግለፅ ላይ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከባህላዊ ስርዓቶች ጋር ያላቸው ትስስር ማሳየት ወይም ደግሞ መግለፅ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ የሞላ ጀምበሬ ጥናት ግን ከመስክ የሰበሰባቸውን ተረቶች መመደብ እንዲሁም ደግሞ የይዘት ትንተና ማድረግ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ይበልጥ ተቀራራቢ ያደርገዋል፡፡

በእነዚህ ጥናቶች የታዩትን ጠንካራ ጎኖች ለጥናቴ ማጠናከርያነት እጠቀምባቸዋለሁኝ፡፡ በጥናቶቹ የሚታዩ ክፍተቶች ደግሞ እንደ ትምህርት በመውሰድ ክፍተቶቹን ለሞምላት ጥረት አደርጋለሁኝ፡፡

### 2.2.2. በኩናማ ብሔረሰብ ፎክሎር ላይ የተደረጉ ቀደምት የባችለር እና የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች

በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ እንደተገለፀው በኩናማ ብሄረሰብ ላይ የተደረጉ ፎክሎራዊ ጥናቶች በቁጥር እጅግ አነስተኛ ናቸው፡፡ ትኩረታቸው በኩናማ "ተረቶች" ላይ ያደረጉ ጥናቶች እስካሁን ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በተረት የተደረጉ ጥናቶች ባይኖሩም ከተረት ውጭ ባሉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ሁለት የመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፎችና አንድ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናት ተገኝተዋል፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ውጪ አንድ የኩናማ ብሄረሰብ የሰርግ ስነ ስርዓት ላይ በ2005 ዓ.ም. የተሰራ የመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ መኖሩ በትምህርት ክፍሉ ቢነገረኝም ቤተ መፃህፍት ላይ ስላልገባና ስላላገኘሁት በዚህ ጥናት ቅኝት አልተደረገበትም፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና ራቅ ያለ ነው፡፡ ነገር ግን የብሄረሰቡ ፎክሎር ላይ ምን ያህልና በምን ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥናቶች እንደተካሄዱ ለማስተዋወቅ ይረዳ ዘንድ ጥናቶቹ እንደሚከተለው እቃኛለሁ፡፡

"የአባያዊ ቋንቋዎች ዘርፍ ክፍል አንድ-አንድ የኩናማ ቋንቋ አፋዊ ኪነተ-ቃላት ስብስቦች መዘርዝር" በሚል ርእስ ኒቆዲሞስ ኢድሪስ በ1973 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ጥናት አቅርቧል፡፡ ይህ ጥናት በኩናማ ብሄረሰብ ፎክሎር ላይ ከተደረጉ ጥናቶች ቀዳሚ መሆኑ ይነገርለታል ሃፍታይ (2003) እና Angesom (2012)፡፡

የጥናቱ ዓላማ በኩናማ ብሄረሰብ ውስጥ የሚገኙ የስነቃል አይነቶችን ማስተዋወቅ ነው፡፡ የስነቃል አይነቶቹ በስም በመዘርዘር ከማስተዋወቅ ውጪ የተሰበሰበም ሆነ የተተነተነ የስነቃል ዘርፍ አላካተተም፡፡

"የኩናማ ብሄረሰብ ትውፊታዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና ተውኔታዊ አላባዎች" በሚል ርእስ ሰጉም አስመላሽ በ1999 ዓ.ም ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የኩናማ ብሄረሰብ ትውፊታዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ የሚታዩትን ወይም የሚኖሩትን የተውኔት አላባውያን ከዘመናዊ የተውኔት አላባውያን ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር፤ እንዲሁም የግጭት አፈታት ስርዓቱ ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ማብራራት እና መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ መቅድም ላይ የኩናማ ብሄረሰብ ታሪክ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ የጋብቻ ስነ ስርዓት፣ ባህላዊ ጨዋታዎች እና የሀዘን ስነ ስርዓት በተመለከተ በጣም ባጭሩ ቢሆንም ለማስተዋወቅ ሙከራ አድርጓል፡፡

ሰጉም ለጥናቱ ግብአት የሚሆን መረጃ ቃለ መጠይቅን ተጠቅሞ እንደሰበሰበ በጥናቱ ዘዴ ላይ ገልፅዋል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመላክተው በኩናማ ብሄረሰብ የግድያ ግጭት የሚፈቱ "ሳንጋኔና" በመባል እንደሚታወቁ እና ከአራቱ የኩናማ ጎሳዎች ከ "ካላዋ" ጎሳ የተመረጡ አስታራቂዎች እንደሆኑ፤ ሌሎች ቀላል ግጭቶችን የሚፈቱ ደግሞ "ላጋኬ" ተብለው የሚጠሩ በህዝብ የተመረጡ አስታራቂዎች ናቸው፡፡ የኩናማ ብሄረሰብ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ተገዢ እንደሆነ፣ ስርዓቱን የማያከብር የብሄረሰቡ አባል እንደሌለ ጥናቱ ገልፅዋል፡፡ ሰጉም ጥናቱን ያጠቃለለው የኩናማ ብሄረሰብ በዕለት ተዕለት ውሎው የሚያጋጥሙት ግጭቶች ፈትቶ ሰላማዊ ህይወት የሚያገኘው በመንግስታዊ የዳኝነት ስርዓት ሳይሆን በልማዳዊ የእርቅ ማውረጃ ዘዴዎችን በመሆኑ የእርቅ ስነ ስርዓቱን ባህላዊ እሴቱን ሳይበረዝ እንዲቀጥል አዲሱን ትውልድ እንዲያውቀው ቢደረግ የሚል ይሁንታ በመስጠት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ስር  በኩናማ ብሄረሰብ ፎክሎር ላይ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያነት አንድ ጥናት ተካሂዷል፡፡ ይህ ጥናት "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሄረሰብ" በሚል ርእስ ሃፍታይ ገብረእግዚአብሄር በ2003 ዓ.ም ያቀረበው ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በኩናማ ብሄረሰብ የሚከናወነውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና ያለውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሣወቅ፣ እንዲሁም አስታራቂ ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ምን ዓይነት ስልቶች እንደሚጠቀሙና ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደቱ ምን እንደሚመስል መግለፅ ነው፡፡ ዋና አላማውን የሚያሳኩ ዝርዝር

አላማዎችንም ተገልጸዋል፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ዘዴዎችን እንደተጠቀመ ገልፅዋል፡፡

የሃፍታይ ጥናት በግኝቱ  በኩናማ ብሄረሰብ ግጭትን የሚቀሰቅሱ ምክንያቶች ክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት እና በኃላ የተለያዩ ናቸው፡፡ በቅድመ ክርስትና ወደ ግጭት የሚያስገቡ ምክንያቶች ድንበር መግፋት፣ ሌብነት፣ ጎሳዊ አስተሳሰብ፣ መጠጥ፣ አሉባልታ ወሬዎች እና ፀያፍ ስድቦች እንደነበሩ፤ ከክርስትና ሃይማኖት መቀበል በኃላ ደግሞ ከሴቶች ጋር (በትዳር መወስለት) የተያያዙ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ ይገልጻል፡፡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን በተመለከተ ተራ ግጭቶችን “ላጋኬ” በሚባሉ ሽማግሌዎች፣ የግድያ ግጭቶችን ደግሞ “ሰንጋኔና” ወይም የአጥንት አስታራቂዎች በመባል በሚታወቁ ሽማግሌዎች እንደሚፈቱ ገልጽዋል፡፡ “ላጋኬ” እና “ሳንጋኔና” በመባል የሚታወቁ ሽማግሌዎች የሚፈቱዋቸው የግጭት ዓይነቶች እና የሚከተሉትን ስርዓት በማብራራት አቅርቧል፡፡ የኩናማ ብሄረሰብ ከየመንግስት ዘመናዊ የፍትህ አሰራር የበለጠ ባህላዊ ህጋቸውን በማክበር እና በመፍራት የሚኖሩ መሆናቸውን፤ እንዲሁም ባህላዊ ተቋሙ ለአካባቢው ሰላም እና እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይገልጻል፡፡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ የአካባቢው ዘመናዊ የፍትህ አካላት እውቅና ሊሰጡት ይገባል ሲል ጥናቱን አጠቃልሏል፡፡

በአጠቃላይ በኩናማ ብሄረሰብ ፎክሎር ላይ የተደረጉ ሁለት የመጀመርያ እና አንድ የኤም.ኤ. ጥናቶች ከእኔ ጥናት ያላቸው ዝምድና የራቀ ነው፡፡ ምክንያቱም የእነሱ ጥናቶች ከተረት ውጪ ባሉ ሌሎች የፎክሎር ዘሮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የብሄረሰቡ “ተረት” ላይ ያተኮረ ነው፡፡

እነዚህ በኩናማ ብሄረሰብ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር በአንድ ብሄረሰብ ፎክሎሮች ላይ የተካሄዱ በመሆናቸው፤ እነሱም በጥናታቸው መግብያ ላይ ስለ ብሄረሰቡ ዳራ እና ባህል በጥቂቱ መዳሰሳቸው፣ በእኔ ጥናት ውስጥ ደግሞ ከነሱ ሰፋ ባለ መልኩ የብሄረሰቡ አካባቢያዊ ዳራ በጥናቴ ምዕራፍ ሶስት ላይ መዳሰሴ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የኩናማ ብሔረሰብ አጠቃላይ ዳራዎች

ይህ ምዕራፍ ጥናቱ የተካሄደበትን ኩናማ ብሔረሰብ አጠቃላይ ገፅታ የሚያስተዋውቅ ነው። በስሩም የኩናማ ብሔረሰብ አመጣጥ ታሪክ፣ ቋንቋ እና እምነት፣ መልከዓ ምድር፣ የአየር ንብረት እና ስነ ህዝብ፣ ኢኮኖሚ እና የኩናማዎች የስም አወጣጥ ስርዓት በተመለከተ በአጭሩ ገለፃ ይቀርባል። የብሔረሰቡ ዳራዊ ማስረጃዎችን ያካተትኩት ከመስክ የተሰበሰቡትን ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ለመተንተን አጋዥ ሆኖ ስላገኘሁት ነው። "አንድን ተረት ለመረዳት የባለቤቱን ባህል ማወቅ ይገባል" በማለት (Fischer, 1963, 247) እንደገለፀው እነዚህ ማስረጃዎችም በሚቀጥለው ምዕራፍ ለሚደረገው ትንተና የራሳቸው ድርሻ አላቸው የሚል እምነት አለኝ።

## 3.1. የኩናማ ብሔረሰብ አመጣጥ ታሪክ

የኩናማ ብሔረሰብን ጥንተ አመጣጥ በማያሻማ መንገድ የሚገልጽ የታሪክ ወይም የምርምር ሰነድ ማግኘት አልተቻለም። በብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚሉት የኩናማ ብሔረሰብን አመጣጥ በተመለከተ አንድ ቁርጥ ያለ መደምደምያ እንደሌለ ነው ሃፍታይ (2003)፣ Angesom (2012)። እንደሌሎች ብዙ የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የኩናማ ብሔረሰብም ታሪካዊ አመጣጡን ቃላዊ በሆነ መልኩ ይተርካል እንጂ ፅሑፋዊ የሆነ ሰነድ እምብዛም ነው። ይህ እንደዚህ ሆኖ የብሔረሰቡ ታሪክ አዋቂዎች፣ የሀገር እና የውጭ ፀሐፊዎች ስለብሔረሰቡ አመጣጥ ታሪክ የሚሰጡትን ሀሳብ እንደሚከተለው ነው።

የኩናማ ብሔረሰብ የዘር ሀረጋቸው መቁጠር የሚጀምሩት ከአክሱም ንጉስ ባዜን እንደሆነ ብርሃነ (2003፣2); Angesom (2012፡1); Nikodimos (1987:17); Alexander (1982:3) ይገልፃሉ። ንጉስ ባዜን ከልደተ ክርስቶስ በፊት ስምንት ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በኃላ ደግሞ ዘጠኝ ዓመት በአጠቃላይ 17 ዓመት በንግስነት እንደቆየ ታየ ገብረማርያም (1955፣62) ገልፀዋል። የንጉስ ባዜን ባለቤት ንግስት "ኩናሜ" እንደነበረች እና ለኩናማ ብሄረሰብ የስም መጠርያ መነሻ እንደሆነች Nikodimos (1987:17) ገልጸዋል። እንዲሁም የብሔረሰቡ ተወላጅ የሆኑት አቶ ግደይ ቱርካ ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ የብሔረሰቡን አመጣጥ እንዲህ ሲሉ ያብራራሉ።

*እኛ ኩናማዎች ጥንተ አመጣጣችን ከአክሱም ነው። አባታችን ንጉስ ባዜን ሆኖ የምንጠራውም በሚስቱ በእናታችን ንግስት ኩናሜ ነው። ንጉስ ባዜን ንግስና ላይ በነበረበት ወቅት ተደጋጋሚ ጦርነቶች ይገጥሙት ስለነበር በአንድ ወቅት በገጠመው ጦርነት ተሸንፎ ህይወቱ አልፏል። በንጉሱ ሞት የተደናገጠው የኩናማ ህዝብ ከውቕሮ ክልተ ኣውላዕሎ በመጣ ንጉስ ዳጌና ተገፍቶ "አቦ" በሚባል ወንድ እና "ኣዳቦ" በምትባል የኩናማ ተወላጆች እየተመራ አክሱምን ለቆ ወደ ሽረ መጣ (አቶ ግደይ ትርኺ ጥር 13፣2009 ዓ.ም)።*

አቶ ብርሃነ ኬኖ፣ አቶ ገብረሚካኤል ገራሬ፣ አቶ ነጋ ሚኮ እና አቶ ሃይለ ወለላ ካደረግኩላቸው ቃለ መጠይቅ እንደተረዳሁትም የኩናማ ብሔረሰብ "ጥንተ አመጣጣችን ከአክሱም ነው" የሚል እምነት እንዳለው ነው። ሃፍታይ (2003) በበኩሉ ስለ ኩናማ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ ሲያብራራ ገብረኪዳን ወልደሃወርያትን ጠቅሶ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍርዋል።

*የኩናማ ብሄረሰብ የትውልድ ዘር ሐረጋቸው ከአክሱማዊው ንጉስ ባዜን በማገናኘት መቁጠር ይጀምራሉ። ከንጉስ ባዜን በፊትም አክሱም አካባቢ ይኖሩ እንደነበር እና በቦታው ከፍ ያለ አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ይነገራል (ሃፍታይ፣ 2003፣ 14)።*

በመካከለኛው ትግራይ በየወቅቱ ይከሰቱ በነበሩ ግጭቶች እና ጦርነቶች እየተሸነፈ እና እየሸሸ በአሁኑ ጊዜ ወደ ሚገኝበት ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ እንደደረሰ፣ ከሽረ ተነስቶ የአዲያቦ መሬት ረግጦ ባድመ፣ ኤሬነ፣ ቢያራ ወደ ተባሉ ሰፍራዎች እንደደረሰ፤ ከዚያም ህዝቡ በሁለት ጎራ ተከፋፍሎ አንዱ ጎራ የመረብ ወንዝ ተሻግሮ ወደ ኤርትራ መሄድ እንደመረጠ ሌላው ደግሞ በተጠቀሱት የትግራይ መሬቶች ለረዥም ዘመናት እንደኖረ ነው።

ከዚህ ሀሳብ ለየት ባለ መልኩ የኩናማ ብሄረሰብ የመጣው ከሱዳን ነው የሚል እምነትም አለ። ሃፍታይ Travaskis (1980) ጠቅሶ እንደገለፀው፣ ኩናማዎች ከሱዳን የመጡ ህዝቦች ናቸው የሚል መላምትም አለ። ኩናማዎች የኤርትራ ቀደምት ነዋሪዎች እንደሆኑ እንደሚታመን እና ከሚኖሩበት ጫካ በምስራቃዊ ሱዳን ወደ ጋሽ እና ሰቲት የተባሉ ቆላማ ቦታዎች ተበትነዋል ብሎው የሚያምኑ ምሁራን እንዳሉ ሃፍታይ (2003፣15) ገልፅዋል። ብርሃነ ሃይለስላሰ በበኩሉ ይህንን መላ ምት እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል።

*ኩናማዎች ለመጀመርያ ጊዜ የሰፈሩበት ልዩ ቦታ በኢትዮጵያ እና ሱዳን ጠረፍ ሲሆን ቆይቶ ወደ መካካለኛው የትግራይ አካባቢ በመጉረፍ በአክሱም ከተማ እና አካባቢዋ በንጉስ ባዜን እየተመራ ሲኖር የነበረ ህዝብ ነው (2003፣3)፡፡*

በማለት ከአክሱም ተገፍቶ ነው ወደ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ የሄደው የሚለውን ሀሳብ መጀመሪያ በሱዳን ጠረፍ አካባቢ ይኖር የነበረ መሆኑን በመግለፅ ይቃረነዋል፡፡

የኩናማ ብሄረሰብ ኒሎ ሳሃራን ተብሎ ከሚጠራ የቋንቋ ቤተ ሰብ ከሚናገር ነገድ የሚመደብ እንደሆነ Angesom (2012:16)፣ Bender (2000:54)፣ ብርሃነ (2003፣2) ይገልፃሉ፡፡ "አድያቦና" መፅሔትም "የኩናማ ብሄረሰብ ኒሎ ሳሃራን ተብሎ ከሚታወቅ ነገድ የሚመደብ ሲሆን የዚህ ነገድ ቋንቋ ተናጋሪዎች በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ሲሆን ለመጥቀስ ያክል እነ አኝዋክ፣ በርታ፣ ጉምዝ፣ ኑዌር… የመሳሰሉ ናቸው" (አድያቦና፣ 2001፣ 30) በማለት ገልፀዋል፡፡

አንዳንድ ፅሑፎች እና የብሔረሰቡ ተወላጆች የሚሉትን ሐሳብ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የኩናማ ብሄረሰብ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ጀምሮ አክሱም አካባቢ ይኖር የነበረ ህዝብ ነው፡፡ የብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ ከአክሱም ሆኖ በየወቅቱ ባጋጠሙት ጦርነቶች፣ ኃላ ደግሞ በንጉስ ባዜን መሞት ምክንያት አቅሙ ተዳክሞ አክሱምን ለቆ አሁን ወደ ሚገኝበት አካባቢ እንደተበታተነ ይነገራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከሱዳን ምስራቃዊ ጫካ መጥተው ወደ መኸል ትግራይ ነው ግዛታቸውን ያስፋፉት የሚል የእነ Travaskis (1980) ሀሳብ ቢኖርም፣ የበለጠ የታሪክ ጥናት እና ምርምር ተካሂዶ የዚህን ብሔረሰብ ትክክለኛ አመጣጥ የሚገልፅ ሰነድ እስኪገኝ ድረስ ግን ከኩናማ ብሔረሰብ አፈታሪኮች እና የኬት መጣን ተረኮች በመነሳት ብሔረሰቡ ከአክሱም እና አካባቢው ፈልሶ አሁን ወዳለበት ቆላማ እና በረኸማ ስፍራ የመጣ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 3.2. የኩናማ ብሔረሰብ ቋንቋ እና እምነት

የኩናማ ብሔረሰብ ቋንቋ ከኒሎ ሳህራዊ የቋንቋ ቤተ ሰብ የሚመደብ ሲሆን "ኩናማ" ይባላል፡፡ ኩናማ የሚለው ቃል ለህዝቡም ለቋንቋውንም መጠሪያነት ያገለግላል፡፡ ኩናምኛ ከኒሎ ሳሃራን የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ እንደሆነ ብዙ ተመራማሪዎች Bender (2000:54); Alexander (1982:1); እና Angesom (2012:5) ገልፀዋል፡፡ የኩናማ ብሔረሰብ ከኩናምኛ ቋንቋ በተጨማሪ ትግርኛ እና አማርኛ ለመግባብያነት ይጠቀማል፡፡ እንዳንድ የብሔረሰቡ ተወላጆች እንደነገሩኝ እና ተዘዋውሬ እንደተመለከትኩት በአዋሳኝ አካባቢ የሚኖሩ የብሄረሰቡ

አባላት አብዛኞቹ ትግርኛ በደምብ ይጠቀማሉ። የወረዳው የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ የሆኑት ብርሃነ ኬኞ ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ እንደሚሉት አብዛኛውን የኩናማ ነባር ባህል በትግርኛ ተናጋሪዎች ባህል (በነሱ አጠራር በሐበሻ ባህል) እየተዋጠ እንደሆነ እና ህዝቡ በእለት ተእለት እንቅስቃሴው ትግርኛ በብዛት እንደሚጠቀም፤ እንዲሁም በኩናምኛ ሲነጋገሩ የትግርኛ ቃላት እየደባለቁ እንደሚያወሩ ገልፀውልኛል (ብርሃነ ኬኞ፣ ጥር 19፣2009 ዓ.ም)።

የኩናማ ብሔረሰብ እምነት በተመለከተ ቀደም ባሉ ጊዜያት የራሳቸውን ባህላዊ እምነት ይከተሉ ነበር። የብሔረሰቡ ተወለጆችና አንዳንድ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች Nikodimos (1973:11); Angesom (2012:3) እና ብርሃነ (2003፣30-31) እንደገለፁት የኩናማ ብሄረሰብ እስከ 1942 ዓ.ም የባህላዊ እምነት ተከታይ ነበር። በእምነታቸውም በታላላቅ ዛፎች እና መቃብሮች ያመልኩ ነበር። አቶ ግደይ ቱርካ ስለ እምነታቸው ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ።

> *በድሮ ጊዜ ኩናማ የራሱ የሆነ ጠንካራ እምነት ነበረው። የታላላቅ ወላጆቹ መቃብር እና ታላላቅ ዛፎች ላይ ሲደርስ አረፍ ብሎ፣ ሰግዶ እና ጸልዮ ይሄድ ነበር፤ እንዲሁም “ቢሻ” የሚባል ከማሽላ እና ሰሊጥ የሚሰራ የኩናማ ባህላዊ ምግብ በጥብጦ ጠጥቶ፣ ከዛፉ ስር ወይም ከመቃብሩ ላይ አፍስሶ ይኄዝ ነበር። መቃብሩ ላይ ወይም ዛፉ ላይ የሚደፋበት ምክንያት ሟቹ ሊጠቀምበት ይችላል፤ በስጋ እንጂ በመንፈስ ከእኛ አልተለየም በሚል እምነት ነው። ከ1942 ዓ.ም በኃላ ግን በአቡነ ይሳቅ ተጠመቅን፤ የመድኃኒአለም ቤተ ክርስቲያን ተሰራልን። አሁን ሁሉንም የኩናማ ህዝብ ክርስትያን ነው (አቶ ግደይ ቱርካ፣ 14፣2009ዓ.ም)።*

በ1942 ዓ.ም በአቡነ ይስሐቅ የተባሉ የትግራይ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ጳጳስ መሪነት በሽራሮ ከተማ ቤተ ክርሰትያን እንዲሰራ ተደረገ። ከዚያም ቀስ በቀስ በሰባክያነ ወንጌል እየተማረ እና እየተጠመቀ የክርስትና ሃይማኖት ተቀብለዋል።

ብርሃነ ሃይለስላሰ (2003፣30-31) በበኩሉ ይህንን ሀሳብ ይጋራል። በዚህም በአሁኑ ሰዓት በትግራይ ውስጥ የሚኖሩ ኩናማዎች ሙሉ በሙሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ናቸው።

## 3.3. መልከዓ ምድር፣ የአየር ንብረት እና ስነ ህዝብ

የኩናማ ብሔረሰብ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች አንዱ ሆኖ የራሱ የሆነ የመገኛ ስፍራ ያለው ብሔረሰብ ነው፡፡ ይህ ብሔረሰብ በትግራይ ክልል ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች ይገኛል Angesom (2012:13):: የመልከአ ምድር አቀማመጡ ኮረብታማ እና ተራራማ ሲሆን ለመተ ጋገዝ እና ጠላት ለመከላከል በሚመች መልኩ ቅርብ ለቅርብ ቤት ሰርተው ይኖራሉ፡፡ በመስክ ተገኝቼ እንደተመለከትኩት እና የብሔረሰቡ ተወላጆች እንደገለፁልኝ የኩናማ ብሔረሰብ አሰፋፈሩ ኮረብታማ እና ለጦርነት እስትራቴጂ በሚመቹ ሰንሰለታማ ኮረብታዎች ላይ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ቀደም ባሉ ግዚያት ብሔረሰቡ በቅርብ ከሚገኙ ትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች (በኩናማ ብሄረሰብ አባባል ከ “ሐበሾች” ጋር) በየጊዜው ጦርነት ይገጥሙ ስለነበር ለመከላከል እና ጠላት ከሩቅ ሲመጣ በቀላሉ ለማየት ሲባል እንደሆነ ነው፡፡

የኩናማ ብሄረሰብ በብዛት የሚገኝበት የታሕታይ አድያቦ ወረዳ የቆዳ ስፋት 353,655 ሄክታር ሲሆን 18 ቀበሌዎች እና 65 ጎጦች አሉት፡፡ ከዚህ የቆዳ ስፋት 25% በደን የተሸፈነ ሲሆን ቀሪው 75% ደግሞ ቆላ እና ከፊል በረሃማ የአየር ፀባይ አለው (Nikodimos,1987:13)፡፡

### የኩናማ ብሄረሰብ የሚገኝበት አካባቢ የሚጠቁም ካርታ




በትግራይ ክልል የሚገኙ የኩናማ ብሔረሰብ በሰሜን ምዕራብ ዓዲጎሹ እና ሒለት ኮካ የተቀሩት ደግሞ አድመይቲ፣ መንጠብጠብ፣ ገዛ መቐር፣ ገዛ አዱራ፣ መዳበ፣ ዕርዲ ወያነ፣ ሽምብሊና፣ ዋዕላ ንህቢ እና ቢያራ በሚባሉ ቀበሌዎች ተበታትነው እንደሚኖሩ Angesom (2012:13) እና ሃፍታይ (2003፣20) አስፍረዋል፡፡ እንዲሁም የወረዳው ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊ የሆኑት አቶ ብርሃነ ኬኞ ነግረውኛል፡፡

የኩናማ ብሔረሰብ የህዝብ ብዛት በተመለከተ በ1999ዓ.ም በተካሄደው የህዝብና የቤት ቆጠራ መረጃ መሠረት ከወረዳው የመንግስት እና ህዝብ ግንኙነት ጽህፈት ቤት የተገኘው አሃዛዊ መግለጫ 4860 መሆኑ ሲያሳይ (አድያቦና መጽሄት፣2001ዓ.ም) እንደ የኩናማ ብሔረሰብ

ተወካይ እና የወረዳው የባህል እና ቱሪዝም ኃላፊ የሆኑት አቶ ብርሃነ ኬኞ ገለፃ ደግሞ በአሁኑ ወቅት የኩናማ ብሔረሰብ የህዝብ ብዛት 7000 አካባቢ ይገመታል፡፡ በታሕታይ አድያቦ ለምለም አካባቢ 3300 በአደባይ እና ሒለት ኮካ 3100 የተቀሩት 600 ደግሞ በተለያዩ ከተሞች ይገኛሉ፡፡

## 3.4. ኢኮኖሚ

ቀደም ባሉ ዘመናት የኩናማ ብሔረሰብ ዋነኛ መተዳደርያው አደን ነበር፡፡ እንዲሁም በየሄደበት ፍራፍሬ በመልቀም እና ስራስር በመቆፈር ነበር የሚኖረው፡፡ እንደ አቶ ገብረሚካኤል ገራሬ እና አቶ ሰሎሞን ገብረክርስቶስ ገለፃ የኩናማ ብሔረሰብ የክርስትና ሃይማኖት ከመቀበሉ እና ከትግርኛ ተናጋሪ ማህበረሰብ ከመቀራረቡ በፊት ያገኘውን አድኖ ነበር የሚበላው፡፡ እንዲሁም ዓየ፣ መቑዕ፣ ሳዳ፣ መልያ የሚባሉ በአካባቢው የሚበቅሉ ፍራ ፍሬዎች ለቅሞ ይበላ ነበር (ገብረሚካኤል ገራሬ እና ሰሎሞን ገብረክርስቶስ፣ ጥር 28፣2009ዓ.ም)፡፡

በአሁን ጊዜ ግን የኩናማ ብሔረሰብ ኑሮ የተመሠረተው በዋናነት በእርሻ ነው፡፡ ከብሔረሰቡ 85% የሚሆነው ህዝብ በእርሻ ይተዳደራል፡፡ ባህላዊ እና ዘመናዊ የአተራረስ ስልት በመጠቀም ማሽላ፣ በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ ዳጉሳ፣ ገብስ እና ስንዴ የመሳሰሉት የሰብል ዓይነቶች ያመርታል፡፡ ከእነዚህ ሰብሎች ሰሊጥ ዋነኛው የገቢ ምንጭ ነው፡፡

ከብሔረሰቡ 10% የሚሆኑት ደግሞ በእደ ጥበብ ይተዳደራሉ፡፡ የሰንበሌጥ ውጤቶችን፣ ወንበር ኩርሲ እና የገመድ አልጋ በመስራት ወደ ሽራሮ፣ ሑመራ እና ሽረ ከተሞች ወስደው በመሸጥ ገቢ ያገኛሉ፡፡ የተወሰኑ የብሔረሰቡ አባላት ደግሞ በሚኖሩበት መንደር እና በአቅራቢያቸው ባለው ከተማ ተወዳጅ የሆነውን “ዳጋ” የተባለ የብሔረሰቡ ባህላዊ መጠጥ በመሸጥ ይተዳደራሉ፡፡ የቀሩት 5% የብሔረሰቡ አባላት ደግሞ ከብት በማርባት እና በእረኝነት ይተዳደራሉ፡፡ ከብት፣ ፍየል፣ ግመል እና አህያ በማርባት ኑሮዋቸውን ይገፋሉ (የወረዳው ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ብርሃነ ኬኞ፣ ጥር 10፣2009ዓ.ም)፡፡

## 3.5. የኩናማዎች የስም አወጣጥ ስርዓት

የኩናማ ብሔረሰብ የሚታወቅባቸው በርካታ ያልተበረዙ ስነ ስርዓቶች ያለው ብሔረሰብ ነው፡፡ ሌላ ባህል እና ሃይማኖት እንዲሁም የተለየ የአኗኗር ዘይቤ ባላቸው ህዝቦች ባህል ተፅዕኖ ሳያድርበት የራሱን ባህል እና እምነት ጠብቆ ቆይቷል፡፡ ብሔረሰቡ ከሚታወቅባቸው እና

ለየት ያለ ሆኖ ያገኘሁትን የስም አወጣጥ ስርዓታቸውን ለማስተዋወቅ ጥርት አደርጋለሁኝ። ይህንን ስርዓት እዚህ እንዲካተት ያደረኩበት ምክንያት ደግሞ ከአንድ የኩናማ ስያሜ በስተጀርባ አንድ ራሱን የቻለ ትረካ ያለ በመኾኑ እና ከጥናቱ ጋር ይሄዳል ብዬ ስለማምን ነው።

መረጃ ለመሰብሰብ መስክ ላይ በቆየሁበት ወቅት ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ አንዱ የሆኑት የወረዳው የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ እንዲሁም የኩናማ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑት አቶ ብርሃነ ኬኞ ጋር ጥር 10፣2009 ዓ.ም ቢሮዋቸው አካባቢ ሻይ ቡና እያልን የጥምቀት በዓል አከባበር በኩናማዎች ዘንድ ምን እንደሚመስል ማየት እንደምፈልግ ስነግራቸው ጥያቄየን በደስታ ነበር የተቀበሉት። "እንዲያውም ካለኝ የስራ እና የስብሰባ ብዛት ነገ ከእኔ ጋር መሆንህ ሰፊ ጊዜ ይኖረናል፤ በዚያውም ብሔረሰቡ በብዛት ያለበትን አካባቢ ትጎበኛለህ" በማለት መልካም ፍቃዳቸውን ገለፁልኝ። እንዲህ እየተጫወትን ሳለ አንድ ጓደኛቸው መጣ እና "ቦሶ" ብሎ በመጥራት ሰላም አላቸው። እኔም "boss" የሚለውን የኢንግሊዘኛ ቃል ለመጠቀም ፈልጎ ይሆናል ብየ ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር።

በነጋታው በጥዋቱ ተገናኝተን የጥምቀት በዓል ወደ ሚከበርበት ቦታ በእግር እየተጓዝን ሳለ ሰውየው ታዋቂ ከመሆናቸው የተነሳ ብዙ ሰው ነበር ሰላም የሚላቸው። ታድያ ሰላም ሲሉዋቸው የተለያዩ ስሞች እየጠሩ ነበር። እኔም "ትክክለኛ ስምህ ብርሃነ ተብሎ ነው የተነገረኝ፣ ሰዎች ግን በተለያዩ ስሞች ሲጠሩህ እየሰማሁኝ ነው ለምንድን ነው?" ብየ ጠየቅኩዋቸው። የሰጡኝን ምላሽ ትኩረቴን ስለሳበው እንሆ የስም አሰጣጥ ስርዓታቸውን በተመለከተ የበለጠ እንድጠይቅ እና መዛግብት እንዳገላብጥ ምክንያት ሆኖኝ ለማስተቃወቅ ፈለኩኝ።

የኩናማ ብሔረሰብ ከሌላው ብሔረሰብ የሚለይበት እኔ ከማውቀው የትግርኛ እና አማርኛ ተናጋሪ ህዝብ የተለየ የስም አወጣጥ ስርዓት አለው። አንድ ሰው ወላጆቹን ያወጡለት ስም ፀንቶለት በሱ ብቻ የሚጠራ ሳይሆን በነዋሪዎች እና ዘመድ አዝማዱ የሚጠራባቸው ከአስር በላይ ስሞች ይኖሩታል። ከእነዚህ ስሞች በጣም የታወቀ እና የተለመደ ስም "ኡዳኪዳ" ይኖረዋል። ብረሃነ ሃይለስላሰ ይህንን በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍረዋል።

> *ተወለድቲ ብሄረሰብ ኩናማ ኣብ ሓደ ጣብያ ወይ ከዓ ቁሸት ብሓባር እናተቐመጡ ናይ ሓደ ሰብ ፍሉጥ መፀውዒ ንምፍላጥ ብጣዕሚ እዩ ዘፀግም። ምኽንያቱ ስም*

*እንትወፅእ ወድዓዊ ኩነታት እናተረዳእካ ናሃቱ ዓሌት ይኹን ነባራይ ብዝመስሎ ናይ ምስያም መሰሉ ሕልው እዩ (ብርሃነ፣2003፣ 47)።*

*የኩናማ ብሔረሰብ ተወላጆች በአንድ ቀበሌ ወይም ጎጥ አብረው እየኖሩ የአንድ ሰው የታወቀ መጠርያ ለማወቅ በጣም ነው የሚያስቸግረው። ምክንያቱም ስም ሲወጣ ወቅታዊ ሁኔታ እየተገነዘቡ ዘመድ አዝማዱ ይሁኑ ነዋሪዎቹ በመሰላቸው የመሰየም መብታቸው የተጠበቀ ነው (ብርሃነ፣2003፣ 47)።*

በኩናማ ብሔረሰብ ለአንድ ህጻን ስም ሲያወጡለት አብዛኛውን ጊዜ ከአጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ ነው። ህጻኑ በተወለደበት ወቅት ያጋጠሙ ለየት ያሉ ክስተቶች ካሉ ለህጻኑ መጠርያ ይሆናሉ። በኩናማዎች አንድ ህጻን በእንስሳ፣ በተራራ፣ በቦታ፣ በገጠመኝ ሊጠራ ይችላል።

የብሐየረሰቡ ተወላጅ እና የጎሳ መሪ የሆኑት አቶ  ግደይ ቱርካ ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ እንደገለፁልኝ በኩናማ ብሔረሰብ አንድ ህጻን ተወልዶ እስኪ ጎረምስ ድረስ በርካታ ስሞች ይኖሩታል ብለዋል። “ለምሳሌ አባቱ ከእንስሳ ጋር ገጥሞ ከነበረ ያንን ለማስታወስ ልጁ በእንስሳው ይጠራል። ለምሳሌ “ኮይታ” የምንለው ሰው አለን። አባቱ ከነብር ጋር ገጥሞ ነበር ያንን ለማስታወስ “ነብሮ” እንደ ማለት ነው። አሁን ብርሃነ ስሙ “ቦሶ” ነው ሲወለድ በጣም ወፍራም ስለ ነበር ነው። “ቦሶ” ቦርጫም እንደ ማለት ነው” በማለት አብራርተውልኛል (ግደይ ቱርካ ጥር 14፣ 2009ዓ.ም)።

የኩናማ ብሔረሰብ የስም አወጣጥ ስርዓት ከገጠመኝ እና ከታሪክ ጋር የተያያዘ መሆኑ የሚያሳዩ በርካታ ስሞች አሉ። ለምሳሌ “ወለጋ”፣ “ጅግጅጋ” የሚሉ ስሞችን አግኝቻለሁኝ። ትርጉማቸውም በእነዚህ ስሞች የሚጠሩ ሰዎች አባቶቻቸው ወለጋ እና ጅግጅጋ ደርሰው ከተመለሱ በኃላ ስለተወለዱ ነው።  “አባይ” የሚባል የሶስት አመት ህጻን አግኝቼ አባይ የተባለበትን ምክንያት ስጠይቅ አባቱ የአባይን ግድብ ሊጎበኝ ሂዶ ሚስቱ ወልዳ ስለጠበቀችው እንደሆነ ወይዘሮ ውጁ ሚኮ (ጥር 14፣2009ዓ.ም) ነግረውኛል።  እንዲሁም “ሻብያ”፣ “ወራር”፣ “ገምሃሎ” እና “ባድመ” የሚል መጠርያ ያላቸው የብሔረሰቡ አባላት አሉ። ይህንን መጠርያ ሊይዙ የቻሉት በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ወቅት ስለተወለዱ እና አባቶቻቸው ወደ እነዚህ ግንባሮች ዘምተው ስለነበር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ህጻኑ ወይም ህጻኗ ሲወለዱ ኃይለኛ ዝናብ ከነበረ፣ የህጻኑ ወላጆች የአረም ወይም የአውድማ ዘመቻ ከነበራቸው በዚያ አጋጣሚ ስም ይሰጣቸዋል። ለምሳሌ “አምሊ”

የምትባል ሴት አለች። እሷ ስትወለድ ኃይለኛ ዝናብ ስለነበር እና አላስወጣ አላስገባ ስላላቸው ያወጡላት ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በኩናማ ብሔረሰብ የስም አወጣጥ ስርዓት ላይ ዘመድ አዝማድ እና በርካታ ነዋሪዎች የሚሳተፉ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ግን የአንድን ህጻን ስም በመስጠት ቅድሚያ የሚሰጣቸው አጎቶች (በእናት በኩል)፣ አባት እና እናት ናቸው። የህጻኑ መጠርያ ስም የሚወጣለት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ አራስ ለመጠየቅ ሲሄዱ ነው። "እንኳን በሰላም ተገላገለሽ" ለማለት እና ሊጠይቁዋት ሲሄዱ "በሉ እኔ እገሌ ብየዋለው ብለው ስም አውጥተውለት ይሄዳሉ (ብርሃነ ኬኞ፣ ጥር 11፣2009 ዓ.ም)።

ሌላው በኩናማ ብሔረሰብ የስም አወጣጥ ስርዓት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው "ኣናኢላ" የሚባል ስነ ስርዓት አለ። በኩናማ ብሔረሰብ ወንዶች ከልጅነት ወደ ጉርምስና መሸጋገራቸውን የሚያረጋግጡበት "ኣናኢላ" የሚባል ከበራ አላቸው። ይህ "የመላጨት ስርዓት" ነው። ለአቅመ አዳም የደረሱ ወጣቶች ሰብስበው ወደ በረኻ በመውሰድ ወንድነትን የሚፈትኑ ፈተናዎች ይፈትኑዋቸዋል። ከዚያም ፈተናው እንዳለፉ ፀጉራቸውን ላጭተው በ "አ" የሚጀምር አዲስ ስም ያወጡላቸዋል። ለምሳሌ "አበዳር"፣ "አማማ"፣ "አጊዳር"፣ "አሱጋ"፣ "አሎንጋ"… በማለት ይጠሩዋቸዋል (ብርሃነ፣ 2003፣ 11)። እነዚህ ስያሜዎች የመላጨት ስነ ስርዓት የተካሄደበት አጋጣሚ ወይም ወቅት ያሳያሉ። ለምሳሌ ሳር ወይም ልምላሜ ባለበት ወቅት ከተላጨ "አሰና" የሚል ስም ይወጣለታል።

# ምዕራፍ አራት

# 4. የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና

ይህ ምዕራፍ ሁለት ዓበይት ርእሶች አሉት፡፡ የመጀመርያው ከኩናማ ብሄረሰብ የተሰበሰቡ ተረቶች ምደባ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በተመረጡ ተረቶች ላይ የይዘት ትንተና የተካሄደበት ነው፡፡

## 4.1. የተረት ምደባ

ይህ ንኡስ ርእስ ከመስክ የተሰበሰቡትን የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በምዕራፍ ሁለት ባደራጀሁዋቸው አንፃሮች አማካይነት ተረቶቹን ለመመደብ የምሞክርበት ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በአካባቢያዊ እና በምሁራን የመመደብያ ስልቶች ተመድበዋል፡፡

### 4.1.1. ከአካባቢያዊ ምደባ አንፃር

በአካባቢያዊ ምደባ አንፃር የኩናማ ብሔረሰብ አባላት ተረቶቹን ለመመደብ የሚጠቀሙባቸው መስፈርቶች እውነተኛ (Fact) ወይም የፈጠራ (Fiction) መሆናቸውን እና የሚተረኩበትን ዓላማ ናቸው፡፡ በዚህ መስፈርት መሰረትም የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶቹ “ሳማ ኬካ” እና “ኔላ ሳማ” ተብለው በሁለት ይመደባሉ፡፡

#### ሀ. ሳማ ኬካ

“ሳማ ኬካ” ተብለው የሚታወቁ የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ስለ ብሔረሰቡ ጥንት አመጣጥ፣ የቦታ እና የጎሳ ስያሜዎች፣ ብሔረሰቡ ስላካሄዳቸው ጦርነቶች፣ ስለ ነገስታት እና የጎሳ መሪዎች ጀግንነት፣ ስለ ፍርድ አሰጣጥ፣ ወዘተ. የሚተርኩ ናቸው፡፡ ተረቶቹ በብሔረሰቡ አባላት እውነት ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ እንደገለፁልኝ “ሳማ ኬካ” በመባል የሚታወቁ ተረቶች ብሔረሰቡ ያለፈባቸውን እውነተኛ የታሪክ አጋጣሚዎች፣ ስላጋጠሙት ፈታኝ ወቅቶች፣ ስለ አሰፋፈሩ፣ ስለ ጎሳዎች እና ቦታዎች ስያሜዎች አመጣጥ ወዘተ. የሚተርኩ እና እውነት ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው (አቶ ግደይ ቱርኳ፣ አቶ ሃይለ ወለላ፣ ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ የካቲት 21/2009 ዓ.ም)፡፡ በአጠቃላይ ከተሰበሰቡት ተረቶች መካከል አስር ተረቶች በዚህ

ምድብ ስር የሚካተቱ ናቸው። ከእነዚህ ተረት ሃምሳ ሰባት በማሳያነት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ተረት ሃምሳ ሰባት የኩናማ ብሔረሰብ በየወቅቱ ሲያጋጥሙት ከነበሩ አደጋዎች እንዴት እንዳመለጠ እና ዘሩ እንዴት ማስቀጠል እንደቻለ የሚተርክ ነው።

> *በድሮ ዘመን በኩናማ እና በሌሎች ህዝቦች መኻከል ጦርነት ነበር፡፡ ሁሌ ሽሽት እና ስደት ነበር፡፡ ኩናማዎቸ ጠላት ሲመጣ  እና ሲሰሹ አካል ጉዳተኛ እና አቅመ ደካማ ሽማግሌዎች ሲኖሩ በጠላት እጅ እንዳይወድቁ በማለት ገድለው ነበር የሚተውዋቸው ይባላል፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ጠላት ይመጣባቸው እና ዘበኞች አዋጅ ያውጃሉ፡፡ "ጠላቶቻችን እየመጡ ስለሆነ ጓዛቹህን ጠቅልሉ፣ አቅመ ደካሞቹን ግደሉ እና ቅበሩ" ይላሉ፡፡ ከዚያ አንድ ወጣት የተባለውን ነገር ሽማግሌ አባቱን  ይነግራቸዋል፡፡ አባቱም "ሽማግሌ ብሆንም እጠቅምሀለው እና ሳትገድል ከጓዞችህ ጋር ደብቀህ ግመሉ ላይ ውሰደኝ" አሉት፡፡ ሌሎች ሽማግሌዎች እና አቅመ ደካሞቹን ገድለው ጓዛቸውን ጠቅልለው ለሽሽት ሲዘጋጁ እሱ ግን አባቱን ከእቃ ጋር ደብቆ ገመል ላይ ጭኖ ጉዞ ጀመሩ፡፡ የት ደረስን ብለው ሲጠይቁት የደረሱበትን ይነግራቸው ነበር፡፡*
>
> *ፀሐይ ልትጠልቅ ስትል እንደዚህ ያለ ቦታ ላይ ደረስን አላቸው፡፡ "በል ሜዳ ላይ እንዳታርፍ፣ ወደ ከረብታማው ቦታ ወጣ ብለህ ከግድሙ እረፍ" አሉት፡፡ ሌላው ህዝብ ሜዳው ላይ ተዘርግቶ ሲያርፍ እሱ ግን ከፍ ወዳለ ቦታ ሂዶ አርፈ፡፡ በነጋታዉም ሲጓዙ ውለው ከአንድ ትልቅ ሸለቆ/ወንዝ ዳር ለማደር ህዝቡ አረፈ፡፡ እሱ ግን "ከሸለቆው ወጥተህ ተራራው ላይ እረፍ" አሉት፡፡ እንደዚያም አደረገ፡፡ ከዚያም ለሊት በዚህ መጣ የማይባል ጎርፍ መጥቶ ድካም ላይ የሰነበተውን ህዝብ ጠራርጎ ሲወስደው እሱ እና ቤተሰቡ ብቻ ቀሩ፡፡ ከዚያ በኃላም በሽማግሌ ሰውየው ምክንያት ነው የኩናማ ህዝብ ዘር የቀጠለው ይባላል፡፡ (ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ የካቲት 21/2009ዓ.ም)፡፡*

አንድ ማሕበረሰብ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ላይ የሚፈፅማቸው በርካታ ተግባራት አሉት፡፡ እነዚህ ተግባራት (ልማዶች) አመጣጣቸው እና ተገቢነታቸው እንዴት እንደሆነ በፎክሎሩ አማካኝነት ያብራራል፡፡ ይህ ተረት የኩናማ ብሔረሰብ አኗኗር ላይ የሚታዩ ልማዶች መነሻቸው ከየት እንደሆነ መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ ከነዚህ ልማዶች አንዱ የብሔረሰቡ አሰፋፈርን ይመለከታል፡፡ ለምንድን ነው ከሜዳ ርቆ ተራራማ ቦታ ላይ ተበታትኖ የሚኖረው? ለሚል ጥያቄ በዚህ ተረት ማሳያነት ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

የኩናማ ብሂረሰብ በድሮ ጊዜ በርካታ ቁጥር የነበረው መሆኑ ቢታመንም በየጊዜው ሲያጋጥሙት በነበሩ ጦርነቶች እና ሽሽቶች ምክንያት ቁጥሩ ተመናምኖ ወደ መጥፋት ደረጃ ደርሶ እንደነበረ፣ ከዚያ እንዴት አድርጎ ዘሩ መቀጠል እንደቻለ እናያለን፡፡ በተረቱ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ (ጊዜው በውል ባይታወቅም) የኩናማ ብሂረሰብ ተራራማ

እና ለጠላት እና ለተፎጥሮአዊ አደጋዎች (ጎርፍ፣ በወባ ትንኝ የመነከስ የመሳሰሉትን) ለመከላከል በሚያመች ስፍራ ላይ መኖር እንደ ጀመረ በብሔረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡ በምዕራፍ ሶስት የብሔረሰቡ አጠቃላይ ዳራ ላይ ለማስተዋወቅ እንደሞከርኩት ብሔረሰቡ የሚኖርበት አካባቢ ቆላማ በመሆኑ ከፍተኛ የወባ ወረርሽኝ ያለበት ቦታ ነው፡፡ ብሄረሰቡ ይህንን እና ሌሎች አደጋዎች እንዴት ተቋቅሞ እዚህ እንደደረሰ በዚህ ተረት አማካኝነት ይገልፃል፡፡ ከዚህ ፋይዳው በተጨማሪ ተረቱ ታሪክ ቀመስ እና በትክክል ተፈፅሟል ተብሎ እንደሚታመን መረጃ አቀባዮቹ (አቶ ግደይ ቱርኳ፣ ሃይለ ወለላ እና መድህን ብስራት፣ የካቲት 21/2009 ዓ.ም) ገልጸውልኛል፡፡

"ሳማ ኬካ" ተረቶች ሲተረቱ እንደ ሌሎች ተረቶች የራሳቸውን የሆነ የአተራረክ ስርዓት አላቸው፡፡ አንድ ተረት መተረት የሚፈልግ ሰው በመጀመርያ "አሺ አንዳቴ" በማለት የተሰበሰቡትን ሰዎች ወይም አድማጮች ትኩረት እንዲሰጡት ያደርጋል፡፡ የተረቱ ታዳሚዎች ደግሞ "ኤ ሴሴ" በማለት ዝግጁ መሆናቸውን ይገልጹለታል፡፡ ከዚያም በድሮ ጊዜ ነው አሉ በማለት ይጀምር እና ይተርታል፡፡ በሚተርትበት ወቅት አድማጮች "ኤ" (እህ፣ ከዚያስ እንደማለት ነው) በማለት እየተከታተሉት እንደ ሆነ ያረጋግጡለታል፡፡ ተራቹ ተረቱን ሲጨርስ ከዚያ በኃላ እንዲህ ሆነ ወይም ተባለ ይባላል በማለት ቋጭቶ ተረቱን ለመተረት ካነሳሳው ጉዳይ ጋር በማገናኘት ገለጻ እንደሚያቀርብ አቶ ገብረክርስቶስ ቶሊ (የካቲት፣ 27/2009 ዓ.ም) ባደረኩላቸው ቃለምልልስ ነግረውኛል፡፡

"ሳማ ኬካ" በመባል የሚታወቁ የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች አብዛኛውን ጊዜ ወላጆች እና ጎሳ መሪዎች ልጆቻቸውን ለማስተማር፣ ታሪካቸው እና ባህላቸውን ለማውረስ የሚተርኩዋቸው ናቸው፡፡ የማህበረሰቡን አባላት በብዛት የሚያሳትፉ እንደ እርቅ እና ሽምግልና የመሳሰሉ አጋጣሚዎች ሲኖሩ ይተረካሉ፤ እንዲሁም ማታ ማታ ከእራት በኃላ እሳት እየሞቁ የአንድ ቤተሰብ አባላት፣ ጎረቤቶች ሰብሰብ ብለው ታሪክ እና ባህል ለማስተማር እንደሚተርቱዋቸው ብርሃነ ኬኞ ጥር፣ 10/2009 ዓ.ም ገልጸውልኛል፡፡

**ለ. ኔላ ሳማ**

በዚህ ምድብ የሚካተቱ የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ደግሞ የፈጠራ መሆናቸውን የሚታመንባቸው ናቸው። በጥናቱ ግኝት እንደተገነዘብኩት ታሪክ እና ባህልን ከማስተማር ይልቅ ለማዝናናት፣ ስነ ምግባር፣ ብልህነት እና የመሳሰሉ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለማስተማር እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተብለው የሚተረቱ ናቸው። የብሔረሰቡ አባላት እንደሚሉትም

ለጨዋታ እና ሳቅ ለመፍጠር የሚተረቱ ናቸው (አቶ ግደይ ቱርኳ፣ አቶ ሃይለ ወለላ፣ ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ የካቲት 21/2009 ዓ.ም)፡፡ ከተሰበሰቡት ሰባ ስምንት ተረቶች አብዛኞቹ ማለትም ስልሳ ስምንት በዚህ ምድብ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ "ኤላ ሳማ" በመባል ከሚታወቁ ተረቶች  በማሳያነት ተረት 15 እና 37 እንመልከት፡፡

ተረት አሰራ አምስት ቁራ ቀበሮ የሰቀለችውን ቋንጣ ሰርቆ በመብላቱ ቀበሮ እሱን ለመግደል መላ ስትፈልግ፣ ቁራ ደግሞ በበኩሉ ከቀበሮ እጅ ለማምለጥ ሌላ ብልሐት ፈልጎ ህይወቱን ማትረፍ እንደቻለ የሚተርክ ነው፡፡

> *ከእለታት አንድ ቀን ቀበሮ በግ አረደች፡፡ የአቅሟን ያህል ከበላች በኃላ የቀረውን ስጋ ቋንጣ እንዲሆን ፀሐይ በሚያገኘው ቦታ ሰቀለችው፡፡ ከዚያም ቁራ በዚያ አካባቢ ሲያንዣብብ አየው እና አንስቶ በላ፡፡ ቀበሮ ልትይዘው ብትሮጥ ክንፉን ዘርግቶ በሮ ሄደ፡፡ ቀበሮ በጣም ተናደደች እና እሱን የምትይዝበት ዘዴ ታሰላስል ጀመር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን አዲስ የተገፈፈ ቆዳ ለብሳ፣ የሞተ እንስሳ መስላ ሜዳ ላይ ተቀመጠች፡፡ ቁራም ምግቡን ፍለጋ በሚበርበት ጊዜ ከሩቅ አያት እና ወረደ፡፡ ጠጋ ሲል በቅርቡ የተበላ እንስሳ ነው፡፡ ከዚያ ጠጋ ብሎ ለመብላት ሲሞክር ቀበሮ ቀርቀም አድርጋ ያዘችው፡፡ "አገኘሁህ አንተ ሌባ እኔ ማን መሆኔን አታቅም ማለት ነውን?" አለቸው፡፡ እሱም "አንቺ ቀበሮ እህቴ የፈለግሽውን አድርጊኝ፣ ብቻ ገደል ላይ እንዳትወረውርኝ" አላት፡፡ "ለምን?" ብላ ጠየቀችው፡፡ "አባት እና እናቴ በህጻንነቴ ረግመው ገደል ውስጥ ገብቼ እንደምሞት ነግረውኛል፣ ስለዚህ እባክሽ" ብሎ ተማጸናት፡፡ እሷም የምትገድልበትን መንገድ በማወቅዋ በጣም ተደሰተች እና ገደል ላይ ወስዳ ቁልቁል ወረወረችው፡፡ ከዚያ ቁራ ክንፎቹን ዘርግቶ ተንሳፈፈና ከበለይዋ መጥቶ "ቁዋቅ…ቁዋቅ…" አለ፡፡ ቀበሮ ምንም እንኳ በውስጧ ብትቃጠልም "ለወንድምነት ስል ለቀቅኩህ" አለችው፡፡ እሱም "በወንድነቴ አመለጥኩሽ እንጂ" አላት ይባላል (አቶ ግደይ ዮሐንስ፣ ጥር 23/2009 ዓ.ም.)፡፡*

በተለያዩ አጋጣሚዎች በጠላት እጅ የመውደቅ አደጋ ቢያጋጥም ከመደናገጥ እና ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ በተቻለ መጠን መውጫ ቀዳዳ መፈለግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ተረት አማካኝነት ተስተማስሎ የቀረበ ጉዳይም ይህንን ነው፡፡ ብሔረሰቡ ልጆቹን እያዝናና ብልህ እና አስተዋይ እንዲሆኑ የሚያስተምርበት ነው፡፡

ተረት ሳላሳ ሰባት ደግሞ ቀበሮ እና እንቁራሪት ተፎካክረው የሩጫ ውድድር ሲያካሂዱ በመጨረሻም እንቁራሪት ስታሸንፍ የሚያሳይ ነው፡፡

> *አንድ ቀን ቀበሮ እና እንቁራሪት ተገናኝተው ሲያወሩ ሲያወሩ ቀበሮ እንቁራሪትን ጣል ጣል ታደርጋታለች፡፡ ከዚያም ለምን ሩጫ ውድድር አንገጥምም በማለት ተሳለቀችባት፡፡ እንቁራሪት ደግሞ የቀበሮን ንቀት ስላናደዳት እሺ አለቻት፡፡ ከዚያ በኃላ ቀጠሮ አድርገው ተለያዩ፡፡ ቀጠሮዋቸው እስኪደርስ ድረስ እንቁራሪት ወደ ጓደኞቿ ሂዳ አግዙኝ አለቻቸው፡፡ እነሱም ምንም ችግር የለም ብለው ተስማሙ፡፡ ዳኞችም ተመረጡ፡፡ ከዚያ በኃላ የቀጠሮው ቀን ደረሰ እና ለሩጫ ተዘጋጁ፡፡ "ለየብቻችን ስለምንሮጥ የቀደመ ድምፅ ማሰማት አለበት" ተባባሉ፡፡ ከዚያ የእንቁራሪት ጓደኞች ውድድር በሚካሄድበት መንገድ ዳር ዳር*

*ላይ ተበታትነው ሳር ውስጥ ተሸሽገው ድምፅ ለማሰማት ተዘጋጁ፡፡ ከዚያ ዳኛ ውድድሩን ካስጀመረ በኃላ እንቁራሪት ሁለት ጊዜ ዘል ዘል ብላ ሳር ውስጥ ገብታ ተደበቀች፡፡ ቀበሮ ብቻዋን ትሮጥ ትሮጥ እና ቆም ብላ ድምፅ ታሰማለች፡፡ ከዚያም አንዷት ከፊቷ የተደበቀች እንቁራሪት "ቆ…ቅ" ስትል ለካ ቀድማኛለች ብላ ልቧን እስኪጠፋ ትሮጣለች፡፡ ብዙ ከሮጠች በኃላ እንደገና ድምፅ ታሰማለች፡፡ አሁንም ከፊቷ ያለችው "ቆ…ቅ" ስትል ትሮጣለች፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ድምፅ አሰምታ እንቁራሪት ከፊቷ ሆና ስትመልስላት እውነትም ትቀድመኛለች ብላ አቋረጠች ይባላል (ወ.ሮ ፊንጃን ግደይ፣ ጥር፣* 20/2009 *ዓ.ም)፡፡*

በየትኛውም ማሕበረሰብ ማለት ይቻላል ጉራ እና ትዕቢት ተቀባይነት የሌላቸው ባህርያት ናቸው፡፡ የአንድ ማሕበረሰብ ወይም ቡድን አባላት ተቻችለው እና ተስማምተው እንዲኖሩ የአብዛኛው ፍላጎት ነው፡፡ በዚህ ተረት ተስተማስሎ የቀረበው ሰብአዊ ጉዳይም ይህንን ነው፡፡ አንዳንድ ወጣ ያለ ባህሪ የሚያሳዩ እና ከስርዓተ ማህበሩ ባላቸው ነገር ለማፊንገጥ የሚሞክሩ ሰዎች ባህርያቸው በቀበሮ አማካኝነት አስመስሎ በማቅረብ ጉራ መንዛት እና ሌሎችን ማጣጣል ተገቢ እንዳልሆነ፣ መጨረሻውም ውድቀት መሆኑ ያሳያል፡፡ በዚህም ከስነቃል ተግባራት አንዱ ብሔረሰቡ እኩይ የሚላቸውን ተግባራት እንዳይስፋፉ የሚቆጣጠርበት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንድን ነገር ለመሞኮር ወይም ለመጋፈጥ ተስፋ መቁረጥ እና አልችልም ማለት ሳይሆን ብልሀትን መጠቀም፤ እንዲሁም “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” እንደሚባለው ከወገኖችህ ጋር መተባበር ድል እንደሚያቀዳጅ በእንቁራሪት አማካኝነት የሚያሳይ ተረት ነው፡፡

“ኄላ ሳማ” ተረቶች የሚተረቱት ለማዝናናት እና ማህበረሰቡ አሉኝ የሚላቸውን መልካም እሴቶችን፣ ግብረ ገብነት እና ስነ ምግባር ለማስተማር መሆኑን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ በተረቶቹ ውስጥ የሚገኙ ገጸባህርያት ሰዎች፣ እንስሳት እና መናፍስት ናቸው፡፡ በተለያዩ የስራ ድርሻዎች ተበታትነው የዋሉትን የቤተሰብ አባላት እራት ከተበላ በኃላ ወላጆች ለልጆቻቸውን ይተርታሉ፤ ልጆቹንም እንዲተርቱ ያበረታታሉ፡፡

ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ እንደገለጹልኝ በኩናማ ብሔረሰብ ተረት የመተረት ድርሻ አብዛኛውን ጊዜ የበእድሜ የገፉ አባቶች እና እናቶች ነው፡፡ ልጆች የሰሙትን ተረት ምን ያህል እንደያዙት ለማረጋገጥም ደግመው እንዲተርቱ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ሴቶች በስራ ቦታ ማርገብገብያ፣ ሽሌን እና ኮፍያ ሲሰሩ፣ አረም ሲያርሙ… ተረት ይርታሉ፡፡ አባቶች ደግሞ ታሪክ ለመንገር፣ ባህል እና እምነት ለማስረዳት፣ የተጣሉትን ለመሸምገል የሚፈጸሙ

ተግበራት ልጆች እንዲያውቁዋቸው እና እንዲወርሱዋቸው በማለት ይተርታሉ (ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሰ፣ የካቲት 23/2009 ዓ.ም)፡፡

በኩናማ ብሔረሰብ በአሁኑ ጊዜ ተረት የመተረት ባህል እየቀነሰ መምጣቱን መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለይ በወጣቶቹ ተረት መተረት የኃላ ቀርነት እና የገጠርነት መገለጫ ተደርጎ እንደሚወሰድ እና ተረት ለመተረትም ይሁን ለማዳመጥ ፍላጎቱ እየቀነሰ መምጣቱን፣ ተረት ከመስማት ይልቅ ሬድዮ ማዳመጥን፣ከተማ ሂደው ስላዩት ፊልም መተረክን እንደሚመርጡ (ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ እና ወ.ሮ መድህን ብስራት የካቲት 23/2009 ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡

### 4.1.2. ምሁራን ከተከተሉት የምደባ ስልት አንፃር

የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በአካባቢያዊ ምደባቸው ላይ ተመስርተን በምሁራኑ የመመደቢያ ስልት አንፃር ስንፈትሻቸው "ሳማ ኬካ" ተብለው የሚጠሩ ተረቶች Thompson (1946) እና Okpewho (1992) "ሚታዊ አፈታሪክ" በማለት በገለፁት ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ቢሆንም "ኤላ ሳማ" ተረቶች ግን የተለያየ ባህርይ ያላቸው በመሆኑ በተለያዩ ምድቦች ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ተረቶቹን ለመመደብ በምሁራን ከተሰነዘሩ ሐሳቦች እና የአከፋፈል ስልቶች Okpewho (1992) ሌጀንድ፣ ገላጭ ተረቶች እና ፉቡላ በማለት የተከተለውን የአከፋፈል ስልቶች መከተል ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ይህ አከፋፈል ስልት ተገቢ ነው የምልበት ምክንያት አንደኛው ያወጣቸው መስፈርቶች በአፍሪካ ተረቶች ላይ የተመሰረቱ እና የቅርብ መሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በመስፈርቱ ሊመደቡ በመቻላቸው የOkpewho (1992) መመደቢያ ዘዴዎች ለዚህ ተግባር መርጫለሁ፡፡

### ሀ. ሌጀንድ

ሌጀንድ (ፈቃደ እና ዘሪሁን "አፈ ታሪክ" ይሉታል) በማለት የሚጠሩ ተረቶች መነሻቸው እውነተኛ ታሪክ ሆኖ ቀስ በቀስ ግን ፈጠራዊ መልክ እየያዙ የሚመጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረቶች ስለ በታሪክ የታወቁ ሰዎች እና ታሪካዊ ፍፃሜዎችን የሚተርኩ ሆኖው፣ አንድን ብሔረሰብ ስላለፈባቸው ጦርነቶች፣ ብሔረሰቡን ስላስተዳደሩ ነገስታት፣ ስለብሔረሰቡ ጀግንነት ወዘተ. የሚመለከቱ ታሪኮች የሚቀርቡባቸው እንደሆኑ Okpewho (1992፣1833) እና ፈቃደ (1991፣55-57)፡ ገልጸዋል፡፡ ዘሪሁን (1991፣31-32) ደግሞ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡፡

*አፈ ታሪክ በአንድ በተወሰነ አከባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገጽታ በመውሰድ ስነ ቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ አላማው አንዳንድ አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ በታሪክ የተፈጸመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈጸም ቻለ? ለምን ተፈጸመ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ መልስ ይሰጣል፡፡ ስለ ንጉሶች፣ በጎሳዎች መካከል ስለተደረገ ግጭት ወይም ጦርነት፣ ስለ ስደት፣ስለ ተፈጥሮ አደጋ፣ ስለ አካባቢ ስያሜዎች፣ ስለ ሰፈሮች አቆራቆር… ይናገራል፡፡*

ስለዚህ በዚህ ስር የሚካተቱ ተረቶች ቀደም ሲል ተፈጽመዋል ተብለው በሚታመንባቸው ታሪኮች ላይ ተመስርተው የሚነገሩ እና አንድን ማህበረሰብ እራሱን የሚገልጽባቸው፣ ታሪኩን እና እምነቱን የሚያስተምርባቸው ናቸው፡፡ ከኩናማ ብሔረሰብ ከተሰበሰቡ እና በዚህ ምድብ ከሚካተቱ ተረቶች ተረት ሰባ ስድስትን በምሳሌነት እንመልከት፡፡

*የአክሱም ንጉስ የነበረ ንጉስ ባዜን ከሞተ በኃላ የኩናማ ብሔረሰብ ያስተዳድር የነበረ መሪ ሽረ ይባላል፡፡ በንጉስ ባዜን መሞት ምክንያት የብሔረሰቡ ኃይል ተዳክሞ ከአክሱም ተገፍቶ እንዲወጣ ተገዷል ይባላል፡፡ የኩናማ ብሔረሰብ እየተዋጋ እና እየተከላከለ ከአክሱም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ አፈግፍጎ በአሁኑ ሰዓት "ሽረ" ተብሎ ወደ ሚታወቀው ቦታ መጥቶ ይኖር ነበር፡፡ ሽረ ላይ እየኖረ ሳለ ደግሞ አሁንም የገጠመውን ጦርነት መቋቋም ተሳነው እና ቦታውን ለቆ ወጣ፡፡ በዚያ ጊዜ ሽረ የተባለውን የኩናማ መሪ ስለ ሞተ "አቦ" የተባለ ተተኪ መሪ ህዝቡን እየመራ በአሁኑ ጊዜ ላዕላይ አድያቦ እና ታሕታይ አድያቦ ወደ ሚባል ቦታ አመጣው፡፡ እዚያውም መኖር ጀመረ፡፡ ከዚያም ቦታው "ዓዲ-አቦ" ወይም የአቦ አገር ተባለ፡፡ ከዚያም ነው "አድያቦ" የሚል ቃል የመጣው ይባላል (አቶ ሃይለ ወለላ፣ 23/2009 ዓ.ም)፡፡*

በዚህ መሠረትም ከተሰበሰቡ ተረቶች መካከል ተረት 35፣ 45፣ 50፣ 57፣ 73፣ 74፣ 75 እና 76 በአፈ ታሪክነት የሚመደቡ ናቸው፡፡

## ለ. ገላጭ ተረቶች

በዚህ ምድብ ስር የሚመደቡ ተረቶች በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ገላጭ ተረቶች በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ የሚታዩትን ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አጋጣሚዎች መነሻቸው ከየት እንደሆነ የሚገልፁ ናቸው Okpewho, (1992፣203) እና ፈቃደ (1991፣57)፡፡ Thompson (1946፣9) ደግሞ "*Explanatory tales are stories explaining the origions and characteristics of various animals and plants, the stars, and mankind and his institutions."* በማለት ገልፆታል፡፡ የአንድን ህዝብ የተለያዩ ባህላዊ እምነቶች፣ ለየት ያለ አፈጣጠር ስላላቸው እንስሳት፣ ተራራ ወዘተ. ይህ ለምን ሆነ? እንዴት መጣ ወይም ተከሰተ? በማለት ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች በገላጭ ተረቶች መልስ ያገኛሉ፡፡ ከተሰበሰቡት የኩናማ ብሔረሰብ

ተረቶች ውስጥ ተረት 18፣ 27፣ 34፣ 67፣ 73፣ 74፣ 75፣ 76 እና 77 በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ተረት ሃያ ሰባትን በምሳሌነት እንመልከት፡፡

ተረት ሃያ ሰባት ጅግራ ከሌሎች እንስሳት በተለየ መልኩ ለምን ራሷ መላጣ ሆነ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ነው፡፡

> *በአንድ ቀን ቀበሮ እና ጅብ ለአደን ሄዱ፡፡ ለአደን ከሄዱ በኃላ ጅብ ላም አገኘ፡፡ ቀበሮ ደግሞ በሬ አገኘ፡፡ ይዘው መጥተው በየተራ ይጠብቋቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን የቀበሮ ተራ ላይ የጅብ ላም ወለደች እና .... የበሬ መቀመጫ ላይ አደረገው፡፡ ከዚያም የኔ በሬ ወለደ አለ፡፡ ጅብ ደግሞ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል በጭራሽ አላምንም አለ፡፡ ቀበሮ ግን ድሮ ድሮ ላም ጥጃ ትወልድ ነበር አሁን ግን በሬ ነው ጥጃ የሚወልደውብሎ ድርቅ አለ፡፡ ከዚያም ጅብ በል አሁን ሳር እና ጥጃ አንድ ላይ አስቀምጠን ላም እና በሬ እንልቀቃቸው እና ማን ወደ ማን እንደ ሚሄድ እናያለን አለ፡፡ እንዲያ አደረጉ እና በሬ ወደ ሳር ሲሄድ ላም ደግሞ ወደ ጥጃ ሄደች፡፡ ቀበሮ አሁንም አላምንም አለ፡፡ ጅብ ደግሞ ይህንን ካላመንክ በል አንተ በሬህን እኔ ደግሞ ላሜን እንለብ እና ትክክለኛው ወተት የተኛው እንደሆነ ጠንቋዮች ዘንድ ወስደን እናረጋግጥ አለው፡፡ ከዚያ ጅብ ላሚቷን አልቦ አፍልቶ ያዘ፣ ቀበሮ ደግሞ ሊጥ አፍልቶ ይዘው ሄዱ፡፡ ጠንቋዮቹ ጅግራ ናቸው እና ፀጉራቸው እየተሰሩ ጠበቁዋቸው፡፡ ከዚያም ጅብ እስቲ የያዝነውን ቅመሱልን አላቸው፡፡ ከዚያም ይህ ወተት ነው ይህ ደግሞ ሊጥ (አብሲት) ነው ብለው እውነቱን መሰከሩ፡፡ ከዚያ ቀበሮ ተናድዶ ትኩሱን አብሲት አናታቸው ላይ ደፋላቸው እና ፀጉራቸው ተመለጡ፡፡ ከዚያ በኃላም ጅግራ መላጣዎች ሆኑ ይባላል (አብርሀት ቱላ፣ ጥር 22/2009 ዓ.ም)፡፡*

ገላጭ ተረቶች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ጥያቄ ለሚጭሩ ክስተቶች ምላሽ የሚሰጡ እንደመሆናቸው መጠን በዚህ ተረት ውስጥም የጅግራ ራሰ መላጣነት በተመለከተ ገለጻ ቀርቧል፡፡ ጅግራዎች ምንም እንኳ ሲፈጠሩ ፀጉር የነበራቸው ቢሆንም ባንድ ወቅት ጅብ እና ቀበሮ በሬ ወለደ በሆነ ምክንያት ተጣልተው ፍርድ እንዲሰጡ ተጠይቀው ትክክለኛ ፍርድ በመስጠታቸው ቀበሮ ተናድዶ ትኩስ አብሲት እራሳቸው ላይ ስለደፋባቸው ፀጉራቸው መገፈፉን፣ ከዚያ በኃላም ፀጉር ሊያበቅሉ ባለመቻላቸው ራሰ መላጣ ሆነው እንደቀሩ ያብራራል፡፡ በዚህም ተረቱ በገላጭ ተረት ስር የሚመደብ ነው፡፡

### ሐ. ፉቡላ

Okpewho ፉቡላ ተብለው መመደብ ስላለባቸው ተረቶች ሲያስረዳ "እንደ ሌጀንድ ታሪክ የመሰነድ አልያም ደግሞ እንደ ገላጭ ተረቶች የክስተቶች እና ልማዶች አመጣጥ የመግለፅ እና የማብራራት አላማ የሌላቸው ተመክሮን በምናባዊ ድራማዊ የሚያቀርቡ ተረቶች ሆነው፣ በገፀ ባህሪነትም የሰው ልጅ፣ እንስሳት እና መናፍስት የሚያሳትፉ ተረቶች ናቸው" ብሏል

(1992፣209። የOkpewhoን የተረት አከፋፈል መንገድ ተከትሎ ተረትን ለመመደብ ጥረት ያደረገው ፈቃደ ደግሞ ይህን ሐሳብ “ፉቡላ አላማው እና ትኩረቱ የገጠመኞችን ምናባዊ ድራማ በማቅረብ በሚያስደስት መንገድ ሰዎች፣ እንስሳትና መናፍስት ገጸ ባህርያት ያሉበት ትረካ መተረክ ብቻ ነው” ብሏል (1991፣62)። በዚህ ምድብ ስር ከሚካተቱ የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች መካከል ተረት አርባ ሶስትን በምሳሌነት እንመልከት።

ተረት አርባ ሶስት ግመል እና ዝንጀሮ አብረው ሲኖሩ ዝንጀሮ ጓደኝነታቸውንና የገቡትን ቃል ባለማክበሩ ምክንያት የተነሳ በመኸከላቸው ቂም ተፈጥሮ ሲለያዩ እና ዝንጀሮ ህይወቱን ሲያጣ የሚያሳይ ነው።

> *በድሮ ጊዜ ግመል እና ዝንጅሮ በጓደኝነት አብረው ይኖሩ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ምግብ ፍለጋ አብረው ሄዱ፡፡ በፍቅር እያወሩ እና እየሳቁም ይጓዙ ነበር፡፡ ከዚያም ስሄዱ ስሄዱ አንድ ትልቅ ወንዝ አገኙ፡፡ ዝንጅሮ "እኔ እንዴት ልሻገር ነው? በቃ እዚህ መቅረቴ ነው" አለ፡፡ ግመል "አይዞህ ጓደኛየ ትቼህ አልሄድም" አለውና አዝሎ አሻገረው፡፡ ከተሻገሩ በኃላ ትንሽ ተጉዘው አንድ የማሽላ ማሳ አገኙ፡፡ ከዚያ ግመል "ስማ ጓደኛየ እዚህ ገብተን እንብላ፣ ታድያ እኔ ሆዴ ትልቅ ስለሆነ እስክጠግብ ድረስ ታገሰኝ፣ የሆነ ድምጽ እናዳታሰማ እና ሰዎች እንዳይመጡብን" አለው፡፡ እሺ ተባብለው ገቡ እና ዝንጀሮ ትንሽ በልቶ ጠገበ፡፡ ከዚያ ማሽላ ቆርጦ በእጁ ይዞ ዛፍ ላይ ወጣ እና መጮህ ጀመረ፡፡ ከዚያ ማሽላ ጠባቂዎች መጥተው ግመልን ቀጥቅጠው አባረሩት፡፡ ከዚያም ወደ ሌላ ቦታ ሂደው መብላት ጀመሩ፡፡ ግመል ደግሞ "ቅድም ለምን ጮህክ? በል አሁንም እንደዛ እናዳታደርግ ዝምብለን እንብላ" አለው፡፡ ዝንጀሮ ደግሞ በልቶ ጠገበ እና አሁንም ዛፍ ላይ ወጥቶ ጮሀ፡፡ ሰዎች መጥተው ግመልን መትተው አባረሩት፡፡ ከዚያም ወደ ሌላ ኣከባቢ ሂደው መብላት ሲጀምሩ ዝንጀሮ ለሶስተኛ ጊዜ እንደዛ አደረገ እና ሰዎች መጥተው ግመል ሳይበላ አባረሩት፡፡ ከዚያ በኃላ መሸ እና ወደ ቤታችን እንመለስ ብለው ጉዞ ጀመሩ፡፡ ከዚያም የቅድሙ ወንዝ ላይ ደረሱ፡፡ ዝንጀሮ "አሁንስ እንዴት ነው ምሻገረው?" ብሎ ግመልን ጠየቀው፡፡ ግመል ደግሞ "እንደ ተግባርህ እንኳ አይገባህም ነበር፣ ለጓደኝነታችን ስል ግን ና ላሻግርህ" አለና አዘለው፡፡ ከዚያ ወንዙ ማኸል እንደደረሱ ግመል "እኔ ጀርባየ ስለአቃጠለኝ ልንከባለል (ውኃው ላይ በጀርባየ ልተኛ) ነው" አለው፡፡ ዝንጀሮም ተደናግጦ "እህ እኔስ እንዴት ልሆን ውኃው ቢወስደኝስ?" አለው፡፡ ትንሽ ተጓዙ እና አሁንም ግመል "ላንከባልል ነው" አለው፡፡ ዝንጀሮ "አረ እባክህ ለኔ ስትል ተው" አለው፡፡ ግመል ደግሞ "የራስህ ጉዳይ እንጂ ላንከባልል ነው" ብሎ ውኃው ላይ ተኛ፡፡ ከዚያ ዝንጀሮን ጎርፍ ወሰደው፡፡ በዚህም ግመል ብድሩን መልሶ አገሩ ገባ ይባላል (ወ.ሮ ህይወት ተሰፋማርያም፣ ጥር 27/2009 ዓ.ም)፡፡*

የፉቡላ ተረቶች ገጸ ባህርያት ከሆኑት መካከል እንስሳት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ ተረትም ገጸ ባህርያቱ እንስሳት በመሆናቸው የፉቡላ ተረት ነው። ምንም እንኳ ግመል ዝንጀሮን እንደ ጓደኛ ተቀብሎ ከእሱ እንዳይለይ እና ምግብ እንዲያገኝ አስቦ አዝሎ ወንዝ ቢያሻግረውም፣ ከተሻገሩ በኃላ ዝንጅሮ ባደረገው ነገር ግመል ቂም ይዞ ሲመለሱ ወንዝ ውስጥ ጨምሮ ጎርፍ እንዲወስደው ሲያደርግ እንመለከታለን። ይህ ተረት ገጸ ባህርያቱ እንስሳት በመሆናቸው እና ፈጠራዊ በመሆኑ በፉብላ ተረቶች ስር

የሚመደብ ነው፡፡ ከመስክ ከተሰበሰቡ የኩናማ ብሄረሰብ ተረቶች ውስጥ ከተረት 18፣ 27፣ 34፣ 35፣ 45፣ 57፣ 67፣ 73፣ 74፣ 75፣ 76 እና 77 በስተቀር የቀሩት 66 ተረቶች በዚህ ምድብ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡

## 4.2. የይዘት ትንተና

ይህ ክፍል በምዕራፍ አንድ በተለምኩት የመተንተኛ ዘዴ እና በምዕራፍ ሁለት ባበጀሁት ንድፈ ሓሳባዊ ዳራ አማካኝነት የተረቶቹን ይዘት ለመተንተን ጥረት የማደርግበት ነው፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡትን የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ጥብቅ ንባብ በማድረግ እና ፍሬ ነገራቸውን በመመርመር በተረቶቹ አማካኝነት ተስተማስለው የቀረቡ ሰብአዊ ጣጣዎች ለመሳየት የምሞክርበት ነው፡፡ ይህ ለማድረግም በመጀመርያ ተቀራራቢ ይዘት ያላቸውን በአንድ ምድብ የመደብኳቸው ሲሆን፤ በአንድ ተረት ከአንድ በላይ ይዘት ሊኖር የሚችልበት አጋጣሚ ተረቶችን መመደብ ፈታኝ ያአድርጎታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት ይህንን ችግር ለማቃለል ከአንድ በላይ ይዘቶች ያሉት ተረት ሲያጋጥም ከይዘቶቹ ጎልቶ የሚታየውን ወይም የተረቱ ዋና ሐሳብ በመውሰድ ምደባ አድርጌያለሁ፡፡ በዚህ መሠረትም ከመስክ የተሰበሰቡትን ሰባ ስምንት ተረቶች በ አምስት ዋና ይዘቶች ተመድበው በሰንጠረዥ መልክ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | የተረቶቹ ይዘት | የተረት መለያ ቁጥር | የተረት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የት መጣነትን የሚያሳዩ | 18፣27፣34፣64፣69፣73፣74፣75፣76፣77 | 10 |
| 2 | ብልህነትን የሚመለከቱ | 2፣3፣4፣8፣11፣14፣15፣19፣21፣24፣26፣28፣31፣32፣33፣35፣39፣40፣41፣42፣48፣56፣57፣64፣66፣71 | 26 |
| 3 | መጥፎ ባህርያትን የሚመለከቱ | 5፣6፣9፣10፣12፣13፣20፣23፣25፣30፣36፣37፣45፣46፣47፣49<br>50፣51፣53፣54፣59፣60፣61፣63፣65፣72፣78 | 27 |
| 4 | ጓደኝነትን የሚመለከቱ | 1፣7፣16፣17፣29፣43፣55፣62፣68፣70 | 10 |
| 5 | ጥንካሬና ሙሉ ጤንነትን የሚመለከቱ | 22፣38፣44፣52፣58 | 5 |
| 6 | ድምር | | 78 |

ከእነዚህ ተረቶች ውስጥ ከእያንዳንዱ ምድብ ይወክላሉ ብዬ የመረጥኳቸውን ተረቶች ትንተናቸውን እንደሚከተለው አቀርባለሁኝ፡፡

### 4.2.1. የት መጣነትን የሚያሳዩ

በገላጭ ተረቶች አማካኝነት አንድ ማሕበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ እንዲሁም ሰው ሰራሽ ክስተቶች ባህሪ እና አመጣጥ ያስረዳል Thompson (1946:9)፡፡ ኬት መጣነትን የሚያሳዩ በማለት የተለዩት የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶችም ብሔረሰቡ በአካባቢው ስለሚገኙ እንስሳት አፈጣጠር፣ ስለ መንደሮቹው አቀራቀር እና ስያሜ አወጣጥ፣ ብሔረሰቡ ከሌሎች ህዝቦች ስላካሄዳቸው ጦርነቶች ወዘተ በተመለከተ የሚያብራሩ እና መልስ የሚሰጡ ናቸው፡፡

ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች በመነሳት የኩናማ ብሔረሰብ ከሚያሳስቡት ተፈጥሮአዊ ክስተቶች መካከል በአከባቢው በብዛት የሚገኙ እና አድኖ ለምግብነት የሚያውላቸውን ጅግራዎች፣ እንዲሁም ማሳ ውስጥ ገብተው የእርሻ ምርቱን እንዳያወድሙበት ሲያባርራቸው የሚውል ዝንጀሮዎችን አፈጣጠር በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ጅግራ እንደ ደሮ እና ቆቅ ሙሉ አካሏ በፀጉር እና በላባ የተሸፈነ ቢሆንም አንገቷና ራሷ የተገፈፈ ፀጉር ይመስል መላጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሌሎች እንስሳት የተለየች ያደርጋታል፡፡ በዚህም እንዴት ከሌሎች በተለየ መልኩ መላጣ ሆነች የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ መልስ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው እና ብሔረሰቡ አካባቢያዊ የሆነ መልስ ይሰጣል፡፡ ይህን ለየት ያለ አፈጣጠር እምዴት ሊከሰት ቻለ? ለሚል ጥያቄ አንድ ሚቶሎጂያዊ ታሪክ በማበጀት በተረት ሃያ ሰባት  አማካይነት መልሶታል፡፡ አንድ ቀን ጅብ እና ቀበሮ “በሬ ወለደ” በሚል ምክንያት ተጣልተው ጅግራዎች ፍርድ እንዲሰጡ ተጠይቀው እውነት በመፍረዳቸው ምክንያት የተናደደው ቀበሮ በደፋባቸው አብሲት ሳቢያ ነው መላጣ ሆነው የቀሩት በማለት ድራማዊ በሆነ አገባብ እያዝናና ተፈጥሮአዊ ክስተቱን ይገልፃል፡፡

በአፈጣጠራቸው ከሚያስገርሙ በአካባቢው ከሚገኙ እንስሳት ሌላው ዝንጀሮ ነው፡፡ የዝንጀሮ መቀመጫ እንዴት ከሌሎች እንስሳት ተለይቶ የተቃጠለ ሆነ? ዝንጀሮዎች ከየት መጡ? የሚሉ ጥያቄዎች በአእሙሮው በመመላለስ እረፍት ይነሳዋል፡፡ በዚህም ይሆናል ያለውን መልስ በተረት አስራ ስምንት አማካኝነት ሰጥቷል፡፡ ዝንጀሮዎች ከሰው ልጅ ጋር የሚያመሳስላቸው በርካታ ነገሮች አሉዋቸው፡፡ በብዙ አካባቢዎች በሚተረቱ ተረቶች ውስጥም ሰው እንደነበሩ፣ እንዴት ወደ እንስሳ እንደተቀየሩ፣ የመቀመጫቸው መላጣነት ትርጉም

ወዘተ. በተመለከተ ሲተረት እንሰማለን፡፡ በዚህ የኩናማ ብሔረሰብ ተረት ላይ ደግሞ ዝንጀሮዎች ሰው የነበሩ ቢሆንም የመፈጠራቸው ምክንያት ደግሞ በትዳር ላይ ሲማግጡ በነበሩ አንዲት ሴት እና ወንድ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ተረት ተስተማስሎ የቀረበው ጉዳይ በትዳር ላይ መማገጥ አላስፈላጊነትን ነው፡፡ ዝንጀሮዎች በሰሩት ነውር ምክንያት ህፍረት ተሰምቶዋቸው እና በፈጣሪ ተኮንነው ነው በርኸ የሄዱት፣ መቀመጫጨው ደግሞ የዚያ ቅጣት ውጤት ነው በማለት የአፈጣጠራቸውን ምክንያት የሚያብራራ ሲሆን፣ በሌላው በኩል ደግሞ ድራማዊ ታሪክ በመመስረት የሚዝናና ነው፡፡

የብሔረሰቡ አባላት ከተፈጥሮአዊ ክስተቶች በተጨማሪ በአካባቢያቸው የሚገኙትን መንደሮች እና ከተሞች እንዴት እንደተቆረቆሩ፣ ስያሜያቸው እንዴት እንዳገኙት ወዘተ ይጠይቃሉ፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት እና ማስረዳት ስላለበት በተረቶቹ አማካኝነት ምክንያቱ ያቀርባል፤ የአእሙሮ እረፍት እንዲያገኝ ጥረት ያደርጋል፡፡ ለዚህ እንደምሳሌነት ተረት ሰባ ሶስትና ሰባ ስድስት መመልከት ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ተረት ሰባ ሶስት የኩናማ ብሔረሰብ በብዛት ከሚገኝባቸው ቦታዎች አንድ የሆነችው ሽምቢሊና እንዴት እንደተቆረቆረች እና ስያሜዋ እንዴት እንዳገኘች የሚመለከት ታሪክ ይዟል፡፡ "ሽምቢሊና" የሚል ቃል መገኛው ኩናምኛ ቋንቋ ሆኖ "ትንኝ" ማለት ነው፡፡ ታድያ ይህ ቃል የአንድ ቦታ ስያሜ ሆኖ ያገኘው አንድ የኩናማ ተወላጅ ወይም ደግሞ ቋንቋውን የሚያውቅ ሰው እንዴት ይህንን መጠርያ ሊገኝ ቻለ? ብሎ እንዲጠይቅ ይገደዳል፡፡ በተረቱ አማካኝነትም የስያሜው ጥንተ አመጣጥ ተገልፅዋል፡፡ ሽምቢልና በመባል የሚጠራው ቦታ በድሮ ዘመን የኩናማ ህዝብ መጀመርያ ላይ ሲረግጡት የሚናደፉ ትንኞች በብዛት የነበሩበት ቦታ እንደነበረ እና ይህን የተመለከቱ ሰዎች በመገረም "አ ሽምቢሊና" (የትንኝ አገር) ብለው እንደተናገሩ እና በዚህም ስያው ሆኖ እንደቀረ እንረዳለን፡፡

ተረት ሰባ ስድስት ስንመለከት ይህንንም በተመሳሳይ ከቦታ ስያሜ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ "አድያቦ" እየተባለ ስለሚጠራ አካባቢ አሰያየም ኬት መጣነትን የሚያብራራ ነው፡፡ ታሪኩ በአጭሩ ይህን ይመስላል፡፡ የንጉስ ባዜን መሞት ተከትሎ የኩናማ ብሔረሰብ አክሱምን ለቆ ወደ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ እንዲሄድ ተገዷል፡፡ በዚያን ወቅት ከአክሱም እስከ ሽረ ያለውን ቦታ ሽረ በተባለ መሪ እየተመራ ሄዷል፡፡ ሽረ ከሞተ በኃላ ደግሞ "አቦ" የተባለ መሪ ተተክቶ ህዝቡን እየመራ ከሽረ ወደዚህ ቦታ አምጥቶታል፡፡ አገሩን ለመጀመርያ ጊዜ እሱ ስለረገጠው "ዓዲ አቦ" ወይም የአቦ አገር ተብሎ ተጠራ፡፡ በዚያም "አድያቦ" የሚል ስያሜ እንደተገኘ ይነገራል፡፡

በአንድ ማህበረሰብ የሚተገበሩ ልማዶች እና ስርዓቶች አጀማመራቸው እና የሚፈፀሙበት ምክንያትም በኬት መጣነትን የሚያሳዩ ተረቶች አማካኝነት ይብራራሉ፡፡ ለዚህ ጉዳይ እንደማሳያነት ተረት ሰባ አራት መመልከት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በኩናማ ብሔረሰብ ባህል መሰረት አብዛኛውን ስራ ለሴቶች የተተወ ነው፡፡ ምግብ ማብሰል፣ እንጨት መልቀም፣ ውኃ መቅዳት፣ አረም ማረም፣ አጨዳ፣ የእጀ ጥበብ ስራ ወዘተ. ሴቶች ናቸው የሚያከናውኑት፡፡ ወንዶች ሳይሰሩ ናቸው የሚኖሩት ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ታድያ የብሔረሰቡ አባላት የዚህን ባህል አመጣጡ በተረቶቻቸው አማካኝነት ይገልፃሉ፡፡ በድሮ ጊዜ በኩናማዎች ባህል መሰረት ሁሉንም ስራ ለወንዶች የተተወ እና ሴቶች ቁጭ ብለው ይቀለቡ እንደነበር፤ ከዚያም ሴቶች ስራ ላይ እንዲሳተፉ ቢጠየቁ እና ቢለምኑ “አንሰራም” በማለታቸው ወንዶች ተመካክረው ከመንደራቸው ርቀው ጫካ ውስጥ መኖር እንደጀመሩና ተለምነው አገር እንደገቡ ነው፡፡ በዚህ ሴቶች ባሎቻቸው እንዳይሄዱባቸው ሰግተው ሁሉንም ስራ እራሳቸው እየሰሩ ይኖራሉ በማለት ምክንያቱን ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምድብ የተካተቱ ተረቶች የኩናማ ብሔረሰብ ስለ አኗኗሩ እና ከአከባቢው ጋር ያለውትስስር የሚያሳዩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚነሱ ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ክስተቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎች የት መጣነታቸውን ለመመርመር የሚያደርገው ጥረት በተረቶቹ ውስጥ ይገልጻል፡፡ በምርምሩም የእንስሳት እና የተራሮች አፈጣጠር፣ የአካባቢው ስያሜዎች እና የመንደሮች አመሰራረት እንዲሁም የነገስታቱና መሪዎቹ ጅግንነትና ታሪክ፣ ስለባህላዊ ልማዶቹ፣ ወዘተ. በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች ይሆናል ያለውን መልስ በመስጠት የማህበረሰቡ አባላት የተረጋጋ ህይወት እንዲመሩ፣ የነገሮች አፈጣጠር እንዲያውቁ እና እንዲጠነቀቁ ያደርጋል፡፡

### 4.2.2. ብልህነትን የሚመለከቱ

ኑሮ ለመምራት ብልህ መሆን ያስፈልጋል፡፡ በህይወት ዘመንህ ለሚያጋጥሙህ ፈተናዎች እንደየባህርያቸው ለመመለስ እና አሸንፎ ለመውጣት ብልህ አእምሮ ያስፈልጋል፡፡ ብልህነት በየተኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ ሊኖሩ ከሚፈለጉ እሴቶች አንዱ ነው፡፡ ሰዎች በማህበራዊ ህይወታቸውና ግንኙነታቸው ውስጥ ለሚገጥሙዋቸው ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰብአዊ ፈተናዎችና አጋጣሚዎች መፍትሔ እንዴት እንደሚያበጅላቸው፣ ከገቡበት መከራ ውስጥ እንዴት ማምለጥ እና መውጣት እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል፡፡ በዚህም የሚገጥሙዋቸውን መሰናክሎች አልፈው የተረጋጋ ህይወት ለመምራት ብልህ መሆን እንደሚገባቸው አበክረው ይሰብካሉ፡፡

የኩናማ ብሔረሰብ ከሌሎች አጎራባች ብሄረሰቦች የሚገጥሙትን ፈተናዎች እየተጋፈጠ እና መላ እየፈጠረ ዘሩን ማስቀጠል እንደቻለ ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ብሔረሰቡ ከሌሎች ብሔረሰቦች፣ ከተፈጥሮ እና በብሔረሰቡ አባላት ውስጥ የሚገጥሙትን ፈታኝና አስቸጋሪ ገጠመኞችን በብልሐት መፍትሔ አበጅቶ ኑሮውን እየመራ እንደመጣ፣ የብሔረሰቡ አባላትም ብልህ እና አስተዋይ እንዲሆኑ በተረቶች እያስተማረ መጥቷል፡፡ ይህንን የሚያረጋግጥልን ከተሰበሰቡ 78 ተረቶች ውስጥ 26 ተረቶች ማለትም አንድ ሶስተኛ የሚሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የብልህነት አስፈላጊነት የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ብልህነት የሚያመላክቱ በማለት ከተመደቡ ተረቶች ውስጥ ተረት 14፣24፣28፣31፣57 እና 66 እንደማሳያነት ይቀርባሉ፡፡

በተረት አስራ አራት አንድ ወንድ ሶስት ሚስቶች አግብቶ መኖር ይፈልጋል፡፡ ሶስቱንም ሴቶች ማናቸውን እንደሚወድ ማረጋገጥ ይፈልጉ ነበር፡፡ ሰውየውም ይህንን እንደሚመጣ ያውቅ ነበር እና አንድ መላ ፈልጎ አንድ አይነት ሻሽ ገዝቶ ለሶስቱንም ሴቶች ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚያም "ማንን ነው የምትወደው?" ብለው ሲጠይቁት "ለዛች ቀይ ሻሽ የሰጠሁዋት" በማለት ይመልሳል፡፡ ከዚያም ሁሉንም ሴቶች እኔን ነው የሚወደው፣ እኔን ነው የሚወደው ብለው ሲሄዱ እናያለን፡፡ ይህንን ተረት የተረኩልኝ መረጃ አቀባይ እና ሌሎች የብሔረሰቡ አባላት እንደገለጹልኝ ቀደም ባለ ጊዜ በኩናማ ብሔረሰብ ባህል መሠረት አንድ ሰው እስከ ሶስት ሚስቶች ማግባት ይችል እንደነበረ ነው፡፡ ታድያ እንዲህ ሲያደርግ አንዳቸውንም ላለማጣት ጥረት እና ብልሀት ያስፈልገዋል፡፡ በዚህ ተረት አማካኝነት ተስተማስሎ የቀረበው ጉዳይም ይህ ባህላዊ ስርዓታቸው ነው፡፡ ሰውየው ሶስቱንም ሚስቶቹ ማጣት አይፈልግም፤ ላለማጣት ደግሞ ብልህ መሆን ነበረበት እና መላ ፈጥሮ ሲያስደስታቸው እንመለከታለን፡፡

በተረት ሃያ አራት ውስጥ አንበሳ ጦጣን ለመግደል ፈልጎ እቤቷ ገብቶ ተደብቆ እስክትመጣ ድረስ ይጠባበቅ ነበር፡፡ ጦጢት ደግሞ ንቁ እና ተጠራጣሪ በመሆኗ የሆነ ብልሐት ፈልጋ ህይወቷን ስታተርፍ እንመለከታለን፡፡ ጠላቶችህ በተለያየ አጋጣሚ ሊያጠቁህ ይችላሉ፤ ስለዚህ ሁሌ ንቁ፣ ተጠራጣሪ እና ብልህ ሁን የሚል መልእክት አለው፡፡

ተረት ሃያ ስምንት ዝንጀሮ አዞ በነገራት የሚያስጎመጅ ወሬ ተገፋፍታ ከዛፏ ወርዳ ድግስ ለመብላት ወደ ሀይቁ ትገባለች፡፡ በሀይቁ መኻል እንደደረሰች አዞ ሊበላት እንደሚፈልግ ሲነግራት ግን ወድያው ነቃች እና በመላ አዞን አታልላ ከሞት ታመልጣለች፡፡ ተረቱ በሁለት ነገር ማየት ይቻላል፡፡ አንድም "የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ አይደለም" እንደሚባለው የተነገረህን ሁሉ አትመን፣ የነገሮችን ባህሪ ለመመርመር የሚያስችል ብልሐት ይኑርህ

የሚል ነው፡፡ ይህንን በዘንጅሮ ዘውብሎ መግባት እና አደጋ ላይ መውደቅ ተገልጽዋል፡፡ ሌላው ደግሞ በተለያየ አጋጣሚ በጠላት እጅ ከወደክ ደግሞ በፍርሐት ከመርበት እና ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ የሆነ የምታመልጥበትን ዘዴ ፈልግ የሚል አንድምታ ያለው ነው፡፡ ይህን ደግሞ በዘንጅሮ አለመርበትበት እና ምክንያት የማበጀት ክህሎት አማካኝነት ተገልጽዋል፡፡

በተረት ሳላሳ አንድ ድመት እና ደሮዎች በአንድ ቤት ውስጥ ከጌቶቻቸው በሰላም ይኖሩ የነበረ ቢሆንም አንድ ቀን ጨጨራ ሲሰርቅ ተይዞ ህይወቱ ለማትረፍ ሲል የተናገረውን ወሬ ድመት ሳይጠረጥር በመስማቱ ከደሮዎች ጋር ሲጣሉ እናያለን፡፡ በዚህም የሰሙትን ወሬ ሳይጠረጥሩ እንዳለ መቀበል ተገቢ እንዳልሆነ የሚነግር ተረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ጠላት በመኻከል ክፍተት ለመፍጠር የተለያየ አሉባልታ ሊነዛ ይችላል (ጨጨራ ከውጭ መጥቶ በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖሩ የነበሩትን አጣልቷልና)፤ የሚነዛውን ወሬ ለምን አላማ እንደሆነ ቆም ብሎ ማሰብ እና ብልህ መሆን ይገባል የሚል ፍሬ ሐሳብ አለው፡፡

ተረት ሐምሳ ሰባት የኩናማ ብሔረሰብ ከጥፋት የተረፈው በአንድ ብልህ አባት አማካኝነት እንደሆነ የሚተርክ ነው፡፡ ብሔረሰቡ በታሪኩ በገጠሙት ጦርነቶች እና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ምክንያት ቁጥሩ ተመናምኖ ወደ ጥፋት ደረጃ ደርሶ የነበረ ቢሆንም በአንድ አባት ብልህነት ግን የብሔረሰቡ ዘር ሊቀጥል ችሏል፡፡ በዚህ ተረት አማካኝነት የተገለፀው ሰብአዊ ጉዳይ በኑሮ ውስጥ የብልህነት ጠቀሜታ ነው፡፡ የዚህን ዓለም ፈተናዎች ለመጋፈጥ እና አሸንፎ ለመኖር የሚያስችል ጥበብ አስፈላጊ መሆኑን ሽማግሌው ለእያንዳንዱ ሊያገጥም የሚችል ፈተና በሚወስዱት መፍትሔ እና ውጤቱ አማካይነት ተገልፅዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዕድሜ የገፉ ሽማግሌዎች ምንም እንኳ ጧሪ የሚፈልጉ እና ሽክም ተደርገው የሚታዩበት ሁኔታ ቢኖርም ቅሉ ግን ለወጣቱ ትውልድ የሚያወርሱት እውቀት ችና ጥበብ ስላለ ተንከባክቦ መያዝ ስፈልጋል የሚል ሐሳብ አለው፡፡

በተረት ስልሳ ስድስት አንድ አባት ልጆቹ በርሃብ እንዳይሞቱበት አንድ መላ ፈጥሮ ሲታደጋቸው እንመለከታለን፡፡ በአካባቢው ባጋጠመ ከፍተኛ ድርቅ ምክንያት የሚበላ ጠፍቶ የተቸገረው አባት የልጆቹን ህይወት ማትረፍ ስለነበረበት ፍየል ከጎረቤት ሰርቆ አምጥቶ ሊያበላቸው ፈለገ፡፡ ነገር ግን ነገ ጧት መስረቁን ከታወቀበት ሌላ ጣጣ ውስጥ ይገባል፡፡ ልጆቹ ደግሞ ገና ህጻናት በመሆናቸው ምስጢር ይጠብቃሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ በዚህም አንድ ዘዴ መፈለግ ነበረበት፡፡ ነገሩን "እኔ የምጠይቅህ የትናንት ምሽት፣ አንተ ምታወራው የአምና ክረምት" እንደሚባለው ለማድረግ ብልህ መሆን ነበረበት እና ልጆቹን እደጅ እንዲተኙ አድርጎ ከተኙ በኃላ ፍየል አምጥቶ በማረድ ስጋውን አብስሎ ዝናብ የዘነበ በማስመሰል ወደ

ቤት አስገብቶ ራታቸውን እንዲበሉ አድርጎ በርሃብ ከመሞት ይታደጋቸዋል፡፡ ሰውየው ብልህ በመሆኑ የመከራውን ዘመን ተሻግሮ፣ ያለውን ማሕበራዊ ህይወት ሳይነጋ ማለትም ከጎረቤቶቹ ሳይጣላ መኖር ችሏል፡፡ በዚህም ብልሐት በህይወት ዘመናችን እና ማህበራዊ ግንኙነታችን ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑ ማሳየት የተረቱ ዋና ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምድብ ስር የተካተቱ የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ኑሮ ለመምራት፣ ከአካባቢው እና ከማሕበረሰብ ተስማምቶ ለመኖር ብልሐት አስፈላጊ መሆኑ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ትዳር እንዳይ ፈርስ፣ ንብረት እንዳይወድም፣ በጠላት እጅ ላለመውደቅ እና ለማምለጥ፣ የሚጠቅምህንና የማይጠቅምህን ለመለየት፣ ወዘተ. ብልህ መሆን አስፈላጊ መሆኑ የሚያሳዩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

### 4.2.3. መጥፎ ባህርያትን የሚመለከቱ

ከመስክ ከተሰበሰቡ የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ውስጥ 27ቱ የመጥፎ ባህርያት መገለጫዎች የሆንትን ሌብነት፣ ስስት፣ ሚስጥር አባካኝነት፣ ተንኮል፣ ጉራ፣ ክፋት፣ ቅናት ወዘተ የያዙ ናቸው፡፡ በዚህ ምድብ ከተመደቡ ተረቶች ውስጥ እነዚህንና ሌሎች በመጥፎነት የሚታዩ ባህርያትን ይወክላሉ ብዬ ያመንኩባቸው ተረቶች በማሳያነት ተረት 9፣10፣12፣13፣ 30፣49፣60፣61 እና 63 እንደሚከተለው አቀርባለሁኝ፡፡

በተረት አስራ አንድ የስስትን አላስፈላጊነት በአንድ ገበሬ እና ነጋዴ አማካኝነት ቀርቧል፡፡፡ የሰው ገንዘብ እና ንብረት የሚመኝ ስስታም ሰው የራሱንም እንደሚያጣ በስስታሙ ነጋዴ አስረጂነት ቀርቧል፡፡ ነጋዴው የገበሬውን ንብረት ለመውሰድ እና ሳይደክም ሃብት ለማግኘት አስቦ ያልወሰደበትን ገንዘብ ወስደህብኛል በማለት ይከራከረዋል፡፡ ክርክራቸው ዳኛ ዘንድ ደርሶ ዳኛውም ደግሞ የነጋዴው ተንኮል ገብቶት “ገበሬው ያገኘው ሁለት ሺ ብር ነው፤ አንተ ደግሞ የጠፋብህ ሶስት ሺ ብር ነው፡፡ ስለዚህ ሌላ ቦታ ሂደህ ፈልግ፣ አንተ ደግሞ ሶስት ሺ ብር የጠፋበትን ሰው እስኪመጣ ድረስ ገንዘቡ ተጠቀምበት” በማለት ይፈርድላቸዋል፡፡ “የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል” እንደሚባለው ነጋዴው የጠፋበትን ገንዘብ በማግኘቱ ገበሬውን አመስግኖ ከመሄድ ይልቅ የራሱ ያልሆነውን፣ ያልደከመበትን ገንዘብ ለመብላት ፈልጎ ሲተናኮለው በመጨረሻም ስስታም ባህሪው ገንዘቡን ሁሉ ሲያሳጣው እንመለከታለን፡፡ በዚህም ስስት አጥፊ እንጂ ጠቃሚ አይደለም የሚለውን ሐሳብ ለማስረጽ ነጋዴው እንዲቀጣ በማድረግ የብሔረሰቡ አባላት ከዚህ የተኮነነ ባህሪ እንዲታቀቡ የሚቆጣጠር ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ስስታም ካልሆንክ፣ በራስህ ንብረት እና ገንዘብ የምትረካ ከሆነ ደግሞ መልካም ነገር እንደሚገጥምህ በየዋሁ ገበሬ ማሳያነት ተገልጽዋል፡፡ ገበሬው ገንዘቡን ካገኘ በኃላ ገንዘብ በማግኘቱ ተደስቶ ወይም ለገንዘቡ ጓግቶ አላገኘሁም ማለት ይችል የነበረ ቢሆንም፣ ዳሩ የሰው ገንዘብ ነውና አልፈለገም፡፡ በዚህ ንፅህናው ደግሞ ሲሸለም እንመለከታለን፡፡ ይህ በማድረግም የራስ ያልሆነ፣ ወድቆ የተገኘ ንብረት ለባለቤቱ መመለስ ተገቢ መሆኑን፣ ውጤቱንም ያማረ እንደሆነ ለማስገንዘብ የታለመ መሆኑ እንረዳለን፡፡ አንድ ማሕበረሰብ ያሉትን ቃላዊ ሃብቶች መልካም የሚላቸውን ተግባራት እንዲስፋፉ እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ እኩይ የሚላቸውን ደግሞ እንዳይስፋፉ ለመቆጣጠር ይጠቀምባቸዋል በማለት እንደገለፅነው የዚህ ተረት ዋነኛው ጉዳይም እኩይ ምግባርን የሚቀጣ፣ ሰናይ ምግባርን ደግሞ የሚያሞግስ እና የሚያበረታታ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ተንኮል በየተኛውንም ማህበረሰብ ማለት ይቻላል ተቀባይነት የሌለው መጥፎ ባህሪ ነው፡፡ ከኩናማ ብሔረሰብ ከተሰበሰቡ ተረቶች ውስጥም ተንኮልን በተመለከተ የሚተረቱ በርካታ ተረቶች እናገኛለን፡፡ በተረት አስራ ሁለት ውስጥ ተኩላ እና ዝንጀሮ ቀበሮን ለመግደል የቆፈሩትን ሴራ ለራሳቸው ሲያጠፋቸው እንመለከታለን፡፡ ምንም እንኳ የዱር እንስሳቱ ተከባብረው በፍቅር ይኖሩ የነበረ ቢሆንም ተኩላ እና ዝንጀሮ ከመሬት ተነስተው ቀበሮን ለማጥፋት ተንኮል ይጠነስሳሉ፡፡ ቀበሮ ደግሞ ከእነሱ በላይ ተንኮለኛ ነበር እና ነገሩን ወደ እነሱ ጠምዝዞ ሲያጠፋቸው እንመለከታለን፡፡ በእነዚህ እንስሳት ገፀ ባህሪነት የቀረበው ጉዳይ ከሁሉም ጋር በመቻቻል እና በመተባበር አስፈላጊ እና ማንንም የማይጎዳ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ ይህንን ልብ ሳይሉ በማይረባ ነገር ሌላውን መተናኮል ግን "የዘሩትን ያጭዳሉ" እንደሚባለው ነውና ውጤቱ በራስ ላይ መፍረድ መሆኑ ማሳየት ነው፡፡

በተረት ሰላሳ ውስጥ ሶስት ጓደኛሞች ተመካክረው ከአንድ ሃብታም ቤት ንብረት ሰርቀው በመውሰድ ንብረቱን በመከፋፈል ላይ ግን ሲተናኮሉ እንመለከታለን፡፡ ተረቱ እንዲህ ነው፡፡ ባድመ እና ጋላ "ንብረቱ እኛ እንጠበቃለን፣ አንተ ሂድና ምግብ አምጣልን" ብለው አሮሺን ይልኩታል፡፡ እሱ ምግብ ሊያመጣ ሲሄድ ተንኮል ያስቡና "ለምን እሱን ገድለን ንብረቱን ብቻችን አንካፈለውም" ይላሉ፤ እሱ ደግሞ በበኩሉ "ለምን እነሱን ገድዬ ብቻየን አልጠቀምም" ብሎ ተንኮል ይጠነስስ እና ምግቡ ላይ መርዝ ጨምሮ ይዞ ይሄዳል፡፡ እንደደረሰም ወድያው ይገድሉታል፡፡ እነሱም ምግቡን እንደበሉ ወድያው ይሞታሉ፤ ንብረቱም ማንም ሳይጠቀምበት ቀረ፡፡ በዚህ ተረት ሁለት የማይፈለጉ ተብለው የተኮነኑ ሰብአዊ ባህርያት በአፅንኦት ተገልፀው እናገኛለን፤ ተንኮል እና ሌብነት፡፡ ቀዳሚው ጉዳይ

“እሾህ ለአጣሪው…” እንደሚባለው ሰውን ለመጉዳት እና የራስን ጥቅም ብቻ ለማስቀደም ተንኮል ስትቆፍር አንተንም የእጅህን ታገኛለህ የሚል አንድምታ እናያለን፡፡ በመቀጠል ስርቆት መጥፎያህ፣ ከጓደኞችህ እና ወገኖችህ የሚለያይ ክፉ ባህሪ ነው፤ ሰው ሰርቆ አያልፍለትም የሚል ይመስለኛል፡፡ በዚህም በማሕበረሰቡ እነዚህ ባህርያት እንዳይስፋፉ የማድረግ ተግባር አለው ማለት እንችላለን፡፡

ተረት አስራ ሶስት ውስጥ ነብር ድመትን አግኝቶ ለምን ደቃቃ እንደሆነ ሲጠይቀው ሰው ከሚባል ፍጡር ጋር የሚኖር በመሆኑ የሰው ተግባር እንዳደቀቀው ሲነግረው እንዲያሳየው ይማጸነዋል፡፡ ምንም እንኳ ድመት ይቅርብህ፣ ሰው ማለት ኃይለኛ ፍጡር ነው፤ አያዋጣህም ቢለውም ሊሰማው አልቻለም፡፡ በመጨረሻም ሲያሳየው በትዕቢት “በል አሳይሀለሁኝ አሁኑኑ ነው ከመሬት ጋር የምደባልቀው” ብሎ ፎከረ እየዘለለ ሰውየውን ሊያንቅ ሲሄድ ሰውየው ዛፍ ላይ ወጥቶ በያዘው ገመድ አንቆ ሲገድለው እንመለከታለን፡፡ በተረቱ አማካኝነት የቀረበው ጉዳይ በመጥፎነት ከሚፈረጁ ባህርያት አንድ የሆነውን ጉራ ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ አባላት ኑሮዋቸው አካባቢያቸውን በመመስል እና በትህትና ሊመሩ እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አቅምን ሳይመዝኑ በማን አለኝነት ስሜት የምፈፅማቸው ስህተቶች ግን ዋጋ የሚያስከፍሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተረት ስልሳ  በተመሳሳይ መልኩ አቅምህን አለማወቅ የሚያስከትለው ጣጣ የሚያመላክት ነው፡፡ የተረቱ ታሪክ ባጭሩ እንደዚህ ነው፡፡ ጅብ ዘጠን ልጆች ሲኖር አንድ ቀን ልጆቹ ከአንበሳ ጋር አደን ላይ ውለው አንዲት ላም ይዘውለት ይመጣሉ፡፡ ውሎዋቸው ሲጠይቃቸው አስር ላሞች አግኝተው አንበሳ ዘጠኙን ወስዶ አንዷ ለነሱ እንደሰጣቸው ነገሩት፡፡ በአንበሳ ተግባር የተናደደው ጅብ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ፡፡ እንዴት እሱ አንድ ሆኖ ዘጠኝ ሲወስድ እናንተን ዘጠኝ እያላቹህ አንዲት ላም ይሰጣቹሃል? እኩል መካፈል ነበረባቹህ ብሎ ፎከረ፡፡ ከዚያም አንዷ ለሱ ሰጥቸ ዘጠኙን አመጣለው ብሎ ሄደ እና የአንበሳን ፊት ሲያይ በፍርሐት ቅዘን በቅዘን ሆኖ አንዷንም ላም አስረክቦ ይመልሳል፡፡ ቀደም ሲል በተረት አስራ ሶስት ላይ እንዳየነው ሁሉ በዚህ ተረት ደግሞ ጅብ አቅሙን ባለማገናዘቡ ምክንያት የነበረውን ሲያጣ እንመለከታለን፡፡ በዚህም ጉራ ምንም ጥቅም እንደሌለው የሚያሳይ ነው፡፡ የጅብ ልጆች ከአስሩ ዘጠኙ አንበሳ ሲወስድ እያዩት ባይዋጥላቸውም አቅማቸውን መዝነው የተሰጣቸውን ነው የተቀበሉት፡፡ አባታቸው ግን በባዶ ሜዳ ፎክሮ ውጤቱም ኪሳራ ሆኗል፡፡ ስለዚህ አቅምህን አውቀህ በዘዴ እና በትህትና ኑር እንጂ አጉል መንጠራራት አያስፈልግም የሚል ይዘት አለው፡፡

ሌብነት በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ አለመረጋጋት እና አለመተማመን የሚፈጥር በመጥፎነት የሚፈረጅ ተግባር ወይም ባህርይ ነው፡፡ የተለያዩ ማሕበረሰቦች የሌብነትን መጥፎነት በተመለከተ የተለያዩ አጋጣሚዎች ተጠቅመው ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ከተሰበሰቡት ተረቶች መካከል ሌብነትን የሚመለከቱ አሉ፡፡ ከእነዚህ ተረት ዘጠኝ እና ስልሳ አንድ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በተረት ዘጠኝ ላይ ሁለት አገር ያስመረሩ ሌቦች የሰውን ንብረት ለመስረቅ በቆፈሩት ሴራ ለራሳቸው አደጋ ላይ ሲጥላቸው እንመለከተላን፡፡ ሰውየውን ለመዝረፍ እንዲመቻቸው የፈጠሩትን ዘዴ ተመልሶ ለራሳቸው ሲጎዳቸው እንመለከታለን፡፡ የተረቱ አላማ የሌብነትን አስከፊነት ማሳየት ነውና ያ ለማስመሰል የሞተውን ሌባ የእውነት እንዲሞት፣ ያ ንጹህ ሰው ደግሞ እንዲድን በማድረግ አቅርቦታል፡፡ እንደዛ በማድረግም የሰው ህይወትን በማጥፋት ንብረትን ለመዝረፍ የሚደረገውን መጥፎ ባህሪ እንዲኮነን በማድረግ የብሔረሰቡ አባላት ከዚህ ባህሪ እንዲቆጠቡ የሚያስጠነቅቅ ነው፡፡

በተረት ስልሳ አንድ ውስጥ አንድ የሌብነት ባህሪ የተጠናወተው ሰው ሌብነት እንዲያቆም ባገር ቢመከርም ሊሰማ አልቻለም፡፡ ታድያ አንድ ቀን የገዛ ራሱን ንብረት የሰው መስሎት ሲሰርቅ እንመለከታለን፡፡ ሌብነት መጥፎ ባህሪ በመሆኑ አንዴ ከተለመደ ለመተው የሚከብድ መሆኑን ከዚህ ተረት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሰውየው ስርቆት ከመልመዱ የተነሳ የራሱን ንብረት ሳይቀር ለመስረቅ ሲሞክር ይታያል፡፡ ስለዚህም ይህንን መጥፎ ተግባር የሚኮንን መልእክት የያዘ ተረት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በትዳር ውስጥ ተጠራጣሪነት እና ቅናት አላስፈላጊ ባህርያት ናቸው፡፡ ከተሰበሰቡ ተረቶች ውስጥ አንድን ሰው ማለትም የትዳር አጋርን በእምነት እንጂ በሌላ መንገድ መጠበቅ እንደማይቻል የሚያሳዩ ተረቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ተረት አርባ ዘጠኝ በማሳያነት እንመልከት፡፡

በዚህ ተረት ውስጥ በአንድ ቀናተኛ ባል እና በባለቤቱ አማካኝነት በትዳር ውስጥ የመተማመንን ፋይዳ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ሰውየው ቀናተኛ በመሆኑ ሚስቱን ማመን እና ተረጋግቶ መኖር አቅቶታል፡፡ ምንም እንኳ ታማኝ መሆኗ ብታረጋግጥለትም ሊሰማት አልቻለም፡፡ በዚህ ባህሪው የተናደደች ሚስት እሷ ከፈለገች ባለቤቷ ፊትም ቢሆን የፈለገችውን ማድረግ እንደምትችል ስታሳየው እንመለከታለን፡፡ ስለዚህም ትዳርን በእምነት እንጂ በመጠራተር አይመራም የሚል አንድምታ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ተረቱ ቅናት ማያስፈልግ እና የትዳር ግንኙነትን የሚያበላሽ ባህሪ መሆኑን ለማሳየት ቅናት የተናወጠውን

ሰውየ ሚስቱ ፊት ለፊቱ ከሌላ ሰው ጋር ስትማግጥ በማድረግ ይሳለቅበታል፡፡ በዚህም ቀናተኛ አትሁን፣ ትዳር ላይ እምነት ይኑርህ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ስር የተመደቡት የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች በብሔረሰቡ ዘንድ በመጥፎነት የሚገለጹ ባህርያትን አስከፊነት በመግለጽ እና ውጤታቸው በማሳየት የብሔረሰቡ አባላት በስነ ምግባር ተቀርጸው፣ መልካም ስብእና ተላብሰው እንዲያድጉ የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ስነ ቃል የመገሰፅ እና የመቆጣጠር ተግባር አለው እንደተባለው ሁሉ እነዚህ ተረቶችም የብሔረሰቡ አባላት ባህሉ የማይቀበላቸው እና የማያምንባቸውን ባህርያት እንዳይተገብሩ፣ መጥፎ ባህርያት እንዳስፋፉ የሚቆጣጠሩ እና የሚገስፁ ናቸው፡፡

### 4.2.4. ጓደኝነትን የሚመለከቱ

የሰው ልጅ አኗኗሩ ማህበራዊ በመሆኑ በአካባቢው ከሚገኙ መሰሎቹ ጓደኝነት መስርቶ ይኖራል፡፡ በጓደኝነት ውስጥ መመካከር፣ አብሮ መዋል፣ አብሮ መሰደድ፣ ተባብሮ ችግር መፍታትና ጠላት መከላከል ወዘተ የመሳሰሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በተመሰረተው ጓደኝነት ላይ ምቀኝነት፣ ቅናት፣ መናናቅ… የመሳሰሉ አላስፈላጊ ባህርያት ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ከኩናማ ብሔረሰብ ከተሰበሰቡ ተረቶች ውስጥ በጓደኝነት ዙርያ ላይ የሚያጠነጥኑ ተረቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ተረት 7፣29፣43፣55 እና 70 በማሳያነት እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

በተረት ሰባት አንበሳ እና ቀበሮ በጓደኝነት አብረው እየኖሩ ሳለ ቀበሮ ክርስትያን እንሁን ተባብለው የገቡትን ቃል ባለማክበሩ ጓደኝነታቸው ሲፈርስ፣ ኃላ ግን አንበሳ ለጓደኝነታቸው ሲል ይቅርታ አድርጎለት ጓደኝነታቸው ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲመለስ እንመለከታለን፡፡ ይህንን ተረት የተረኩልኝ መረጃ አቀባዬ አቶ ዮሐንስ እንደገለጹልኝ ይህንን ተረት እውነትነት ያለው ነው፡፡ የኩናማ ብሔረሰብ የክርስትና እምነት የተቀበለው በቅርቡ ነው፡፡ ክርስትና ከመቀበሉ በፊት ያገኘውን አድኖ እየበላ ነፃ ሆኖ በፍቅር ይኖር ነበር፡፡ ክርስትና ሃይማኖት ከመጣ በኃላ ግን በአመጋገብም ይሁን በሌላ አንተ እንዲህ ታደርጋለህ፣ አንተ እንደዚህ አታደርግም የሚሉ ነገሮች እንደተከሰቱ ገልጸውልኛል ( አቶ ዮሐንስ፣ ጥር፣ 23/2009 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ በመነሳት ታድያ ይህንን ተረት ለብሔረሰቡ አባላት በአመጋገባችን ሆነ በእምነታችን ምክንያት ከጓደኞቻችን ጋር ልንጣላ አይገባም፤ ከሁሉም በላይ ጓደኝነት እና አንድነት ይበልጣል የሚል አንድምታ ያለው ሆኖ አግኝቸዋለው፡፡

ጓደኝነት ሲመሰረት አቅምን፣ ባህሪን ወዘተ. ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው ከእነማን ጋር እንደሚውሉ ጓደኞቻቸው እነማን እንደሆኑ ያሳስባቸዋል፡፡ ጓደኞቻቸው መምረጥ እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡ ተረት ሃያ ዘጠኝ ጓደኞችን መምረጥ እንደሚገባ የሚያስተምር ነው፡፡ ተረቱ የተለያየ ባህሪ ባላቸው ቀበሮ፣ ጅብ፣ አንበሳ፣ ከርከሮ እና አህያ አማካኝነት ተመስርቶ የቀረበ ነው፡፡ የተረቱ ዋና ጉዳይም ጓደኝነት ስትመሰርት ጓደኞቼ እነማን ናቸው? ብለህ አስብ፤ ጓደኞችህ ምረጥ መቻል አለብህ የሚል ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በተረቱ ውስጥ የምናገኛቸው እንስሳት ጓደኝነትን ለመመስረት እና አንድ ላይ ለመጓዝ የሚያስችል ባህሪ የሌላቸው ናቸው፡፡ አህያ፣ ጅብ እና ከርከሮ ከየዋህነታቸው የተነሳ ከአጥፊዎቻቸው ጋር ነው ጓደኝነት የመሰረቱት፡፡ በኃላም በማይረባ ምክንያት ህይወታቸው ሲገብሩ እንመለከታለን፡፡ አንበሳም ቢሆን ጉልበቱን ተማምኖ ሁሉንም ጓደኞቹ እንዳሰኘው እንደሚያደርግና በራሱ እንደሚተማመን ቢያውቅም ቀበሮ ባቀነባበረው ተንኮል ህይወቱን አጥቷል፡፡ በዚህም ጓደኝነታቸው ጤነኛ እና በልክ ያልተሰፋ እንዳልነበረ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ ይህ ተረት ጓደኝነት ስትመሰርት እና ጓደኞችህ ላይ እምነት ስትጥል መጀመርያ እነማን መሆናቸውን በአግባቡ እወቅ፣ አንተን የሚመስሉና የማይከዱህ መሆናቸውን አረጋግጥ የሚል ሐሳብ የያዘ ነው፡፡

ተረት አርባ ሶስት በጓደኝነት መካከል ራስ ወዳድነት አላስፈላጊ መሆኑን የሚያስተማር ነው፡፡ አንዱ ያለውን ለሌለው ማድረግና መከባበር እንደሚገባ፣ እንጂ እኔን ብቻ ይመቸኝ ማለትና ራስ ወዳድ መሆን ትርፍ እንደሌለው የሚገልፅ ነው፡፡ ዝንጀሮና ግመል አብረው ሲኖሩ ግመል ለጓደኝነታቸው ሲል የቻለውን ሁሉ ሲያደርግ፣ ዝንጀሮ ደግሞ በአንጻሩ ብልጣ ብልጥ በመሆን ግመልን ሲጎዳ ተደርገው ነው የተሳሉት፡፡ ቀበሮ ታድያ ይህን ባህሪው መጨረሻ መጥፊያው ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ተረት የተገለጸው ጉዳይ ጓደኝነት በመተጋገዝ እና እርስ በርስ በመከባበር ላይ መመስረት እንዳለበት ነው፡፡ የራስን ጥቅም ብቻ ማስቀደም ግን ጓደኝነት ለማፍረስ የሚዳርግ ዋና ምክንያት እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡

ተረት አምሳ አምስት የጓደኛ አስፈላጊነት የሚገልፅ ነው፡፡ በህይወት ዘመናችን ደስታ፣ ሐዘን፣ መከራ እና ተድላ ያጋጥሙናል፡፡ ታድያ እነዚህን ስሜቶች እና አጋጣሚዎችን የሚጋሩን የኛ የምንላቸው ጓደኞች እንደሚያስፈልጉን በዚህ ተረት ጥረት ተደርጓል፡፡ በመስክ ቆይታየ እንደተገነዘብኩት እና የብሔረሰቡ አባላት (አቶ ብርሃነ ኬኞ እና ግደይ ቱርኳ፣ ጥር 13/2009 ዓ.ም) እንደገለፁኝ በኩናማ ብሔረሰብ ሐዘን የበለጠ በሴቶች እንደሚፀና ነው፡፡ አንድ ሰው ሲሞት ሴቶች እራሳቸውን የበለጠ በመጎዳት እና ከቤት ሳይወጡ፣ ምግብ

በአግባቡ ሳይበሉ፣ ልብስ ሳይቀይሩ ለረዥም ጊዜ (እስከ አንድ አመት ድረስ) በሐዘን ይጎዳሉ፡፡ እንዲህ አይነት አጋጣሚ ሲከሰት ሐዘን ይብቃ በማለት የሐዘንተኛዋ ሴት የቅርብ ጓደኞች "የሐዘን ሻሽ የማስጣል" ስርዓት ያከናውናሉ፡፡ የሐዘን ሻሽ ማስጣል ስነ ስርዓት ከተካሄደ በኃላ ሐዘንተኛዋ ሴት ወደ ቀድሞ ማህበራዊ ህይወቷ እንድትመለስ ይደረጋል፡፡ በዚህም ነፃ በመሆን በሰርግ፣ በአረም እና አጨዳ ዘመቻዎች ትታደማለች፣ ትዘፍናለች፣ ትጨፍራለች፡፡ እንዲህ ለማድረግ እና ሐዘኗን ለማስረሳት ግን አሁንም የቅርብ ጓደኞቿ የላቀ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ በዚህ ተረት ውስጥም በሐዘንተኛ ቆቅ፣ በጅግራ እና ጦጣ አምሳያነት የቀረበው ጉዳይ ይህ የጓደኞች ሚና ነው፡፡ ትክክለኛ ጓደኞቻችን ከገጠመን ችግር ወጥተን ሰላማዊ ኑሮ እንድንመራ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው የሚያሳይ ተረት ነው፡፡

በተረት ሰባ ውስጥ በጓደኝነት መኸከል የመስማማት እና የመደማመጥ አስፈላጊነት ተገልፅዋል፡፡ "አለመስማማት ለጠላት ይበጃል" እንደሚባለው በሁለት ጓደኛሞች ድመቶች እና ቀበሮ አማካኝነት የቀረበው ሐሳብ ከጓደኞቻችን ጋር መስማማት እንዳለብን፣ ካልሆነ ግን ለጠላት እንደሚያጋልጥ ነው፡፡ ድመቶቹ እራታቸውን በስምምነት መብላት አቅቶዋቸው አሳቢ በመምሰል የመጣውን ቀበሮ ሲበላባቸው እንመለከታለን፡፡ በዚህም ህይወታችን ከጓደኞቻችን ጋራ ተደማምጠን በአንድነት ካልመራነው ጠላት አለመስማማታችን ተጠቅሞ ያጠቃናል፡፡ ስለዚህ በጓደኝነት መኸከል መስማማት ተገቢ ነው በማለት በጓደኛሞች መኸከል ስምምነት እና እንድነት እንዲኖር ለማስተማርያነት የቀረበ ነው፡፡

### 4.2.5. ጥንካሬ እና ሙሉ ጤንነትን የሚመለከቱ

በምዕራፍ ሶስት ስር የብሔረሰቡ አጠቃላይ ዳራ ላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የኩናማ ብሄረሰብ ለበርካታ ዘመናት ከሌሎች አጎራባች ብሔረሰቦች ከሚገጥሙት ግጭቶች እና ጦርነቶች እየተከላከለ እና እየሸሸ የነበረ ህዝብ ነው፡፡ አኗኗሩም እስከ ቅርብ ጊዜ አደን ላይ የተመሠረተ አንደ ነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት ጠላቶቹን ገጥሞ ለማሸነፍ፣ አልያም ደግሞ ሸሽቶ ለማምለጥ ጠንካራ እና ደልዳላ ሰውነት እንዲሁም ሙሉ ጤንነት ሊኖረው ይፈልጋል፡፡ አውሬ አድኖ እና ታግሎ ለማሸነፍ እንዲሁ ጠንካራ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ለማድረግም የተለያዩ ጥንካሬን የሚፈትኑ ባህላዊ ከበራዎች ይከውናል፡፡ የጥንካሬ አስፈላጊነትም ይሰብካል፡፡ ለምሳሌ "አናኢላ" በማለት የሚታወቀውን ስርዓተ ከበራ የዚህ ማሳያ ነው፡፡ በተረት ሐምሳ ላይ እንደተገለፀው አካል ጉዳተኞች እና አቅመ ደካሞች በሸሽት ጊዜ ይገደሉ እንደነበር እና ተረቱ አውነት መሆኑ እንደሚያምኑ መረጃ አቀባዮቼ አረጋግጠውልኛል፡፡ በዚህ መሠረትም ከተሰበሰቡ ተረቶች ውስጥ ብሔረሰቡ

አባላቱ ጠንካራ ሰውነት እና ሙሉ ጤንነት እንዲኖራቸው የሚሰብኩ ተረቶች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ተረቶች ውስጥ በማሳየነት ተረት 22፣ 44 እና 58 እንመልከት፡፡

ተረት ሃያ ሁለት ሶስት የተለያየ የአካል ጉዳት ያላቸው ሰዎች ወደ አደን ሄደው ሳይመለሱ ሲቀሩ ያሳያል፡፡ አንዱ ከመጠን በላይ በመወፈሩ፣ አንዱ እግሩ በጣም በመቀጨጩ፣ አንዱ ደግሞ ጉንጩ የተሰፋ በመሆኑ የገጠማቸውን ፈተና መቋቋም ተስኖዋቸው በረኸ ላይ ሲቀሩ እንመለከታለን፡፡ ስለዚህም የጥንካሬ እና ሙሉ ጤንነት አስፈላጊነት የሚገልፅ ተረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ባሉ ጊዜያት የብሄረሰቡ ኑሮ አደን ላይ የተመሰረተ የነበረ በመሆኑ አካል ጉዳተኞች እና አቅመ ደካሞች አደን ሊያድኑ ብለው በረኸ እንዳይሄዱ የሚያስጠነቅቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተረት አርባ አራት ውስጥ ሶስት ሰዎች ወደ አደን ይሄዳሉ፡፡ ሰዎቹ አንዱ ቦርጫም፣ አንዱ እንድ አይኑ፣ አንዱ ደግሞ ጠንካራ ተዋጊ ናቸው፡፡ አደን ቦታ ላይ እንደደረሱ ቦርጫሙ እና ባለ አንድ አይኑ አጋዘን ከበው ለመያዝ ጥረት ሲያደርጉ ዘንዶ መጥቶ ቀምቶ አጋዘኖቹ ይበላባቸዋል፡፡ ያ የመዋጋት ክህሎት ያለው ጠንካራ ሰውየ ግን አይደለም ከአጋዘን ጋር ከሚያስፈራው ዘንዶ ጋርም ገጥሞ፣ ዘንዶውን ገድሎ ነፃ ያወጣቸዋል፡፡ ስለዚህ ይህንን ተረት መልካም ጤንነትና ጠንካራ ሰውነት (የተዋጊነት ብቃት) ይኑርህ፣ ካልሆነ ጠላቶችህ በቀላሉ ያጠቁሃል፣ ያለህን ሃብትና ንብረት ይዘርፉሃል የሚል ይዘት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

ተረት ሃምሳ ስምንት በኩናማ ብሔረሰብ በድሮ ዘመን ተፈፅሟል በማለት የሚታመንበት አፈ ታሪክ ነው፡፡ አንድ ወገን ዘመድና አቅም የሌለው ሰው ንብረቱ ሲዘረፍ እና አይኑ እያየ ከብቶቹ እተነዱ ሲሄዱ ዝም ከማለት ውጪ የሚያደርገው ነገር አልነበረውም፡፡ ታግሎ ለማሸነፍ እና ጥቅምህን ለማስከበር ሐይል እና ወገን እንደሚያስፈልግ ሲገባው የእህቶቹ ልጆቹ ከህፃንነታቸው አሲዞ ፍልምያ፣ ሩጫ እና ቀስት ውርወራ እያስተማረ ጠንካራ እና ደልዳላ ሰውነት እንዲኖራቸው አድርጎ ያሳድጋቸዋል፡፡ በመጨረሻም አቅመ ደካማ በመሆኑ ያጣውን ንብረቱ በነዚህ የፈረጠመ ጡንቻ ባለቸው የእህቱ ልጆች አስመልሶ ተከብሮ ሲኖር እንመለከታለን፡፡ በዚህም ይህ ተረት የብሔረሰቡ አባላት ጠንካራ ሰውነት እና የተከላካይነት መንፈስ እንዲያዳብሩ የሚያስተምር ነው ማለት ይቻላል፡፡

አቶ ፀጋይ ገብረማርያም እና ብርሃነ ኬኞ በቀን 23/05/2009 ዓ.ም ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ እንደገለፁልኝ ኩናማዎች "አናኢላ" ወይም "የፀጉር መላጨት" የሚባል ስነ ስርዓት

አላቸው፡፡ በዚህ ስርዓተ ከበራ የብሔረሰቡ አባላት ወደ በርኸ በመውሰድ የተለያዩ ጥንካሬ እና ሙሉ ጤንነትን የሚፈትሹ ፈተናዎች እንደ እሳት መጨበጥ፣ መዝለል፣ ከአቻዎቻቸው ጋር ትግል መግጠም፣ ከእንጀራ ጋር አሸዋ ማኘክ ወዘተ. የመሳሰሉትን ይፈትኑዋቸዋል፡፡ ይህ በወጣቶች ከፍተኛ የውድድር መንፈስ የሚያሳድር ባህላዊ ከበራ በመሆኑ ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል ጠንካራ ሆኖ ለመገኘት የቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ገልፀውልኛል፡፡ ማንም ሰው ሰነፍ መባል አይፈልግም፡፡ በመላጨት ስነ ስርዓት ላይ ተፈትኖ የወጣ ወጣት ሚስት ሊያጭ፣ ትዳር ሊመሰርት ባህሉ ይፈቅድለታል፡፡ ካልሆነ ግን ማለትም ፈተናውን ሳይወጣ ሲቀር ግን እንደ ወጣት ሊታይም አፉን ሞልቶ ሊናገርም አይችልም፡፡ ስለዚህ ጠንካራ መሆን ይጠበቅበታል ብለውኛል፡፡ ከዚህ ባህላዊ መሠረት ያለው እምነት በመነሳትም በዚህ ምድብ ስር የተካተቱትን የብሔረሰቡ ተረቶች የጥንካሬ እና ሙሉ ጤንነትን አስፈላጊነት የሚገልፁ፣ ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል ጠንካራ እና ወታደራዊ ቁመና ያለው እንዲሆን የሚሰብኩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያና ይሁንታ

ይህ ክፍል በጥናቱ ውስጥ ለተነሱ ጉዳዮች አጭር ማጠቃለያ የሚቀርብበት፣ እንዲሁም የይሁንታ ሐሳቦችንም የሚሰነዘርበት ነው፡፡

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በሰሜናዊው የአገራችን ጫፍ የሚገኙትን የኩናማ ብሔረሰብ ተረቶች ሰብስቦ በዓይነትና በይዘት በመመደብ የይዘት ትንተና ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለጥናቱ እንደ ዋና መነሻ ምክንያት የሆነው የብሔረሰቡ ፎክሎራዊ ሃብት ያልተጠና በመሆኑ፣ በተለይ ደግሞ “ተረቶች” ላይ የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ ይህንን ክፍተት ለመሙላት እና ተረቶቹ ወደ አካዳምያ ለማምጣት ጥናት ማድረግ የሚያስፈልግ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በዚህ መነሻነትም ከብሔረሰቡ 78 የሚሆኑ ተረቶች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህ ተረቶች በዓይነታዊ ምደባ በአካባቢያዊ መጠርያ “ሳማ ኬካ” እና “ሴና ሳማ”፤ በሙያዊ ምደባ ደግሞ አፈ ታሪክ፣ ገላጭ እና ፋብላ ናቸው፡፡ በጥናቱ እንደተገኘው ከጠቅላላ ስብስቡ ውስጥ 10 ተረቶች በ “ሳማ ኬካ” ምድብ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ ከሙያዊ ምደባ አንፃር ሲታዩ ደግሞ ከጠቅላላ ስብስቡ ውስጥ 66 ተረቶች “ፋቡላች” ስር በመካተት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ “ኤላ ሳማ” በመባል የሚታወቁት ተረቶች በሙያዊ ምደባ ሲታዩ ሙሉ በሙሉ በ “ፋቡላ” ተረቶች ናቸው፣ “ሳማ ኬካ” በመባል የሚታወቁት ደግሞ አፈ ታሪክ እና ገላጭ ተረቶች ውስጥ የሚመደቡ መሆናቸው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከኩናማ ብሔረሰብ የተሰበሰቡ ተረቶች ከይዘት አንፃር ሲታዩ በአምስት ዋና ዋና ይዘቶች ስር የሚመደቡ ሲሆኑ፤ እነሱም የት መጣንነትን የሚያሳዩ፣ ብልህነትን፣ መጥፎ ባህርያትን፣ ጓደኝነትን እና ጥንካሬን የሚመለከቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚነዚህ ምደባዎች መካከል መጥፎ ባህርያትን የሚኮንኑ እና የብልህነትና አስተዋይነትን አስፈላጊነት የሚሰብኩ ተረቶች አብላጫ ቁጥር ይዘው ተገኝተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ብሔረሰቡ መጥፎ ለሚላቸው ባህርያት ያለውን ከፍለኛ ጥላቻ እና ማህበራዊ ህይወት ለመምራት ደግሞ ብልህና አስተዋይ መሆን እንደሚያስፈልግ የሚያምን መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከተረቶቹ የይዘት ትንተና በመነሳት አብዛኞቹ ተረቶች ብሔረሰቡ ጠቃሚ የሚላቸውን እሴቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የብሔረሰቡ አባላት በስነ ምግባር እና ግብረ ገብነት የታነፁ እንዲሆኑ የሚያስተምሩ፣ የብሔረሰቡ ባህላዊ ስርዓት እንዳይናጋ ደግሞ የሚያስጠነቅቁ፣ ታሪክን የሚተክሉ እና ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው ሰራሽ እንቆቅልሾችን በመፍታት የህሊና እረፍት እንዲገኝ የማድረግ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡

## 5.2. ይሁንታዎች

ይህንን ጥናት ከግብ ለማድረስ ከተደረጉ ጥረቶች እና ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሐሳቦች ቀርበዋል፡፡

- የኩናማ ብሔረሰብ ባህሉ፣ ታሪኩ እና ከአካባቢው ጋር ያለውን ትስስር ሲያስተምርባቸው የቆየ ተረቶቹ በአሁኑ ጊዜ እየተረሱ እና ብዙም አገልግሎት ሲሰጡ አይታዩም፡፡ በዚህም የሚመለከታቸው አካላት ተረቶቹን ለመሰነድ እና ለመቀረስ እንዲሁም ወጣቱ ትውልድ እንዲያውቀው በማድረግ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ ቢወጡ፤
- በአሁኑ ጊዜ የኩናማ ብሔረሰብ ቋንቋው የመማር እድል ተመቻችቶለት ተማሪዎች እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ኩናምኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት እየተማሩት እንደሆነ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በመፅሐፍ ዝግጅት እና ሰርዓተ ትምህርት ቀረፃ የሚሳተፉ አካላት ለስነ ቃል ትኩረት ሰጥተው በሚዘጋጁ መፃሕፍት የብሔረሰቡ ተረቶች እንዲካተቱ ቢያደርጉ፤
- የኩናማ ብሔረሰብ እንደሌሎች ብዙ የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋው የመፃፍ እና ባህሉን የማሳደግ መብቱ ተነፍጎ የቆየ በመሆኑ የብሔረሰቡ ታሪክ፣ ባህልና አገር በቀል እወቀት ቃላዊ በሆነ መልኩ በእድሜ በገፉ ሰዎች ላይ ነው የሚገኘው፡፡ ይህንን ቃላዊ ሃብት እንዳይጠፋ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም የብሔረሰቡ ተወላጆች በፅሑፍ ለመሰነድም ሆነ በተለያየ መልኩ ለመቀረስ ጥረት ቢያደርጉ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሃፍታይ ገብረእግዚአብሔር፡፡ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ፡፡" የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2003 ዓ.ም. ፡፡

ለማ ንጋቱ፡፡ "በየም ብሔረሰብ ፆታ ተኮር ተረቶች የወንድ እና የሴት ምስል ትንተና፡፡" ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1999 ዓ.ም. ፡፡

ማንያለው አባተ፡፡ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ትረካ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው፡፡" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣1999 ዓ.ም.፡፡

ምንዳ ገብሬ፡፡ "የጌድኦ ልማዳዊ ስርዓትና ዝርው ቃል ተረኮች፡፡" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣2000 ዓ.ም.፡፡

ሞላ ጀምበሬ፡፡ "በአሳይታ ወረዳ የአፋር ብሔረሰብ ተረቶች ምደባ እና የይዘት ትንተና፡፡" የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2002 ዓ.ም.፡፡

ሰጉም አስመላሽ፡፡ "የኩናማ ብሔረሰብ ትውፊታዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና ተውኔታዊ ዓላባዎች፡፡" የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፣1999 ዓ.ም.፡፡

ብርሃነ ሃይለስላሰ ፡፡ **ራህዋ** ፡፡ ፒኮሎ ማተምያ ድርጅት፣ መቐለ፣ 2003 ዓ.ም.፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ " የስነ-ቃል ምንነት፣ ዘውጎችና አተናተን፡፡" በወጣቶች፣ ስፖርትና ባህል ሚንስተር የተዘጋጀ አገር አቀፍ የስነ ቃል ዎርክሾፕ ላይ የቀረበ፣ ግንቦት 12-14/1995ዓ.ም. ፡፡

ታየ ገብረማርያም፡፡ **የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ**፡፡ ንግድ ማተምያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣1995፡፡

አማረ ሞላ፡፡ "የሻካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና፡፡" የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

ከሁሉም በላይ፡፡ "የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች፡፡" የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2004 ዓ.ም.፡፡

ኒቆዲሞስ ኢድሪስ፡፡ "የአባያዊ ቋንቋዎች ዘርፍ ክፍል አንድ-አንድ የኩናማ ቋንቋ አፋዊ ኪነተ-ቃላት ስብስቦች መዘርዝር፡፡" የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣1973 ዓ.ም.፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ **የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን**፡፡ ንግድ ማተምያ ድርጅት፣1992 ዓ.ም.፡፡

የታሕታይ አድያቦ ወረዳ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት፡፡ *አድያቦና መጽሔት፡፡* ቤት ማሕተም ፐላኖግራፊ፣ መቐለ፣ 1ይ ሕታም፣ ቁፅሪ 3፣ 2001 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ **የስነ ቃል መምርያ**፡፡ አልፋ አታሚዎች፣ 1991 ዓ.ም.፡፡

Abrams, M. H. **A Glossary of Literary Terms**. (7th edn). Boston: Heinle and Heinle, 1999.

Angesom Abadi. "Marking of syntactic Relations In kunama." M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Linguistics, 2012

Arewa, O.E. ***A* Classification of the Folktales of the Northern East African Cattle Areas by Types.** A New York Times Company, New York: 1980.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore." The Journal of African Folklore, Vol.67, No.266 (Oct- Dec, 1954), 333-349, American Folklore Society, http:// WWW.Joster.org/ stable/URL.

Bender, M. Lionel. **Nilo-Saharan.** In Bernd Heine and Derek Nurse (eds.), *African languages: An introduction.* Cambridge: Cambridge University Press, 2000.

Cittadini,M. “The Kunama and Marriage Ceremonies: A Kunama Marda Marriage” A Paper Prepared In Advance for the Interdisciplinary Seminar of the Faculties of Arts and Education, *In Journal of Ethiopian Studies*. Addis Ababa University, 1967.

Donald A. Macdonald. **Field Work: Collecting Oral Literature**. 1972.

Dorson, Richard M. (ed.) **Folklore and Folk Life: An Introduction**. Chicago: The University of Chicago Press, 1972.

Fischer, J.L.“The Sociopsychological Analysis of Folktales.” The Journal of *Current Anthropology*, Vol. 4, No. 3 (Jun., 1963), p. 235-295, The University of Chicago Press, http:// WWW.Joster.org/ stable/URL.

Gray, Martin. **A Dictionary of Literary Terms**. (2nd revised edition), Longman Singapore Publisher Ltd, New York Press, Longman, 1992.

Finnegan, Ruth. **Limba stories and Story Telling.** Oxford: Clarendon Press, 1967.

------------------ . **Oral Literature in Africa.** Oxford: Clarendon Press, 1970.

Goldstein, Kenneth. **A Guide for field works in folklore**. The American folklore society: folklore association Inc. 1964.

Kumar Ranjit. **Reseach Methodology: A setp-by- step guide for beginners** (3rdedn). London: SAGE Publication Ltd, 2011.

Leach, Marea. (Ed.) **Funk and Wagnalls Standard Dictionary of Folklore, Mythology and Legend.** New York: Funk and Wagnalls, 1949.

Natty**,** Alexander “The Impact of Euro- Christian mission of Kunama Traditional Culture.” M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Linguistics, 1982.

Nikodimos Idries. “The Kunama and Their Languages.” M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Linguistics, 1987.

Okpewho, Isidore. **African Oral literature**. Bloomington and Indiana Polish, Indian University Press: 1992.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. **Living Folklore: An Introduction to the study of People and their Traditions.** Logan, Utah: State University Press, 2005.

Thompson, Stith. **The Folktale.** The Dryden Press, New York, 1946.

V.propp. **Morphology of the Folk the Folktale.** (2nd revised edition), Austin, University of Texas Press, 1968

# የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | ዕድሜ | አድራሻ | የተረት ብዛት | ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሂወት ተ.ማርያ (ወ.ሮ) | 46 | መዳበ | 2 | 27/05/2009 | |
| 2 | ሃይለ ወለላ (አቶ) | 83 | ገዛ መቐር | 4 | 26/06/2009 | ጎሳ መሪ |
| 3 | ለታይ ኬኛ (ወ.ሮ) | 45 | ገዛ መቐር | 2 | 19/05/2009 | |
| 4 | ሐረጉ ንጉሰ (ወ.ሮ) | 48 | ዕርዲ ወያነ | 2 | 16/05/2009 | |
| 5 | መድህን ብስራት (ወ.ሮ) | 71 | መዳበ | 7 | 20/06/2009 | |
| 6 | ሚኪኤለ ጆቦ (አቶ) | 38 | ሽራሮ | 1 | 19/05/2009 | |
| `7 | ሰሎሞን ገ.ክርስቶስ (አቶ) | 54 | ዒላ ኩናማ | 2 | 28/05/2009 | |
| 8 | ሳህለ ገራሪ (አቶ) | 75 | ሽምቢሊና | 2 | 20/05/2009 | ጎሳ መሪ |
| 9 | ሽቱ አዋዱ (ወ.ሮ) | 57 | ዓዲ ጎሹ | 3 | 17/06/2009 | |
| 10 | ብርሃነ ኬኛ (አቶ) | 43 | ሽራሮ | 2 | 15/05/2009 | ባ/ት/ቢ ሃላፊና የብሄረሰቡ ተወካይ |
| 11 | ተተ ቶሊ (አቶ) | 46 | መዳበ | 3 | 18/05/2009 | |
| 12 | ተኽላይ ማትዮስ (አቶ) | 73 | ዓዲ ጎሹ | 5 | 15/06/2009 | |
| 13 | አቶ ነጋ ሚኮ (አቶ) | 76 | ዒላ ኩናማ | 1 | 23/06/2009 | |
| 14 | አለማሽ ገ.ዮሐንስ | 63 | ገዛ መቐር | 2 | 22/05/2009 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | (ወ.ሮ) | | | | | |
| 15 | አስመረት ሰሎሞን (መ.ርት) | 32 | ዓዲ ጎሹ | 1 | 19/05/2009 | ተርጓሚ |
| 16 | አሽብር ጃምቦ (መ.ር) | 38 | ዓዲ ጎሹ | 1 | 25/06/2009 | ተርጓሚ |
| 17 | አበዶም ገ.ዮሐንስ (መ.ር) | 40 | ሽምቢሊና | 4 | 25/05/2009 | ተርጓሚ |
| 18 | አብርሀት ቱላ (ወ.ሮ) | 80 | ገዛ አዱራ | 3 | 22/05/2009 | |
| 19 | ክፍላይ አራራይ (አቶ) | 49 | ዒላ ኩናማ | 1 | 13/05/2009 | |
| 20 | ኮንታለ ሊ.ጋ (አቶ) | 55 | መዳበ | 3 | 11/05/2009 | |
| 21 | ውጁ ሚኮ (ወ.ሮ) | 60 | ዒላ ኩናማ | 1 | 19/06/2009 | |
| 22 | ዓንዶም አይጋው (አቶ) | 47 | መዳበ | 1 | 18/05/2009 | |
| 23 | ጅኔ ሃይለስላሴ (ወ.ሮ) | 68 | ገዛ አዱራ | 5 | 23/05/2009 | |
| 24 | ገብረሚካኤል አራሪ (አቶ) | 48 | ዕርዲ ወያነ | 3 | 17/05/2009 | |
| 25 | ገብረማርያም ጎደ (አቶ) | 58 | ዓዲ ጎሹ | 3 | 16/06/2009 | |
| 26 | ገ.ክርስቶስ ቶሊ (አቶ) | 87 | ሽምቢሊና | 4 | 24/06/2009 | |
| 27 | ገ.ዮሐንስ ሐመዳይ (አቶ) | 80 | አደባይ | 1 | 21/06/06 | |
| 28 | ግደይ ቱርኳ (አቶ) | 81 | ዒላ ኩናማ | 3 | 13/05/2009 | |
| 29 | ግደይ ዮሐንስ (አቶ) | 76 | አደባይ | 2 | 23/05/2009 | |
| 30 | ፀጋይ ገ.ማርያም (አቶ) | 60 | ሽራሮ | 1 | 25/06/2009 | |
| 31 | ፊንጃን ግደይ (ወ.ሮ) | 51 | ገዛ መቐር | 3 | 20/05/2009 | |

# አባሪ-1 ከኩናምኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ተረቶች

## ተረት አንድ

በአንድ ወቅት አሞራ በአንድ ትልቅ ዛፍ ላይ ጎጆዋን ሰርታ እንቁላል ጥላ በሰላም ትኖር ነበር፡፡ አንድ ቀን ቀበሮ በዛፉ ስር ሲያልፍ ቀና ብሎ አሞራ የሰራችውን ጎጆ ያይና ተንኮል አሰበ፡፡ በነጋታው ከጭቃ የተሰራ መጥረብያ ይዞ መጣ እና "ስሚ አሞራ ዛፉን በዚህ መጥረብያ ከስሩ ቆርጬ እጥለው እና ጎጆሽን ይፈርሳል፤ መኖርያም አይኖርሽም፡፡ ስለዚህ ይህ እንዳይሆን ከፈለግሽ ከእንቁላሎችሽ አንድ ስጪኝ፤ አለበለዝያ እቆርጠዋለው" በማለት አስፈራራት፡፡ እሷም ፈራች እና አንድ እንቁላል ሰጠችው፡፡ በነጋታውም ከጭቃ የተሰራውን መጥረብያ ይዞ በመምጣት ያስፈራራት እና እሷም እንድ እንቁላል ትሰጠዋለች፡፡ እንዲህ እያደረገ አስቸገራት፡፡ አንድ እንቁላል ብቻም ይዛ ቀረች፡፡ አንድ ቀን ፀጉሯ ልትሰራ ጓደኛዋ ጋር ሄደች፡፡ ቀበሮ ባደረሰባት ችግር ከስታ እና ጠቁራ ነበር፡፡ ጓደኛዋ ምን ሆና እንደተጎሳቀለች ስትጠይቃት "አንድ በአራት እግሩ የሚሄድ፣ ረዥም ጭራ ያለው ፍጡር መጥረብያ ይዞ እንቁላል ካልሰጠሽኝ ዛፉን እቆርጠዋለሁኝ እያለ እያስፈራራ ልጆቼን ጨረሰብኝ፤ አንድ እንቁላል ብቻ አስቀረብኝ" ብላ ነገረቻት፡፡

ጓደኛዋም ያ ተንኮለኛ ቀበሮ መሆኑን ገባት እና ሌላ ቀን ቢመጣ እምቢ እንድትለው፣ የያዘው መጥረብያም የውሸት መሆኑን ነገረቻት፡፡ በነጋታውም ቀበሮ እንደለመደው መጣ እና እንድትሰጠው ጠየቃት፡፡ እሷም "እስከ ዛሬ ያታለልከኝ ይበቃሀል፣ ከፈለክ ቁረጠው እንጂ አለልሰጥህም" አለችው፡፡ ከዚያ ቀበሮ በያዘው መጥረብያ ዛፉን ህህ ሲለው መጥረብያውን ስብር አለ፡፡ ከዚያም ስለነቃችበት በጣም ተናደደ እና "ቆይ ከነማን ጋር እንደዋልሽ ገብቶኛል አሳይሻለው" ብሎ ፎክሮ ሄደ ይባላል፡፡

(ብርሃነ ኬኞ፣ 15/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሁለት

በድሮ ዘመን ባል እና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባልየው ለአደን መሄድ ስለፈለገ ሚስቱ ስንቅ እንድታዘጋጅለት ነገራት፡፡ እሷም ውሽማ ለምዳ ነበር እና በጣም ደስ አላት፡፡ ስንቁን በሚፈልገው መልኩ አዘጋጀችለት እና "አንተ አደን ደርሰህ እስክትመለስ ድረስ እንዳልፈራ ቤተሰቤ ጋር ሂጄ እህቴን ይዣት ልምጣ" አለችው ፡፡ ፈቀደላት እና ወደ ውሽማዋ ሄደች፡፡ ከዚያም ውሽማዋ ሴት ኢንዲመስል

ኣደርጋ ፣ ፀጉሩ ሽሩባ ተሰርቶ፣ የሴት ቀሚስ ለብሶ ይዛው መጣች፡፡ ለባለቤቷ በሴት ድምፅ ስለአዋራው ምንም ሳይጠረጥር "በሉ ደህና ሰንብቱ" ብሎ ተሰናብቶዋቸው ለአደን ሄደ፡፡ ሚስቱ እና ውሽማዋ እሱ ከአደን እስኪመለስ አብረው ሰነበቱ፡፡ ከአደን እንደተመለሰ ውሽማዋ "በዪ እንግዲህስ እንዳያውቅብን እኔ መሄድአለብኝ" ብሎ ለጉዞ ተነሳ፡፡ ከዚያ ባለቤቷ "አማቼን እኔ ነው ምሸኛት" አለ፡፡ ሚስትየውም የባለቤቷን አመል ታውቃለች እና "አይሆንም እኔ ነው ምሸኛት ብላ ተቃወመች፡፡ ባልየውም "ከመቼ ነው ሴት ሸኚ የሆነችው?" ብሎ እሱ ሊሸኘው ጉዞ ጀመሩ፡፡ በመንገድ ላይ ባልየው አማቹን ደስ ስላለችው ሊዘርፋት ትግል ገጠሙ፡፡ ከስንት ክርክር በኃላ እውድቆ ቀሚሷን ሲገልበው ወንድ ሆኖ አገኘው፡፡ ነገሩን ገብቶት በጣም ተናደደ እና ሚስቱን ቀጥቅጦ ለመግደል አስቦ ትልቅ ዱላ ቆርጦ እየተጣደፈ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ሚስቱ ደግሞ እቤታቸው ደጃፍ ተቀምጣ ሁኔታውን ታጤን ነበር እና ቀረብ ሲል "ወይኔ ጉድ ሆነናል ጉድ…ጉድ…ጉድ" በማለት እሪታዋን ለቀቀችው፡፡ ባሏም ተደናግጦ "ምን ሆነሻል? የምን ጉድ ነው?" ብሎ ጠየቃት፡፡ እሷም ቤተሰቦቼ በመላ ታመዋል አሉኝ፣ ወንዶች የነበሩትን ሴት፣ ሴት የነበሩትን ደግሞ ወደ ወንድ እየተቀየሩ ነው" አለችው፡፡ እሱም "እና አንቺ ወደ ወንድ ተቀይረሻል?" አላት፡፡ "አዎ ጀምሮኛል" ብላ የእንትንዋን ጫፍ አሳየችው፡፡ እሱም ቀድሞ እህቷ ወደ ወንድ ተቀይራ አይቷል እና "በይ በቃ አታልቅሺ ይህ የፈጣሪ ስራ ነው" ብሎ አጽናናት ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ሐረጉ ንጉሰ፣ 16/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሶስት

በአንድ መንደር የሚኖሩ ሁለት ጅል ባል እና ሚስት ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ደሮ አርደው መብላት ፈለጉ፡፡ አርደው ሊበሉ መአድ ሲቀርብ ሚስትየው "ከበላን በኃላ ጥርሳችን የምናጸዳበት ሰርዶ አላቀርብንም፤ ስለዚህ መጀመርያ በርኸ ሂደን ማምጣት ይኖርብናል" አለችው፡፡ እሱም በሀሳቧ ተስማማ እና ተያይዘው ሰርዶ ፍለጋ ሄዱ፡፡ መንገድ ላይ የቤታቸውን አቅጣጫ ይዘው የሚጓዙ ሰዎች አገኙና "እናንተ እቤታችን መንገድ ዳር ነው፣ ደሮ አርደን አዘጋጅተን ከበላን በኃላ ጥርሳችን ይምናፀዳበት ሰርዶ ልናመጣ እየሄድን ነው፤ ስለዚህ ቤታችን ገብታቹህ እንዳትበሉብን አደራ" አሉዋቸው፡፡ ሰዎቹም በጅልነታቸው ተገርመው ሄዱ እና የጅሎቹ ቤት እንደደረሱ ጎራ አሉና ደሮ ወጡን ጥርግርግ አድርገው በልተው ሽክላ ድስቱን ክፍት አድርገውት ሄዱ፡፡ ባል እና ሚስት ሰርዶ ይዘው ሲመለሱ ያስቀመጡትን ደሮ ወጥ አላገኙትም፡፡ በምትኩ ድስቱን ዝምቦች

ወሮዉት ሲያዩ እነዚህ ናቸው ወጣችን የበሉብን ብለው ዱላ አንስተው ሸክላ ድስቱን እንክትክት አደረጉት፡፡ አንድ ዝምብ ዘሎ ሴትዮዋ ሆድ ላይ አረፈ እና ለባልዋ በምልክት ስታሳየው ዝምቡን እገድላለው ብሎ በዱላሚስቱን ሆዷ መታት፡፡ እሷም እርጉዝ ነበረች እና ወድያው ሞተች ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ሐረጉ ንጉሰ፣ 16/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አራት

በአንድ አካባቢ አቡ ጉጄ የሚባል ስራ የማይወድ ሰነፍ ሰው ነበረ፡፡ ሰው ሲሰራ እሱ ግን እንደ ሴት እየተኳኳለ ይውላል፡፡ አንድ ቀን ባል እና ሚስት አረም እያረሙ ሳለ አቡ ጉጄ አሸብቆ በዚያ ሲያልፍ ያዩታል፡፡ ዝም ብሎ ሲመላለስ ሴትዮዋ አትኩራ ትመለከተዋለች፡፡ ይህን ስታደርግ ባሏ ልብ ብሏል፡፡ ከዚያም ማታ "እኔ ስራ አለብኝ" ብሎ በነጋታው እንደሚመለስ ነግሯት ይሄዳል፡፡ ከጨለመ በኃላ ማንነቱን ሙሉ በሙሉ ቀይሮ አቡ ጉጄ መስሎ መጣ እና አንኳኳ፡፡ ማነህ ስትለው አቡ ጉጄ ነኝ አላት፡፡ ሴትየዋም በጣም ተደስታ እየሮጠች ሂዳ በሩን ከፍታ እንዲ ገባ ጋበዘችው፡፡ ከዚያም "ትልቁ ሙክት ልረድልህ?" ስትለው አይሆንም አላት፡፡ "እሺ መካከለኛውስ?" ብላ ጠየቀችው፡፡ አሁንም ተቃወማት፡፡ "እሺ ትንሹ ወጠጤ ልረድልህ?" ስትለው ተስማማ እና አርዳ እራት በልተው የቀረውን ሥጋ ጎተራ ላይ ደበቀቺው፣ ፈርሱ ደግሞ ፍግ ላይ ቀበረችው፡፡ ከዚያም አብረው አደሩ፡፡ በለሊት ተነስቶ ተሰናብቷት ሌላ ቀን እንደሚገናኙ ቃል ገብቶላት ሄደ፡፡ በነጋታው ከባለቤቷ ጋር እርሻ ቦታ ላይ ተገናኝተው "እንዴት አደራቹህ ቤት ንብረት እንዴት ነው?" ብሎ ሲጠይቃት "ሁሉም ደህና ነው ነገር ግን ትንሹ ወጠጤ ለሊት ማን እንደወሰደው ጠፍቷል" አለችው፡፡ ማታ እቤት እንደገቡ "በይ ወጠጤው ማን እንደ ወሰደው ልጠነቁል ነው የማሽላ ንፍሮ አዘጋጂልኝ" አላት፡፡ ካዘጋጀችለት በኃላ "ማታ አቡ ጌጃ መጥቶ ነበር፣ ከዚያም ትልቁ ምኩት ልረድልህ አልሽው አይሆንም ሲልሽ ወጠጤዉ አረድሽለት የቀረውን ሥጋ ደግሞ ጎተራ ላይ ደበቅሽው… እ" ሲላት ክው ብላ ደነገጠች፡፡ ከዚያም "እኔ ሁኜ ነው እንጂ ሰውየው ቢሆን ኖሮ እማ ትልቁን ምኩት ታርጂው ነበር" አላት ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ለታይ ኬኞ፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አምስት

በድሮ ጊዜ የአንድ ሰፈር ወጣቶች ውኃ ፍለጋ ወደ ሩቅ ቦታ ሄዱ፡፡ አብዛኞቹ ከወንድማቸው ጋር ነው የሄዱት፡፡ በመኸከላቸው አንድ ልጅ ብቻ ነው ወንድም ያልነበረው፡፡ ሩቅ እንደተጓዙ የዳይናሶር የውኃ ጉድጓድ አገኙ እና ከጉድጓዱ ገብቶ የሚቀዳላቸው ሰው ፈለጉ፡፡ ከዛ ከመኸከላቸው አንዱን ገብቶ እንዲቀዳላቸው ቢጠይቁት "እንትና ወንድሜ ይቆጣኛል፣ ለሌላው ሲጠይቁትም ወንድሜ ይቆጣኛል" እያሉ እምቢ አሉ፡፡ በመጨረሻም ያ ወንድም የሌለውን ሲጠይቁት እሺ ብሎ ከጉድጓዱ ገብቶ እየቀዳ ያጠጣቸው ጀመር፡፡ ከዚያም ለሁሉም እየቀዳ ሲያቀብላቸው የጠጡትን እየሄዱ በመጨረሻም ብቻውን ከጥልቁ ጉድጓድ ትተዉት ሄዱ፡፡ የሚያወጣውን ሰው አጥቶም እዚያ ቀረ፡፡

ለብዙ ሰዓታትም እዚያ አሳለፈ፡፡ አመሻሽ ላይ አንዲት ትልቅ ሴትዮ በዚያ መንገድ ሲያልፉ ወደ ጉድጓዱ ጎራ ብለው "ውኃስ ነበር ግን ማን ይቀዳልኛል" ሲሉ ሰማቸው፡፡ "እኔ ልቅዳልዎት? ይጠጡ" ሲላቸው ደንግጠው፣ "ከጉድጓዱ ምን ትሰራለህ? እንዴትስ ልትገባ ቻልክ?" ብለው ሲጠይቁት የሆነውን ሁሉ ነገራቸው፡፡ ከዚያም "ጉድጓዱ እኮ የዳይናሶር ነው እዚህ ቢያገኝህ ይበልሃል፤ እኔ አልችልም እንጂ አስወጣህ ነበር፤ አንድ ምክር ግን ልንገርህ ዳይናሶሩ መጥቶ ሊጠጣ ሲያጎነብስ ተዘጋጅተህ ጠብቅ እና አንገቱን ያዘው፡፡ ከዚያ ደንግጦ ወደ ኃላ ይወረውርሀል ከዚያ ትወጣለህ" አሉት እና ሄዱ፡፡

ከዚያ ዳይናሰሩ መጣ እና ተዘጋጅቶ ቆይቶ አንገቱን ቀርቀብ ሲያደርገው ከመቅጽበት ወደ ኃላ አርቆ ወረወረው፡፡ ከዚያ ዳይናሶሩ ምንድነው የወረወርኩኝ ብሎ ሊፈልግ ከጉድጓዱ ሲወጣ ልጁ ጉድጓድ አግኝቶ ተደብቆ ስለነበር አላገኘውም፡፡ ተመልሶ ወደ ውኃ ጉድጓዱ ሲገባ ልጁ ከዚያ ቦታ አመለጠ፡፡ ከዚያ በኃላ ወዴት እንደሚሄድ መንገዱ ጠፋበት እና ወደ እልም ያለ በረኻ ሄደ፡፡ ደክሞት እና እርቦት ከአንድ ዛፍ ስር አረፈ፡፡ በዛፉ ላይ አንዲት አሞራ ለልጆቿ ምግብ እያመጣች ስትሰጥ አየ እና ከነሱ እየቀማ እየበላ ይኖር ነበር፡፡ ያቺ አሞራ በየቀኑ ምግብ ለማምጣት የምትሄድበትን ቦታ በሙዚቃ ለልጆችዋ ትነግራቸው ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ወደ አገሩ እንደምትሄድ ሲሰማ ቀስ አድርጎ እግሯ ላይ ገመድ አሰረ እና ይዛው ሄደች፡፡ አገሩ እንደደረሰ ገመዱን በጠሰ እና ወረደ፡፡

አባት እና እናቱ አንድ እሱ ብቻ ነበር የወለዱት፡፡ በመንገድ እየሄዱ ሳለ እሾህ ያገኙ እና ባልየው "እሾሁን ከመንገድ አንሸው ሰው እንዳይወጋ" ሲሏት፤ "ሰው ቢወጋ ምን ቸገረኝ ልጄ እንደሆነ አገር ተመካክሮ አጥፍቶታል ስለዚህ ለማን ብየ?" አለች እና

ሳያነሱት አለፉ፡፡ ከዚያ እሾሁ ልጃቸውን ወደ ቤቱ ሲሄድ ወጋው እና እያነከሰ ሄደ፡፡ ሲያዩት አላምን ብለው ደነገጡ፡፡ ሁሉንም ነገር አጫወታቸው እና ተገረሙ፡፡ ከዚያም አንድ መላ ዘየዱ፡ ልጁን ሰው እንዳያየው ደበቁት፡፡ ሙቷል ብለውም ተዝካር አደረጉለት፡፡ የተዝካሩ ዕለት የአገሩ ህዝብ እንዳለ ተሰብስቦ መጥቶ እየበላ እና እየጠጣ ነበር፡፡ እነዚያ ጉድጓድ ውስጥ ትተውት የመጡትም እንዲሁ እዚያ ነበሩ፡፡ ከዚያም ልጁን ከተደበቀበት አውጥተው በህዝቡ መኻከል እንዲቆም አደረጉ፡፡ ሁሉንም ሰው አዲስ ትእይንት ሆነበት እና ተገረመ፡፡ ከዚያም ያጋጠመውን ሁሉ ያገሩ ህዝብ እንዲሰማ አደረገ፡፡ ከዚያ በኃላም መላው ያገሩ ህዝብ ተመካከረ፡፡ "ይህንን ልጅ በድለነዋል፣ ነገር ግን ፈጣሪ በተአምሩ አትርፎታል፤ ስለዚህ እያንዳንዳችን አዋጥተን ካሳ እንስጠው አሉና ብዙ ከብቶች፣ ፍየሎች እና ግመሎች ሰጡት፡፡ ከዚያ በኃላ ሃብታም እና ደስተኛ ሆኖ ይኖር ነበር ይባላል፡፡

(አቶ ክፍላይ አራራይ፣ 13/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስድስት

በድሮ ዘመን የዱር እንስሳት ከፍተኛ የሆነ የውኃ እጥረት ገጠማቸው እና ተሰብስበው መከሩ፡፡ እንደ መፍትሔም ለምን ተባብረን የውኃ ጉድጓድ አንቆፍርም የሚል ሀሳብ አቀረቡ፡፡ በዚህ ሀሳብ ከቀበሮ በስተቀር ሁሉም እንስሳት ተስማሙ፡፡ ቀበሮ ግን አልቆፍርም አላቸው፡፡ ከዚያም ቀበሮ ሄደ እና ሌሎቹ ተጋግዘው ኩልል ያለ የምንጭ ውኃ ቆፍረው አወጡ፡፡ በኃላ "ቀበሮ ከዚህ ውኃ እንዳይጠጣ ምን ማድረግ አለብን?" ብለው ተወያዩ እና ጉድጓዱን በየተራ እንዲጠብቁት ተስማሙ፡፡ በመጀመርያው ቀን አይጥ ተረኛ ነበር፡፡ ቀበሮ መጣ እና አይጥን አባርሮ ጠጥቶ ታጥቦ ሄደ፡፡ በነጋታዉም ውሻ ተረኛ ጠባቂ ነበር እና ለሱም አባርሮ ጠጥቶ ታጥቦ ሄደ፡፡ በዚህ ተግባሩ ሁሉንም እንስሳት ተቆጡ እና አንበሳ እኔ ጉድጓዱን እጠብቃለው አለ፡፡ ቀበሮ እንደ አመሉ መጣ እና ዘበኛው አንበሳ መሆኑ ሲያይ ተመልሶ ሄደ እና ከቤቱ ማር ይዞ መጣ፡፡ ከዚያም አንበሳ እያየው መብላት ጀመረ፡፡ አንበሳም ማር መብላት አማረው እና "ስጠኝ" አለው፡፡ ቀበሮም "ማር እንድሰጥህ ከፈለክ በል መጀመርያ ውኃ ልጠጣ?" አለው፡፡ ከዚያም "ጠጣ" አለው፡፡ ቀበሮም "እየጠጣሁ ሳለ መጥተህ እንዳትይዘኝ ስለፈራሁኝ መጀመርያ ልሰርህ?" አለው፡፡ አንበሳም ተስማማ እና በሰንበሌጥ አሰረው፡፡ ከዚያም ውኃዉን ጠጥቶ ማር ሳይሰጠው እንደታሰረ ትቶት ሄደ፡፡ በነጋታው ዝሆን እኔ ልጠብቅ እና ሲመጣ ይዤ እገድለዋለው ሲል ዛተ፡፡ ቀበሮም ልክ አንበሳን እንዳደረገው አደረገው፡፡ በመጨረሻም

ኤሊ እኔ መላ አለኝ እኔ ነኝ የሚይዘው አለና ውኃ ውስጥ ገብቶ ቀበሮ እስኪመጣ ይጠብቅ ነበር፡፡ ቀበሮ መጣ እና ሲያይ ማንም የለም፡፡ በውስጡም ሰለ ሰለቻቸው ትተውኛል ሲል አሰበ እና በነጻነት ሊጠጣ ገባ፡፡ ኤሊ ደግሞ ተዘጋጅቶ ነበር እና ዘሎ ያዘው፡፡ ከዛ በኃላ በሰንበሌጥ አስረው ምን እንደሚያደርጉት ተመካከሩ እና በእሳት እንዲያቃጥሉት ወስነው ታስሮ እያለ እሳት ላይ ወረወሩት፡፡ ሰንበሌጡን እሳት ሲነካው ተበጠሰ እና ተወርውሮ አመለጣቸው ይባላል፡፡

(አቶ ግደይ ቱርኳ፣ 13/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባት

በድሮ ጊዜ አንበሳ እና ቀበሮ በጓደኝነት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ከዚያም ከእንግዲህ ወድያስ ክርስቲያን እንሁን ብለው ተስማሙ፡፡ አንድቀን አብረው እየሄዱ መንገድ ላይ የሞተ ዓጋዘን አገኙ እና ቀበሮ እንብላ አለ፡፤ አንበሳ ደግሞ አይሆንም ክርስቲያን እንሁን ብለናል እኮ የበከተ አንበላም ብሎ ተቃወመው፡፡ ከዛ በኃላ ቀበሮ ጫማውን አውልቆ የሞተውን ዓጋዘን ቀንድ ላይ ሰካው እና መንገድ ጀመሩ፡፡ ትንሽ እንደተጓዙም ቀበሮ ጫማየን ረስቻለው ብሎ ተመለሰ፡፡ አንበሳም ሲዘገይበት ምን ሆኖ ነው ብሎ ተመለሰ እና ቀበሮ የበከተውን ስጋ እየበላ አገኘው፡፡ አምበሳ በጣም ተናደደ እና በቃ ከእንግዲህ በኃላ እኔ እና አንተ ጓደኛሞች ልንሆን አንችልም፣ እኔ ክርስትያን ነኝ አንተግን አይደለህም ስለዚ እንለያይ ብሎት ሄደ፡፡ ከዛ አንበሳ እራሱ አድኖ ዓጋዘን ያዘ እና አርዶ እየበላ ቀበሮ መጣ እና እየዞረ በተደጋጋሚ አንተ ጮማ ጮማውን ብላ እንጂ ይለዋል፡፡ አንበሳም መብላት እንደፈለገ ገባው እና መብላት ፈልገህ ነው አይደል በል ና ብላ አለው እና ታረቁ ይባላል፡፡

(አቶ ግደይ ቱርኳ 13/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስምንት

በአንድ ወቅት ቀበሮ እና ጅብ ጓደኛሞች ሆነው በአንድ አከባቢ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ በየቀኑም የሚበላ ለማግኘት አብረው አደን ይወጡ ነበር፡፡ ከእለታት አንድቀን አብረው እየተጓዙ ጅብ በጣም የሚያስጎመጅ በጥሩ አገባብ የተገነባ ቤት ሲያገኝ ቀበሮ ግን የማያምር እና ባለ ብዙ በር ቤት ሊባል አገኘች፡፡ ቀበሮ ባገኘቻው ቤት ስላልተደሰተች የጅብ ቤት የራስዋን ለማድረግ አሰበች፡፡ ከዚያም ጅብን በቀላሉ ልታታልለው እንደምትችል አሰበች፡፡ ጠጋ ብላም አያ ጅብ የሚያምር ቤት አግኝተሃል፣ ግን ምንዋጋ

አለው አንበሳ በዚች በር ቢመጣብህ ወዴት ትሸሻለህ እኔ ግን በአንዱ በር ቢመጣብኝ ሰባት በሮች አሉልኝ በአንዱ ሽሉክ ብየ እወጣለሁኝ ስትለው ጅብ ዘሎ እንቅ አደረጋት እና ቀይሪኝ አልያም ደግሞ እገድልሻለው አላት፡፡ ቀበሮ ደግሞ ተስማማች፡፡

ከዚያ ቀጥለው ምግባቸውን ሲፈልጉ ቀበሮ አህያ አገኘች፣ ጅብ ግን እድለኛ ነበር እና በሬ አገኘ፡፡ አሁንም ቀበሮ በውስጧ በጣም ተናዳ ጅብ ጋ በመሄድ ስማ አያ ጅብ ያገኘሁትን አህያ እጅግ የሰባ ከመሆኑ የተነሳ በዱላ ወገቡን ስነትረው ጮማው እንደ አቧራ ይበናል፤ ያንተ ግን አይቦንም ስትለው ጅሉ ጅብ ደግሞ ለውጪኝ በማለት በሀይል ቀማት፡፡ ከዚህ በኃላ የሚያርዱበት ነገር ጅብ ምላጭ የሆነ ቢላዋ ሲያገኝ፣ ቀበሮ ግን ፈልጋ ስለ አጣች ብዙ ላባዎች ሰብስባ እንደ አመሏዳ ጅብ ቤት ሂዳ አያ ጅቦ አንድ ብቻ ነው እንዴ ያገኘሽው ውይ እድልህ፤ እኔ ግን አንዱ ስትሰበር አንዱ እያልኩ… ብላ ንግግሯ ሳትጨርስ ለውጪ በማለት ቀማት፡፡

ጅብ በላባ ስጋ ለመቁረጥ ሲታገል አምሽቶ በጣም ስለደከመው መተኛት እንኩዋ ቢፈልግ ንፋስ በስምንቱ በሮች እየገባ እንቅልፍ ነሳው፤ ብሎም የአንበሳ ራት ሆኖ አደረ፡፡ ያቺ ተንኮለኛ ቀበሮ ግን እቤቷ ከውስጥ ቀርቅራ እራቷን በሰላም በልታ በሰላም አደረች ይባላል፡፡

(ወ.ሮ አብርሀት ቱላ 22/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ዘጠኝ

በአንድ ሰፈር ሁለት አገር ያስመረሩ ሌቦች ነበሩ፡፡ አገሩን በጣም ነበር የበጠበጡት፡፡ ሰፈር ውስጥ የሚሰርቁትን አልበቃ ብሏቸው በርሽ እንውጣ ተባብለው ተመካከሩ እና አርቀው ሄዱ፡፡ ብረት (መሣርያ) ግን አልያዙም፡፡ ከገበያ አህያ፣ ግመል ጭኖ የሚመጣ አግኝተን ዘርፈን እንብላ ብለው አድፍጠው መጠባበቅ ጀመሩ፡፡ ከሩቅ አንድ ግመል ላይ ተቆናጥጦ የሚመጣ ሰው አዩ፡፡ ከዚያም ምን እናድርግ አሉ፤ በእግሩ የሚመጣ ቢሆን ኑሮ ችግር አልነበረውም፣ ግን ግመል ላይ ነው ብለው ተመካከሩ እና አንዱ እንዲህ ሲል ሀሳብ አቀረበ አንተ እንደሞትክ መንገድ ላይ ተኛ እና ነጠላ ላልብስህ፣ ከዚያ እንድቀብረው አግዘኝ እለዋለሁኝ፣ ሬሳ እያየ ትቶኝ አይሄድም እና፤ ከዚያም ጉድጓድ እየቆፈርን እያለ አንተ ተነስተህ እና እሱን ገድለን ቀበረነው ንብረቱን እና ግመሉን እና ንብረቱን ይዘን እንሄዳለን አለው፡፡ ጓደኛውም ተስማማ፡፡ ከዚያ እንደተመካከሩት አንዱ ተኛ እና ባለ ግመሉ እየቀረበ ሲመጣ ያኛው ማልቀስ ጀመረ፡፡ ምን ሆንክ ሲለው ከወንድሜ ጋር ነበር የመጣሁት፣ መንገድ ላይ ድንገት ታሞ ሞተብኝ፤ አገራችን ደግሞ

እሩቅ ነው እባክህ እንድቀብረው አግዘኝ አለው፡፡ ሰውየውም በጣም አዘነ እና ግመሉን አምበርክኮ ወረደ እና ከመንገድ ወጣ ብለው ጉድጓድ ይቆፍሩ ጀመሩ፡፡ በየተራ እጉድጓዱ እገቡ ሲቆፍሩ የተኛውን ሳይመጣ ሲዘገይበት ምን ሆኖ ነው የማይመጣው ቆፍረን እስክንጨርስ ነው እንዴ ሚጠብቀው በማለት አሰበ እና ሊጠራው ፈለገ፡፡ ከዚያ እስቲ ሬሳውን ፀሐይ ግብቶነት እንዳይ ሆን አይቸው ልምጣ እየቆፈርክ ጠብቀኝ አለው፡፡ ባለግመሉም አዎ እውነትህ ነው ሬሳ ብቻውን አይተውም እና ሂድ እየው አለው፡፡ ከዚያም እየሮጠ ሂዶ አንተ ምን ነካህ ተነስ እንጂ ቆፍረን ጨርሰናል እኮ፣ ተነስ እንጂ ብሎ ነጠላውን ሲገልጠው የምር ሙቷል፡፡ ቢቀሰቅሰው ቢያገላብጠው የለም፡፡ ከዚያም በጣም ጨነቀው እና አንተ ሞቱ አሁን ብሏል እና በደምብ አድርገህ ቆፍረው አለው ይባላል፡፡

(ብርሃነ ኬኞ፣ 15/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስር

አንድ ከአገር አገር እየዞረ የሚነግድ ስስታም ነጋዴ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ሊነግድ ረዥም መንግድ በእግሩ ሲጓዝ ደከመው እና ከመንገድ ዳር ባገኘው ትልቅ ዛፍ ስር አረፍ አለ፡፡ ፀሐዩ አለፍ ሲልለት ተነስቶ መንገዱን ቀጠለ፡፡ ረዥም እንደተጓዘ ኪሱ ሲዳብስ በኪሱ የነበረ ለንግድ የያዘው ሁለት ሺ ብር የለም፡፡ ከዚያ የት ጣልኩት ብሎ ሲያስብ እዛ የተኛሁበት ዛፍ ስር ነው ወድቆ የሚሆን አለና ወደ ኃላተመለሰ፡፡ እዛ ጥላ ስር እንደደረሰም አንድ ሲያርስ ውሎ ደክሞት ከነ ጥንድ በሬዎቹ አረፍ ያለ ገበሬ አገኘ፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኃላ ጌታየ ሆይ ቅድም በዚህ ሳል ደክሞኝ እዚህ ጥላ ስር አረፍ ብየ ነበር እና ገንዘብ ጥያለሁኝ፣ አግኝተሀል እንዴ ሲል ጠየቀው፡፡ ገበሬውም በጣም ቅን ነበር እና አዎ ያንተ ከሆነስ ሁለት ሺ ብር አግንቻለሁኝ ይኸው አለው፡፡ ከዚያም ነጋዴው ተንኮል አሰበ እና አንዱን በሬውን ሽጦም ቢሆን ይሰጠኛል ብሎ በማሰብ አይ ጌታው እኔ የጠፋብኝ ሶስት ሺ ብር ነው የጠፋብኝ አንድ ሺ ብሩስ የት አደረከው ሲል አፈጠጠበት፡፡ ገበሬውም አንተ ምን ነካህ ትልቅ ሰው ትመስላለህ፣ ግን አይደለህም፡፡ እኔ የሰው ገንዘብ ምን ያደርግልኛል ገንዘብህ ብፈልገው ኑሮ አላገኘሁም ባልኩህ ነበር፤ ስለዚህ አትሳሳት አለው፡፡ ነጋዴው ግን ድርቅ ብሎ አንድ ሺ ብር ቀንሰህ ወስደሃል አለው፡፡ በዚህ ተጨቃጭቀው ስምምነት ላይ መድረስ ስላልቻሉ ዳኛ ይፍረደን ብለው በአካባቢው ወደ ሚኖሩ የአገር ሽማግሌ ሂደው ጉዳያቸውን አቀረቡ፡፡ ሽማግሌዉም የሁለቱን ንግግር በጥሞና ካደመጡ በኃላ የነጋዴውን ተንኮል ስለገባቸው

እንዲህ ሲሉ ውሳኔ ሰጡ በሉ እንግዲህ ነገሩ እንደዚህ ነው አንተ የጠፋብህ ገንዘብ ሶስት ሺ ነው፤ እሱ ደግሞ ያገኘው ብር ሁለት ሺ ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘቡ ያንተ ሳይሆን የሌላ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም አንተ ገንዘብህ ሌላ ቦታ ፈልገው፤ አንተ ደግሞ ሁለት ሺ ብር የጠፋው ሰው እስኪመጣ ድረስ ገንዘቡን ተጠቀምበት ብለው አሰናበቷቸው ይባለል፡፡

(አቶ ሳህለ ገራሪ 20/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ አንድ

ድሮ ድሮ ዝሆን የዱር እንስሳት ጌታ ነበር፡፡ ከዛም እንስሳቱን ሳይደክም እንዲበላቸው ፈለገ እና አንድ ብልሐት ፈጠረ፡፡ አሞኛልብሎ እቤቱ ተኛ፡፡ እንስሳቱም ጌታችን ታምሟል ብለው ሊጠይቁት እቤቱ ድረስ ሄዱ፡፡ አንዱ ቀድሞ ይገባል፣ ከሱ ቀጥሎም አንድ፡፡ የሚገባ እንጂ የሚወጣ ግን አልነበረም፡፡ ምክንያቱ ዝሆን ተዘጋጅቶ እየያዘ ይበላቸው ስለ ነበር፡፡ ከዚያም እደጅ ሆነው የሚታዘቡት መግባት እየገቡ ነው የሚወጣ ግን የለም ምንድን ነው ነገሩ ምንስ ንናድርግ ብለው ተመካከሩ፡፡ ከዛ ቀበሮ አንድ ሐሳብ መጣለት እና እኔ ገብቸ ሁኔታውን አጣራለሁኝ ብሎ ረዥም ሸምበቆ ይዞ ሄደ፡፡ እደጅ እንደደረሰም አያ ዝሆን እንደምን ሰንብተሀል አሞሀል አሉ አለ፡፡ ዝሆንም አዎ አሞኛል ግባ እስቲ እየኝ አለዉ፡፡ ቀበሮም በረዥሙ ዘንግ ከሩቅ ሆኖ ነካ አደረገው እና አዎ እውነትህ ነው ትኩሳት አለብህ በጣም ሙቀሀል ብሎት ሄደ ይባላል፡፡

(አቶ ገብረሚካኤል ገራሬ፣ 17/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ሁለት

በጥንት ዘመን የዱር እንስሳት በአንበሳ መሪነት አንድ ላይ ተሰብስበው ይኑሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ተኩላ እና ዘንጅሮ ቀበሮ የሚያደርገውን ሁሉ አልጥም ስላላቸው እንዲያጠፉት አንድ ላይ መከሩት፡፡ ከዚያ ስብሰባ ላይ በመጥፎ ዓይን ሲመለከቱት አየ እና እሱም የደህና እንዳይደለ ተገንዝቦ ፈረሱን ጋልቦ ሄደ፡፡ ተኩላ እና ዝንጅሮም ወደ አንበሳ ሄዱ እና ስማ እስቲ አያ አንበሳ ቀበሮ እኮ ጫማ መስራት ይችላል ለምን አይሰራልህም ሲሉት፣ አንበሳ ተናደደ እና ሂዱና ጥሩት አላቸው፡፡ ቀበሮ ተጠርቶ አንበሳ ፊት ቀረበ፤ አንበሳም ስማ እስቲ ቀበሮ ለምንድን ነው ጫማ መስራት እየቻልክ እስከ ዛሬ ያልሰራህልኝ፣ እንቅፋት ሲመታኝ፣ እሾህ ሲወጋኝ እያየህ ለምን ዝም አልክ ብሎ ጠየቀው፡፡ ቀበሮም የማን ሴራ እንደሆነ ገባው እና "አዎ እችላለሁኝ ጌታየ ግን ጫማውን ለመስራት የተኩላ ቆዳ እና የዘንጅሮ ጅማት ያስፈልጋል፤ ይህንን ካቀረብክልኝ አሁኑ

ልሰራልህ እችላለሁኝ" አለው፡፡ አንበሳም ምን ችግር አለው አለና ሁለቱንም ገድሎ የተኩላ ቆዳ እና የዘንጅሮ ጅማት ሰጠው፡፡ ከዛ በኃላ ቀበሮም ውኃ ውስጥ ልነክረው ነው መጀመርያ አለው፤ ለምን እርጥብ አይደለም እንዴ ሲለው ደንቡ እንደዛ ነው አለና ወስዶ ሀይቅ ውስጥ ጨመረው፡፡ ከዚያም ብዙ ሳይቆይ ወደ አንበሳ ተመልሶ ጌታየ ጫማ እንድሰራልህ የሰጠሀኝ ቆዳ እና ጅማት እንደ አንተን የሚመስል አንበሳ አትወስደውም ብሎ ከውኃ ውስጥ እንዳላወጣው ከለከለኝ አለው፡፡ አንበሳም ተናዶ ማን አባቱ ነው የኔን ንብረት የሚነካ ብሎ እየፎከረ ሄደ እና ሀይቁ ዳር ቁሞ የታለ አለው፡፡ ቀበሮም እየው አውስጥ ነው ብሎ የገዛ ጥላውን አሳየው፡፡ ከዚያ አንበሳ ዘሎ ገባ፡፡ ቀበሮ ደግሞ እንዳይወጣ በዘንግ ወደታች ተጫነው እና ብዙ ውኃ ጠጥቶ ሞተ፡፡ ከዛ ቀን በኃላ ቀበሮ ሁሉንም ጠላቶቹ ስለጠፉ በሰላም ኖረ ይባላል፡፡

(አቶ ገብረሚካኤል ገራሬ፣ 17/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ሶስት

አንድ ቀን ነብር እና ድመት መንገድ ላይ ተገናኙ፡፡ ከዚ ነብር ድመትን ስማ እስቲ ድመት መልክህ ሁሉም ነገርህ እኔን ትመስላለህ፣ የስጋ ዘመዴ ትመስላለህ ነገር ግን እኔ ግዙፍ ነኝ አንተ ግን ደቃቃ ነህ የት ነው የምትኖረው ብሎ ጠየቀው፡፡ እኔ ሰው ከሚባል ፍጡር ነው የምኖረው፡፡ ሰው ደግሞ ክፉ ነው የሰው ክፋት ነው ደቃቃ ያደረገኝ እንጂ እውነትህ ነው ዘመድህ ነኝ አለው፡፡ ነብር በመገረም ያ ሰው የሚባል ፍጡር ከኔ የሚበልጥ ኃይለኛ ነውን እኔን ያሸንፈኛል ማለት ነው ብሎ ጠየቀው፡፡ አዎ በጣም ኃይለኛ ነው ሰውን የሚያሸንፍ የለም አለው፡፡ ነብርም እባክህ አሳየኝ ብሎ ተማጸነው፡፡ ድመትም እሺ አሳይሀለሁኝ አለው እና ሰው እስኪ መጣ ድረስ መጠበቅ ጀመሩ፡፡ እየጠበቁ ሳለ መጀመርያ አንድ ሽማግሌ ሰውየ ይመጣሉ ነብርም ይህ ነው ሰው ማለት ብሎ ድመትን ይጠይቀዋል፤ ድመትም ይህ ሰው ነበር እንጂ ሰው አይደለም አለው፡፡ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ህጻን ልጅ መጣ፡፡ ነብርም ይህ ነው ሰው ማለት አለው፡፡ ድመትም ይህ ገና ሰው ሊሆን ነው እንጂ ሰው አይደለም ብሎ መለሰለት፡፡ በመጨረሻ አንድ ደልዳላ ወጣት መጥረብያ እና መጫኛ ሲመጣ አዩ እና ነብር ይህ ነው ሰው ያልከኝ ሲለው አዎ እሱ ነው ሰው አለው፡፡ ከዚያም ነብር በል እየኝ አሁን ይገፄ መሬት ላይ እንከባልለዋለሁኝ ብሎ እየፎከረ ሄደ፡፡ ድመትም እሺ አይሀለሁኝ አለው እና ነብር ወደ ሰውየው ተወርውሮ ሄደ፡፡ ሰውየው ነብርን ሲያይ አጠገቡ ወደ ነበር ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ ነብርም ሰውየው ዛፍ ላይ ሲወጣ ስላላየው እስኪመጣ ከዛፉ ስር ኾኖ

ይጠብቅ ጀመር፡፡ እየጠበቀም እንቅልፍ አሸለበው፡፡ ሰውየውም ዛፉ ላይ አድብቶ ቆይቶ የያዘውን ገመድ ዕይን ሰራለት እና ቀስ አድርጎ በነብር አንገት ላይ አስገብቶ ነብር እስኪነሳ ይጠብቅ ነበር፡፡ ነበር ከተቀመጠበት ብድግ ሲል ገመዱን ሳብ አደርጎ አጠበቀው እና ነብርን በጎረሮው አነቀው፡፡ ከዚያም ነብር ድመት ድመት እባክ እርዳኝ እባክህ ሲል ተጣራ፡፡ ድመትም አላግዝህም አለው፡፡ በድጋሚ አረ እባክህ እርዳኝ ሲል ተጣራ፡፡ ድመት ደግሞ ቀድሜ እኮ ይቅርብህ ሰው ክፉ ነው ብየህ ነበር አለው ይባላል፡፡

(መምህርት አስመረት ሰለሞን፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ አራት

በአንድ አከባቢ አንድ ወንድ እና ሶስት ሴቶች ነበሩ፡፡ ሴቶቹ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ልጁም ከነሱ ጋር ጓደኝነት መስርቶ አብሮዋቸው ጊዜ ያሳልፍ ነበር፡፡ ሲኖሩ ሲኖሩ ልጁ ሶስቱን ሴቶች አፈቀራቸው:: በተናጠል እያገኘም ፍቅሩን ያጣጥም ነበር፡፡ እንዲህ እንደሚያደርግ እነሱ ባያቁም የአከባቢው ሰው ግን ያውቃል፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ሶስቱንም ላለማጣት ዘዴ ፈለገ እና ለሶስቱንም ሴቶች አንድ አይነት(ቀይ) ሻሽ ገዝቶ ሰጣቸው፡፡ ሴቶቹም ስጦታው እንደደረሳቸው ማናችንን ነው የሚወደው ብለው ተመካከሩ እና ለምን ማንን ነው የምትወደው ብለን አንጠይቀውም አሉ እና ሂደው ጠየቁት፡፡ እሱ ደግሞ ያቺ ቀይ ሻሽ የሰጠሁዋትን ነው የምወደው ብሎ መለሰላቸው፡፡ እነሱም በውስጣቸው እኔን ነው የሚወደው፣ እኔን ነው የሚወደው ብለው ሰስቱንም ተደስተው ሄዱ ይባላል፡፡

(ሚኪኤሎ ጆቦ፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ አምሰት

ከእለታት አንድ ቀን ቀበሮ በግ አረደች፡፡ የአቅሟን ያህል ከበላች በኃላ የቀረውን ስጋ ቋንጣ እንዲሆን ፀሐይ በሚያገኘው ቦታ ሰቀለችው፡፡ ከዚያም ቁራ በዚያ አካባቢ ሲያንዣብብ አየው እና አንስቶ በላ፡፡ ቀበሮ ልትይዘው ብትሮጥ ክንፉን ዘርግቶ በሮ ሄደ፡፡ ቀበሮ በጣም ተናደደች እና እሱን የምትይዝበት ዘዴ ታሰላስል ጀመር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን አዲስ የተገፈፈ ቆዳ ለብሳ፣ የሞተ እንስሳ መስላ ሜዳ ላይ ተቀመጠች፡፡ ቁራም ምግቡን ፍለጋ በሚበርበት ጊዜ ከሩቅ አያት እና ወረደ፡፡ ጠጋ ሲል በቅርቡ የተበላ እንስሳ ነው፡፡ ከዚያ ጠጋ ብሎ ለመብላት ሲሞክር ቀበሮ ቀርቀም አድርጋ ያዘችው፡፡ አገኘሁህ አንተ ሌባ እኔ ማን መሆኔን አታቅም ማለት ነውን አለቸው፡፡

እሱም አንቺ ቀበሮ እህቴ የፈለግሽውን አድርጊኝ፣ ብቻ ገደል ላይ እንዳትወረውርኝ አላት፡፡ ለምን ብላ ጠየቀችው፡፡ አባት እና እናቴ በህጻንነቴ ረግመው ገደል ውስጥ ገብቼ እንደምሞት ነግረውኛል፣ ስለዚህ እባክሽ ብሎ ተማጸናት፡፡ እሷም የምትገድልበትን መንገድ በማወቅዋ በጣም ተደሰተች እና ገደል ላይ ወስዳ ቁልቁል ወረወረችው፡፡ ከዚያ ቁራ ክንፎቹን ዘርግቶ ተንሳፈፈና ከበለይዋ መጥቶ ቁዋቅ…ቁዋቅ… አለ፡፡ ቀበሮ ምንም እንኳ በውስጧ ብትቃጠልም ለወንድምነት ስል ለቀቅኩህ አለችው፡፡ እሱም በወንድነቴ አመለጥኩሽ እንጂ አላት ይባላል፡፡

(አቶ ግደይ ዮሐንስ፣ 23/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ስድስት

ሶስት በሬዎች በአንድነት ይኖሩ ነበር፡፡ በሬዎቹ አንዱ ነጭ፣ አንዱ ቀይ፣ አንዱ ደግሞ ጥቁር ነበሩ፡፡ ሶስቱም በእንድ ላይ ሲኖሩ ጠላት ቢመጣ አብረው እየተከላከሉ በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ከሚፈታተኑዋቸው ጠላቶች አንዱ ጅብ ነው፡፡ ሊበላቸው ቢሞክርም አልቻለም፡፡ ከዚያም መላ ፈጠረ እና አንድ ቀን ቀዩን እና ጥቁሩን በሬዎች ጠርቶ ስሙ እናንተ እኔ ሁሌ እየመጣሁ የማስቸግራቹህ ነጩን በሬ እያየሁ ስለ ምመጣ ነው፡፡ ከርቀት ስለሚታይ እሱን እያዩ ሌሎች ጠላቶች ይመጡና እየተሳቀቃቹህ ትኖራላቹህ፡፡ እሱን ከናንተ ከለያቹሁት ግን በሰላም መኖር ትችላላቹ ብሎ መከራቸው፡፡ እነሱም እውነት መሰላቸው እና ነጩን በሬ ጠርተው እኛ ባንተ ምክንያት መከራ ልናገኝ አይገባም ስለዚህ ለብቻህ ሁን አሉት እሱም ብዙ ለመናቸው ሊሰሙት አልቻሉም፡፡ ተለየ እና አያ ጅቦ በቀላሉ ይዞ በላው፡፡ እሱን በልቶ ከጨረሰ በኃላም አንድ ቀን መጣን ጥቁሩን በሬ ጠራው፡፡ በሬዉም ስማ እስቲ ዛሬስ ምን ፈልገህ መጣህ አለው፡፡ አያ ጅቦም አንተን የሚጠቅም ምክር አለኝ፣ አንተ ጨለማ ነህ ማንም አያይህም ጓደኛህ ግን ቀይ ስለሆነ በቀላሉ ይታያል ስለዚህ እሱን ብለው መጥተው አንተንም ሳያጠፉህ ለብቻህ ብትሆን ይሻልሀል ሲል መከረው፡፡ ከዚያም አመነው እና ተለያዩ፡፡ ከዚያም ጅብ ሁለቱንም በልቶ ጨርሶ እነሱን የመሰሉ ጅሎች ፍለጋ ሄደ ይባላል፡፡

(አቶ ግደይ ዮሐንስ፣ 23/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ሰባት

አንድ ወቅት ስድት ዓይነ ስዉራን ወደ ጦርነት ሄዱ፡፡ ሲሄዱ ሲሄዱ ፀሐይ በረታ እና እንረፍ ብለው ከዲማ ዛፍ ስር አረፉ፡፡ ከዚያም እንቅልፍ ይወስዳቸው እና ይተኛሉ፡፡

ተኝተው እያለ ኃይለኛ ንፋስ መጥቶ የዛፉ ፍሬ ያረግፈው እና ይመታቸዋል፡፡ ከዚያም ጠላቶቻችን መጡብን ብለው እርስ በርሳቸው ይማቱ ጀመር፡፡ ከመኸከላቸው አንዱ የዲማው ፍሬ ዓይኑ ሲመታው ዓይኑ በራ እና ማየት ቻለ፡፡ሲያያቸው እርስ በርሳቸው ነው እየተጨፋጨፉ ያሉት፡፡ ከዚያም እናንተ አቁሙ አቁሙ እርስ በርሳችን ነው እያለቅን ያለነው አላቸው፡፡ እነሱ ደግሞ ሂድ ፈርተህ ነው እንጂ የት አየህን ሲሉት ትቶዋቸው ሄደ፡፡ እነሱ ግን እርስ በራሳቸው እዚያው አለቁ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ አብርሀት ቱላ፣ 22/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ስምንት

ባል እና ሚስት ሲኖሩ ሲኖሩ ሚስትየው ውሽማ ለመደች እና ስራ መስራት እምቢ አለች፡፡ ባሏም ይጨንቀው እና ጠንቋይ ቤት ይሄዳል፡፡ ጠንቋዩ ምን ሆንኸል ሲለው ሚስቴ ድሮ ጥሩ ትሰራ ነበር፣ አሁን ግን አቆመች እና እይልኝ ይለዋል፡፡ ጠንቋዩም አንድ "ፈጊ" የሚባል አውራ ደሮ ነበረው እና በል እየኝ ስራ ልሰራ ነው ይለዋል፡፡ ጠንቋዩ ፈጊ ብሎ ጠራው እና ታረድ ሲለው ታረደ፤ ተገፈፍ አለው ተገፈፈ፤ ብሰል አለው በሰለ፤ ና ውረድ አለው ከእቶኑ ወረደ እና በሉት፡፡ ከዚያ እንደገና ወደ ነበረበት ትክክለኛ ደሮ ተቀየረ፡፡ ከዚያም በል ይህንን ደሮ ይዘህ ሂድ እና ልክ እኔን እንዳሳየሁህ አድርግ ብሎ አሰናበተው፡፡ ሰውየዉም ወደ ቤቱ ወሰደ እና አዘዘው፡፡ ከሚስቱ ጋር በሉ እና ባልየው ወደስራ ሄደ፡፡ ሚስቱም እንደ አመሏ ውሽሚ ይመጣል፡፡ ከተጫወቱ በኃላ ራቆቷ ተኝታ እያለ ደሮዉን ፈጊ ብላ ጠራችው፡፡ ሲመጣም ታረድ አለችው ታረደ፣ ተገፈፍ አለችው ተገፈፈ፣ ብሰል አለችው በሰለ፣ ና ውረድ ስትለው ግን እምቢ አለ፡፡ ከዚያም ልታወርደው ያዝ ስታደርው አለቅ አላት፡፡ ውሽማዋም ልያግዛት መጣን ያዝ ሲያደርገው እሱንም ጥብቅ አድርጎ ያዘው፡፡ ከዚያ አንዲት ሽማግሌ ሰትዮ ከጎረቤት እሳት ሊለምኑ መጥተው ሲያዩ ሁለቱንም ራቆታቸው ከድስቱ ጋር ተጣብቀው አዩ፡፡ ሊገላግሉ እጃቸውን ሲልኩ እሳቸውንም ይዞ አልለቅ አላቸው፡፡ ከዚያ በኃላ ባልየው ከስራው ሲመለስ ሶስቱንም ተጣብቀው አገኛቸው፡፡ ከዚያ ዱላ ቆርጦ መጣ እና ፈጊ ትልቋን ሴትዮ ልቀቃት አለው፤ ለቀቃት፡፡ ከዚያ ሚስቱን በያዘው ዱላ ቂጧን ቀጠቀጣት፡፡ ወደ ዝንጀሮ ተቀይራ ወደ በረሽ ሄደች፡፡ ውሽማዋንም እንዲሁ ቂጡን ሲቀጠቅጠው ውደ ዝንጀሮ ተቀይሮ ሄደ፡፡ ከዚህም ነው ዝንጀሮ የተፈጠረች ይባላል፡፡
(አቶ ኮንታለ ሊጋ፣ 11/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ዘጠኝ

በድሮ ዘመን ባል እና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ወቅቱም ኃይለኛ ድረቅ ነበር፡፡ የሚበላም ሆነ የሚቀመስ አልነበረም፡፡ ሰውየው ለእርሻ ወደ ማሳ እህል ሳይቀምስ ይሄዳል፡፡ ሚስቱም የሚበላ ነገር ስላልነበራቸው ምሳ ሳትይዝ ባዶ እጅዋን ትሄዳለች፡፡ ከዚያ እንደደረሰችም ባለቤቷ እጅግ ደክሞ፣ፊቱ ክሰል መስሎ ስታየው ደነገጠች እና ከዚህ ቀን የሚብስ ጊዜ አይኖርም በማለት "ሙቅ ላዘጋጅልህ ወይ?" ትለዋለች፡፡ እሱም እህል እንደሌላቸው ቢያውቅም በመጎምጀት ካለ እማ ስሪልን አላት፡፡ እሷም ለክፉ ቀን ይሆናል ብላ ይስቀመጠችውን አውጥታ ሙቅ አዘጋጅታ አመጣችለት እና ጠጥተው ሄዱ ይባላል፡፡

(አቶ ኮንታለ ሊጋ፣ 11/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ

አንድ ወቅት አባት እና ልጅ አረም ሊያርሙ ወደ እርሻ ቦታ አንድ ላይ ይሄዳሉ፡፡ እርሻ ቦታቸው ደርሰው እያረሙ ሳለ ወደ እርሻው አንዲት ፍየል ትገባ እና እህሉን መብላት ትጀምራለች፡፡ ከዚያም ልጁ ያያትና አር ይላታል፡፡ ፍየሏም አር አትበለኝ ቆይ ልብላ ትለዋለች፡፡ እንደገና አር ቢላት ቆይ መጀመርያ ልብላ ትለዋለች፡፡ እሱም ለየት ያለች እና የምትናገር ፍየል ከየት መጣች ብሎ በመገረም አባቱን ጠርቶ ይነግረዋል፡፡ አባቱም እንዳያት አር ሲል ተጣራ እሷም ለልጁ እንዳለችው አልወጣም አለችው፡፡ ከዚያ ዱላ ቆርጦ ይመታት እና አልሄድ ብላ ድርቅ አለች፡፡ ከዚያም አርደው ስጋዋን በልተው ከቆዳ ደግሞ ክታብ ሰርተው ክንዳቸው ላይ ያስራሉ፡፡ ከዚያ በኃላ ወደ አደን ሄዱ፡፡ አደን እንደ ሄዱ ከሩቅ ሽፍቶች ሲመጡ አዩና እንዳይ ገድሉዋቸው ፈርተው ዋሻ ውስጥ ገብተው ይደበቃሉ፡፡ ከዚያም ሽፍቶቹ በዚያ ሲያልፉ ያሰሩትን ክታብ ድምፅ ኣውጥቶ እዚህ  ተደብቀናል ኑ እና ግደሉን ብሎ ተጣራ፡፡ ሽፍቶቹም መጥተው ገደሉዋቸው ይባላል፡፡

(አቶ ኮንታለ ሊጋ፣ 11/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ አንድ

ዝሆን ከሶስት ሚስቶቹ ጋር ይኖር ነበር፡፡ ሚስቶቹ አይጥ፣ ጭሩ(የወፍ ዓይነት) እና እርግብ ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ዝሆን ጓደኞቹን ጠርቶ አደን እንሂድ አላቸው እና ሄዱ፡፡

በርኸ ሰንብተው ሲመለሱም እቤቱ አቅራቢያ እንደደረሱ ተደበቀ እና በሉ እናንተ ወደ ቤቴ ሂዱ እና ባላቹ ሙቷል በሉዋቸው እና ማናቸው ጥሩ አድርገው እንደ ሚያለቅሱልኝ ልወቅ አላቸው፡፡ እነሱም እሺ ብለው ሄዱ እና ለጭሩ መርዶውን አረዱት፡፡ እሷም ወይ ባለቤቴ ያ ባለ ትልቅ እግር እሱ እንደሞተልኝ መሬቱ ሰፋልኝ ብላ አለቀሰች፡፡ ከዚያ ቀጥለው ለአይጥ ነገሯት፡፡ አይጥ ደግሞ ዋይ ዋይ ያ ግም የት ቀረ ያ ግም ስትል አለቀሰች፡፡ በመጨረሻ እርግብን ነገሯት፡፡ እርግብም ዋይ ዋይ ውዱ ባለቤቴ ያ ሁላ አርሰህ አብልተህኝ ጋግሬ አብልቼህ የት ቀረህ ምን ገጠመህ ብላ አምርራ አለቀሰች፡፡ ከዚያ ባለቤቷ ጭሩን እና አይጥን ገድሎ ከእርግብ ጋር ኖረ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ሁለት

አንድ ቦርጫም፣ አንድ ቀጭን እግር እና አንድ ደግሞ ጉንጩን የተሰፋ ሰዎች  አንድ ላይ ወደ አደን ይሄዱ ነበር፡፡ ከዚያም በመንገድ ያ ቦርጫም ሰውየ እንዳድዕ (የፍሬ ዓይነት) ሊለቅም ዛፍ ላይ ይወጣ እና ወድቆ ሆዱ ተቀዶ ሞተ፡፡ ያ ጉንጩ የተሰፋ ደግሞ ውኃ ጠምቶት መጠጣት ሲጀምር ጉንጩ ተቀደደ እና ሞተ፡፡ ከዚያ ያ ባለ ቀጭን እግር ሰዎችን እንዲ ነግር እየሮጠ ሲሄድ ተደናቅፎ ወድቆ እግሩ ተሰበረ፡፡ ከዚያም የሚያነሳው አጥቶ እዚያው ሞተ፡፡ በዚህም የወሬ ነጋሪ ሳያገኙ ቀሩ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ሶስት

አንድ ቀን ዝሆን እና ቀበሮ እንዳድዕ ለመልቀም ወደ ጫካ ሄዱ፡፡ ሲለቅሙም አንተ በዚህ ሂድ እኔ ደግሞ በዚህ ልሂድ፤ ለቅመን ከጨረስን በኃላም እዚህ ቦታ እንገናኝ ተባብለው ተለያዩ፡፡ ከዚያ ዝሆን ብዙ ፍሬ ለቀመ፡፡ ቀበሮ ግን ምንም ሳይለቅም አንድ ጥላ ላ ተኝቶ ዋለ፡፡ አንዲት ወፍ ገድሎ ደሟን እግሩ ላይ ቀብቶ ምርኩዝ ቆርጦ እያነከሰ ወደ ተቀጣጠሩበት ቦታ ሄደ፡፡ ከዚያ ዝሆን ሲያየው ደነገጠ እና ምን ሆነኸል ሲል ጠየቀው፡፡ ቀበሮም እየለቀምኩ እያለ ከዛፍ ወድቄ እንዲት ፍሬ እንኳ አልቀምኩም አለው፡፡ ዝሆንም በጣም አዝኖ በል አይዞህ ካልቀምክ እኔ ላካፍልህ እንካ ብላ ብሎ የተወሰነ ሰጠው እና በል እንሂድ መሽቷል እኔ በእጅህ እየጎተትኩ ልውሰድህ አለው፡፡ ቀበሮም የሰጠውን ፍሬ እየበላ አይ ከምትጎትተኝ እማ እዚህ መቅረት ይሻለናል አለ፡፡ ዝሆን ደግሞ በል ና ከጀርባየ ልዘልህ አለው፡፡ ቀበሮም ጀርባህ ላይ አይመቸኝም ቁስሌን

እንዳለው ከቻልክ ትክሻህ ላይ ተሸከመኝ አለው፡፡ ከዚያ በኃላ በትክሻው ላይ ተሸክሞት ጉዞ ጀመሩ፡፡ ከዚያም ቀበሮ ትንሽ ቅፀል ቆርጠህ ስጠኝ ዝምብ ላባርርበት አለው፡፡ ቆርጦ አቀበለው እና በቅጠሉ እየመታ፣ ዝሆን ለቅሞ በጆሮው ያስቀመጠውን እንዳድዕ እየበላ ተጓዙ፡፡ ዝሆን ሳይታወቀው እያወጣ በልቶ ጨረሰበት፡፡ በአንዷት ጆሮው ሁለት ፍሬ፣ በእንዱ ጆሮውንም ሁለት ፍሬ ብቻ አስቀርቶ ሌላውን በላው፡፡ ከዚያ እቤታቸው አከባቢ እንደደረሱ ሴቶቹ እንዳይደነግጡ መታን ከዚህ አውርደኝ አለ እና ሲያወርደው አያ ዝሆን ግንድ ያዝ... ግንድ ያዝ ንፋስ እንዳይወስድህ እኔን እየወሰደኝ ነው ብሎ ዝምብሎ ሮጠ፡፡ ከዚያ ዝሆን እቤቱ ገብቶ ልጆቹን ሰብስቦ በሉ ቅርጫት አቅርቡ እና ፍሬውን ልስጣቹህ አላቸው፡፡ ጆሮውን ሲፈትሽም ከዚያ ሁለት ከዚያም ሁለት ፍሬ ብቻ አገኘ፡፡ ከዚያም የቀበሮ ተንኮል ገባው እና ቀበሮ ነው እንዲህ ያደረገኝ እና አባታችን ታሞ ተኝቷል ብላቹህ አምጡት አላቸው፡፡ ሂደው ሲነግሩት ቀበሮ ቀለብ እና ውኃ እንዲኹም ረኾም ዘንግ ይዞ ወደ ዝሆን ቤት ሄደ፡፡ ዝሆንም ንቦች እና ውሾችን ለቀቀበት፡፡ ከዚያ ቀበሮ ንቦቹን በውኃ አባረራቸው፡፡ ለውሾቹ ደግሞ ከያዘው ስጋ ወረወረላቸው፡፡ ሌሎች ውሾች ሲቀሩ አንድ ውሻ ግን እየተከተለ አባረረው፡፡ ከዚያ በመንገድ የሚሄዱ ሰዎች አገኘ እና እርዱኝ ብሎ ተማጸናቸው፡፡ ሰዎቹም ውሻውን ገደሉት፡፡ ቀበሮም እኔኮ የዝሆን ነውና የዙት እንጂ መቼ ግደሉት አልኳቹህ አላቸው ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ አራት

አንድ ቀን አንበሳ እንደ ጠጣ ተንኮል አሰበ እና ጠጣን መግደል ፈለገ፡፡ ከዚያ ጠጢት ጧት ተነስታ ምግብ ፍለጋ በረኸ ሄደች፡፡ ስቲሄድ አንበሳ አያት እና እቤቷ ገብቶ ተደበቀ፡፡ ጠጣ አመሻሽ ላይ ወደ ቤቷ ስትመለስ እቤቷ አከባቢ እንደደረሰች ተጠራጠረች እና ምንድን ነው የዛሬ እንግዳስ ዝም አለ፣ ድሮ ድሮ እቤቴ የገባ እንግዳ እሕሕ...ሕ ይል እና ውኃ እና ምግብ አቀርብለት ነበር፤ የዛሬ እንግዳ ግን የደህና አይደለም መሰለኝ አለች፡፡ አንበሳም እሕሕ አለ፡፡ ከዚያ ጠጣ አያ አንበሳ በል ደህና እደር እቤቴን ተውኩልህ፣ እኔን ግን አታገኝኝም ብላ ከሞት አመለጠች ይባላል፡፡

(አቶ ገብረሚካኤል ገራሬ፣ 17/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ አምስት

በአንድ አገር የሰው ስጋ የሚበሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ አንድ ሰው ከታመመ ወደ ህክምና ሳይሆን የሚወስዱት አርደው በሉት ነበር፡፡ ከዚያ አንድ ቀን አንድ ሰውየ ሚስቱ ትታመም እና ልጇ ውኃ ልትቀዳ ወንዝ ስትሄድ ሰውየው ጓደኞቹ ጋር ሂዶ ሚስቴ አሚታል እና ኑ እንብላት አላቸው፡፡ ከዚያም አርደው በሏት፡፡ የእጆቿ ጣቶችም ከበሩ ኃላ ሰቅለውት ሄዱ፡፡ ከዚያም ልጅ ውኃ ቀድታ ስትመለስ እናቴስ ብላ ስትጠይቀው ቤተሰብ ልትጠይቅ ሄደች አላት፡፡ ትመጣለች ብላ ስትጠብቅ ስትጠብቅ አንድ ቀን ጎረቤታቸው እናትሽማ አባትሽ አርዶ በልቷል ብላ ነገረቻት፡፡ ለጅቱም በጣም አዘነች እና እንጀራ ላይ መርዝ ጨምራ አብልታው እሩቅ አገር ሄደች ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ስድስት

አንድ ቀን ደሮ፣ ጊንጥ፣ እባብ እና አሞራ አራት ሆኖው ወደ አደን ሄዱ፡፡ አደን ውለው ወደ ቤት ሲመለሱ ዝናብ ይዘንብ እና ጎርፍ አላሳልፍ ይላቸዋል፡፡ ከወንዙ ዳር ቁመው እንዴት እንደሚሸገሩ ተመካከሩ፡፡ ከዚያም ደሮ እኔማ በርሬ እሻገራለሁኝ ይብላኝ ለእባብ እና ጊንጥ እንጂ አለች፡፡ አሞራም እኔም እድሜ ለክንፎቼ አለ፡፡ ከዚያ እባብ ከሁሉንም ቀድሞ ዋኝቶ ተሸገረ፡፡ እባብ ከተሸገረ በኃላ አሞራ በረረና ተሻገረ፡፡ ከዚያ በኃላ ደሮ ለመብረር ሲዘጋጅ ግንጥ ክንፏ ላይ ወጣ እና ይዛው ተሻገረች፡፡ ከዚያም ደሮ ሁላችንም ተሻግረናል ጊንጥ ቀረ እንጂ አለች፡፡ ጊንጥ ደግሞ ከክንፏ ዘሎ ወረደ እና እኔስ የኸው ተሻግሬ የለም እንዴ ለዛውም ቀድሜሽ ነው የመጣሁት አላት ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ሰባት

በአንድ ቀን ቀበሮ እና ጅብ ለአደን ሄዱ፡፡ ለአደን ከሄዱ በኃላ ጅብ ላም አገኘ፡፡ ቀበሮ ደግሞ በሬ አገኘ፡፡ ይዘው መጥተው በየተራ ይጠብቋቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን የቀበሮ ተራ ላይ የጅብ ላም ወለደች ቀበሮ የበሬን መቀመጫ ደም ቀባው፡፡ ከዚያም  የኔ በሬ ወለደ አለ፡፡ ጅብ ደግሞ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል በጭራሽ አላምንም አለ፡፡ ቀበሮ ግን ድሮ ድሮ ላም ጥጃ ትወልድ ነበር አሁን ግን በሬ ነው ጥጃ የሚወልደውብሎ ድርቅ አለ፡፡ ከዚያም ጅብ በል አሁን ሳር እና ጥጃ አንድ ላይ አስቀምጠን ላም እና በሬ

እንልቀቃቸው እና ማን ወደ ማን እንደ ሚሄድ እናያለን አለ፡፡ እንዲያ አደረጉ እና በሬ ወደ ሳር ሲሄድ ላም ደግሞ ወደ ጥጃ ሄደች፡፡ ቀበሮ አሁንም አላምንም አለ፡፡ ጅብ ደግሞ ይህንን ካላመንክ በል አንተ በሬህን እኔ ደግሞ ላሜን እንለብ እና ትክክለኛው ወተት የተኛው እንደሆነ ጠንቋዮች ዘንድ ወስደን እናረጋግጥ አለው፡፡ ከዚያ ጅብ ላሚቷን አልቦ አፍልቶ ያዘ፣ ቀበሮ ደግሞ ሊጥ አፍልቶ ይዘው ሄዱ፡፡ ጠንቋዮቹ ጅግራ ናቸው እና ፀጉራቸው እየተሰሩ ጠበቁዋቸው፡፡ ከዚያም ጅብ እስቲ የያዝነውን ቅመሱልን አላቸው፡፡ ከዚያም ይህ ወተት ነው ይህ ደግሞ ሊጥ (አብሲት) ነው ብለው እውነቱን መሰከሩ፡፡ ከዚያ ቀበሮ ተናድዶ ትኩሱን አብሲት አናታቸው ላይ ደፋላቸው እና ፀጉራቸው ተመለጡ፡፡ ከዚያ በኃላም ጅግራ መላጣዎች ሆኑ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ አብርሀት ቱላ፣ ጥር 22/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ስምንት

በአንድ ሀይቅ ዳር አንዲት ፍሬዋ ያማረ ተክል ነበረች፡፡ ዝንጀሮም በየቀኑ እየሄደች ዛፉ ላይ እየወጣች ፍሬውን ትበላ ነበር፡፡ ይህን ስታደርግ ደግሞ አዞ ሀይቅ ውስጥ ሆኖ ሁሌ ያያት ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዘንጅሮ ከዛፉ ላይ ወጥታ ፍሬ እየበላች ሳለ አዞ ወደ ሀይቁ ዳር መጣ እና "ደህና አደርሽ ዝንጀሮ ዛሬ የእህቴ ሰርግ አለ ተጠርተሻል" አላት፡፡ እሷም "አመሰግናለው ነገር ግን ዋና ስለ ማልችል ሰርጉ ላይ መገኘት አልችልም" አለችው፡፡ አዞ ደግሞ "ስለ ዋናው አትቸገሪ እራሴ አዝየ አደርስሻለው፣ እዚህ የዛፉ ፍሬ ከምትበዪ ድግሳችን ላይ ተገኝተሽ የፈለግሽውን በልተሽ ተጥተሽ ትመለሺያለሽ" አላት፡፡ ይህንን ሲላት ደስ አላት እና በሀሳቡ ተስማምታ ከዛፉ ወርዳ አዞ አዝሏት ጉዞ ጀመሩ፡፡ ከዚያም ሀይቁ ማኸል እንደደረሱ አዞ "ስሚ ዝንጀሮ አሁን ያመጣሁሽ ለእህቴ ሰርግ ሳይሆን እናቴ ታምማ ጠንቋይ ዘንድ ወስደናት እንድትድን የዘንጅሮ ልብ ፈልጉላት ስላለን ልብሽን እንድትሰጪኝ ነው" አላት፡፡ ዝጅሮም ወድያው ነቃች እና "በጣም ደስ ይለኛል፣ የእናትህ መድሐኒት ልሰጥህ በመቻሌ እድለኛ ነኝ፤ ነገር ግን ልቤ ዛፉ ላይ ነው ትቻት የመጣሁት ስለዚህ ወደ ዛፉ መልሰኝ እና አውርጄ አመጣልሀለሁኝ" አለችው፡፡ ከዚያ አዞ በጣም ተደሰተ እና እሺ ብሎ ወደ ዛፉ መለሳት፡፡ ሀይቁ ዳር ካደረሳት በኃላ ዘላ ወረደች እና "በል ከንግዲህ በኃላ እኔን አታገኝም ድሮዉንም እርስበራሳቹህ ነው የምትባሉት እና ሂዱ እዛ ተባሉ" ብላው ዛፉ ላይ ወጣች ይባላል፡፡

(አቶ ተተ ቶሊ፣ 18/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ዘጠኝ

አንድ ቀን ቀበሮ፣ ጅብ፣ አንበሳ፣ አህያ እና ከርከሮ ወደ አደን ሄዱ፡፡ መንገድ ላይ ውኃ ጥም ያዛቸው እና አንበሳ ቀበሮን "ውኃ አምጪልን" ብሎ ሐርቢ (ከቆዳ የሚሰራ ውኃ መያዣ) አስይዞ ይልካታል፡፡ ከሄደች በኋላ ውኃ መያዣውን በጥርሷ ቀደደችው እና "እያፈሰሰ አልይዝ ብሎኛል" ብላ ባዶ እጇ ተመለሰች፡፡ አምበሳም "ታድያ ምን እናድርግ?" ሲላት "ከጅብ ቆዳ ለምን አንጠግነዉም?" ስትለው ከጅብ ቆዳ ትንሽ ገፎ ሰጣት፡፡ ቀበሮም ቆዳውን ማር ነክራ "አያ አንበሳ በመርፌ አልወጋ ብሎኛል እና እንካ በጥርስህ አለስልሰህ ስጠኝ" አለችው፡፡ አፉ ውስጥ ሲከተው ጣፈጠው እና ዋጠው፡፡ ከዚያም ጅብ ቆዳው እንዲህ ከጣፈጠ ሥጋው ምንኛ ጣፋጭ ይሆናል ማለት ነው አለና ጅብን አርደው በሉት፡፡ ከዚያ በኋላ አህያን "ሂድ ሥጋ ፈልገህ አምጣልን" አሉት፡፡ አህያም ሥጋ ስለማይበላ ሳሩን በልቶ ባዶ እጁ ተመለሰ፡፡ እነሱም ለራሱ በልቶ ሳያመጣልን ቀረ ብለው አርደው በሉት፡፡ ከዚያ አንበሳ ቀበሮ እና ከርከሮ ቀሩ፡፡ ከዚያ የቀበሮ ተራ ደረሰ እና "ሥጋ አምጪ" አሏት፡፡ ቀበሮም ትንሽ ተጉዛ እያለቀሰች ተመለሰች፡፡ አንበሳ "ምን ሁነሽ ነው?" ሲላት "አያ አንበሳ እናትህ ሙታለች ብለውኝ ነው የማለቅሰው" አለችው፡፡ ከዚያም አንድ ላይ ያለቅሱ ጀመር፡፡ የከርከሮ ጥርስ ከውጭ ነው እና ቀበሮም "አያ አንበሳ አንተ ስታለቅስ ከርከሮ እየሳቀብህ ነው" አለችው፡፡ አንበሳም ተናድዶ ገደለው እና በሉት፡፡ ከዚያ በኋላ አንበሳ ቀበሮን ሂጂ የሚበላ ፈልገሽ አምቺ አላት እና ሄደች፡፡ ከዚም ትንሽ ቆይታ ተመለሰች እና አያ አንበሳ ሥጋ ይዣልህ ስመጣ አንድ ካንተ በጉልበት የሚበልጥ ፍጡር መንገድ ላይ አግኝቶ ቀማኝ አለችው፡፡ አንበሳም በጣም ተናደደ እና እኮ ከኔ የሚበልጥ! ነይ እስቲ አሳኝ ብሎ ፎከረ፡፡ ከዚያ ሲሄዱ ሲሄዱ አንድ ጥልቅ ኩሬ አገኙ እና ቀበሮ ፈጠን ብላ ተሻግራ አያ አንበሳ ይሄው ያ ያልኩህን ፍጡር ብላ ወደ ውኃው አመላከተችው፡፡ አንበሳ ወደ ውኃው ጠጋ ብሎ ሲያይ የገዛ እራሱን ጥላ አየና ዘሎ ሊያንቀው ከውኃው ገብቶ ሞተ፡፡ በዚህም ቀበሮ ሁሉንም ጨረሳቸው ባላል፡፡

(ወ.ሮ አለማሽ ገብረዮሐንስ፣ 25/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ

ባድመ፣ ጋላና እና አሮሺና የሚባሉ ሶስት ሌቦች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ወደ አንድ የሀብታም ቤት ገብተው ብዙ ገንዘብ ሰረቁ፡፡ ከሰረቁ በኋላ ሰው ከማይንቀሳቀስበት ቦታ ሂደው ሊካፈሉት ተስማሙ፡፡ ወደ በረሃ ሲሄዱ ውኃ ጥም እና ርሀብ አልቻሉም፡፡

ተመካክረውም አንድ ሰው ሂዶ ምግብ እንዲያመጣ ተስማሙ፡፡ አሮሺ ሂዶ እንዲያመጣ እጣ ደረሰው፡፡ በእድሜም እሱ ያነሰ ነበር፡፡ እሱ እንደ ሄደ ባድመ እና ጋላ ተንኮል ጠነሰሱ፡፡ ሲመጣ እንዲገድሉት እና ገንዘቡን ለሁለት እንዲካፈሉት ተስማሙ፡፡ አሮሺ በበኩሉ ሌላ ተንኮል አሰበ፡፡ ሁለቱንም አጥፍቶ ገንዘቡን ለብቻው ማድረግ አሰበ፡፡ ከዚያም ምግብ ላይ መርዝ ጨምሮ ይዞላቸው ሄደ፡፡ ቀጥታ እንደደረሰ ባድመ እና ጋላ መቱት እና ሞተ፡፡ ከዚያ ያሰብነውን አሳክተናል ብለው ምግቡን በሉት፡፡ ብዙ ሳይቆዩ እነሱም ወድያው ሞቱ፡፡ ያ ገንዘብ ሶስቱንም ሳይጠቀሙበት ምስጥ በላው ይባላል፡፡

(መ.ር አበዶም ገብረዮሐንስ፣ 27/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ አንድ

አንዲት ሽማግሌ ሴት ነበሩ፡፡ አንድ ቀን መሰሶ (ለዳጋ የሚሆን ቂጣ) ጋግረው ፀሐይ ላይ ያሰጡታል፡፡ ድመት ከመሰሶው አጠገብ እንጨት ላይ ተደብቆ ተኝቶ ነበር፡፡ ደሮ ደግሞ እዚያው አከባቢ መሬት እየጫረች ትለቃቅም ነበር፡፡ ከዚያ በኃላ ጨጨራ ምግብ ፍለጋ ወደዛ ይመጣ እና ድመት አይቶት አባርሮ ይይዘዋል፡፡ ሲይዘው ጨጨራ "ቆይ ቆይ አትምታኝ ሰዎች አንተን ምን እንዳሉህ ልነግርህ ነው የመጣሁት" አለው፡፡ ድመት ደግሞ "እስቲ ንገረኝ ምንድን ነው?" አለው፡፡ ጨጨራም በፍርሐት "ትናንት ደሮዎቹ እናሸንፈዋለን አሉ እና ልነግርህ ስፈልግህ ነበር" አለው፡፡ ከዚያ ለቀቀው እና ደሮዎቹን ሰብስቦ አንዷን "ስሚ እስቲ አንቺ እኔን አታውቂኝም ማለት ነው እንደዛ ብለሽ የምታወሪው?" አላት፡፡ እሷም እንዳልተናገረች ስለምታውቅ "እኔ እንደዛ አላልኩህም ስለዚህ ማን እነደነገረህ ንገረኝ?" አለችው፡፡ ከዚያ ድመት ፎከረ፣ ደሮም ፎከረች፡፡ ገጠሙ እና ድመት ደሮን በጉሮሮዋን አንቆ አሸናት፡፡ ከዚያ በኃላ ጨጨራ እየሮጠ መጥቶ አገላገላቸው እና "አንተ ለምንድን ነው ጉሮሮዋን የምታንቃት?" ሲለው ድመት ደግሞ "እኔ እኮ በቀልድ ነው ያነቅኳት" አለ፡፡ ደሮ ደግሞ "ጉሮሮ በማነቅ ምን ቀልድ አለ?" አለችው ይባላል፡፡

(መ.ር አበዶም ገብረዮሐንስ፣ 27/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ ሁለት

አህያ እና ውሻ እንሸፍት ተባባሉ እና በረሽ ሄዱ፡፡ ቀኑን ሙሉ ሲጓዙ ውለው መሸባቸው፡፡ ከመሸ በኃላ ማደርያ አጥተው ይጨነቁና ሲፈልጉ ሲፈልጉ አንዲት ዖና አግኝተው እዚህ አድረን እንሂድ ብለው ጎራ አሉ፡፡ አህያ በየመንገዱ ያገኘውን ለምለም

ሳር እየበላ እንዲሁም ውኃ እየጠጣ ሲጓዝ ስለዋለ እጅግ ጠግቦ ነበር፡፡ ትንሽ ከተኙ በኃላም "ሳል ይዞኛል እና ልሳል ወይ?" ብሎ ውሻን ይጠይቀዋል፡፡ ውሻ ደግሞ "ምን ላይ እንዳለን አላወቅክም እንዴ የምትስል?" አለው፡፡ ትንሽ ቆይቶ እንደገና "ልሳል ወይ?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ በል "ድምፅህን ዝቅ አድርገህ ይሁን" አለው፡፡ አህያም አፉን በሙሉ ከፍቶ "ሀ..ሀ…ሀ….ሀ" አለ፡፡ ከጨረሰ በኃላ ውሻ ብርክ ያዘው እና "እኔ ቀስ ብለህ ስልህ እንዲያ ትጮሀለህ እንዴ? ጅብ ቢመጣብን ማን ይገላግለናል?" አለው፡፡ ብዙም ሳይቆይ ጅብ ድምፅ ሰምቶ መጣ እና አህያን ይገድለዋል፡፡ ውሻ ደግሞ እቶን ውስጥ ገብቶ ተደበቀ፡፡ ጅብ ውሻን ሲያው "ና አንትን ምንም አልልህም፣ ይልቅ ና ስጋ ጥበስ እና እንብላ" አለው፡፡ ከዚያ ውሻ ስጋ ጠበሰ እና እሱን በልተው ሌላ ፍለጋ ሄዱ ይባላል፡፡

(መ.ር አበዶም ገብረዮሐንስ፣ 27/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ ሶስት

አንበሳ እና ቀበሮ አንድ ላይ አደን ሂደው አንበሳ በሬ፣ ቀበሮ ደግሞ ላም አግኝተው ተመለሱ፡፡ ከዚያም በየተራ አንድ ላይ ይጠብቁዋቸው ነበር፡፡ ላሚ እርጉዝ ነበረች እና አንድ ቀን አንበሳ እየጠበቃቸው ሳለ ወለደች፡፡ ከዚያም የበሬውን መቀመጫ ደም ቀባው እና ቀበሮ ሲመጣ "የእኔ በሬ ወለደ" አለው፡፡ ቀበሮም በመገረም "ስማ አያ አንበሳ ከመቼ ጀምሮ ነው በሬ የሚወልደው? የኔ ላም ነች የወለደችው እንጂ" አለው፡፡ አንበሳም "እውነት ነው ድሮ ድሮ ላም ትወልድ ነበር አሁን አሁን ግን በሬ ነው የሚወልደው" አለው፡፡

ቀበሮ ይህንን ሐሳብ ስላልተዋጠለት ወደ ዳኛ እንሂድ ተባባሉ፡፡ አንበሳ ደግሞ የእንስሶች ሁሉ ንጉስ እኔ ነኝ ስለዚህ ሐሳቤን ማንም ደፍሮ የሚቃወም አይኖርም ብሎ በመተማመን እንሂድ አለው፡፡ ከዚያም በመንገድ ጅብን አግኝተው "ሽምግለን" አሉት እና አንበሳን ስለፈራ "አላውቅም" አለ፡፡ በመጨረሻ ጦጣ ዘንድ ሄዱ እና ጉዳያቸውን አቀረቡ፡፡ ጦጣ ደግሞ ሐሳባቸው ካደመጠ በኃላ መልሱን አስቤ እነግራቹዋለው ብሎ ሄደ፡፡ ከዚያም ትንሽ ራቅ ብሎ አለት ይፈለፍል ጀመር፡፡ አንበሳ ደግሞ "አንተ ምን እያደረግክ ነው?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ጦጣም "አለት እየላጥኩ" አለው፡፡ አንበሳ ደግሞ "አለት ይላጣል እንዴ?" አለው፡፡ ጦጣ ደግሞ "ታድያ በሬስ ይወልዳል እንዴ?" ብሎ መለሰለት፡፡ ከዛ በኃላ አንበሳ ጦጣን እያባረረ ደረሰበት እና ጭራውን ሲነክሰው የጭራውን ጫፍ ተቆርጣ እንበሳ አፍ ላይ ቀረች፡፡ ጦጣ ደግሞ ዛፍ ላይ ወጥቶ "እሰይ

ያቺ አማቼን ታስጠላባሃለች የሚሉኝን ጭራየ ቆርጠህ አሳመርክልኝ" ብሎ ይበልጥ በንዴት አቃጠለው ይባላል፡፡

(ዓንዶም አይጋው፣ 17/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ አራት

ከላላ የሚባል ሰውየ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ንጉስ ሲሞት በህልሙ ያያል፡፡ ከዚያም ህልሙን የሚፈታለት ሰው ፈለገ፡፡ ከዚያም አስቦ አስቦ ንጉሱ በሰው ከሚሰማው ለምን እኔ እራሴ አልነግረውም አለና ንጉስ ዘንድ ሄደ፡፡ ከዚያም ንጉስን "በህልሜ አንተ ስትሞት አየሁኝ ምን ማለት ነው?" አለው፡፡ ንጉስ ደግሞ "ሞትክ ብለህ የምታልምልኝ ምን ማለትህ ነው?" ብሎ ቀጥቅጦ "ከእንግዲህ በኃላ ይህን አይነት ህልም እንዳታይ" ብሎ አባረረው፡፡ ከዚያ በኃላ ከተኛሁኝ ህልም አያለሁኝ ብሎ ተሳቀቀና ላለመተኛት ይዞር ነበር፡፡ እየዞረ ሳለ የከተማው ዘበኞች ያዙት እና "አንተ በዚህ ሰዓት ምን ትሰራለህ? ለምን አትተኛም?" አሉት፡፡ "በእንቅልፌ ላይ ምን አገባቹህ? የበደልኩት ካለ ንገሩኝ" አላቸው፡፡ እነሱም "የሆነ ያደረግከው ነገር አለ፤ ንገረን አለበለዚያ ንጉስ ዘንድ እንወስድሀለን" አሉት፡፡ "ውሰዱኝ እንጂ ያጠፋሁት ነገር የለም" አላቸው፡፡ ንጉስ ዘንድ ወሰዱት እና "ዛሬ ደግሞ ምን አድርገህ ነው የተያዝከው?" አለው፡፡ ከዘበኞቹ አንዱ "ጌታየ ያደረገው ነገር እንኳ የለም፤ነገር ግን በዚህ በውድቅት መንገድ ላይ እየዞረ አግኝተን ነው ያመጣነው" አለ፡፡ ንጉስ ደግሞ "እስከዚህ ሰዓት ምን እያደረግክ ነበር ለምን አልተኛህም?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ከለላ ደግሞ "እህ ከተኛሁ እማ እንደ ባለፈው ህልም እንዳለይ ብየ ነው" አለው፡፡ ንጉስ ደግሞ "ምንም አልልህም፣ ህልም ፈርተው ሳይተኙ አያድሩም እና ሂድ በሰላም ተኛ" አለው፡፡ ከዚያም ወደ መኝታው ሄደ፡፡ የአገሩ ህዝብም “ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም” ብሎ ተረተ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ለታይ ኬኞ፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ሰላሳ አምስት

በድሮ ጊዜ የአንድ አገር ንጉስ ነበረ፡፡ ከዚያም  አንድ ቀን ህዝቡን ሰበሰቦ "ለነገ ከአሸዋ ገመድ ሰርታቹህ እንድትመጡ" ብሎ አዘዛቸው፡፡ ከተሰብሳቢዎቹ መኻከል አንድ ቢያ የሚባል ሰውየ ነበር፡፡ እናም ቢያ ወደ ቤቱ እንደ ሄደ ካለወትሮው ይጨነቅ ነበር፡፡ ሚስቱም "ምንድን ነው የሆንከው? አቀርቅረህ ምን እያሰብክ ነው?" ስትል ጠየቀችው፡፡ እሱም "ንጉስ ከአሸዋ ገመድ ሰርታቹህ ኑ ብሎ አዝዞናል እና እንዴት እንደምሰራው

እያሰብኩ ነው" አላት፡፡ እሷም "ይህ እማ ቀላል፡፡ ነው ዝምብለህ ራትህን ብላ እና እንዴት እንደምትሰራው እነግርሀለው" አለችው፡፡ ከዚያም ደስ ብሎት ተኝቶ አደረና በነጋታው ሚስቱ "በል ህዝብ ከተሰበሰበ በኃላ ሰርታቹዋል ብሎ ሲጠይቅ እኛንስ ከብዶናል፣ አንተ ንጉስ ነህ እና ጀምረህ ስጠን በለው" አለችው፡፡ ከዚያም ንጉስ ህዝቡን ሰበሰበና ጠየቀ፡፡ ሁሉም ሰው መልስ ስላልነበረው አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ፡፡ ከዚያ ቢያ እጁ አወጣ እና ሚስቱ የነገረችውን አለ፡፡ ንጉስም "እውነት ነው ይህ ጥያቄ ከባድ ነው በቃ ተዉት፣ ሌላ ጥያቄ ልስጣቹህ" አለ፡፡ ከዚያም "ነገ በሰማይ ያሉትን ከዋክብት ስንት እንደሆኑ ቆጥራቹህ፣ እንዲሁም የምድር እምብርት የት እንደሆነ አረጋግጣቹህ እንድትመጡ፣ ታድያ ነገ ስንገናኝ አጫጭር ሰዎች እንዳትመጡ" አላቸው፡፡ ቢያ በሚስቱ ተማምኖ ምንም ሳይጨነቅ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ሚስቱ "የነገርኩህ መልስ ትክክል ነበር ወይ?" ብላ ጠየቀችው፡፡ "አዎ ውዴ ነገር ግን ዛሬ ደግሞ ሌላ ጥያቄ ጠይቆናል፣ በዚያ ላይ አጭር ሰው እናዳይመጣ ብሎናል" ብሎ ትዕዛዞቹን ነገራት፡፡ "ይህም ቀላል ነው አንተ አጭር ብትሆንም ትሄዳለህ፣ አሁን እግርህን ታጠብ እና አረፍ በል" አለቸው፡፡ ቢያ በሚስቱ ብቃት ተደስቶ እግሩን ታጥቦ ራቱን በላ እና ተኛ፡፡ በነጋታው ሚስቱ ቁርሱን ካቀረበችለት በኃላ ቡልትግ (የማሽላ ዓይነት) በሰሀን እና ችካል አቀረበች እና "በል ይሄንን ይዘህ ትሄድ እና ንጉስ ተነስታቹህ ቁሙ ሲል ድንጋይ ላይ ወጥተህ ትቆም እና ከነሱ ጋር እኩል ትሆናለህ፡፡ ከዚያም መልሱን ሲጠይቅ እጅህን አውጥተህ በሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብት ብዛታቸው ልክ በዚህ ሳህን ካለው ብልቱግ እኩል ነው ካላመንከኝ ቁጠር በለው፣ የመሬት እብርት የት ነው ለሚለው ጥያቄው ደግሞ ንጉስ ከተቀመጠበት ፊት ለፊት መሬት ላይ ችካሉን ትተክል እና እዚች ቦታ ነው ካላመንክ መለካት ትችላለህ በለው" አለችው እና ሄደ፡፡ ከዚያም በኃላ ንጉስ ቁሙ ሲላቸው ድንጋይ ላይ ወጥቶ ቆመ፡፡ የጥያቄዎቹ መልስ ሲጠይቅ ደግሞ ማንም የመለሰለት ሰው አልነበረም፡፡ ከዚያ ቢያ እጁን አውጥቶ ሚስቱ እንደነገረችው መለሰ፡፡ ከዚያም በኃላ ንጉስ "አንተ ለዚህ ህዝብ ለማስተዳደር የሚያስችል ብሩህ አእምሮ አለህ" ብሎን ግስናውን አወረሰው ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ፊንጃን ግደይ፣ 20/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ ስድስት

አንድ ቀን ጅግራዎች ተሰባስበው አረም ሊያርሙ ወደ ማሳ ሄዱ፡፡ ከዚያ እንደደረሱ ጠላ እየጠመቁ ሳለ ቀበሮ በአጠገባቸው ሲያልፍ ጠርተው "ና ጠላ ቀምሰህ እለፍ" አሉት፡፡

እሱም "ለዛ ባለቀይ ዓይን ወንድማቹህ አንበሳን እንኳ ያሸነፍኩ ሰውየ ምን ብየ ነው ኮምጣጣ ጠላቹህን የምጠጣው?" ብሎ አጣጥሎዋቸው ሄደ፡፡ ከዚያ አንበሳ ሲመጣ ቀበሮ እንዲህ ብሎህ ሄደ አሉት፡፡ አንበሳም ሊፈልገው ሄደ፡፡ ቀበሮ አንበሳን ሲያየው ወደ እሱ እየመጣ "አያ አንበሳ ጅግራዎች ለአረም ጠርተውኛል እና ለወጥ የሚሆን ስጋ አድኘ እመጣለው ጠብቀኝ" አለው፡፡ አንበሳም አመነው እና ጥላ ላይ ተቀምጦ ይጠብቀው ነበር፡፡ ከዚያ ቀበሮ ወፍ ገደሎ ስጋዋን በልቶ ደሟን እግሩ ላይ ነክሮ እያነከሰ መጣ፡፡ አንበሳ ደንግጦ ሲጠይቀው "ወድቄ ነው" አለው፡፡ ከዚያም "ና ልዘልህ" ብሎ አዝሎት እየሁዱ ጅግራዎች ካሉበት አከባቢ ሲደርሱ በያዘው ቅጠል አንበሳን እየደበደበ "የኸው ወንድማቹን ተቆናጥጬ እየደበደብኩ አመጣሁት" ብሎ ወርዶ አመለጠ፡፡ ሲያመልጥ አንበሳ እያባረረ ጭራዉን ቆረጠው፡፡ ከዚያም "ያ ቆማጣ ጭራ እገድለዋለው" ብሎም ዛተ፡፡ ቀበሮም ሰማው እና ወደ ሌሎች ቀበሮዎች ሂዶ "እናንተ ለምንድን ነው ጭራቹህን ያልቆረጣቹሁት? አንበሳ ካገኛቹህ ይገድላቹዋል፣ ስለዚ ተሎ ቁረጡት" ብሎ የሁሉንም ጭራ አስቆረጠ፡፡ ከዚያ በኃላ ከሌሎች ተመሳስሎ አንበሳ ሳይለየው በሰላም ይኖር ነበር ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ፊንጃን ግደይ፣ 20/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ ሰባት

አንድ ቀን ቀበሮ እና እንቁራሪት ተገናኝተው ሲያወሩ ሲያወሩ ለምን ሩጫ ውድድር አንገጥምም አሉ እና ተፎካከሩ፡፡ ከዚያ ቀበሮ በንቀት "አረ እረፊ አትችልኝም" አለቻት፡፡ እንቁራሪትም እንዲሁ "አረ አትቀድምኝም" አለቻት፡፡ ከዚያ በኃላ ቀጠሮ አድርገው ተለያዩ፡፡ ቀጠሮዋቸው እስኪደርስ እንቁራሪት ወደ ጓደኞቿ ሂዳ አግዙኝ አለቻቸው፡፡ እነሱም ምንም ችግር የለም ብለው ተስማሙ፡፡ ከዚያ በኃላ የቀጠሮው ቀን ደረሰ እና ለሩጫ ተዘጋጁ፡፡ "ለየብቻችን ስለምንሮጥ የቀደመ ድምፅ ማሰማት አለበት" ተባባሉ፡፡ ከዚያ የእንቁራሪት ጓደኞች ውድድር በሚካሄድበት መንገድ ዳር ዳር ላይ ተበታትነው ሳር ላይ ተሸሽገው ድምፅ ለማሰማት ተዘጋጁ፡፡ ከዚያ ዳኛ ውድድሩን ካስጀመረ በኃላ እንቁራሪት ሁለት ጊዜ ዝል ዝል ብላ ሳር ውስጥ ገብታ ተደበቀች፡፡ ቀበሮ ብቻዋን ትሮጥ ትሮጥ እና ቆም ብላ ድምፅ ታሰማለች፡፡ ከዚያም አንዷት ከፊቷ የተደበቀች እንቁራሪት "ቆ…ቅ" ስትል ለካ ቀድማኛለች ብላ ልቧን እስኪጠፋት ትሮጣለች፡፡ ብዙ ከሮጠች በኃላ እንደገና ድምፅ ታሰማለች፡፡ አሁንም ከፊቷ ያለችው

"ቆ…ቅ" ስትል ትሮጣለች፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ድምፅ አሰምታ እንቁራሪት ከፊቷ ሁና ስትመልስላት እውነትም ትቀድመኛለች ብላ አቋረጠች ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ፊንጃን ግደይ፣ 20/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ ስምንት

አንድ ዓይነ ስውር እና አንድ መስማት የተሳነው ሰዎች ነበሩ፡፡ አንድ ላይ ሆነው ወደ በርኸ ሂደው ሊሰርቁ ተስማሙ፡፡ በርኸ ሂደው ከአንድ ማሳ ገብተው "ያዋ" የሚባል የሚበላ ፍሬ ያ መስማት የተሳነው ለዓይነ ስውሩ እየለቀመ ያበላው ነበር፡፡ ከዚያ በመኸል ያ መስማት የተሳነው ባለ ማሳው ከርቀት ሲመጣ ስላየው ሸሽቶ ሂደ፡፡ ዓይነ ስውሩ ግን ዝም ብሎ ፍሬውን ይቆረጥም ነበር፡፡ ከዚያ የእርሻው ባለቤት ድምፅ ሳያሰማ ቀስ ብሎ ተጠጋ እና ወገቡን በዱላ ደሰቀው እና ያ አብሮት እየሰረቀ ያለው መስሎት በደምብ አድርጌ ነው እንዴ የቆረጠምኩት አለው ይላል፡፡

(ወ.ሮ ፊንጃን ግደይ፣ 20/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰላሳ ዘጠኝ

ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ እና ነብር ጅብን አግኝተው "እድር መስርተናል እና ከኛ ጋር ዕድርተኛ እንድትሆን እንፈልጋለን" አሉት፡፡ ከዚያም እሺ ብሎ እድርተኛ ሆነ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን የሚበላ ምንም ነገር ስላላገኙ፣ "ዛሬ ጅብ እናርዳለን እና ሁለት እግር ላንተ እንሰጣሃለን የቀረውን ደግሞ ከእድርተኛው እኩል ትካፈላለህ፤ ምን ይመስልሀል?" አሉት፡፡ ጅብ ደግሞ "መልሱን  ከቤተሰቦቼ ተመካክሬ ልንገራቹሀ" ብሎዋቸው ሄደ፡፡ ከዚያም ሚስቱን እና ልጆቹን ሰብስቦ ነገራቸው፡፡ እነሱም "ምን እያልክ ነው? አንተን እኮነው የሚያርዱህ ትሞታለህ እኮ፤ ከሞት በኃላ መብልእ አለ እንዴ?" አሉት፡፡ እሱም "አየ የልጅ እና የሴት ነገር፣ እግርን በላይ ልሰጡኝ እኮ ነው" አላቸው ይባላል፡፡

(አቶ ገ.ክርስቶስ ቶሊ 28/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ

ከእለታት አንድ ቀን አንበሳ፣ ቀበሮ እና ጅብ አብረው ለአደን ሄዱ፡፡ ሙሉ ቀን ሲጓዙ ውለው በጣም ደክመው እና ተርበው እያለ በመንገድ ውኃ አግኝተው ሊጠጡ  ጎራ አሉ፡፡ ከውኃው አጠገብ  አንድ የደረቀ ቆዳ አገኙ፡፡ ሊበሉት ቢሞክሩም አንበሳ እና

ቀበሮ "ጥርሳችን ይቸጨርሰናል" ብለው ትተውት አለፉ፡፡ ጅብ ግን ቆዳውን ውኃ ውስጥ አስገብቶ ለትንሽ ጊዜ ጠበቀ እና ትንሽ ከለሰለሰ በኃላ በልቶ ደረሰባቸው፡፡ ሲጓዙ አምሽተውም ከአንድ መንደር ደረሱ እና አንዲት ብቻዋን የምትበላ ላም አግኝተው ገደሉዋት፡፡ ከገደሏት በኃላ "እኛ ሶስት ነን፣ በዛ ላይ በጣም እርቦናል እና እቺ አንዲት ላም አትበቃንም ስለዚህ ሌላ እንጨምር" አሉ፡፡ ከዚያ ቀበሮን የሞተችውን ላም ጠብቂ ብለው አንበሳ እና ጅብ ለፍለጋ ሄዱ፡፡ እነሱ ከሄዱ በኃላ ቀበሮ የላሟ ልብ አውጥታ በላቻት፡፡ አንበሳ እና ጅብ ዞረው ዞረው ምንም ስላላገኙ ባዶ እጃቸው ተመለሱ፡፡ ከዚያም ተካፍለን እንብላ ብለው ስጋውን እኩል ለሶስት ከፈሉት፡፡ እግር፣ ሳንባ፣ ጨጓራ… ሁሉንም ለሶስት ከፍለው ሲጨርሱ ልብ እንዳልደረሳቸው ሲያረጋግጡ ጅብ "እያ አንበሳ ልብ የት አለች?" አለ፡፡ አንበሳም "እኔም አላገኘሁዋትም" አለ፡፡ ከዚያ ቀበሮ "ውይ እናንተ እኔኮ ሌላ የምትፈልጉ መስሎኝ ነበር፣ ጅሎች ናቹህ ልበል? እቺ ላም ልብ ቢኖራት ጓደኞቿ ሁሉንም እቤታቸው ገብተው በሰላም ተኝተው እያለ እዚህ ባልቆየችን እና ባልገደልናት" አለቻቸው ይባላል፡፡

(አቶ ተተ ቶሲ፣ 18/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ አንድ

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰውየ በጉዞ ላይ እያለ ከአንድ ወንዝ ዳር ላይ እባብ አገኘ፡፡ ከዚያም እባብ "እባክህ ወንድሜን ይችን ወንዝ አሻገረኝ" አለው፡፡ ሰውየውም "እንዴት አንተ ጠላትህ ከሆነ የሰው ልጅ እርዳታ ትጠብቃለህ? ቀልደኛ ነህ ልበል?" አለው፡፡ "እባክህ አሻግረኝ" ብሎ ተማፀነው፡፡ ሰውየውም አይሆንም ብሎ ትቶት ሊሻገር ሲል እባብ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ትተህኝ እናዳትሻገር አለው፡፡ ሰውየው ምንም እንኳ ቢፈራውም የእግዜር ስም ጠርቶ ስለለመነው ተመለሰ፡፡ ከዚያም "እሺ እንዴት አድርጌ ነው የማሻግርህ?" ብሎ ጠየቀው፡፡ እባብም "አንገትህ ላይ አድርገህ፣ እንደተሻገርን ሰተት ብየ እወርድልሀለው" አለው፡፡ ከዚያ ሰውየው እየፈራ አንገቱ ላይ ተሸከመው እና ተሻገሩ፡፡ እንደተሻገሩ "በል ውረድልኝ" አለው፡፡ እባብም ስለተመቸው "አልወርድም ዝም ብለህ ቀጥል ካልሆነ…" ብሎ ምላሱን አውጥቶ አስፈራራው፡፡ "ታድያ ምን እናድርግ?" ብሎ ሲጠይቀው "ከፈለክ ዳኛ ዘንድ እንሂድ ወደ ላይ ቀጥል እንጂ ወደ ታች ውረድ የሚል የለም" አለው፡፡ ከዚያ ዳኛ ይፍረደን ተባብለው ዳኛ ጋር ሄዱ እና ጅብን አገኙት፡፡ ጅብ ደግሞ ጉዳዩን ከሰማ በኃላ እባብን ስለፈራው "ይህን ጉዳይ ልፈርድ አልችልም ጦጣ ጋር ሂዱ" አላቸው፡፡ እሺ ብለው ጦጣ ጋር ይሄዱ እና

ጉዳያቸውን በየተራ ያቀርባሉ፡፡ ከዚያ ጦጣ "በሉ ፍርድ ልሰጥ ነው እና ከሳሽ በቀኝ ተከሳሽ ደግሞ በግራ እኩል መሬት ላይ ቁሙ" አላቸው፡፡ ከዚያ የዳኛ ቃል ነው እና እባብ ሰተት ብሎ ወርዶ መሬት ላይ ቆመ፡፡ ከዚያ ጦጣ "ሰውየ ዱላ በእጅህ እባብ ከእግርህ ከዚህ በላይ ምን ትጠብቃለህ" አለው፡፡ ሰውየውም ነገሩ ወድያው ገባው እና እባብን ቀጥቅጦ ገደለው ይባላል፡፡

(አቶ ተተ ቶሊ፣ 18/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ ሁለት

አንድ ሰውየ  ቆንጆ ሚስት አግብቶ ይኖር ነበር፡፡ ሚስቱ ቆንጆ በመሆኗ ሁሉም ሰው ነበር የሚፈልጋት፡፡ እንዴት አድርገን ነው የምናገኛት ብለውም ያስቡ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰውየ ባልዋ አለመኖሩን አረጋግጦ እቤቷ ሂዶ ጠየቃት እና እሺ አለቻው፡፡ በዚህም የአገሩ ወንዶች ለመዱዋት፡፡  በዚህ ተግባሯ የተበሳጨ ባለቤቷ መላ ፈለገ እና አገር ቀይሮ ይዟት ሄደ፡፡ በሄዱበት አገርም ቆንጆ ናት እና ብዙ ሳታደርግ የአገሩ ወጣቶች ለመዷት እና ባለቤቷ ተማረረ፡፡ ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ አገር ቀይሮ ይዟት ሄደ፡፡ እንዲ እንዲህ እያለ አገር እየቀየረ ሰባት አገር ደረሰ፡፡ ለሰባተኛ ጊዜ አገር ቀይሮ እንደ ሄደ አንድ ቀን የአገሩ ህዝብ ስብሰባ ነበራቸው እና ወደ ስብሰባው ሂዶ ከነሱ ጋር ተሰበሰበ፡፡ ስብሰባው አንዳለቀ ሀሳብ ያላቹህ ሲባል እጁን አውጥቶ "ሚስቴ አገር ቤት እያለን ወንዶችን እየሰለበች ታስቸግረኝ ነበር ለዚያም ነው አገር ለቅቄ ስደት የመጣሁት፤ ስለዚህ እኔ ሳልኖር እቤት እናዳትሄዱ ተጠንቀቁ" አላቸው፡፡ እነሱም ገርሞዋቸው ዝም ዝም አሉ፡፡

ከዚያ አንድ ቀን አንድ እረኛ በቤታቸው አጠገብ ሲያልፍ ያያት እና ጓደኞቹን "ይህቺ ሴት እንዲህ ታምር ነበር እንዴ? ለምንስ እስተዛሬ ሳትጠይቁዋት?" አላቸው፡፡ እነሱም ባህሪዋ አስረዱት፡፡ ምንም እንኳ ቢፈራም እሷን ማግኘት አለብኝ ብሎ ስላሰበ አንድ ጓደኛውን "እኔ እቤቷ እሄዳለሁኝ፣ እጠይቃታለውም፡፡ ስለዚህ አንተ በዚህ ገመድ እሰረኝ እና ልትሰልበኝ ካለች እሪ እላለሁኝ እና ጎትተኝ" አለው፡፡ በዚህ ተስማምተው ሄዱ እና እቤት ገብቶ ቁንጅናዋን አድንቆ እንደፈለጋት ገለጸላት፡፡ በሀሳቡ ተስማምታ አስተኛት፡፡ ከዚያም እጇን ልካ ልትዳብሰው ስትል ልትሰልበኝ ነው ብሎ ምድር እና ሰማዩን ደባለቀው፡፡ ከዚያም ጓደኛው ጎትቶ አወጣው እና ሸሹ፡፡ ከዚያ ቀን በኃላም ሰውየው ሚስቱ ሌላ ሰው ሳያይበት በሰላም ይኖር ነበር ይባላል፡፡

(አቶ ሰሎሞን ገ.ክርስቶስ፣ 28/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ ሶስት

በድሮ ጊዜ ግመል እና ዝንጀሮ በጓደኝነት አብረው ይኖሩ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ምግብ ፍለጋ አብረው ሄዱ፡፡ በፍቅር እያወሩ እና እየሳቁም ይጓዙ ነበር፡፡ ከዚያም ስሄዱ ስሄዱ አንድ ትልቅ ወንዝ አገኙ፡፡ ዝንጅሮ "እኔ እንዴት ልሻገር ነው? በቃ እዚህ መቅረቴ ነው" አለ፡፡ ግመል "አይዞህ ጓደኛየ ትቼህ አልሄድም" አለውና አዝሎ አሻገረው፡፡ ከተሻገሩ በኃላ ትንሽ ተጉዘው አንድ የማሽላ ማሳ አገኙ፡፡ ከዚያ ግመል "ስማ ጓደኛየ እዚህ ገብተን እንብላ፣ ታድያ እኔ ሆዴ ትልቅ ስለሆነ እስክጠግብ ድረስ ታገሰኝ፣ የሆነ ድምጽ እናዳታሰማ እና ሰዎች እንዳይመጡብን" አለው፡፡ እሺ ተባብለው ገቡ እና ዝንጀሮ ትንሽ በልቶ ጠገበ፡፡ ከዚያ ማሽላ ቆርጦ በእጁ ይዞ ዛፍ ላይ ወጣ እና መጮህ ጀመረ፡፡ ከዚያ ማሽላ ጠባቂዎች መጥተው ግመልን ቀጥቅጠው አባረሩት፡፡ ከዚያም ወደ ሌላ ቦታ ሂደው መብላት ጀመሩ፡፡ ግመል ደግሞ "ቅድም ለምን ጮህክ? በል አሁንም እንደዛ እናዳታደርግ ዝምብለን እንብላ" አለው፡፡ ዝንጀሮ ደግሞ በልቶ ጠገበ እና አሁንም ዛፍ ላይ ወጥቶ ጮሀ፡፡ ሰዎች መጥተው ግመልን መትተው አባረሩት፡፡ ከዚያም ወደ ሌላ ኣከባቢ ሂደው መብላት ሲጀምሩ ዝንጀሮ ለሶስተኛ ጊዜ እንደዛ አደረገ እና ሰዎች መጥተው ግመል ሳይበላ አባረሩት፡፡ ከዚያ በኃላ መሸ እና ወደ ቤታችን እንመለስ ብለው ጉዞ ጀመሩ፡፡ ከዚያም የቅድሙ ወንዝ ላይ ደረሱ፡፡ ዝንጀሮ "አሁንስ እንዴት ነው ምሻገረው?" ብሎ ግመልን ጠየቀው፡፡ ግመል ደግሞ "እንደ ተግባርህ እንኳ አይገባህም ነበር፣ ለጓደኝነታችን ስል ግን ና ላሻግርህ" አለና አዘለው፡፡ ከዚያ ወንዙ ማኸል እንደደረሱ ግመል "እኔ ጀርባየ ስለአቃጠለኝ ላንከባልል (ውኃው ላይ በጀርባየ ልተኛ) ነው" አለው፡፡ ዝንጀሮም ተደናግጦ "እህ እኔስ እንዴት ልሆን ውኃው ቢወስደኝስ?" አለው፡፡ ትንሽ ተጓዙ እና አሁንም ግመል "ላንከባልል ነው" አለው፡፡ ዝንጀሮ "አረ እባክህ ለኔ ስትል ተው" አለው፡፡ ግመል ደግሞ "የራስህ ጉዳይ እንጂ ላንከባልል ነው" ብሎ ውኃው ላይ ተኛ፡፡ ከዚያ ዝንጀሮን ጎርፍ ወሰደው፡፡ በዚህም ግመል ብድሩን መልሶ አገሩ ገባ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ህይወት ተስፋማርያም 27/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ አራት

ሶስት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ለአደን ሄዱ፡፡ ሰዎቹ አንዱ ቦርጫም፣ አንዱ አንድ ዓይኑ፣ አንዱ ደግሞ ኃይለኛ ተዋጊ(ተከላካይ) ናቸው፡፡ የአደን ቦታ ላይ እንደደረሱ ብዙ አጋዘኖች ያገኙ እና አንዱን አጋዘን ከበን እንያዘው ተባባሉ፡፡ ከዚያም ለዚያ አንድ

አይኑ ጠባብ ቦታ ላይ አስቀምጠው እዚህ ጠብቅ አሉት፡፡ ትተዉት እንደ ሄዱ ትልቅ ዘንዶ መጥቶ "አንተን ወይስ አጋዘኑን ልብላ?" አለው፡፡ "አጋዘኑን ብላ" አለው፤ አጋዘኑን ውጦ ቦርጫሙ ሰውየ ጋር ሄደ እና "አንተን ወይስ አጋዘኑን ልዋጥ?" አለው፡፡ እሱም "አጋዘኑን" አለው እና አጋዘኑን ውጦ ወደ ኃይለኛው ሰውየ ሄደ እና "አንተን ወይስ አጋዘኑን?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ኃይለኛው ሰውየ ደግሞ "እኔን" አለው፡፡ ከዚያ ዘንደው ሰውየውን ለመዋጥ ተወርውሮ አፉን ሲከፍት አንገቱን ቆርጦ ገደለው ይባላል፡፡

(አቶ ሰሎሞን ገ.ክርሰቶስ፣ 28/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ አምስት

በድሮ ጊዜ የኩናማ ወጣቶች ተሰባስበው ለአደን ሄዱ ይባላል፡፡ የአደን ቦታ ላይ እንደደረሱ ከመኸከላቸው አንዱን ገድለው እዛው ትተዉት ይመለሳሉ፡፡ የሟቹ ሚስት ባሏ ሲዘገይባት ጨነቃት እና ጓደኞቹን ልጠይቅ ብላ አንዱ ጋ ሄደች እና ስትጠይቀው "ሌሎቹ ጋ ነው ያለው ሂጂ እና እነሱን ጠይቂ" ብሎ ላካት፡፡ እነሱ ጋ ስትሄድ ደግሞ መጀመርያ ላይ የጠየቀችውን ሰው ጋ ሂጂ አሉዋት፡፡ ተመልሳ እሱ ጋ መጣች እና "አንተ ጋ ነው አሉኝ" አለችው፡፡ እሱም አይ እነሱ ጋ ነው ሂጂ አላት፡፡ ከዚያም ጨነቃት እና ወደ ቤቷ ተመልሳ ቁጭ ብላ

"ወደ ግራ ስሄድ ወደ ቀኝ ይሉኛል፣
ወደ ቀኝ ስሄድ ወደ ግራ ይሉኛል፣
የወንድ መንገድ ገጠመኙ በዙ ነው፤
እና ገጥሞህ ቀረህ ወይ ቀረህ ወይ!!!" ብላ አለቀሰችለት ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ህይወት ተስፋማርያም፣ 27/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ ስድስት

ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ሲኖሩ ከፍተኛ ድርቅ ገጠማቸው፡፡ ከዚያም ቀለባቸው አልቆ አንዲት ጣሳ ማሽላ ብቻ ቀራቸው፡፡ ሰትዮዋ ማሽላውን ፈጭታ ሙቅ አዘጋጀት፡፡ ከዚያ ባሏ ይሳሳ እና ሙቁን ብቻውን መጠጣት ፈለገ፡፡ ከዚያም ሚስቱን "ሂጂ እና የከብቶቹን በረት ዘግተሽው ነይ" ይላታል፡፡ እሷ ደግሞ በመገረም "ከመቼ ነው ሴት የከብቶችን በረት የምትዘጋው?" ብላ ተከራከረችው፡፡ ሊሰማት አልቻለም፡፡ ከዚያ ሳይዘጉ ከሚያድሩ ብላ ልትዘጋ ሄደች፡፡ እሷ እንደሄደች ባልየው ሙቁን ተጣድፎ ግልብጥ አድርጎ ጠጣው እና ትኩስ ስለነበር አቃጥሎ ገደለው፡፡ ሚስቱ ደግሞ ልትዘጋ ስትሄድ

አንዲት ላም ዓይኗ አከባቢ ትወጋት እና "ዓይኔ ዓይኔ" እያለች ተመለሰች፡፡ እቤት እንደገባች "እኔ ዓይኔ ልጠፋ ነው አንተ ግን ጥርስህን ከፍተህ ተኝተሃል፤ ተነስ እንጂ ተነስ" አለቻው፡፡ ተነስ ብላ ስትቀሰቅሰው አልሰማ ሲላት ስታየው ለካ ሙቷል፡፡ ከዚያ እሪ አለች እና ጎሮቤት ተሰባሰቡ ይባላል፡፡

(አቶ ተኽላይ ማትዮስ፣ 15/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ ሰባት

በአንድ ወቅት በአንድ አካባቢ ከፍተኛ የኾነ ድርቅ አጋጠመ ይባላል፡፡ ከዚያም የአንድ ቤተሰብ አባላት ድርቁ ባደረሰው ጉዳት ተጎሳቅለው ችግር ደረሰባቸው፡፡ ከዚያም ባል እና ሚስት ተመካክረው ሰርተው ልጆቻቸውን መቀለብ እናዳለባቸው ወሰኑ፡፡ ከዚያም ልጆቻቸውን አንድ ቤት ውስጥ ዘግተው እየሄዱ ምግብ እያመጡ ይቀልቡዋቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን አባት እና እናት ለስራ ከሄዱ በኃላ አንድ ትልቅ ሰው በዚያ ሲያልፉ ልጆቹን ጠርተው "ኑ እስቲ ቁስሌን ቅርፊት ብሉልኝ" አሉዋቸው፡፡ ልጆቹ ደግሞ ፈርተው የሰውየውን ቁስል ልጠው በሉት፡፡ በየቀኑም እየመጣ የቁስሉን ቅርፊት እንዲበሉ ያደርግ ነበር፡፡ ከዚያም ልጆቹ እየከሱ መጡ፡፡ አንድ ቀን አባት እና እናት ምን ኾነው ነው እነዚህ ልጆች ሰውነታቸው የተበላሸው? ያ ሁላ እየቀለብን ምን ሆኑ ብለው ተጨነቁ፡፡ ከዚያም ልጆቹን ጠየቁዋቸው፡፡ ልጆቹም እነሱ እንደ ሄዱ አንድ ትልቅ ቁስል ያለው ሰውየ በየቀኑ እየመጣ ቁስሉን እንዲያኩለት እና የቁስሉን ቅርፊት እንዲበሉ እንደ ሚያስፈራራቸው ነገሩዋቸው፡፡ ከዚያም በነጋታው የሰውየውን መምጣት ይጠባበቁ ጀመር፡፡ ሰውየው ደግሞ እንደ አመሉ መጥቶ ልጆች "ኑ እስቲ የቁስሌን ቅርፊት በልታቹህ ሰኙኝ" አለ፡፡ ከዚያም አባት እና እናት ወጥተው "ለካ አንተ ነበርክ ልጆቻችን የማይበላ እያበላክ እንዲሰቃዩ ስታደርግ የነበር!" ብለው መትተው ገደሉት፡፡ ከዚያም የድርቁ ዘመን አልፎ በሰላም ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡

(አቶ ተኽላይ ማትዮስ፣ 15/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ ስምንት

አንድ ባል እና ሚስት ይኖሩ ነበር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ሴትዮዋ ወደ ገበያ ሂዳ ደሮ ገዝታ ስትመለስ መንገድ ላይ አንድ ቁመናው የሚማርክ እጅግ መልከ መልካም ሰውየ አየች እና ወደደችው፡፡ ከዚያም "የት ነበር የማውቅህ? ታውቀኛለህ ወይ?" ስትል ጠየቀችው፡፡ ከዚያም "አታውቅኝም እንግዳ ነኝ፣ አንቺ የት ነው የምትኖሪው" ሲል

መለሰላት፡፡ ከዚያም የምትኖርበት አከባቢ ነገረችው እና በል "ስለምፈልግህ ማታ ወደ ቤት እንደ ምትመጣ" አለችው፡፡ "ባል አለሽ ወይስ የለሽም?" አላት፡፡ "አለኝ እንጂ" ስትለው ታድያ "ባልሽ እያለ እንዴት አድርጌ እመጣለው?" አላት፡፡ ከዚያም "ችግር የለም ስትመጣ ራቆትህ፣ በእጅህ ደግሞ ቢላዋ ይዘህ ና" አለችው እና ተለያዩ፡፡

እቤቷ እንደደረሰች ደሮውን አርዳ እየሰራች ሳለ ከባለቤቷ ጋር ያወሩ ጀመር፡፡ ከዚያም "ዛሬ ገበያ ላይ ጉድ አይቼ ነው የመጣሁት፤ አንድ ሰውየ ራቆቱ ሁኖ በቢላዋ ያገኘውን ወንድ እያረደ ሲፈጅ ነበር የዋለው" አለችው፡፡ አሁንም ወደ መንደራችን አከባቢ እየመጣ ስለሆነ ወደ ደጅ እንዳትወጣ፤ ተደበቅ" አለችው፡፡ እሺ አላት እና ደሮ ወጡን አቅርበው መብላት ሲጀምሩ ባሏ ሰውየው ሲመጣ ከሩቅ አየው፡፡ ወደ ጓዳ ገብቶም ተደበቀ፡፡ ሰውየው ቢላዋ ይዞ ቀጥ ብሎ ወደ ቤት ገብቶ ተቀመጠ፡፡ ከዚያም ሚስቲቱ ወደ ጓዳ ገብታ ባሏን "ሰውየው እንጀራ ስጪኝ ካልኸኝ ባልሽ እገድለዋለው እያለኝ ነው፤ ልስጠው ወይ" ብላ አስፈቀደችው፡፡ "ሂጂ እና ስጭው" አላት፡፡ ሄደች እና ደሮ ወጡን አቀረበችለት፡፡ በልተው ከጨረሱ በኃላ ተመልሳ ወደ ጓዳ ገባች እና "ነይ ከኔ ጋር ተኚ ካል ሆነ ግን... ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ ፈርቶ "ሂጂ ተኚ" አላት፡፡ ከዚያ ሰውየው ስራውን ሰርቶ ሄደ ይባላል፡፡

(አቶ ተኽላይ ማትዮስ፣ 15/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት አርባ ዘጠኝ

አንድ በጣም ቀናተኛ ባል የነበራት ሚስት ነበረች፡፡ ሰውየው ሚስቱ ከሱ እንድትለይ፣ ከቤት እንድትወጣ አይፈልግም፡፡ ምንም እንኳ እንዲያምናትና እንዲተማመንባት ብትነግረውም አልሰማ አላት፡፡ ከዚያ በዚህ ባህሪው ተናደደች እና "ፊት ለፊትህ ማለት የሰራሁትን ምግብ ቀምቶ የሚበላ፣ አንተ እያየህው የሚተኛኝ ወንድ አለ" አለችው፡፡ እሱም በመገረም "እኔ በዓይኔ እያየሁት ደፍሮ ይህን የሚያደርግ ወንድ፣ ሙቻለው በይኛ ታድያ" አላት፡፡ "በል ምግብ ልስራ እና ሂደን እንፈልገዋለን" አለችው፡፡ በዚህ ተስማምተው ደሮ ወጥ ሰርታ በአገልግል ተሸክማ ሰውየውን ፍለጋ ሄዱ፡፡ መንገድ ላይ ከአንድ ጎረምሳ ጋር ይገናኙ እና "ጎረምሳው ወዴት ናቹህ?" ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ ከዚያ ባሏ "እኔ የማላውቀው ሚስቴ ግን የምታውቀው አንድ ሰውየ አለ፣ እኔ እያየሁት ሚስቴ የያዘችውን ምግብ ቀምቶ የሚበላ እንዲሁም እያየሁት የሚተኛት እና እሱን ፍለጋ ነው እየሄድን ያለነው" አለው፡፡ ከዚያ ሰውየው ወደ ሴትየዋ ጠጋ አለና የያዘችውን አገልግል ከፍት አድርጎ "እንዲህ አድርጎ የሚበላ ነው?" ብሎ በላ፡፡ "አዎ" አለው፡፡

ከዚያም ጠጋ ብሎ "እንዲህ አድርጎ የሚያወድቃት ነው" አለው፣ ባሏ ደግሞ አለው፡፡ ሰውየውም እንደዚህ አድርጎ "ቀሚሷ የሚገልብ ነው" አለው፡፡ ባልየው ደግሞ አዎ አለው፡፡ ከዚያ ሰውየው ተኛት እና "እንዲህ አድርጎ የሚተኛት ነው" አለው፡፡ አሁንም "አዎ" ብሎ መለሰለት፡፡ ከዚያም ሰውየው "አላውቀዉም እና ሂዳቹህ ፈልጉት" ብሎዋቸው ሄደ፡፡ ከዚያ ሚስቱን "በይ እንሂድ" አላት፡፡ እሷም "ወዴት ነው የምንሄደው?" አለችው፡፡ "ሰውየውን ፍለጋ" አላት፡፡ "ሰውየው አላየሀውም እንዴ ምን ምን አድርጎ ነው እንዴ የሄደው" አለችው ይባላል፡፡

(አቶ ተኽላይ ማትዮስ፣ 15/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ

በኩናማ ባህል መሰረት አንዲት ያገባች ሴት ለመጀመርያ ያረገዘች ሴት ወደ ውጭ አትወጣም፣ ሰውም አያያትም፡፡ እቤት ውስጥ ነው የምትቀመጠው፡፡ አንድ አቦና የሚባል ወጣትም ሚስቱ የቦክር ልጇን አርግዛ እቤት ውስጥ ነበር የምትውለው፡፡ አንድ ቀን አቦና በርኽ ውሎ ሲመለስ ሚስቱ ከቤት ወጥታ ከጓደኛዋ ጋ ከጎረቤት ትጫወት ነበር፡፡ ስለዘገየችም አማቹ እርቦት ይሆናል ብለው ምግብ ሲያቀርቡለት ሊያመሰግን ጎንበስ ሲል ፈስ ያመልጠዋል፡፡ አማቹም "አቦና!" ብለው ፈከሩ፡፡ ከዚያም ህፍረት ተሰማው እና አማቹ ሲወጡ ምግቡን ሳይበላ እንዳለ አስቀምጦ ሰው ሳያየው ጠፍቶ ሄደ፡፡ ከዚያ በኃላ ልጁ ተወልዶ አደገ እና ፍየሎች እንዲጠብቅ ወደ በርኸ ሄደ፡፡ ከዚያ ኣቦና  አግኝቶ "የማን ልጅ ነህ?" ይለዋል፡፡ "እኔ እንኳ አባቴ አላውቀዉም ሳልወለድ ጠፍቶ እንደ ሄደ ነው፣ ሰዎች ግን የአቦና ፈሳም ልጅ ነው የሚሉኝ" አለው፡፡ ከዚያም አቦና "እህ አንተ እንኳ ሆድ ውስጥ የነበርክ ያልረሳህው ሌላው እንዴት አድርጎ ይረሳዋል" ብሎ ተመልሶ ጠፋ ይባላል፡፡

(አቶ ተኽላይ ማትዮስ፣ 15/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ አንድ

በድሮ ዘመን  ባል እና ሚስት  ይኖሩ ነበር፡፡ ከዚያም ድርቅ ሆነ እና የሚበላ ነገር አጡ፡፡ ሴትዮዋ ደግሞ አራስ ነበረች፡፡ ባለቤቷ ምግብ ፍለጋ እንደ ሄደ እጅግ ይርባት እና ተጨነቀች፡፡ ሲጨንቃት ምጣድ አነደደች፡፡ የሚጋገር ነገር ስላልነበረ ልጇን ጠብሳ ልትበላት አስባ ወደ ምጣዱ ጠጋ ታደርጋታለች፡፡ ጨቅላዋ ደግሞ ይሞቃት እና ታለቅሳለች፣ ከዚያም ራቅ ታደርጋታለች፡፡ ዝም ስትል ደግሞ ጠጋ ታደርጋት እና

አምርራ ስታለቅስ ሆዷ አላስችል ሲላት ታሸሻታለች፡፡ እንዲህ ስታደርግ መልአክ ይመጣ እና "ምን እያደረግሽ ነው?" ብሎ ይጠይቃታል፡፡ "የሚበላ ነገር አጥቼ ጠብሼ ልበላት አልኩኝ፤ ስታለቅስ ደግሞ ሆዴ አላስችል አለኝ" አለችው፡፡ እሱም "በዪ ተዪ እንዳትጠብሺያት፡፡ አልጋዋ ላይ አስተኝተሽ ቤትሽን ጠርገሽ ቁጭ በዪ" አላት፡፡ ከዚያ እንደዛ አደረገች፡፡ ከዚያ እህል ከሰማይ መጥቶ የቤቷ ወለል ሞላው፡፡ ተደሰተች እና ተነስታ ፈጭታ ቂጣ ጋግራ በልታ ጠገበች፡፡ ከዚያ ህጻንዋ ሽንቷ ስትሸና እናትየው ደግሞ ከቂጣው እየቆረሰች ትጠርግላታለች፡፡ ሽንት የጠረገችበት ቂጣ ትሰበስበዋለች፡፡ ከዚያ ባሏ መጣ እና "ውይ እህል ከየት ተገኘ?" ብሎ የጨቅላዋ ሽንት የተነከረውን ቂጣ በላው ይባላል፡፡

(አቶ ገረማርያም ጎደ፣ 16/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ ሁለት

አንድ ቀን አንዲት መስማት የተሳናቸው ትልቅ ሴትዮ ወደ ማሳ ሂደው አረም ያርሙ ነበር፡፡ አንድ መስማት የተሳናቸው ትልቅ ሰውየ ፍየሎች ጠፍቶዋቸው ሊፈልጉ በዚያ ሲሄዱ ሴትዮዋን "በምልክት በመኸከላቸው አንዲት የምታነክስ ፍየል የለቻቸው ፍየሎች እዚህ አከባቢ አላዩም ወይ" ብለው ጠየቁዋቸው፡፡ እሳቸው ደግሞ በእጃቸው እያመላከቱ "ከዚያ ጀምሬ ይሄ ሁሉ ዛሬ ነው ያረምኩት" አሉዋቸው፡፡ በዚህ አልፈዋል ያሉዋቸው መሰላቸው እና አልፈው ሄዱ፡፡ ትንሽ እንደ ተጓዙ ፍየሎቻቸው ያገኙዋቸው እና ወደ ሴትዮዋ ተመልሰው ሄዱ እና "ባንቺ እገዛ ነው ያገኘሁዋቸው እና ይህቺ አንካሳ ፍየል እንኪ አርደሽ ቢያት" አሉዋቸው፡፡ እሳቸው ደግሞ አንቺ ነሽ የመታሻት የሚሉ መስሎዋቸው "እኔ አልመታሁም" አሉ፡፡ በዚህ ሲከራከሩ መግባባት ስላልቻሉ ወደ ዳኛ እንሂድ ብለው ሄዱ፡፡ ዳኛውም መስማት የተሳነው ነበር እና ምን ሁናቹህ ነው አላቸው፡፡ ከዚያም ሴትዮዋ "አንቺ ነሽ የሰበርሻት አለኝ" ብለው ለማስረዳት መከሩ፡፡ ዳኛው ደግሞ "ሂጂ ባልሽ ነው ያስረገዘሽ" ብሎ አሰናበታቸው ይባላል፡፡

(አቶ ገረማርያም ጎደ፣ 16/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ ሶስት

አንድ ሰውየ ሁለት ሚስቶች ነበሩት፡፡ አንዷ መኸን ስትሆን አንዷ ግን ልጆች ወልዳለች፡፡ ሰውየው በአደን ነው የሚያስተዳድራቸው፡፡ ያቺ የልጆች እናት የሰጣትን ስትቀበል ያቺ ግን ነገሮችን ትጸየፋለች፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ዓሣ አግኝቶ ይዞላቸው

ይሄዳል፡፡ ያቺ የልጆች እናት ዝም ብላ ስትቀበል አንዱ ግን "አልፈልግም" አለችው፡፡ ከዚያም ጨንቆት ወደ ገበያ ወስዶ ሊሸጠው/ሊለውጠው አሰበ እና ሄደ፡፡ ከዚያም የሚገዛው ሰው ጠፋ እና ይዞት ሲመለስ አንድ ድመት የያዘ ሰው ያገኝ እና "እንለዋወጥ" አለው፡፡ ከዚያ "ድመት ምን ያደርግልኛል?" አለው፡፡ "አንድ ቀን ይጠቅምሃል?" አለው፡፡ በዚህ ተስማምተው ድመቱን ይዞ ሲጓዙ ይመሽ እና ማደርያ ፈልገው ከአንድ ሀብታም ሰው ተጠጉ፡፡

ያ ከገበያ ሲመለሱ መንገድ ላይ የሚታደርበት ሀብታም ሰውየ እቤቱ ውስጥ ዘንዶ አለው፡፡ ከዚያም ሰዎች ገበያ ውለው ሸጠው፣ ሸምተው ሲመለሱ በዘንዶው እንዲዋጡ ያደርጋል ከዚያም ንብረታቸውን ይዘርፋል፡፡ በዚህም ነው ሀብታም የሆነው፡፡ ከዚያም ግቡ ብሎ ማረፍያ ሰጣቸው፡፡ ከዚያ ድመቱን ንፋስ እንዲያገኝ ብሎ ፈትቶት ነበር እና ሀብታሙ ሰውየ ደግሞ ዘንዶው ሲለቅባቸው ድመቱ ገደለው፡፡ ከዚያ ሰዎቹ በዘንዶው ተበልተው ይሆናል ብሎ ሲመጣ ዘንዶው ሙቶ ነበር፡፡ ከዚያ ማን እንደ ገደለው ሲጠይቅ ድመቱ ነው አሉት፡፡ ሃብታሙ ሰውየ ዘንዶ የሚገድል ኃይለኛ ፍጡር ነው፤ ስለዚህ የበለጠ ሀብታም እሆናለው ማለት ነው ብሎ "ለውጠኝ" አለው፡፡ "በምን ልለውጥህ?" ሲለው "የድመቱን ጺም ቆጥሬ የብዛቱን ያህል ከብት እሰጣሀለሁኝ" አለው፡፡ በዚህ ተስማምቶ የድመቱን ጺም ቆጥሮ በዚያ ልክ ከብቶች ሰጥቶ ሰኘው፡፡ በዚያም ሀብታም ሁኖ ይኖር ነበር ይባላል፡፡

(አቶ ገረማርያም ጎደ፣ 16/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ አራት

አንድ ባል እና ሚስት ከተጋቡ ብዙ ጊዜ ቢሆናቸውም ልጅ ግን መውለድ አልቻሉም ነበር፡፡ በዚህም በጣም ይጨነቁ ነበር፡፡ ከዚያ አንድ ቀን ለአንድ ሰውየ ጭንቃቸውን ሲያካፍሉት "ይህ እማ ቀላል ነው እኔ የሚያስወልድ መድኃኒት አለኝ" አላቸው፡፡ ከዚያም ባለ ቤቷ በጣም ተደስቶ "ካስወለድካት እኔ ደግሞ ከከብቶቼ አካፍልሀለው" አለው፡፡ ከዚያ ሰውየው የማሽላ ስር ቆፍሮ አመጣ እና "እንኪ ይህንን ቀጥቅጠሽ ጠጭው" አላት፡፡ ከዚያም ጠጣችው፡፡

በነጋታው መድኃኒት አውቃለሁኝ ያለውን ሰውየ "ለምንድን ነው ግን መድኃኒት የሌለኝ አውቃለው ብየ የሰጠሁዋት?" ብሎ አሰበ እና በዚህ ድርጊቱ ተፀፅቶ አገር ለቆ ሄደ፡፡ ከተወሰኑ ዓመታት በኃላ ተመልሶ መጣ እና ነገሮችን ቀስ ብሎ ማጣራት ጀመረ፡፡ ከዚያም ባረፈበት ቤት ላይ ያ ሚስቱን መድኃኒት የሰጠለት ሰውየ ነበር፡፡ ከዚያም "እነዛ

ልጅ ያልነበራቸው ባል እና ሚስትስ እንዴት ሆኑ? ወለዱ ወይ?" ብሎ ሲጠይቅ "አዎ ወልደናል እኔ እኮ ነኝ" አለው፡፡ ከዚያ ሰውየው ተደስቶ "ታስታውሰኛለህ እኔ እኮ ነኝ መድኃኒት የሰጠሁዋቸት" አለው፡፡ "አንተ ነህ እንዴ ስንፈልግህ ነበር እኮ" ብሎ ወደ ቤቱ ወስዶ በደምብ አስተናግዶ ከብት አካፈለው፡፡ ከዚያም ሃብታም ሆኖ በአገሩ በሰላም ይኖር ነበር ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ 20/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ አምስት

አንዲት ባሏ የሞተባት ሐዘንተኛ ቆቅ ነበረች፡፡ በባለቤቷ መሞት ብዙ ጊዜ ካዘነች በኃላ የአገሩ ሰዎች ተሰብስበው መጥተው የሐዘን ሻሽዋን አስጣሉዋት፡፡ ከዚያም የሀዘን ጊዜዋ ጨርሳ ከህዝቡ ተቀላቀለች እና የአረም ዘመቻ ላይ ተጠርታ ሄደች፡፡ ዘመቻው ላይ ጅግራ ዘፈን ጀመረች፤ "እረኞች ኑ ቅረቡ ሽም እስክትሽም በሉ… ተጨወቱ" አለች፡፡ ጦጣ ደግሞ ቆቅን ይዞ "ነይ ሐዘን ቀርቷል ከህዝብሽ ጋር ተስተካከዪ አላት" እና ገብታ መዝለል ጀመረች፡፡ ጦጣም እየዘለለ "ሃ…ሃ…ሃ.. ነጭ ማሽላው ላይ እርግብ፣ ኮደን(የማሽላ ዘር) ላይ ደግሞ ቆራ፤ እኔ ደግሞ በነጋፋደ መኸል እንደ በቆሎ ጺም አውጥቸ ሃ…ሃ…ሃ" እያለ እየያዛቸው ጨፈረ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት የካቲት፣29/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ ስድስት

አንድ መሳሳኪ የሚባል ዝንጅሮ ነበር፡፡ ከዚያ ትዳር መስርቶ ዋሲኒ የሚባል ልጅ ወልዶ ይኖር ነበር፡፡ የዝንጅሮ ነገር እንደሚታወቀው አድኖ፣ ለቃቅሞ መብላት ነው እና አንድ ቀን ከጓደኞቹ ጋር ለአደን ሂዶ አድኖ ሲመለስ ጓደኞቹን "ሚስቴ በጣም ነው የምትወደኝ ነገር ግን ስታለቅስ ሰምቻት አላውቅም፤ ስሞት ምን ብላ እንደምታለቅስለኝ ለመስማት ስለምፈልግ በረኸ ላይ ገድለዉታል ብላቹህ ንገሩዋት" ብሎዋቸው ተደበቀ፡፡ ከዚያ ሂደው መርዶውን ነገሩዋት፡፡ እሷም ደንግጣ ልቅሶ ጀመረች፤

"አንተ ለቃሚ መሰቋ(የፍሬ ዓይነት) በቀን ተጓዥ፣

የዋሲኒ አባት ምን ወሰደብኝ እባክህ ወደ ልጅህ ተመለስ

መሳሳኪየ እባክህ ተመለስ ተመለስ!!!" ብላ አምርራ አለቀሰች፡፡ ከዚያም መሳሳኪ "እውነትሽ ነው እውነት አለቀስሽልኝ" ብሎ ተቀላቀለ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ 20/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ ሰባት

በድሮ ዘመን በኩናማ እና በሌሎች ህዝቦች መኻከል ጦርነት ነበር፡፡ ሁሌ ሽሽት እና ስደት ነበር፡፡ ኩናማዎቾ ጠላት ሲመጣ እና ሲሰሹ አካል ጉዳተኛ እና አቅመ ደካማ ሽማግሌዎች ሲኖሩ በጠላት እጅ እንዳይወድቁ መታን ገድለው ነበር የሚተውዋቸው፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ጠላት ይመጣባቸው እና ዘበኞች አዋጅ ያውጃሉ፡፡ "ጠላቶቻችን እየመጡ ስለሆነ ጓዛቹህን ጠቅልሉ፣ አቅመ ደካሞቹን ግደሉ እና ቅበሩ" አሉ፡፡ ከዚያ አንድ ወጣት አባቱን ይነግረዋል፡፡ አባቱም ሽማግለ ብሆንም እጠቅምሀለው እና ሳትገድል ከጓዞችህ ጋር ደብቀህ ግመሉ ላይ ውሰደኝ አሉት፡፡ ሌሎች ሽማግሌዎች እና አቅመ ደካሞቹን ገድለው ጓዛቸውን ጠቅልለው ለሽሽት ሲዘጋጁ እሱ ግን አባቱን ከእቃ ጋር ደብቆ ገመል ላይ ጭኖ ጉዞ ጀመሩ፡፡ የት ደረስን ብለው ሲጠይቁት የደረሱበትን ይነግራቸው ነበር፡፡

ፀሐይ ልትጠልቅ ስትል እንደዚህ ያለ ቦታ ላይ ደረስን አላቸው፡፡ "በል ሜዳ ላይ እንዳታርፍ፣ ወደ ኮረብታማው ቦታ ወጣ ብለህ ከግድሙ እረፍ" አሉት፡፡ ሌላው ህዝብ ሜዳው ላይ ተዘርግቶ ሲያርፍ እሱ ግን ከፍ ወዳለ ቦታ ሂዶ አርፈ፡፡ በነጋታዉም ሲጓዙ ውለው ከአንድ ትልቅ ሽለቆ/ወንዝ ዳር ለማደር ህዝቡ አረፈ፡፡ እሱ ግን "ከሸለቆው ወጥተህ ተራራው ላይ እረፍ" አሉት፡፡ እንደዚያም አደረገ፡፡ ከዚያም ለሊት በዚህ መጣ የማይባል ጎርፍ መጥቶ ድካም ላይ የሰነበተዉን ህዝብ ጠራርጎ ሲወስደው እሱ እና ቤተሰቡ ብቻ ቀሩ፡፡ ከዚያ በኃላም በሽማግሌ ሰውየው ምክንያት ነው የኩናማ ህዝብ ዘር የቀጠለው ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ 20/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ ስምንት

በአንድ አገር የሚኖሩ ወንድም እና እህት ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች በጣም ሀብታሞች ቢሆኑም ወገን ግን አልነበራቸውም፡፡ ወገን ስለሌላቸው የአገሩ ሰዎች ከብቶቻቸው እየዘረፉ ይወስዱባቸው ነበር፡፡ ሰውየው ከብቶቹ እየተነዱ ሲሄዱ ቢያይም አቅም ስላልነበረው ዝም ነበር የሚለው፡፡ ስራው ማን ስንት ከብት እንደወሰደበት መቁጠር ብቻ ሆነ፡፡

ከዚያ በኃላ እህቱ አገባች እና ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ ወንድሟ በጣም ተደስቶ በከፍተኛ እንክብካቤ አሳደገው፡፡ እንደገና ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ አሁንም ደስታው ወሰን አልነበረውም እና እየተንከባከበ አሳደገው፡፡ ሶስተኛ ወንድም ወለደች፡፡ ከዚያ እነሱን

እየተንከባከበ አሳደጋቸው፡፡ በየቀኑ በረኸ እየወሰደም የጦር ውርወራ፣ ግጥምያ፣ ሩጫ… ያሰለጥናቸው ነበር፡፡ እርስ በርሳቸው እንዲፋለሙ፣ ከእርሱ ጋር እንዲገጥሙ እያደረገ ከፍተኛ አቅም እንዲገነቡ እና እንዲለማመዱ አደረገ፡፡ ከዚያ አንድ ቀን ልጆቹ "አጎቴ ለምንድን ነው ይህ ሁሉ የምታሰለጥነን?" ብለው ጠየቁት፡፡ እነግራቹዋለሁኝ መጀመርያ ግን በጣም ሰፊ የሆነ የከብቶች ማደርያ እንስራ አለቸው፡፡ እንጨት እና እሾህ እየቆረጡ ሰፊ መካበብያም ሰሩ፡፡ ከዚያ በኋላ ልጆቹን ሰበሰበ እና "በሉ ታሪካችን ልንገራቹህ እዚህ አገር እኛ ብቻ ነበርን ሀብታሞች፤ በዚህ ሰፈር ያሉት ከብቶች የኛ ናቸው፡፡ እንትና የህን ያክል ላም፣ እንታና ይህን ያክል ላም ወስደውብናል…" ብሎ ነገራቸው፡፡ በአገሩ ካሉት ሰዎች "ተዉ የሰው ንብረት አትንኩ" ሲሉ የበሩት እና ንብረቱን ያልነኩበትንም ነገራቸው፡፡ ከዚያም ልጆቹ አጎታቸው  በነገራቸው ታሪክ ሲሰሙ እሳት ሆኑ እና ጦራቸውን መዘው ከብት ወስደዋል ወደተባሉ ሰዎች ቤት በመሄድ ከብቶቹን ጠርንፈው መንዳት ጀመሩ፡፡ ልጆቹ ተወዳዳሪ የሌላቸው ጎረምሶች ነበሩ እና ማንም ሊያስቆማቸው የመከረ አልነበረም፡፡ በዚህም የሌላ ንብረት ሳይነኩ የተወሰዱባቸውን ከብቶች በሙሉ አስመለሱ፡፡ በዚህም በጣም ሀብታሞች ሆነው ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ 20/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃምሳ ዘጠኝ

በድሮ ዘመን የአንድ ሰፈር ሴቶች ተሰባስበው ለዋና ወደ ወንዘ ሄዱ፡፡ ከዚያ አንዲት የሀብታም ልጅ ከነሱ ትንሽ ዘግይታ ደረሰችባቸው እና እንቆቻቸውን አሸዋ ላይ ደብቀው "እንቁዎቻችን ወደ ውኃው ጨምረነዋል፣ አንቺም ጨምሪው አሉዋት፡፡ እሷም እውነት መሰላት እና ከአንገቷ አውጥታ ማሰርያውን በጥሳ ውኃው ላይ በተነችው፡፡ ዋኝተው እንደጨረሱ ሌሎቹ ሴቶች እንቆቻቸው ከደበቁበት አሸዋ አውጥተው "ይሄው የኛ ውኃው ላይ አልከተትነውም አንቺ ብቻ ነሽ የከተትሽው፤ አታልለንሻል" አሉዋት፡፡

ከዚያ ልጅቷ በጣም ተናደደች እና ወደ ቤት አልሄድም ብላ ለብቻዋ እዛው እያለቀሰች ቀረች፡፡ እዚያ እያለቀሰች ሳለ ዳይናሶር መጣ እና "ምን ሁነሽ ነው የምታለቅሽው?" አላት፡፡ እሷም "ጓደኞቼ አታልለዉኝ እንቆቼን ውኃ ውስጥ ገብቶብኝ" አለችው፡፡ ከዚያ በኋላ "ታድያ እኔ ከለቀምኩልሽ ምን ታደርጊልኛለሽ? ሚስቴ ትሆኚኛለሽ ወይ?" ብሎ ጠየቃት፡፡ "እሺ" አለችው፡፡ ከዛ ውኃው ጠጥቶ ጨረሰው እና "ግቢ እና እንቁሽን ልቀሚ" አላት፡፡ ለቅማ ከጨረሰች በኋላ የጠጣውን ውኃ መልሶ ተፋው እና ኃይቁ ወደ ነበረበት ተመለሰ፡፡

ከዚያ ወደ አንድ ትልቅ ዲማ (የዛፍ ዓይነት) ወስዶ እዚያው ያኖራት ጀመር፡፡ ዛፉን ውስጥ ለውስጥ ፈልፍሎ ቤት ሰርቶ ማንም እንደማያያት አድርጎ ነበር የሰራው፡፡ ከዚያ እንዳስገባትም አትወጣም ነበር፡፡ እሱ ግን በየቀኑ ምግብ ፈልጎ ያመጣላት ነበር፡፡ ከዚያ ስትኖር ስትኖር በትንሽዋ የብርሀን ማስገቢያ ቀዳዳ የአባቷ ከብቶች፣ አህዮች እና ፍየሎች ሲያልፉ ስታይ ትዘፍን ነበር፡፡ እሷ ስትዘፍን ከብቶቹ ትልቁን ዲማ በቀንዳቸው፣ አህዮቹ ደግሞ በእግራቸው ይመቱት ነበር፡፡ በየቀኑ እንዲህ ሲያደርጉ እረኛው ይከታተላቸው ነበር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ማታ ጌታውን "ጌታየ ሆይ ከብቶቻችን የሆነች ትልቅ ዲማ ላይ እንደደረሱ ዲማዋን በቀንዳቸው ካልጣልን ብለው ይታገላሉ፤ አህዮቹ እና ፍየሎቹም እንዲሁ፡፡ ከዲማው ላይ ደግሞ የሆነ የሴት የሚመስል ቀጭን ዘፈን ይሰማል፣ ምን ሆን ሚስጥሩ?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ከዚያ ልጄ በህይወት አለች ማለት ነው ብሎ አሰበ እና በነጋታው ከከብቶቹ ጋር አብሮ ሄደ፡፡ እቦታው እንደደረሰ ልጅቱ የአባቷን ጥሪት ስታይ እንደለመደችው መዝፈን ጀመረች፡፡ አባቷ ጠጋ ሲል የልጁን ድምፅ ሰማ፡፡ እንዲሁም አየችው እና ተለቃቅሰው ሁሉንም ነገር ነገረችው፡፡ "ታድያ እንዴት አድርጌ ላድንሽ?" ሲላት ዳይናሶሩ ሳይሞት ከዚያ መውጣት እንደማትችል፣ ኃይለኛ እንደሆነ ነገረችው፡፡ ከዚያም ኣበቷ "እንዴት አድርጌ ልገድለው እችላለው?" ሲል ጠየቃት፡፡ "በርኸ ውሎ ሲመለስ ኃይለኛ የሆነ አውሎ ንፋስ አስከትሎ ነው የሚመጣው፣ ወደ ቤት ሲገባ ደግሞ መጀመርያ ሁለቴ ጎምበስ ቀና ይላል፡፡ ስለዚህ ተዘጋጅተህ ቆይተህ ጎምበስ ሲል አንገቱን ትቆርጠው እና ይሞታል" አለችው፡፡ ከዚያ አባቷ ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ እና በነጋታው ሴፍ ይዞ መጥቶ ተዘጋጅቶ ይጠብቀው ጀመር፡፡ ልጁ እንዳለቹው ዳይናሶሩ ኃይለኛ አውሎ ንፋስ አስከትሎ መጣ፡፡ ዲማው ላይ እንደደረሰ ለመግባት ጎምበስ ሲል ሴፍ መዞ አንገቱን ቁርጥ አደረገው፡፡ ከዚያም ልጁን ይዞ ሄደ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ 20/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ

በድሮ ዘመን ጅብ ከዘጠኝ ልጆቹ ጋር ይኖር ነበር፡፡ ልጆቹም አደን አድነው ይቀልቡት ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ዘጠኙ ልጆቹ ከአንበሳ ጋር ለአደን ሄዱ፡፡ ከዚያም አስር ላሞች አገኝተው እየነዱ አገራቸው እንደደረሱ አንበሳ ድምጹን ጎርነን አድርጎ "በሉ ደርሰናል እና እንካፈል አላቸው፡፡ ከዚያም እናንተ ዘጠኝ ናቹህ አንዲት ላም ትወስዱ እና አስር ትሆናላቹህ፤ እኔ ደግሞ አንድ ነኝ ዘጠኝ ላሞች ስወስድ ከእኔ ጋር አስር

እንሆናለን" አላቸው፡፡ ጅቦቹ ምንም እንኳ አንበሳ አንዲት ላም ብቻ ሰጥቶ ለራሱ ዘጠኝ ላሞች በመውሰዱ ባይዋጥላቸውም ስለፈሩት መቃወም አልቻሉም፡፡ ከዚያም አንዷን ላም እየነዱ አባታቸው ዘንድ ሄዱ፡፡ እቤት እንደደረሱ አባታቸው "ልጆቼ እንደምን ዋላቹህ? እንኳን በሰላም ተመለሳቹህ" ብሎ ተቀበላቸው፡፡ "ውሎ እንዴት ነበር?" ሲላቸው ከልጆቹ አንዱ "ውሎ ደህና ነበር፣ አስር ላሞች አግኝተን ዘጠኙ አያ አንበሳ ወሰዳቸው እኛን ደግሞ አንድ ላም ሰጥቶ ለአባታቹህ ውሰዱለት አለን" አለው፡፡ ከዚያም አባቱ በጣም ተናዶ "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እሱ አንድ ሆኖ ዘጠኝ ሲወስድ እናንትን ግን አንዲት ላም ውሰዱ አላቹህ! እና ዝም ትላላቹህ? ውይ በሞትኩ! በሞትኩ! አልወለድኩም ማለት ነው" ብሎ መሬት ቀወጠው፡፡ ከዚያም "በሉ እንሂድ ላምዋን ንዱዋት እኔ አባታቹህ አሳያቹዋለሁኝ፣ እሱን አንድ ሰጥቸ ዘጠኙን አመጣለው" ብሎ ፎከረ እና ልጆቹን ሰብስቦ ላምዋን እየነዱ አንበሳ ቤት ሄዱ፡፡

ከዚያም ከአንበሳ ቤት እንደደረሱ አንበሳ ክምር ብሎ ተቀምጦ አገኙት፡፡ አባታቸው አንበሳን ሲያይ በፍርሀት ተንቀጥቅጦ "እህ..ህ.. አያ አንበሳ እንደምን ዋልክ?" ብሎ ሰላምታ አቀረበ፡፡ አንበሳም ሳይመልስለት "ወዴት እየሄዳቹህ ነው?" ብሎ ጠየቀ፡፡ ከዚያም "አያ አንበሳ ልጆቹን አንዲት ላም ሙሉ ሰጣሀቸው፡፡" ሲል አንበሳ ድምጹን ከፍ አድርጎ "አዎ ሰጥቻቸዋለሁኝ ምነው?" ሲል ጅብ "ልጆች ስለሆኑ ነው አትፍረድባቸው፤ ለምን ትሰጣቸዋለህ? ስለዚህ እንድንመልስልህ ነው የመጣነው አለው፡፡ አንበሳም "አረ ደህና ለናንተ ውሰዷት" አለው፡፡ ጅብም "በጭራሽ አይሆንም ላንተ ነው የምትገባው" ሲል ተከራከረ እና አንበሳም እሺ ብሎ ተቀበለ፡፡ ከዚያም ጅብ ልጆቹን ሰብስቦ ወደ ቤቱ እየተመለሰ ሳለ ትንሹ ልጁ "አንተ አባየ እኔማ የአንበሳን ቀያይ አይኖችን ሳይማ ቅዘን ሊያመልጠኝ ትንሽ ነበር የቀረኝ" አለው፡፡ አባቱም "ልጄ አንተማ ደህና ነህ እኔ እኮ ተበላሽቻለው" አለው ይባላል፡፡

(ወ.ሮ መድህን ብስራት፣ 20/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ አንድ

አንድ አገር የሚኖር አንድ ሌባ ነበር፡፡ ሰዎች ሌባ ነህ ሲሉት ግን በጭራሽ አይደለሁም ብሎ የከራከር ነበር፡፡ አንድ ቀን ክረምት ሆኖ በሬዎቹን ይዞ ወደ ማሳ ሄደ፡፡ ከዚያ ደርሶ በሬዎቹን ጠምዶ ያርስ ነበር፡፡ ፀሐይ ሲሞቀው ልብሶቹን አውልቆ ከማሳው ጫፍ ላይ ካለው አንድ ዛፍ ላይ ሰቅሎት ያርስ ነበር፡፡ ከዚያም እያረሰ እያረሰ ሳለ የራሱን ልብሶች ቀና ብሎ ሲያይ የሌላ ሰው መሰለው እና በሬዎቹን እንደተጠመዱ አቁሞ ቀስ

ብሎ ተደብቆ ልብሶቹ ጋ ሂዶ ቀስ አድርጎ አውርዶ ይዞ መሮጥ ጀመረ፡፡ ከዚያም ብዙ እንደሮጠ እስቲ ምን የሚረባ ነገር ይኖረው ይሆን ብሎ ሲያየው የገዛ ራሱ ልብስ ነው፡፡ ከዚያም "ውይይ ለካ ልማድ ሆኖብኝ ነው እንጂ የራሴን ልብስ ሰርቄ ነው የምሮጠው" አለና ወደ በሬዎቹ ተመለሰ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ሽቱ አዋዱ፣ 17/06/2009 ዓ.ም)

## ስልሳ ሁለት

እድሪስ እና ሎንጊ የሚባሉ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን እድሪስ ሎንጊ ጋ ሂዶ "ስማ ጓደኛየ በአከባቢያችን ወርቅ ተገኝቷል እየተባለ ነው እና ለምን ሂደን አንለቅምም?" አለው፡፡ ሎንጊ ደግሞ "አዎ ሰምቻለው፣ ታድያ መቼ ሰርተን እናውቃለን እንዴት እንችለዋለን?" አለው፡፡ "እዛ እንደሄድን ሰዎችን አሳዩን እንላለን" አለው፡፡ ከዚያ አሳመነው እና ሚስቶቻቸውን ተሰነባብተው ሄዱ፡፡

ወርቅ ከሚቆፈርበት ቦታ ደርሰው እንዴት እንደሚለቀም ለማየት ሰዎች ጋ ተቀላቀሉ እና አሰራሩን ተማሩ፡፡ ከዚያም መቆፈር ጀመሩ እና እንደ ዕድል ሆኖ ትልቅ ወርቅ አገኙ እና ሸጠው ተካፍለው አገራቸው ገቡ፡፡ በነጋታዉም እንዲሁ ሲቆፍሩ ውለው ተካፈሉ፡፡ አመሻሽ ላይ እድሪስ እንሂድ ይላል፡፡ ከዚያም እየሄዱ ሳለ መንገድ ላይ እንጀራ እንዲበሉ አረፍ አሉ፡፡ ከዚያም እድሪስ ሎንጊን ከገደልኩት ይሄ ሁሉ ወርቅ ለብቻየ አደርገዋለሁኝ ብሎ አሰበ እና "ስማ እስቲ ሎንጊ እዚህ በርሽ ላይ ብገድልህ ማን ይነግርልሃል?" አለው፡፡ "እዚህ ብትገድለኝ ሰው ባይነግርልኝ ምድር ግን ትመሰክርልኛለች" አለው፡፡ ከዚያም "በል ምድር ከመሰከረችልህ እማ እናያለን" ብሎ በያዘው መጥረብያ አናቱን ብሎ ገደለው እና እዚያ ቀብሮት ሄደ፡፡

ከተወሰኑ ዓመታት በኃላ እድሪስ በዚያ ቦታ ሲያልፍ መቃብሩ ሲያየው ብርትኳን አፍርቶ አገኘው፡፡ በጣም ገረመው እና ተወዳጅነት ለማግኘት አስቦ ብርትኳኑን ይዞ ንጉስ ዘንድ ሄደ፡፡ ንጉስ ዘንድ እንደደረሰም አጋፋሪዎቹ "ወዴት ነህ?" ሲሉት "ለጌታየ ገፀ በረከት ይዤ ነው አስገቡኝ" አላቸው፡፡ እንዲገባ ተፈቅዶለት ገባ እና ንጉስ በብርትኳኑ ማማር እጅግ ተደስቶ "በል እስቲ ቁረጠው እና እንቅመሰው" ሲል አዘዘው፡፡ ከዚያም ብርትኳኑ ሲቆርጠው ደም ሆነ፡፡ እድሪስ ገርሞት እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ "ምንድነው ይዘህው የመጣህው? የምን ልታበላኝ አስበህ ነው?" ብሎ ንጉስ አፈጠጠበት፡፡ ከዚያም "ጌታየ ድሮ ጓደኛየ ወርቅ ለቅመን ስንመለስ መንገድ ላይ እዚህ በርሽ ብገድልህ ማን ይነግርልሃል ብየ ስጠይቀው ሰው ባይነግርልኝ ምድር ትመሰክርልኛለች

አለኝ፡፡ እኔ ደግሞ ምድር አፍ አውጥታ ከመሰከረችልህስ ብየ ገድየ ቀብሬው ሄድኩኝ፡፡ ከዚያ በኃላ ኑሬ ኔሬ በዚያ ቦታ ሳልፍ መቃብሩ እንዴት ሆነ ብየ ሳይ የሚያማምር ብርትኳን አፍርቶ ጠበቀኝ፤ ከዚያም ይህን መልካም ፍሬ ለጌታየ ለንጉስ ገፀ በረከት ይሆን ዘንድ ይገሆው መጣሁኝ፡፡ ታድያ እዚ ሳመጣው ይሄው ደም ሆነ" አለ፡፡ ከዚያም ንጉስ ታድያ ምድር ምስክርነታዋን እንደሰጠች አየህ አይደል ብሎ አሰረው ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ሽቱ አዋዱ፣ 17/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ ሶስት

አንድ ድኻ ሰው ነበር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን አምላክ ለምንድን ነው እኔን ድኻ አድርጎ የፈጠረኝ ብሎ ይናደድ እና አምላክን እገድላለሁኝ ብሎ ሴፍ እና ጦር ይዞ ጉዞ ጀመረ፡፡ ትንሽ እንደተጓዘ አምላክ ሰው መስሎ መንገድ ላይ አገኘው፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኃላም "ወዴት እየሄድክ ነው?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ሰውየውም "አምላክ ድኻ አድርጎ ስለፈጠረኝ ልገድለው እየሄድኩ ነው" አለው፡፡ አምላክ ደግሞ "ታድያ አምላክን ታውቀዋለህ ወይ" ብሎ ጠየቀው፡፡ ሰውየውም አላውቀዉም ብሎ መለሰለት፡፡ "በል ሂድ እለፍ" አለው እና ሰውየው ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ከዚያ በኃላ አምላክ ከፊት አልፎ ጠበቀው እና እንደገና ጠየቀው፡፡ እሱም እንደ ቅድሙ አለው፡፡ ከዚያም አምላክ "አሁን አምላክ ብታገኘው የምር ትገድለዋለህን?" ሲል ጠየቀው፡፡ ሰውየው ደግሞ "አዎ" አለው፡፡ ከዚያም "በል እኔ ነኝ አምላክ እና ግደለኝ" አለው፡፡ ከዚያም ሰውየው በድንጋጤ ተርበደበደ፡፡ አምላክ ደግሞ ና ብሎ አንድ ጥላ ላይ ቁጭ አደረገው፡፡ ከዚያም "ከእንግዲህ በኃላ አምላክን እወጋለው ማለት ይቅርብህ እንዲጠቅምህ ግን የዓለም ቋንቋ ሁሉ ሰጥቸሃለው እና ተመልሰህ ወደ ቤትህ ሂድ" አለው፡፡ ሰውየውም አመስግኖ እና ይቅርታ ጠይቆ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

እየተመለሰ ሳለ መንገድ ላይ ደከመው እና ነጠላውን ተከናንቦ ከአንድ ዛፍ ስር ላይ ተኛ፡፡ ከዚያም ሁለት ቁራዎች መጥተው አጠገቡ አረፉ እና አንዷ ቁራ "የሞተ ይመስላል" ስትል ሰማት፡፡ ዝም አለ እና ጠጋ ስትል ቀርቀም አድርጎ ያዛት፡፡ ከዚያም የተያዘችው ቁራ "አረ ሊገድለኝ ነው" ስትል ጓደኛዋ ደግሞ "እንዳይገድልሽ ከፈለግሽ አገልግል ላይ ካኖርሽው ብር ስጭው" አለቻት፡፡ የተነጋገሩትን ሁሉ ይሰማ ስለነበር "ብርሽ ካለበት ቦታ ምሪኝ ካልሆነ እገድልሻለው" ብሎ አስፈራራት እና ወስዳ አገልግል ሙሉ ብር ሰጠችው፡፡ ከዚያ ወደ ቤቱ ተመለሰ እና ሃብታም ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ማታ ላይ ጅቦች ተሰባስበው "ሰው እንብላ" ብለው ሲመካከሩ ሰማ

እና ሰው አይተዋል ማለት ነው ስለዚህ እንዳይበሉት ልርዳው ብሎ ከቤት ወጥቶ እርዳታ ሊሰጥ ወጣ፡፡ ነገር ግን በዚያ ሰዓት የሚበሉት ሌላ ሰው አልነበረም እና ለሰውየው ለራሱ ይዘው በሉት ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ሽቱ አዋጁ፣ 17/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ አራት

በድሮ ጊዜ እርኩም (hornbill) መሬት ቆፍራ ጉድጓድ ሰርታ እንቁላልዋን ጣለች፡፡ ከዚያ በኃላ ቀናቸው ሲደርስ ፈለፈለቻቸው እና በየቀኑ ምግብ ፈልጋ አምጥታ ትመግባቸው ነበር፡፡ እሷ ግን ሌላ ቦታ ነበር የምትኖረው፡፡ ምግብ ፈልጋ አምጥታ ከጉድጓዱ አፋፍ ላይ ሆና ትጠራቸው እና "በሉ እንኩ ሁላቹሁም ብሉ" ትላቸው ነበር፡፡ በየቀኑ እንዲህ ስታደርግ ጥንቸል ተደብቆ ይከታተላት እና ይሰማት ነበር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን እሷ ምግብ ፍለጋ እንደሄደች ጥንቸል ወደ ጉድጓዱ ገብቶ "እኔ ወንድማቹህ ነኝ፣ ስሜ ደግሞ "ሁላቹህ" ይባላል ብሎ ተዋወቃቸው፡፡ አብሮዋቸውም መኖር ጀመረ፡፡ ከዚያም ምግብ አምጥታ "እንኩ ሁላቹህ ብሉ" ስትላቸው ጥንቸሉ "ምግቡ እኮ ለኔ ነው ሁላቹ ይብላው ነው ያለችው" ይል እና ብቻውን ይበላዋል፡፡ እንዲህ እያደረገ የመጣውን ምግብ እየበላ እነሱ በርሀብ ሊሞቱ አሉ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን እናታቸው "ኑ እስቲ ልያቹህ ልጆቼ ውጡ" አለቻቸው፡፡ ወጡ እና ታቀፉዋት፡፡ ስታያቸው በጣም ከስተው ሊሞቱ ብለዋል፡፡ "ምን ሁናቹህ ነው እንዲህ የከሳቹህ ያ ሁሉ ምግብ እየበላቹህ" ስትል ጠየቀች፡፡ እነሱም "እኛ መቼ በላን ሁላቹህ እኮ ነው ብቻውን የሚበላው አሉዋት፡፡ ሁላቹህ ደግሞ ማን ነው እኔኮ ሁላቹህ ስል አንድ ላይ ብሉት ማለቴ ነው፤ ማን ነው ሆላቹህ አለች፡፡ ጉድጓድ ውስጥ አለ አሉዋት፡፡ ከዚያም ማነህ አንተ አጭበርባሪ ና እስቲ ውጣ ስትለው ጥንቸል ደግሞ በዪ እንድወጣ እንኪ መጀመርያ ጫማየን ተቀበዪኝ ብሎ ጆሮውን አስተካክሎ ላከላት፡፡ እሷም ጫማ መስሏት በጣም ተናድዳ በኃይል ያዝ እድርጋ አርቃ ወረወችው እና እስኪወጣ ትጠብቅ ጀመር፡፡ ጥንቸል ደግሞ ከወረወረቹው ተነስቶ ሮጦ አመለጠ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ ውጁ ሚኮ፣ 19/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ አምስት

አንድ በጣም ስስታም ውሻ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከአንድ ቤት ገብቶ ሥጋ አግኝቶ እስኪጠግብ በላ፡፡ የቀረውን ሥጋ በአፉ ተሸክሞ ወደ ቤቱ ይሄድ ነበር፡፡ ወደ

ቤቱ ስሄድ መንገድ ላይ አንድ ኩሬ አገኘቶ ወደ ውኃው ብቅ ሲል የራሱን ጥላ አየ፡፡ ከዚያም ሌላ ሥጋ የያዘ ውሻ ያየ መስሎት እሱን ለማስጣል ለመጮህ አፉን ሲከፍት ከአፉ የነበረ ሥጋ ውኃ ውስጥ ገባ ይባላል፡፡

(አቶ ገብረክርስቶስ ቶሊ 24/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ ስድስት

በድሮ ጊዜ ባል እና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ከዚያም ሁለት ልጆች እንደ ወለዱ ሚስቱ ትሞትበት እና ልጆቹን ለብቻው ያሳድግ ነበር፡፡ ከዚያም በአንድ ወቅት በጋ ላይ ድርቅ ይሆን እና የሚበላ አጥተው ተቸገሩ፡፡ ልጆቹም በርሀብ ሊሞቱ ሆነ፡፡ ጎረቤታቸው ግን አንድ በጣም ሃብታም ሰውየ ነበር፡፡ እና አንድ ቀን ማታ አባትየው ልጆቹን "ሙቀት ስለሆነ ከደጅ እንተኛ" ብሎ ከደጅ አስተኛቸው፡፡ ልጆቹ እንደተኙ ተነስቶ ወደ ሀብታሙ ጎረቤታቸው ቤት ገብቶ አንድ ፍየል ሰርቆ አመጣ፡፡ ከዚያም ፍየሉን እቤት ውስጥ አርዶ ሥጋውን ካበሰለ በኃላ ውኃ በጣሳ ቀድቶ ደጅ ላይ ለተኙ ልጆቹን አርከፈከፈባቸው፡፡ ከዚያም "ልጆቼ ተነሱ ተነሱ ዝናብ መጣ" አለና እቤት አስገብቶ ያበሰለውን ሥጋ አበላቸው፡፡ ከዚያም በነጋታው ጎረቤታቸው ጧት ተነስቶ ፍየሎቹን ሲቆጥር አንዱ ወጠጤ አልነበረም፡፡ ከዚያ ይህ ድሃ ጎረቤት ነው ሰርቆ አርዶ በልቶት የሚሆን ብሎ አሰበ እና የድሃውን ልጆች ጠርቶ "እናንተ ሥጋ በልታቹዋል እንዴ?" ብሎ ሲጠይቃቸው "አዎ ትናንትና ማታ ዝናብ እየዘነበ ሳለ በላን" አሉት፡፡ ከዚያም ሰውየው "ውይ እኔ የማወራው የትናንት ማታ እናንተ የምትሉት የባለፈው ክረምት ማታ" ብሎ ሄደ ይባላል፡፡

(አቶ ገብረክርስቶስ ቶሊ 24/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ ሰባት

በድሮ ዘመን ወፎች እና አይጦች ተጣሉ፡፡ ከዚያም የለሊት ወፍ በማኸል ገብታ ላስታርቃቹህ አለቻቸው፡፡ እነሱም እሺ ብለው ተስማሙ፡፡ ከዚያም ወፎቹ ዘንድ ሂዳ "አይዞዋቹህ እኔ ከናንተ ጋር ነኝ፡፡ እዩኝ እስቲ ክንፌን እናንተን ነው የምመስለው" ትላቸዋለች፡፡ ወፎቹም አምነው እሺ ይላሉ፡፡ አይጦቹ ዘንድም ትሂድ እና "አይዞዋቹህ እኔ ከእናንተ ነኝ፡፡ እዩኝ እስቲ ጥርሴን እና ጡቴን እናንተን ነው የምመስለው፤ ስለዚህ ወፎቹን እናሸንፋቸዋለን" አለቻቸው፡፡ በዚህም አመኑዋት እና እሺ ብለው ለፍልምያ ተዘጋጁ፡፡ በወፎች እና አይጦች መኸከል የነበረ ጥላቻ ተካርሮ ደም ለመፋሰስ ተዘጋጁ፡፡

ከዚያም ሲኖሩ ሲኖሩ ወፎቹ እና አይጦቹ ታዘቡዋት እና ስራዋ ሁሉ ስላልጣማቸው እሷ ሳትኖር ተገናኝተው ታረቁ፡፡ ከዚያም እንዳትጠጋቸው አደረጉ፡፡ ከዚያ በኃላ ነው በተግባሯ አፍራ በለሊት የምትሄደው ይባላል፡፡

(አቶ ገብሪሂንስ ሐመዳይ፣ 21/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ ስምንት

ሁለት ውሾች በአንድ ቤት ከጌቶቻቸው ጋር ይኖሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ባለቤቶቹ ከጎረቤት ዝክር ነበር እና ሁሉም እዛ ሂደው አምሽተው ራታቸውንም በልተው መጡ፡፡ ከዚያም ረስተዉት ውሾቹን ራት ሳይሰጡዋቸው ተኙ፡፡ ከዚያም ውሾቹ ምን እናድርግ ብለው ተመካከሩ፡፡ ከዚያም አንዱ ውሻ "ክረምት ነው አየሩ በጣም ይበርዳል በዛ ላይ ርሀብ፣ እንዴት አድርገን እናድራለን? እኔ ብርድ እና ርሃብ አልቻልኩም" አለ፡፡ አንዱ ደግሞ "አንድ ለሊት ናት አይዞህ" ይለዋል፡፡ ለምን "ዝም ብለን እየጮህን እንቅልፍ አንነሳቸውም? ለራሳቸው ራታቸውን በልተው እኛን ሳይሰጡንማ መተኛት የለባቸውም" ብሎ ተከራከረው፡፡ ከዚያም አንዱ "ለምን የሆነ ነገር ሳናይ እንጮኸለን? አይደለም ሳናይ ጭሆን አይተን ጭሆንም እውሮች ነን እየወለድን ያለነው ስለዚህ መጮኽ የለብንም" አለው፡፡ ከዚያም ባለመጮኻቸው ባዶ ሆዳቸው አደሩ ይባላል፡፡

(አቶ ገብሪሂንስ ሐመዳይ ፣ 21/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስልሳ ዘጠኝ

በአንድ አገር የታወቀ በር ሰሪ ነበር፡፡ የራሱ ቤት በር ሳይኖረው የሌሎች በር ግን እየዞረ ይሰራ ነበር፡፡ ከዚያም ሚስቱ "አንተ ለምንድን ነው ቤታችን በር ሳይኖረው የሰው በር የምትሰራው? መጀመርያ ቤታችን መዝግያ አበጅለት" ስትለው እሺ አንድ ቀን አበጅለታተው ይላታል፡፡ በዚህም በዛሬ ነገ በር ሳይሰራለት ክረምት ገባ፡፡ አንድ ለሊት ኃይለኛ ዝናብ መጣ፤ ድቅድቅ ጨለማም ስለ ነበር የሰውየው ቤት በር ስላልነበረው ጅብ ሳያዩት ገብቶ ልጁን ወሰደው፡፡ ከዚያ በኃላም "የበር ሰሪ ልጅ ጅብ ወሰደው" ይባላል፡፡

(አቶ ነጋ ሚኩ፣ 23/06/2009ዓ.ም)

## ተረት ሰባ

በአንድ ወቅት በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ሁለት ድመቶች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ዘውትር እንደሚያደርጉት ምግብ ፍለጋ እየተዘዋወሩ ሳለ አንድ መስኮቱን የተከፈተ ቤት አይተው ዘለው በመግባት ሰሀን ላይ ስጋ አግኝተው ይዘው ወጡ፡፡ ከዚያም አንዱ ጓደኛውን የያዘው ሥጋ ሲያይ እሱ ከያዘው ሥጋ የሚተልቅ ነው፡፡ ከዚያም "ያንተ ሥጋ ትልቅ ነው የኔ ግን ትንሽ ነው ስለዚህ እኩል እንካፈል" ይለዋል፡፡ እሱም "አላካፍልህም አንተ የያዝከው ብላ እኔም እንደዛው" አለው፡፡ ከዚያም "እንዴት የያዝነውን እንበላለን? አንድ ላይ ነው ያገኘነው ስለዚህ እኩል መካፈል አለብን" አለው፡፡ ሊሰማው ስላልቻሉ ተያይዘው መጣላት ጀመሩ፡፡

በዚህ ጊዜ አንድ ተንኮለኛ ቀበሮ ሲጨቃጨቁ ይሰማ ነበር እና ጠጋ ብሎ "ምንድን ነው የሚያጣላቹህ?" ብሎ ጠየቀ ከዚያም ተበድያለው ብሎ ያሰበው ድመት ጉዳዩን አስረዳው፡፡ ቀበሮም "እውነቱን ነው ጓደኛሞች ናቹህ በዛ ላይ አንድላይ ነው ያገኛቹህት ስለዚህ እኩል መካፈል አለባቹ" አለ እና ሚዛን አምጥቶ አምጡ እኔ ላካፍላቹህ አለ፡፡ ከዚያም ሥጋውን ሚዛን ላይ ሰቅሎ "ይህቺ ትንሽ ትበልጣለች አይደል?" ብሎ ጎረስ ያደርጋል፡፡ አንዱኑ ስታዘነብልም እንዲሁ "ይቺ ትበልጣለች አይደል?" እያለ ይጎርሳል፡፡ እንዲህ እያደረገ ሥጋውን ሊጨርሰው ሲል ድመቶቹ ተያዩ እና "በቃ አምጣው ራሳችን እንካፈለዋለን" አሉት፡፡ ቀበሮም "እህ ስራየን ትቼ እዚህ አምሽቼ እማ መጨረሻውን ሳላይ አልሄድም አካፍላቹዋለሁኝ" አለ፡፡ ከዚያም እንደዛ እያደረገ ስጋውን ጨረሰው፡፡ ድመቶቹም ባለመስማማታቸው ቀበሮ እንዳታለላቸው አውቀው እያጉረመረሙ ወደ ቤታቸው ተመለሱ ይባላል፡፡

(ወ.ሮ አለማሽ ገብሪሃንስ፣ 22/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ አንድ

አንድ የገበሬ ልጅ ተማሪ ነበር፡፡ ከትምህርት ቤት እንደለመለሰ ደብተሩን ይዞ ወደ በረኸ በመሄድ ያጠና ነበር፡፡ ከአንድ ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ያጠና እና ሲደክመው ደብተሩን አጥፎ አስቀምጦ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ በየቀኑ እንዲህ ስያደርግ ጦጣ ዛፉ ላይ ሆኖ ያየው ነበር፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ተማሪው አጥንቶ እንደጨረሰ ደብተሩ እና እስክርቢተውን አስቀምጦ ሊንቀሳቀስ ሲሄድ ጦጣ ከዛፉ ወርዶ ደብተሩን ገለጠ እና ልክ ተማሪውን እንደ ሚያደርገው ለማድረግ እስክርቢቶውን አንስቶ አጨማለቀው፡፡ በነጋታው ተማሪው ደብተሩን ሲያየው ተበላሽቶ ነበር፡፡ ከዚያም ማን ነው እንዲህ

ያደረገው ብሎ አሰበ እና ዛፉ ላይ ሂዶ አጥንቶ እንደጨረሰ ደብተሩን አስቀምጦ ገለል ብሎ ተደብቆ መከታተል ጀመረ፡፡ ከዚያም ብዙም ሳይቆይ ጦጣ ከዛፍ ወርዶ ደብተሩ ላይ ሲፅፍ አየ፡፡ ከዚያም ሰዎቹን አማከረ እና አንጠረኛ ዘንድ ሂድ አሉት፡፡ አኝጠረኛው ደግሞ በጣም ሹል የሆነ ካራ ሰጠው እና አጥንቶ እንደጨረሰ ካራውን አንገቱ ላይ እንዲያንቀሳቅስ ነገረው፡፡ ከዚያም ጦጣውን እንደዛ አደርገላሁኝ ሲል አንገቱን አርዶ እንደሚገድል ነገረው፡፡ ተማሪው በዚህ ምክር ተደስቶ ሄደ እና ልክ ሁሉም ቀን እንደሚያደርገው ካጠና በኃላ ካራውን ወደ አንገቱ አስጠግቶ እንደማረድ አንቀሳቅሶ ደብተሩ ላይ አስቀምጦት ተንቀሳቀሰ፡፡ ይህንን ሲከታተል የነበረ ጦጣም እንደዛ አደርጋለሁኝ ብሎ አንገቱን አርዶ ሞተ ይባላል፡፡

(መ.ር አሸብር ጃምቦ፣ 25/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ ሁለት

ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ፣ ጅብ እና ቀበሮ አብረው ለአደን ሄዱ፡፡ ከዚያም አጋዘን አግኝተው አረዱዋት እና ተካፍለን እንብላ አሉ፡፡ ከዚያም ታድያ ማን ያክፍል ሲሉ አንበሳ ችግር የለም ጅብ አካፍለን፣ ሥጋውን ሶስት ቦታ ላይ ክፈለው ብሎ አዘዘው፡፡ ከዚያም ጅብ እጅግ ተደሰተ እና ማካፈል ጀመረ፡፡ ታድያ ሲያካፍል የሚበዛውን ሥጋ ፊት ለፊቱ ቆለለው፡፡ ከዚያም ይህ ለኔ፤ ይህ ላንተ ይህ ደግሞ ያንተ ብሎ አካፈላቸው፡፡ ከዚያም የሚበዛውን ሥጋ ለራሱ እንዳደረገው አዩ እና አንበሳ ዘሎ ጅብን መንጋጋው ላይ ሲይዘው የጅብ አይኖች ነጥረው ወጡ እንዲሁም ወድያው ሞተ፡፡ ከዚያ በኃላ አንበሳ ቀበሮን ሥጋውን አካፍል አለው፡፡ ቀበሮም አንበሳን በጣም ስለፈራው እሺ ብሎ የጅብን ዕጣ እንዳደርሰው እየሰጋ የሚበዛውን ለአንበሳ አድርጎ አካፈለ፡፡ ከዚያም ይኸው "እያ አንበሳ ይህ ላንተ ነው ይህ ደግሞ ለኔ" አለው፡፡ ከዚያም አንበሳ በጣም ገርሞት "እንዴት አድርገህ እንደዚህ ልታካፍል ቻልክ፣ ማን አስተማረህ" ብሎ ጠየቀው፡፡ ቀበሮ ደግሞ "ከእነዚያ የጅብ ዓይኖች ነው የተማርኩት፣ እነሱ ናቸው ያስተማሩኝ" አለው፡፡ ከዚያ በኃላ ሥጋውን በልተው አብረው ሌላ አጋዘን ፍለጋ ሄዱ ይባላል፡፡

(አቶ ፀጋይ ገ.ማርያም፣ 25/06/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ ሶስት

የኩናማ ብሄረሰብ ከሚኖሩባቸው ቦታዎች አንዱ ሽምቢሊና ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ ሰፈር አመሰራረቱ እንዴት ነው? ስያሜውስ እንዴት ነው ያገኘው? የኩናማ ብሄረሰብ አድርጎ

ጠላቶቹን ሽሽት በአራት ቡድን ተከፋፍሎ ነው ከአክሱም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በሽረ አድርጎ ወደዚህ አከባቢ የመጣው ይባላል፡፡ አድያቦ እንደደረሰ ከአራቱ ቡድኖች በሽዋሊ የተባለ ጅግና መሪ የሚመራውን አንዱ ክንፍ ወደዚህ ቦታ መጣ ይባላል፡፡ ይህ ቦታ በዚያን ጊዜ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነበር ይባላል፡፡ በዛፎቹ ስር ደግሞ በኃይለኛው የሚናደፉ በጣም ብዙ ትንኞች ነበሩ ይባላል፡፡ ከዚያም በትንኞቹ የተማረሩት እና በብዛታቸው የተገረሙ ሰዎች "አሽምቢሊና" ወደ አማርኛ ሲመለስ "ውይ ይህስ የትንኝ አገር ነው" አሉ ይባላል፡፡ በዚህም ነው የቦታው መጠርያ "ሽምቢሊና" የተባለው ይባላል፡፡

(አቶ ሳህለ ገራሪ፣ የካቲት፣ 27/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ አራት

በድሮ ጊዜ የኩናማ ብሄረሰብ ሴቶች እቤት ውስጥ ብቻ ነበር የሚውሉት ይባላል፡፡ እቤት ውስጥ ምግብ አብስለው ከማቅረብ ውጪ በረሽ ወጥተው የእርሻ ስራም ሆነ ውኃ በማምጣት አይሳተፉም ነበር ይባላል፡፡ በዚህ የተነሳም አብዛኛውን አድካሚ ስራ ለወንዶች የተተወ ነበር፡፡ ሴቶች በረሽ ወጥተው እንዲያግዙ ቢጠየቁም አይሆንም በማለት አንሰራም አሉ፡፡ ከዚያ በኃላ ወንዶች ተሰብስበው ተመከካሩ እና አንድ ብልሐት ፈጠሩ፡፡ አንድም ወንድ ሳይቀር ተሰባስበው ጫካ ሄዱ፡፡ ሩቅ ጫካ ሂደው አድነው እየበሉ ወደ መንደራቸው ሳይመለሱ እዛው ሰፈሩ፡፡ በዚህም የኩናማ ሴቶች ተሰብስበው "ባሎቻችን የት ገቡ?" ብለው ቢጠይቁ የሚነግራቸው አጡ፡፡

ከወራት በኃላ ወንዶች ተመካከሩ እና ከማኸከላቸው አንድ ወንድ መርጠው "ሂድ እና ምን እየተደረገ እንዳለ፣ ሴቶቹ ምን እያሉ እንደሆነ አውቀህ ና" ብለው ላኩ፡፡ ከዚያ በኃላ ሰውየው ቀስ ብሎ ሽልኮ ሰፈር ሲደርስ መምጣቱን የተመለከቱ ሴቶች ከበው በጥያቄ አዋከቡት፡፡ የወንድ ጠረን ናፍቆዋቸው ስለነበርም እኔ ነኝ የምነካው፣ እኔ ነኝ የምነካው በማለት ተጣደፉ፡፡ ከዚያ ሰውየው ሲጨንቀው ካንድ ትልቅ ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ ሴቶቹ ደግሞ ከስር ሆነው "ሌሎቹ የት ነው የገቡት? ለምንስ ከኛ ተነጥለው መኖር መረጡ?" ብለው ጠየቁት፡፡ እሱም ሁሉንም ስራዎች ለወንዶች ብቻ የተተዉ በመሆናቸው በስራ ጫና ምክንያት ተማርረው እንደጠፉ፣ ሴቶች የማይሰሩ ከሆነ ደግሞ ጭራሽኑ ተመልሰው እንደማይመጡ ነገራቸው፡፡

ከዚያ ሴቶቹ ተመካከሩ እና "ከእንግዲህ በኃላ ማንኛውንም የቤትም ሆነ የደጅ ስራ እራሳችን እንሰራዋለን፣ ውኃ ማምጣትም ሆነ እንጨት ለቀማ፣ እህል ወደ ገበያ ተሸክሞ

መውሰድ ሆነ ሽምቶ ማምጣት፣ ማንኛውንም የእርሻ ስራ እራሳችን እንሰራዋለን፤ ስለዚህ እባካቹህ ተመለሱ ብለህ ለምንልን" አሉት፡፤ ከዚያም ወደ አገራቸው ገቡ፡፡ አገር እንደደረሱም ሴቶች ቃላቸውን የማያከብሩ ከሆነ ተመልሰው እንደሚጠፉ ተናገሩ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ወንዶቹ እንዳይጠፉባቸው በመስጋት ማንኛውንም ስራ እየሰሩ ወንዶችን እየቀለቡ መኖር ጀመሩ ይባላል፡፡ በዚህም ነው የኩናማ ወንዶች ቁጭ ብለው ሲውሉ ሴቶች ግን ሥራ የሚበዛባቸው ይባላል፡፡

(አቶ ግደይ ቱርኳ፣ የካቲት፣ 21/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ አምስት

በድሮ ዘመን የኩናማ ብሔረሰብ ከሽረ ወደ አዲያቦ ሲመጣ አራት መሪዎች ነበሩት ይባላል፡፡ ህዝቡ በአራት መሪዎች ተመርቶ በአራት ቡድን ተከፋፍሎ ነበር የተጓዘው ይባላል፡፡ መሪዎቹም ሺዋሊ፣ ጣልያን፣ ካሳ እና ሹሊ ይባሉ ነበር፡፡ እነዚህ መሪዎች ህዝቡን ተከፋፍለው ሽዋሊ ወደ ሽምቢሊና፣ ጣልያን ወደ አደሚቲ፣ ካሳ ወደ ሽራሮ፣ ሹሊ ደግሞ ወደ መንጠብጠብ ሄዱ፡፡ በዚያን ጊዜ ጣልያን የሚመራው ህዝብ በቁጥር ትንሽ ነበር ይባላል፡፡ ከዚያም ቀስ በቀስ እየጨመረ፣ ጎጆዎች እየተሰሩ እና መንደሩ እየተስፋፋ ሄደ፡፡ ይህንን የህዝብ መብዛት እና የጎጆዎችን መበራከትን የተመለከተ አንድ ሰው በኩናምኛ "አደሚታ ካሻተ" ወደ አማርኛ ሲመለስ "አንተየ እቺ አገርማ ቁብ ፍየል ሆና የለ እንዴ" አለ ይባላል፡፡ ከዚያ በኃላ አገሩ አደሚቲ በመባል ይጠራ ጀመር ይባላል፡፡

(አቶ ሃይለ ወለላ የካቲት፣ 26/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ ስድስት

የአክሱም ንጉስ የነበረ ንጉስ ባዜን ከሞተ በኃላ የኩናማ ብሂረሰብ ያስተዳድር የነበረ መሪ "ሽረ" ይባላል፡፡ በንጉስ ባዜን ምክንያት የብሂረሰቡ ሀይል ተዳክሞ ከአክሱም ተገፍቶ እንዲወጣ ተገደ.ል ይባላል፡፡ የኩናማ ህዝብ እየተዋጋ እና እየተከላከለ ከአክሱም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ አፈግፍጎ በአሁኑ ሰዓት "ሽረ" በመባል ወደ ሚታወቀው ቦታ መጥቶ ይኖር ነበር፡፡ ሽረ ላይ እየኖረ ሳለ ደግሞ አሁንም የገጠመውን ጦርነት መቋቋም ተሳነው እና ሽረን ለቆ ወጣ፡፡ በዚያ ጊዜ ሽረ የተባለው የኩናማ መሪ የነበረውን ስለ ሞተ "አቦ" የሚባል ተተኪ መሪ ህዝቡን እየመራ በአሁኑ ጊዜ ላዕላይ አድያቦ እና ታሕታይ አድያቦ ተብሎ ወደ ሚጠራ ቦታ አመጣው፡፡ እዚያውም መኖር

ጀመረ፡፡ ከዚ በኃላ ቦታው "ዓዲ- አቦ" ወይም የአቦ አገር ተባለ፡፡ ከዚያም ነው "አድያቦ" የሚል ስያሜ የመጣው ይባላል፡፡ (አቶ ሃይለ ወለላ የካቲት፣ 26/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ ሰባት

በድሮ ጊዜ በኩናማ ባህል መሠረት ሴቶች ወደ ወንዶች ቤት (ጎጆ) በመሄድ ወንድን ይጠይቁ ነበር ይባላል፡፡ አንዲት ኮረዳ ወይም ሴት በፍቅር የመረጠችውን ወንድ ለማግኘት በጨለማ ጎጆው ድረስ በመሄድ ታገኘዋለች እንጂ ወንዱ ወደ ሴቷ ጎጆ መሄድ አይፈቀድለትም ነበር ይባላል፡፡ በዚህ ስርዓት ሲኖሩ ሲኖሩ አንድ ቀን አንዲት ሴት ቀኑ መሽቶ ሰው ከተኛ በኃላ ከጎጆዋ ወጥታ ወደ የፍቅር ጓደኛዋ ለመሄድ ጉዞ ጀመረች፡፡ የምትሄድበት ቦታ ራቅ ያለ ነበር እና መንገድ ላይ ጅብ አገኛት፡፡ ሴት በመሆኗ ከጅብ ጋር ታግላ ማሸነፍ ስላልቻለች ጅቡ አሸንፎ በልቷት አደረ፡፡ በነጋታው ህዝቡ ተሰብስቦ ከጅብ የቀረውን አካሏ ቀበረ እና ምን እናድርግ? ብሎ መከረ፡፡ ከዚያም ለምን ይህን ባህል አንቀይረውም? ሴቶች ከጅብም ሆነ ከሌላ አራዊት ገጥመው ማሸነፍ ስለማችሉ ለምን ወንዶች ሴቶች ጋር አይሄዱም? ብለው ተወያዩ፡፡ በዚህም ሁሉንም ሰው ተስማምቶበት ሴቶች ከጎጆአቸው ሆነው እንዲጠባበቁ እና እንዲተኙ፣ ወንዶች ደግሞ እየሄዱ እንዲጎበኙዋቸው ተወሰነ፡፡ ከዚያ በኃላም ባህሉ ተቀይሮ ወንዶች ወደ ሚፈልጉዋት ሴት እንዲ ሄዱ ሆነ ይባላል፡፡

(አቶ ሃይለ ወለላ የካቲት፣ 26/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባ ስምንት

በአንድ አገር የሚኖሩ ሁለት ሌቦች ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ በረሃ ሂደው የሚሰረቅ ነገር ሲጠባበቁ አንድ ገበሬ በሬዎቹን ጠምዶ ሲያርስ ያዩና ሊሰርቁት ተመካከሩ፡፡ ከዚያም አንዱ "እኔ ወደ መንደር ሂጄ እሪ እላለሁኝ፤ ከዚያ እሱ እርዳታ ሊሰጥ አስቦ ሲመጣ አንተ አንዱን በሬ ፈትተህ ትወስደዋለህ፣ ከዚያ ተመልሶ ሲመጣ አንዱን በሬው አለመኖሩን አይቶ እሱን ፍለጋ ሲሄድ እኔ ደግሞ አንዱን እወስደዋለሁኝ" አለው፡፡ ከዚያም አንዱ ወደ መንደር አካባቢ ሂዶ እሪሪሪ አለ፡፡ ገበሬውም ሊረዳ ሄደና በሬዎቹን ሰርቀው ወሰዱዋቸው፡፡ ከዚያ ወደ በረሃ ወስደው አረዱዋቸው፡፡ ማታ በጭለማ ሥጋውን ወደ ቤታቸው ለመውሰድ አሰቡ፡፡ አንዱ "አንተ ወደ ቤት ሂድና ሥጋ የምንጭነው ገመል ይዘህ ና" አለው፡፡

አንዱ ገመል ለማምጣት ወደ ቤት ሲሄድ ሥጋውን ሲጠብቅ የነበረ ሥጋውን ለብቻው መውሰድ አስቦ አንድ ተንኮል ጠነሰሰ፡፡ ከዚያም ጓደኛው ግመሉን ይዞ ሲመለስ አጠገቡ እንደደረሰ የተገፈፈውን የበሬው ቆዳ ወጥሮ በዱላ እየደበደበ “እሪሪ አረ እባካቹህ ቀስ አድርጉኝ ብቻዬ አይደለሁም የሰረኩት ጓደኛየም አለ፣ ግመል ሊያመጣ ሂዶ ነው እንጂ” ይላል፡፡ ከዚያም ለካ እየደበደቡት ነው ብሎ ለማምለጥ ሸሸ፡፡ ጓደኛው መሸሹን ያረጋገጠ ሌባ ሥጋውን ወደ ቤቱ ማመላለስ ጀመረ፡፡ ከዚያም እቤት እንደደረሰ ሚስቱን በሎሆሳስ ጠርቶ “ተቀበዪኝ ይላታል፡፡ እንዳይደበደብ ሸሽቶ የሄደው ሌባ ወደ ቤቱ ሳይሆን ወደ ጓደኛው ቤት ሂዶ ነበር የተደበቀው፡፡ ከዚያም አንዱ ስጋውን እያመጣ ሚስቴ እየተቀበለችኝ ነው ብሎ ሲሰጣት የሚቀበለው ጓደኛው ነበር፡፡ ከዚያም የሁለቱም በሬዎች ሥጋ ለሁለት አካፍሎ ግማሹን ወደ ቤቱ ነበር የወሰደው፡፡ ከዚያ ማጓጓዙን ጨርሶ  ቤት ሲገባ ሥጋውን ሲያየው አነሰበት እና ሚስቱን “አንቺ ያ ሁላ ሥጋ የት አለ?” ይላታል፡፡ ከዚያም ጓደኛው ከተደበቀበት ወጥቶ ለሁለት ነበር የሰረቅነው ስለዚህ ለሁለት አካፈልኩት” አለው፡፡ ያ ለብቻው መብላት አስቦ የነበረ ሌባ በመደንገጥ “እውነትም ለሁለት ነበር የሰረቅነው፣ ለሁለትም መካፈል ነበረብን፤ ታድያ ልሰርቅህ ነበር ያሰብኩት፡፡ አንተ ደግሞ አልፈህኝ ነበር እና ሰረቅከኝ፤ ስለዚህ አንበላለጥም እና ያደረከው ትክክል ነው” ብለው ተለያዩ ይባላል፡፡

(አቶ ሃይለ ወለላ የካቲት፣ 26/2009 ዓ.ም)

አባሪ-2 በኩናምኛ ቋንቋ የተሰበሰቡ ተረቶች

## ተረት አንድ

ሳላንጋ ውየላላ ኮሺ ጋሲ ዳታ ኣይማ ኪነማ ቡቢያ ካፋሙ ኪላኪኪ ጋኪማላ ኤታ ኣካማሲ ኒሻሊማ ሸሲ ኤታሲ ኢኪዳኖ ዋ ሱኖ ዋይና ዋ ኮኮኘያየኪ ኤላ ፊዳ ካስዲታ ገናሎናስኖ።ኤታ ሳላንጋ ኣውሮሲ ካይሎኪ ፋኪሽኖ ኢኒኪ ኢዊጋሴ ኢሻዲታ ሲፋንጋ ኢወኪ ጋሱመ ኣቦራማ ውያና ኣኮደካ ኮኪ ኢባበራኖ ኢሸኖ ኢኪ ኢጋሱማላ ኤቶማ ላ ጎኪ ፋሲ ኮዲየታ ኣና ካዋ ኪኪ ሱማላ ኮዲያየ ኤቶሲ ኣይ ኤሚኖ ኦላ ፎዳ ፎኖማላ ኤቶማ ዋሴኬ ኡኩና ጋቡሩ ጋቡሩማ ዮኪ ኮኮኘየ ፋዳ ካሰዲታ ናሎ ናኛሱኖ ኡማ ጋፋናስኪ ኦማሙ ዴርናኮም አከስማለሙ ኮዲያየ ኣታሙ ኪኪ ኣሶሱያ ገዳ ካኘዳ ኣኮንኪ ኣይኖ ኢደኪ ኢማላ ሳላንጋ ኣሸየንዳሲኢኪ ፋዳ ኣሰዱታ ናሎናኘ ሱኖ ኣለኘ ሱኖ ጎሱማ ካፋ ኮሻኖ ባሻጋ ኪሳኖ ሳላንጎማ ኣሚንዳ ኣሚቺ ቲያኮ ባዳታ ጎሊኘሲ ኤቶሲ ዳርኪና ባደለ ኣይ ኮሼኖ ጋሚኪ ሚሻድም ሱማላ ኤቶማ ባዳ ማላ ኪሻማ ኘዳይማ ኢኬዳሙ ናወዳ ናማረሴ ለላኢጋ ኦማኪሙ ኤታሲ ኣባና ኢታኖ ኘኮናኬዳኮ ኤ ኬዳሙ ኖ ሻም ሱማለ ቢቢዷ ኸካዳ ኮሙ ናኪ ሱኖ ስላንጋ ሽካሲ ኣጓኪኖ ኤቶማ ስላንዳሲኢቢኪ ባዳታና ገራሲ ሹታታና ገራሲ ኪኪ ኢዳሱኖ ሳላንጋ ኢኬዳሙ ሳማላ ኤታ ኣባ ኢኬዳሙ ለከናኖሻ ኢዳሲ ቢቢዳማኢሚቼኖ ሳላንጋ ባደኪሙ ሹታታ ጋሱማ ኤቶማ ሙቱገለ ሲ ኬላ ሱኖ ዳላንጎማ ዳባሲ ካላሱማላ ኣኒያሲበሃራ ውዳሲ ኪኪ ዱሱማላ ኣንጓ ኪሻ ሱባ ኡዳሲ ጎሊ ፎጌ ሳጊኮ ሺማላ ስላንጋ ዳጊዮሲኪያቲኖ አበሲ ኣሺረ በራይቲ ሲኖ ስላንጋ፡፡ ኣንጉና ኣባዳ ባደሲ ኖማና ኢሺኬር በራይቲ ናታኒ ኤናኪኬዳሙ ኒካሚሺኖሻ ኣፎንጋዳ ሳ ጊኦማየኪሙ ኤላካሶሙ ናኮቱናቲኪ ናስስኖ ኣንጓኪሻ ስላንጋ ኣውራ ሲ ኮቢኪ ፋጋ ፋሼላ ኪሸኖ ኮቲኪ ሺታና ባይና ኬጂኪ ኣላቤ ሱኖ ኤላኮማ ኢኮ ስማላ ስላንጎማ ኣንጓ ኪሻሲ ዋሲ ኪዊኪ ኤጃ ኪጋሴ ኦማኪማ ኣንጓ ኣይላ ጋዳሙ ከኖ ስላንጋተ ሚላኖ ስላንጋሲ ኢሚቦኖጋ ኣፎጋ ማይዳማ ኢካኪ ኒኮኖ ስማላ ኮየታኒኪሴና ናኮፎኪ ካናኖ ኣስኬማ ኤናና ያኪ ሴና ኮፋኪ ኣውዳሙ ኤስ ኣከሱኖ ኣንጓ ሳላንጋ ኣውራ ኮቦኪ ኢኪ ሴና ኮታኪ ኒኘኮሺም ኮኤ አለኪ ሻማላሙ ኣውሱኖ ገዲያላ ሴና ኪናቲም ኣንጓዮ ኬኪ ሴናላ ቶማ ኬሲከቱም ኡኩነላ ቶማ ኢኘመሲኖ ኢቢታኪ ጋሲ ኢማሌ ሳላንጋተ ሚሌም ስላንጋሲ ኣኪዳኪ ኤና ኣባ ከቤኖ ኒኖ ቶማ ኪቱ ኬማ አዋሙ ናቸናኘሴ ኣንጓ ስላንገሲ ስላንጋ ካይሊቲዮካ ኤኬና ኡዳቴ ተማተ ኪከኪ ስዳኪ ኣቾኝ ሱኖ ተማሴሲ ቾቻታ ሱማላ ስላንጋ ኣጀሙ ፋፋላ ኣጉስ ኬየላ ኢኬዳቲየ ኣየኖ ኣንጓ ኡኩኖ ቾቻኑቤና ኢያፋሱኘኖ ኮኤኑቤ ስማሌ ኣንጎማ ስላንጋ ኣውሮማሲ ማሊሙ ኪፋኪ ኮኤ ፋኬ ኣያፋማኪ ኣይናኘ

ናቹማ ማይዳሲ ኣንጎማ ቶማላ ኣያኒያ ኡዋ ኖ ስላንጋ ኢቾኪ ኤሜኬሜ ስላንጎ ሚያነ ስሴ፡፡

(ብርሃነ ኬኞ፣ 15/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሁለት

ኬ ባረ ዳርካተ ኣቢሻተ ዳማ ኣይኒያመ ጎን ሚናኬ፡፡ ኤላሙ ጎንኪ ወይንዬን ሚናማላ ዳርካ ካቲኬ፡፡ ኣመላላ ዳሪኮማ ኣቢሺያሲ ኢኪዳኪ ኣናኘ ኢታ ካኪ ኢኪዳኪ ሺግደ ሊላታ ኣውሳተ ኪከሲ ኢሳመኬ፡፡ ኣቢሻማ ዳርኪያ ኢሳመማ ዳታየ ኪኮናሲ ኤቲየ ኢታ ኪኬ፡፡ ኤቲያና ኢካ ኣቢሻሲ ዋ ኮኬኪ ኦቢን ኮኪ ኢታ ኮዋማለሙና ኮሽደያ ኮማልማ ባደሊሙ ካዊያ አውሲያ ከሰኖ ኢንኪ ኡቡኬ ፡፡ ሱኳ ካባራ ኮኪ ኦማልማ ባዳለሙ ኣይታ ኪማ ኪሳሳኬ፡፡ ዳርካኟ ሺጊዳ ሊላ ካኮ ሲ ኣሳሚኖ ናውከሲ ኤትየሲ ኢሳሳከ፡፡ ኤትየ አቡረ ኮሳማ ሳባታሲ ሺጊዳ ሊለተ ኣውሳተ ኮሶ ኮሳመከ፡፡ ኢካ ኣብሻ ኦሶማ ዳታየ ኢካኪ ቢሽያለሙ ጋን ኪማ ቢሺየማ አምባ ካታራሲ ዳገለሎሙ ፋፋ ሃሙሱኖ ኢንቲኬ፡፡ ኣ ዴታማ ኣይኖሲ ፋካራላ ኪዋከ፡፡ ወይናሙ ቢሻኟ ፈላባዲ ኪበ ዳከኖ ሊለማ ናፉርያ ኪዌናማሲ ኢኮማ ሺጊደ ሊሎማ ፋፎማ ኩፋኮላኪ ዋ ኣውሶኮማ ኪኪ ጋን ኪማ ኣውሰማ ጋንካለ ካንኪ ቴፋሲ ቶኮሲ ኡሊያላ ኪተማላ ካንካላሲ ኣሚኖ ኡኳ ኑጂኪ ኣበላኖ ሲ ካንከሎሲ ላጎሲ ከለ ከዲከ ኢጀረሙ ጋደሰ፡፡ ካንካለ ኣ ኩደኒኖ ዊን ጎሱማላ ኣኪሺኪ ፈደሙ ጋደደሰ፡፡ ኮንካላ ዊን ጎሰ፡፡ ፉዳን ጋደ ናመደሲ ኮካሸሙ፡፡ ካንከለ ኣታውና ዊን ጎን ኪኪማላ ኡጓሙ ፋሲ ኢያ ኩቡኪ ኣውሰማና ኩችክ ኮላኪ ኢዊኪ ኢታ ኣውቢያ ቲጊን ኪኬ፡፡

(ወ.ሮ ሐረጉ ንጉሰ፣ 16/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሶስት

ኬ ባረ ዳርካተ ኣቢሻተ ዳማ ኣይኒያመ ጎን ሚናኬ፡፡ ኤላሙ ጎንኪ ወይንዬን ሚናማላ ዳርካ ካቲኬ፡፡ ኣመላላ ዳሪኮማ ኣቢሺያሲ ኢኪዳኪ ኣናኘ ኢታ ካኪ ኢኪዳኪ ሺግደ ሊላታ ኣውሳተ ኪከሲ ኢሳመኬ፡፡ ኣቢሻማ ዳርኪያ ኢሳመማ ዳታየ ኪኮናሲ ኤቲየ ኢታ ኪኬ፡፡ ኤቲያና ኢካ ኣቢሻሲ ዋ ኮኬኪ ኦቢን ኮኪ ኢታ ኮዋማለሙና ኮሽደያ ኮማልማ ባደሊሙ ካዊያ አውሲያ ከሰኖ ኢንኪ ኡቡኬ ፡፡ ሱኳ ካባራ ኮኪ ኦማልማ ባዳለሙ ኣይታ ኪማ ኪሳሳኬ፡፡ ዳርካኟ ሺጊዳ ሊላ ካኮ ሲ ኣሳሚኖ ናውከሲ ኤትየሲ ኢሳሳከ፡፡ ኤትየ አቡረ ኮሳማ ሳባታሲ ሺጊዳ ሊለተ ኣውሳተ ኮሶ ኮሳመከ፡፡ ኢካ ኣብሻ ኦሶማ ዳታየ ኢካኪ ቢሽያለሙ ጋን ኪማ ቢሺየማ አምባ ካታራሲ ዳገለሎሙ ፋፋ ሃሙሱኖ ኢንቲኬ፡፡ ኣ ዴታማ ኣይኖሲ ፋካራላ ኪዋከ፡፡ ወይናሙ ቢሻኟ ፈላባዲ ኪበ ዳከኖ

ሊለማ ናፉርያ ኪዌናማሲ ኢኮማ ሺጊደ ሊሎማ ፋፎማ ኩፋኮላኪ ዋ ኣውሶኮማ ኪኪ ጋን ኪማ ኣውሰማ ጋንካለ ካንኪ ቴፋሲ ቶኮሲ ኡሊያላ ኪተማላ ካንካላሲ ኣሚኖ ኡኳ ኑጂኪ ኣበላኖ ሲ ካንከሎሲ ላጎሲ ከለ ከዲከ ኢጀረሙ ጋደሰ፡፡ ካንካለ ኣ ኩደኒኖ ዊን ጎሱማላ ኣኪሺኪ ፊደሙ ጋደደሰ፡፡ ኮንካላ ዊን ጎሰ፡፡ ፉዳን ጋደ ናመደሲ ኮካሸሙ፡፡ ካንከለ ኣታውና ዊን ጎን ኪኪማላ ኡጓሙ ፋሲ ኢያ ኩቡኪ ኣውሰማና ኩችክ ኮላኪ ኢዊኪ ኢታ ኣውቢያ ቲጊን ኪኬ፡፡

(ወ.ሮ ሐረጉ ንጉሰ፣ 16/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አራት

ሱከላላ ኣቡ ጉጂ ዳ ደዳ ሳሉጓ ጎን ኪናኬ፡፡ ደዶማ ሳና ኢተከመ፡፡ ከ ሳና ጋሙያ ኡሊያ ኩፊኪ ፎጊያ ሻኪን ኪኪ ኣኒያ ሺላሲ ሱጓ ጋሱና፡፡ ደደነ ኣሰና ኢሻመ ዲታ ዳሪኬ ኣንዳ ኮመና፡፡ ኣማለላ ኬላ ዳርኪያተ ሴና ኮማ ኮኮሺማላ ኣቡ ጉጂ ፎጊየ ኮሺጊዳኪ ኣሚሚየ ኪሚን ኪካኪ ዋ ሴና ማመ ኦኪሽማዋጎማሙ ኪኪ ሻስኬ፡፡ ኢና ደደና ኮንቲማ ሰና ማማየ ቡቢየ ሊንኪ ኦንቲማ ኪሻ ዲታ ዋ ዱማ ኣየኒያዳ ኢታ ኣኒዮማ ኣንዳ ኪታርቢኪ ኣሻክ ኢሞጎሱናታ ኮማ ዋሙ ሊሰ፡፡ ኣከን ሊን ጎሱማላ ኢቲያ ኣቢሾማ ዳርኪዮዋ ኪታቤኪ፡፡ ኢደ ዳርክዮማ ኣቡ ጉጇላ ኮማ ኪናማና ኣንዳ ኪመማና ኪተላለከ፡፡ ወይናሙ ኮዋ ዳሬኬናሲ ኢኬዳሙ ናሚንኪ ደዶማ ኮማ ናታላለሲ ላዋላ ኩዋኬ፡፡ ወይናሙ ላወላ ለዋሰ፡፡ ላዖማ ኮሻ ጋናኬ ናኪ ናበኪ ኣዋዳ ናይኪ ናማማጂፓማሲ ላዋሱማለሙ ዳርኪያሲ ኢኪዳኪ ኣባ ኣዳ ናይኪ ኮሻ ናኮሻኪ ሰላሲ ናደ ናውፓማ ቡሻ ኪሊካሰሙ ጋናሲ ኮኬላኖ ዳርካ ቡሻ ኪሊኪሶኖ ኮሺያ ጋሱመንደሲ ላይን ኩታኪ ሱዳላ ኣማመ ኢጋሳሲ ደደንዳ ኣቡ ጉጂ ኮውደንደ ኮወኪ ኣሚማያና ኡኑ ሻኒ ኪሚንኪኪ ኢኪ ዳርኪዮሲ ቶሚን ኪበኬ፡፡ ዳርካ ፌሲ ናኖ..ናኖ..ናኖ ሲ ኮኬላማላ ኣቢሺዮማ ኣባ ኣባ ኣቡ ጉጂ ደያሲ ኢባይከ፡፡ ዳርኮማ ሰደ ኪናኮሺማኮሻኖ ኮሰዳ ወይከሲ ኡዋ ሱኖ አቢሻ ኡዋ ኪኖ ጎማላ ዳረካ ቢየ ኪሶማ ባዳለሙ ሳራ ማይደላ ኪተ ሱኖ ኣቢሻ ኢተኖ ካሳካፋ ታርሻ(ሽዋ) ኦርኪማላ ኬሳ ኩፋኪ ኞማ ሹዋላ ኩቱሱኖ ሙቱኖ ታረፎማ ኢኮሙ ካፓንኪ ሚጋማ ባደለሙ ኤላሲ ኒኚንኪ ካረማላ አቢሻ ዶርቡዳ ፊሲ ኢዊጋሲ ላኪን ኦዶማ ከዋ ቢሻታ ኪኮ ኪሶናሲ ኪማልኪ ጋሰ፡፡ ወይናሙ ዳርካ አቡ ጉጀተ ካርማኬሲ ወጀቢያ ኮካላ ኦሮባ ካዋ ኩቱ ኪኪ ሙዳማ ዋጎታ ኪማ አቢሺያ ላካን ኮሺኖ ዬኬ፡፡ ዬማላ ኢባታኪ አቢሺያሲ ሳሪፓንዳ ማይዶማ ኢባል ኪሻ ኩታከ ኣሳንዲ ሲ ኢሳሰኬ፡፡ ኢሻ ዲታ ኣቢሻ ታጋመላና ኮሺሜ፡፡ ኢካታ ኪባል ኪሻበሻ ኣይናፓ ሹለ ፋናኪ ሾናፓማ ኪና ጂጋ ኤማ ዋይዳሲ ኢሳሳኬ፡፡ ዳርካ ማይዳማሲ ኪና ጂርጋ ኤማ

ወይሱኖ ፎቶጎሲ ሺረሱማ አቢሻ ኤማ ኩሮሲ ጎሲ ኣከሴ ኣ… ኣይኖ ኛ ሹዋ ካላየ ካሳ ታሻ ኦኮሚላ ኑበ ሲ ሹላ ፋሲ ዳርኪያሲ ኢቢንኬሰ፡፡

(ወ.ሮ ለታይ ኬኞ፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አምስት

ሱከላላ ኦሳሚያ ኪናታ ደዳ ኮሺ ኪናኬ፡፡ ኡየላላ ሱኩማ ኬ ቡቢየ ኦሳሚያዳ ኮሳኖ ደዳሎማ ኦሳሚታ ኣዳ ኮሊኪ ኢሮን ኮከሺማላ ቢያ ኣንዳ ኪያ ኪኖላኬ፡፡ ቢያ ኢያማላ ቢያ ዋ ጋንሰን ኮኮሺማላ ኣዲካ ቱኩራ ጉቡጉባ ኣዲካ ሾንኬ፡፡ ወይናሙ ኬላ ኢሲ ቢያ ጎሱሙ ካኖ ኪ ጎማቶንኬ፡፡ ኣለ ኬላሲ ኮኪዳኪ ኣዲካላ ኢዳማ ኣያ ኣይሻ ኡደናኖ ኢናኒሰ፡፡ ኤሎሲ ኮኬላማ ኣይና ኣውራ ኩዳናኖ ኢናኒሰ፡፡ ኦኮዶካሙ ኦሳሚናየ ቡቢየ ኦኩኬ፡፡ ኦሚን ኮኮሲ ዋ ሚሳማ ኪናቶሲ ኮኬላማ ካና ኪሾና ኢናመ ኪሻማ ሳባታሲ ማይዳ ኣባ ኢናናማ ሲ ኢሲ ጎን ኪሾኖ ኦኖኬ፡፡ ኦኖ ጎማላ ሚለበ ሱማ ማለመንኬ፡፡ ኢደ ጎን ኪሶኪ ሙቡበ ሱማ ማቡራመ ዳሙ ኮሚን ኮኮሲ ኮማልዳላ ኦቡኪ ኣዲኮላ ኮዊኪ ኦሊጋንኬ፡፡ ደዶማ ኦኬሺማ ኪፋኪ ሙቡበ ሱማ ዊን ኮሳኬ ኢኪሺኪ ሙቡበ ሱማ ዊን ኮሳኬ፡፡ ወይናሙ ኦዊኪ ኦሊጋማ ኣበረሲ ኢከዳሙ ቲጊሱኒኖ ዊን ጎን ኮሺማ ኣኒያሲ ዳኪሸላ ቢያ ኢያኖ ጋን ኢሎን ኮሲ ኣዲኮላ ሰላካሲ ኣ ቢያማ ሺዳ ማይዳን ዳኮ ኣይኮሲ ጎን ካሶሙ ናኖሲ ኡዳማላ ደዶማ ኣባ ናኮሰማ ላካዳሙ ጎን ናሶሲ ጎን ኪሾኖ ኢኖከ፡፡ ዳርኪሾማ ቢይያ ኪኖማ ባዳለሙ ኢኪዳኖ ፆ ሱኖ ኢከዳሙ ኣዲካማላ ኢሱማና ኦላ ኮሺማና ኮኬላኖ ዳማኖማ ቡቢያ ኪሳሳማ ባዳለሙ ዳኪሾማ ኮማልዳላ ኢሾዲኪ ኪ ኣ ኣዲካማ ጉቡጉባ ኣዲካኖ ዳማደ ጎን ኮሺያ ፎናማ ፎያ ሰሮሲ ኮቢኒሙ ኢሻታ ኣይኒያ ኤውላናማሲ ኢሳሳኬ፡፡ ላኪን ኢኑ ኢሻያ ሳዊታ ፌፌ ሱናማ ሳዊታ ፌሱያ ኡኑ ኢሻማ ኪታኪ ኮሱኪ ማይዳሙ ኮቢኒሲ ኢሳሳኪ ኢዊ ጋሰ፡፡ ዴዳ ዳርኪሻ ኢሳሳማ ሻኒ ሳዊታ ፌፌ ሱማ ኮሱ ኪሺኖ ጉቡጉባ ኦኪ ሰላካሲ ሰራ ኩተማ ሰራ ባዳሲ ኮቢኖ ኦላ ፋሱኖ ባላ ኬጂ ኩዋኬ፡፡ ጉቡጉባ ኣይናውላ ፋናኖሲ ኢሳኪ ሊሱማ ዳተላና ኮሺመኖ ኢዊኪ ናይያላ ኩዋኬ፡፡ ዴዳ ባ ካንኪ ፌሲ ጋን ኮሺማ ባሃራ ኮላኬ፡፡ ወይናሙ ደዶማ ሱኪያ ጋሱና ሸሱመኖ ኦላ ወይኒፄዳ ኪቢንኬ፡፡ ዋ ኡኑ ኮሺማ ዋጎላ ኤታ ኤላ ባዳላ ሰከዳ ኪሰከዳኪ ደደ ኪሺኪ ጋን ኪቢንኪሾኖ ኦንኬ፡፡ ታማ ዴዶማ ኤታ ኢኬሲሲ ኢኮማ ፓዳዶማ ኤቶማ ኪሻየሲ ኡፋኪ ኢፓና፡፡ ኣከዶካሙ ወይንዮን ኮሺማላ ኤቶማ ዲማ ዲማ ዴደ ፓዳዳ ኪኮፓ ጋሱናላ ኣዋዳ ፌሲ ኡኑ ጋሱና ሰሱማ ሱኮሲ ኣባንጋላሙ ኪያኪ ኢኪዳኪ ኤናኪ ጋሱና፡፡ ኦኮዶካሙ ኪሚን ኮሺማ ዴዶማ ሱኳ ጋሱፓ ሰሲ ኣባን ጋላ ኪሌማ ዴዶማ ኢቲኪ ቴማ ኣ ኤቴማ ሱካፓ ኪኪዳ ጎሰኖ ኣባና ሚነላ ናማሙ

ኣጋሱኟሲ ኪራ ኪገኪ ሸዳሙ ማኪላሲ ኮሊኪ ኤቶማ ሚንደሲና ኪሌኬ፡፡ ኤታ ሞላላ ፈሲ ፈቲቲ ሱማ ዴዳና ኡኑተ ፈቲቲሲ ባሃሮማ ኪከዳማለሙ ኪሮሲ ኢሚንቺ ፋሲ ላጋላ ዱሰ፡፡ ኦማለሙ ኤቶማ ኢዊ ጋሱኖ ዴዶማ ሚንዳሙ ጋን ኮሺማ ሺንጊላ ኦታ ኢለከ፡፡ ዋ ኦቶማ ኦሮባላ ዴዶማ ኒኟተ ኢዋተ ቢሻ ማሚማላ ሚንቲኖ ኣቢሾማ ዳኮሲ ዋ ኦቶማ ታቢላሲ ባያ ጎሰማ ናውዳ ሱማ ዳርኮማ ኣካንዳ ኡሞማ ዩሙ ኢለኟኖ ናወናኟበ አካ ኣሺዲያ ኢባል ኪሻማሲ ናውናኒማ ኢዊሲ ኢዋጋሱማ ኦታን ደያ፡፡ ወይናሙ ዴዳ ሾኪሲ ሾኪሲ ኣዋዳሙ ኢኒኟ ኢታ ኪኪ ያ…ያ..ሱማ ኢኒኟ ያ ሱና ደዳ ናይናመሲ ዊን ኒኺሰ፡፡ ኮኮሻሙ ያ..ያ.. ሱማ ፈሲ ናኖ ሱኖ ኣባ ሱኖ ሚኪዳኪ ኢኬዳሙ ኮማና ኪሳሳኖ ካረንኬ፡፡ ኦማንኪሙ ኢዋተ ኢኒኟተ ጎማቶንኪ ደዳሲ ኢታ ካላ ሙኙማኪ ሱኬሲ ኣላማታ ፌማኬማኪ ኪና መሱኪ ኣይፋ ሙቱኪ ኣጋረ ሙቡቡሬኬ፡፡ ኣጋረና ቡቢየ ኦኮቡቡረኪ ኣይፋ ናና ካዋ ኟዳና ኮቢማለሙ ዴዶሲ ፎጋ ኣሬ ሚወ ሞላኪ ጌጋጂየ ሚሊ ሞላኪ ዳዲያ ሚሺጊዳኪ ኢታንኪ ሞላ ሚኮኖ ደዶማ ኣጋረሲ ሰጋታ ሳላም ቶኮናታ ሳለምሲ ኢሾዲማላ ዋ ኡኑ የተ ኮሊኖ ኦዊ ኮሎማየ ቡቢየ ካቶ ዳላ ኮዋኬ፡፡ አጋረና ማላ ኩቱከ፡፡ ወይናቡ ኣጋረ ቡቢየ ፈንኪ ኤላ ኣይላ፣ ኤላ ናሻ፣ ኤላ ሳንዳ ኦኮዶካሙ ሱኳ ኳ ቡቢያ ሺጊደ ኮኮሶኖ ኣቡራ ኪሻኪ ወይንዬሰ፡፡

(አቶ ክፍላይ አራራይ፣ 13/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስድስት

ኣሚለላላ አዳ ሶሶነ ኦኩቡቸኪ ቢያ ታጋሞንዲከማ ሳማራሙ ካሳኪ አዲካ ካሳንኪ ጎማተንከ፡፡ ታማጋ ኣባ ቢያ ሰናመኖ ኣዲካ ናሳኒሲ ኮዲየ ጎማቶሞንኪ ወይረይሰ፡፡ ዋ ፋውማየ ጎማተላሲ ኮሊኪ ኦዳማ ኮካላ ሳማራሙ ኣዲኬላ ኮሳኬ፡፡ ኦማንኪሙ ታጋሚታ ጋን ኮኖኪ ወይኒዮማላ ታማጋንዳ ናሳኒ ዲኖማ ላይዳሙ ኣዋዳ ኣዋዳ ኪኪ ኩኛ ኪኖና፡፡ ሶሶነ ፋኬላየ ኦሱ ኮሊማላ ታማጋ ሚንዳ ኮንቲና ፡፡ ኣሚለላ ኦኮቡቸኪ ጎማተላ ጎማቶንኬ፡፡ ኣ ታ ማጋማ ኪመ ካኖኪ ጋዲማ ባዳለሙ ላይዳሙ ኮኪ ቢይኟ ኪኖ ጎሰማ ኦሮንዳ ካሳኪ ካቢንኪ ካያ ፋዲንኪ ጎማቶንከ፡፡ ጎማቲዬማሙ ሞርኳ ኤኬና ኣባ ሊናኟሰ ፡፡ ወይናሙ ሞርኳ ኮዲየ ጋማለው ኣዲኮላ ጎንኮሺኖ ታማጋ ኣሺየንደሲ ኣዲኮታ ኮማላ ሞርኳ ኦለ ኮሲ ኢካ ጋኖ ኣታ ናውኛ ናይናኬኖ ሾናከለሲ ቢናታ ሱማ ታማጋ ኢበኪ ኣከሴ "ኣባ ቢየያማንኪ ቢያ ፋሻ ናይናኬ ወይናሙ ኣ ቢየያንዳ ባያማ ናኖኺኖሲ ኡደከ፡፡ ወይናሙ ሞርካ ፋያ ሱኖ ኡኩኖ ኢኬነ ቢየያ ሲ ኮኬላከ፡፡ ታማጋ አይነ ኣ ካንካላማላ ናይናከ ሲ ኡዳማላ ሞርኳ ኪ ኣሶሙ ናኖናንቲ ሲ ኮኬላኬ፡፡ ታማጋ ኪ ማይዳ ቢያኟ ኮኖመ ኪራሙ ናሊሊሙ አኖያ ዲታ ኣዉቢያሙ አኖኒማ ኣዋሙ ናሊሙ

ኢኖኪንቲ ድታ ናሊታ ኪሻየ ናሶኒሰ፡፡ ሞርኳ ላዋን ኮሺኖ ኡኩኖ ኪ ኣሊኪ ኣሶሙ ናኖ ናንቲ ሱኖ ላካ ኪራሙ ባዲ ባዳሙ ኪሊኪ ኣዲኮላ ኢሲ ኢኖኪ ኢዊኪ ኤጂ ኪጋሴ፡፡ ሞርኳ ኮቢሺናሲ ሾሱመኖ ኦሲ ኩታኖ ኮዲየ ኦሎኪ ኣይ ኤሚኖ? ኦይ ኤሊኖ ኪ ኦኬላማላ ሞርኳ ኣ ኤላማ አሊኬሰ፡፡ ኣሚኖኖማ ካይዶሰ፡፡ ወይናሙ ኮዲያየ ኦቢሽኪ ኦኪጋንኬ፡፡ ኦኪሽኪ ኣባርማ ኦሮንዳ ኣቢና ኮዊኪ ጋንኬ፡፡ ታማጋ ኦኪ ኣቢናሲ ሞርኮማ ኪመመንደ ኪራሙ ኪሊኪ ኢዊ ጋሱኖ ኮዲየ አሎኪ ሾማላ ኣቢናና ሞርኬንደ ኤሎማ ኣሊኬሰ፡፡ ኮዲያየ ኣቢኖሲና ኪራንኪ ኦቢሺኪ አሮንዳ ቦባ ኮዶኪ ጋንኬ፡፡ ቦባ ቢያካላ ላይሲ ቱን ኮሺማላ ታማጋ ኮቶኮኒያ ኮካላ ኣዲኮታ ኮኪ ባዳታና ሹታታና ሊሱማ ኬላና ኮሺመ፡፡ ወይናሙ ቴማ ኦሮንዳ ኮሸመማሲ ኣዲካላ ኢሲ ኢኖ ኩቡኪ ጋዳታ ሱማ ቦባ ኬካላ ኮሲ ሚንዳሙ ኪቢን ጎሻሰ፡፡ ታማጋ ካፉ ኢቢማ ኪፉኪ ካፌና ሳከደ፡፡ ካፌና ሰከዳ፣ ሳካዳ ሳካዳ ሱማ ቦባ ሳካሱናሲ ሾሱመ፡፡ ኢቢን ጎሻ ሱኖ ከዲየ ኦሌኬ፡፡ ኮዲየ ኦሎማለሙ ታማጋሲ ቡቢየ አቢንኪ ባዲያላ ፋዳ ኮማ ኮካናሲ ጎማቶንከ፡፡ ጎማቲያ ታማጋሲ ካያ ፋዲንኪ ቶማላ ካቾ ካኟንኪ ፋከለ ኡዳ ኮተኖ ፍኬለ ቶማ ለንኬ፡፡ ታማጋ ጎን ኮሺኖ ኡኩኖ ኤቦኬ ኣወኪ ላካሙ ካሊኪ ፉን ካቱኪ ኤኟ ዲታ አከዳሙ ወይማ ኪረሙ ኢካንድላ ኪሚንቿው አኟኚኖ ሱማላ ማሊሙንኪ ኣማናቶ ንኪ ላካ ኪራሙ ኮሊኪ ቶሞታ ፋን ኮቱማ ላካሙ ኮሊማ ኪሻማ ሳበታሲ ቶሞማ ላኮሲ አሚንቿ ፋሱኖ ኤጂ ኪባታኬ፡፡

(አቶ ግደይ ቱርኳ፣ 13/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሰባት

ኣሚላላ ሞርካተ ኣኟደየዳ ኮሰደየዳ ኟዳ ጋንሚሚማ ላ ዋገለለ ሚላኬ፡፡ ሚለማ ኦኪቶላ ሱኳ ካበራ ሞኮሰማ ባደለሙ ጎማታ ሙቱኬ፡፡ ጎማቲዮማ ኪመ ባረኛ ኮዳመ ካሳኪ ኣዳ ክርስትያና ካሰንኪ ጎማቶንኬ፡፡ ጎማቲየ ኮካላ ባረየ ኣማናቶኪ ኪርስትያና ሚሳኪ ወይንየን ሞከሴ፡፡ ኪርስቲያና ካሰማማ ሺጊዳቻ ኩቺያ ካኟኒ ኣይኒኚዳሙ ካየማ ዲታ ዳሙ ኻላ ሙዋኬ፡፡ አኬዳሙ ጋን ወይንዮም ሞካሺማ ኣመለላ ኮሻን ኪ ጋን ሚሚማ ኣሙሳ ኣቻ ሾንኬ፡፡ ሚኟናሲ ኪሪስትያና ሚሽማ ሳባታሲ ዋካሙ ሚንቲኪ ሚዊኪ ጋዳታማ ሳላንጋ ላይዳሙ ኣሱጓ ኮላኪ ኣሙሰማ ጊራላ ኩቱኪ ኢዊኖ ዋማንኪ ፊንኪ ላጋ ጌራ ሚሚማላ ሰላንጋ ሞርካሲ ኢኪዳኪ ኢምበናይ ኣሱጓኟ ለንናውኬኖ ናይኪ ናኪናውኟማ ኣሲ ላካዳሙ ናውሲ ሞርካሲ ኦሲ ኪዊኪጋሰ፡፡ ሞርካ ሳለንጎማ ኣይታጋሱማ ኪሻምዋ ኢታኪ ኡኑና ዳገላለሙ ሞጎሲ ኢማ ሳላንጋ አሙሳንዳ አቾማ ኪንኮሺኖ ሾሲ ኦምበናይ ኣይጊሚን ጎኖ ኪመ ኪርስቲያንመመበ፡፡ ካላሰ ኣተማለሙ ኣባተ ኤናተ

ካከሳለዳከማ ኣበ ክርስትያና ማ ኣባታ ዳጊኦመ ሲ ኣዊኪ ጋሰ፡፡  ሳላንጋ ኣሙሳ ቻኛ ኢንኩቡኪ ጋን ኢሎን ኮሺማ ሞርኳ ኣይኒይዳሙ ኣሙሳ ኪያኪ ኢንከሺኖ ኢንቲከ ኡኑታ ዳጊን ኪኪ ላካሲ ኣኮሴ፡፡ ኢምቦናይ ዋ ኣፍሪኖማ ኒቻኖ ኡኩበ ኣ ኣፋረናማ ኪቻ ዳቡ ኪካይለኖ ሞሪካ ቻዳ ሱኑኬማ ኣዋቻ ሱኖ ኢኪ ኢቻኖ ሞከነኪ ኤላሙ ጋንኬ፡፡

(ኣቶ ግደይ ቱርኳ፣ 13/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ስምንት

ኣውንጋተ ሳላንጋተ ኮሻ ሚሚከ፡፡ ኦማንኪሙ ኣውንጋ ቡታሾሱኖ ሳላንጋ ሳንደ ሾሰ፡፡ ኦማንኪሙ ሳላንጋ ኣውንጋ ሲ ኣዋሙ ጋፋዲ ኢንቲ ኤቻ ኣፋራ ኣንደ ኪናካሲ ባዶሲ ኪያኖ ቡንቻፈሱኖ ኣውንጋ ማሊሙ ኪፈከኖ ጋፉንከ፡፡ ኢደ ኣውንጋ ኢታ ፋሻ ሹሱኖ ሳላንጋ ዳሻ ሸሰ፡፡ ኢደ ኣዋሙ ጋፋዲ ኣባ ኳ ባየ ኦሎያ ኣለሙ፣ ኣላሙ ዶሙያ ኣላሙናሳና ዳኮ ኣና ኢካለሙ ኒሺሺኖሱኖ ኢደ ጋፉንከ፡፡ ኢደ ኣዉንጋ ኣንጄራ ሾሱኖ ሳላን ኣይታራደ ሰሰ ኢታሙና ኣዋሙ ጋፋዲ ሱኖ ጋፉንኬ፡፡ ኮማልዳላ ኣዋደ ሳላንጋ ቡቶማ ኪተኪቻኖ ኣዉንጋሲ ሞካዮኪ ኢያ ፋሱኖ ኡሱከ፡፡

(ወ.ሮ ኣብርሀት ቱላ፣ 22/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ዘጠኝ

ኬ ባረ ፉጉራመ ጎን ሚናኬ፡፡ ሱኳ ካስካላ ሙኙኛታ ዳታ ኮሺመ፡፡ ኢሻዲታ ሙኙኛሞማ ቡቢያ ኢመሲ ናፎን ኪሾመ፡፡ ኣመለላላ ኢመንኪ ኤሎማ ኢኪዳኪ ላጋ ጌራንኪ ፈደኪ ሳኖዳቻ ቡቢያ ኣኙኞካ ኢደ ካኙኛማ ዳቶማ ቡቢያ ናፎን ካሰና ኩኬ፡፡ ወይናሙ ሚለና ካማኒያ ማይዳን ዳኮ ኣኮሳምበ ሲ ኮዲያሲ ኮኬላከ፡፡ ኮዲዮማ ታጋመላና ኮሹመ ዳኮ ኣይ ካማኑሙ ማይዲኖሲ ከፊያሲ ኮኬላኬ፡፡ኮድያ ሱኳ ካላ ኣኙኛማ ናፉስና ኩኬማ ኪሻማሳባታሲ ቡራ ካሳኪ ታቢላ ቱዳኪ ኬ ካያ ካፋኪ ሸዳ ኣንዳሙ ሹዲሙ ናፎን ካሳያዳታ ኣ ሱኳ ካላ ሚናሙ ሻንካ ሶኒ ናኪ ለዋናኬ ዳኮ ኣማ ማይዳምበሰ፡፡ ከዲያ ጎጎደሙ ማይዳ ኣንዳ ፋሻ ለዋኑኬማ ኣረ ካሚኪ ካያ ካፉሩ ሱኖ ሞከቢንኪ ሱካንኪ ሚሻኪ ለጋ ጌራ ሚሚኪ ሱባ ኣንዲካታላ ኤለሞሰ ኦኮሺማለ ቱንኪ ጎንሞኮሲማ ኬላ ላጋ ገራለሙ ኣርኩባሲ ኣጉሲ ኢሻኖ ሚንተከ፡፡ ኢመንኪ ኤሎማ ኤቦ ዋማኒ ኳ ኣረኩባሲ ኣጉሲ ኢሽረኩ ዳኮ ኢኬዳሙ ኣረኩበንኪ ካለኪ ካያ ካፉሩሰ፡፡ ኣለሎማና ማሊሙ ዳኮ ኢንከዲ፡፡ ኮናላ ቱኳ ካይነመ ጌጋጆና ካይነሙ ኣይካማኒሙ ማይዲኖሲ ኮደያሲ ኢኪሺ ኪሾማላ ላዋዳሙ ለዋደካንኪ ባረየ ዳጊጋታ ዳሚንክሸ ጋይን ለዋማለሙ ኢመንኪ ኤለላ ኤቦ ኤቦ ኣባ ዳተላ ላዋናካሜ ኢሻኒሻ ና ፉያዳካሲ ኣኬሲ ኡዳኬ፡፡ ኤና ኣ ኤለንዳማ

ኦረኮማላ ኒሺዳሙ ሴሳ ናታናውላኪ ታቢሎሲ ናይኪ ናቡለ ጋገናሳኪ ናምቢ ናኮሺሙ ኦያ ኮኬሊታ ሻሲኒኖ ኮኬለሙ ማሳማተ ማምኖ ኮላላ ባዲ እያ ፋሱኖ ታጋሞናኪ ናቡላ ናሳ ጎናኬ ናያ ኳ ኪሻ ኳ ኣበለሲ ኢዊ ሻሱኒኖ አርኩባሲ ቸሲ ኣባተ ኮኪ ኤሳናማ ኣባተ ኮኪ ናቡላ ኬሳኪሺያ ኤና አዋሙ ካያፋዲኪ ሽዶማ ካፋካካ ሲ ኡደኬ፡፡ ከዲያ ኣማና ሚሊሙ ኦደኬማሊ ኡደሞማ ሻኒ ኤለንደ ኦረኮማላ ኒሺሱኖ ኮዲዮማ ሴሰ ኢታ ኮለኪ ዋ ኡደሞማ ሻኒ ኪሚኖ ኳንደ አረኩቢኖማ አኪ ኣ ኣሚኖ ኤለካለ ባ ነሳ ጎኖ ሲ ኮኬላከ፡፡ ኣኙኞማ ኤቦ ማሳማተ ኣዳ ማሺኪ ኢታጋዳሙ ማሞሞማ ኮላላ ባዳ ኢያፋሱኑ ታጋሞናኪ ናቡላ ናሳ ጎናከሰ ኢምባሙ ኪሳሳኬ፡፡ ኣርኩባ ኣይኒያ ኣርኩባሲ ቸሲ ኣይታጋሚ ሾነሲ ናቡላ ኣሳላ ኩዋኬ፡፡ ናቡላ ኣተን መሳጎማላ ኳንዳ አቸንደ ኒሺሱሞማ ፌሲ ኦናኩኬ፡፡ ከዲያንዳ ናቡላ ኣሳሶማ አተን ማረሲ ኮደያታ ሊንኮሺኖ ኦና ኩኩማለሙ ኣርኩባ ኣይኒያሲ ኢኪዳኖ ዎ ሱኖ ኳ ኣቻ (ብርሃነ ኬኞ፣ 15/05/2009 ዓ.ም) ኣንዳ ካዊ ጎደያ በያኖ ኣው ኡያ ኡዋናኖ ናይኪ ሰላታ ናቱኪ ናውኟማ ኤሳኮሺሙ ናውሲ ኮከላማላ ኣረኩባ ኣይኒያ ማሊሙማ ያኪ ኢንቲኪ ኣዋሲ ኢሳሚኖ ኢማላ ኮዲዮሲ ሻማ ዳሙ ኤቦ...አቦ.. ፌደ ኣሚኖ ኒሺንጉኩኖ ሻ ፊዳሙ ኮሲ ካያፋዲዶሱማ ኮዲዮማ ኣቲለ ፌደ ኩኬ፡፡ ኢኪሺኪ ባዳባዳሲ ኪኮዳማና ኡኬ፡፡ ኮማልደላ ሴሳንዳ ኢታኮሺማ ሸሸማ ኬተኪ ሊሱማ ኮዲዮማ ማሊሙ ኩቺኪ ኣልባካኩዳ ኪሻኬ፡፡ ወይናቡ ኮዲዮማ ፋካሮሲ ዋ አረኩባ ኣይኒያሲ ኤቦ... ኤቦ... ኮዳኟማ መለሙንኪ ኣታሙ ኣንዳ ኩቺኬማ ናቡሎማ ማይዳመ ሳዳኪ ኤሳሴ፡፡

(ብርሃነ ኬኞ፣ 15/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስር

ኣሚላላ ቢሺባበ ቢሺያ ኪኪ ቡተ ለይሲ ኢቦ ኮሰ፡፡ ኣተርባለና ታረባሲ ጋንኪታኪ ዋ ቢሻባበ ኮሺማ ዋጎማ ኪማ ኮፋልኪሻኪ ዋ ቢሺባባ ኮሺማ ከሮሲ ኡለንደ ሴለላ ጎሲ ሳኬን ኪኬ፡፡ ሳኬን ኪኮሲ ፌሲ ጋሱማለ ጀቢያንኪሙ ኣልፊ ባረ ሸዳ ሴሎሲ ዱሱኖ ኢዊኪ ጋሴ፡፡ ቢሻባባ ኢቦ ኮሲ ኡኑና ዳማዳ ሳኬን ናካኟሲ ኢማ ኣለፌ ባረ ሸዳ ሸሰ፡፡ ኢኬለማ ኣለፌ ባራኖ ኣይኬ ኢኮፋሴኖሲ ኢቢን ኪኪ ጎንኪሽማ ሸዳ ኣይኒያ ኦኪ ኤባ ሸደን ዳኮ ኒንቲቦ ሲኮኬላኬ፡፡ ቢሺባበ ኤ ኣይነ ሸናኪ ናሺኖ ናኪ ናፋራ ናኮሶ ኤኝ ኪሻያ ዬካሲ ኢሶኬ፡፡ ኣተረቦማ ኢኬላማ አለፊ በረኖ ሸደኟ አለፊ ሳተ ለኪን ኣሾዳየ ኣለፊ ባረማ ዋ ኣለፊሎማ ኤና ኑኟኢ ኣሶ ኦና ኑኟታ ኪሻያ ዮካሲ ኣቾኛከ ሲ ሃደደሰ፡፡ ቢሺባባ ኣባ ናካመ፡፡ ኣኙኛ ናንቲመ፡፡ ወይናሙ ኣባ ናውኞመሰ፡፡ ኣተርባና ኤና ኑኛኬ ሱኖ ሻሮማላ ኮማልዳላ ባነታ ካሚንኪ ሞከቢንኪ ባነላ ሚሚኬ፡፡ ባኖማ ኣይኤሚኖሲ

ኮኬላማለና ታጋመያ ኤሊዳሙ ኮኪ ዳጊሙ ሱማለሙ ኣተርባንዳ ኢሺታ ሰዶማ ኣከሲ ኡዳኬ፡፡ ኣባ ኣተርባ ናካቻናኪ ኤላንዳ ሰላላ ኒሺን ናኮሲ ፊናኪ ጋናማላ ጀባቻንኪ ሾዳ ኣለፊ ሸበ ሳተ ኦባል ኮሳኖ ኣ ቢሺባባማ ናውሲ ኣለፊሎማ ናውሲ ኡችማኪ ኣለፊ ባረኮ ሲ ኣካይሎኖ ኦማ ኒቢን ካሰቻ ሰናኬ ሲ ባናሲ ኢሳካኬ፡፡ ባና ኢኪሺኪ ቢሺባባሲና ኤቻ ኩዳካሲ ኮኬላኬ፡፡ ቢሺባባ ኣርድያለሙ ኣባ ሳናቻ ቢሺባባ፡፡ ቢሻናይኪ ናቦ ኖኮሲ ቡተ ናኮቢሺኪ ዳማደ ሳኬን ናካቻ ናኪ ሰላንዳ ኮሺኖ ናይማ ኣላፊ ባረ ኦላ ኮሺኖ ሾናኬ፡፡ ወይናሙ ኳ ፋን ጋሰ ናኪ ኦያ ኢካናማ ናኪ አሰካ ጎን ናኮሺ ማ ኣ ኣተረባማ ዬኪ ሾዳ ፋናኬ ዳኮ ኒቲበ ሱኖ ኤ አይነማ ኤቻ ኪሻያ ኢካ ናኖ ኦኬላ ኪንቲኪ ሾደኘ ኣላፊ ሳተሰ፡፡ ኣባ ናውናማ ኣለፊ ባረ ወይናሙ ኣባ ኣለፊ ባረ ዲታ ኣለፊ ሳተ ናንቲ ናንቲመ ናኖ ባነታ ካሚ ሱኖ ማከቢን ማሞኬሲ ኣውሪያ ኢማልኬ፡፡ ባኖማ ባረያ ኣውራ ፋያሱማ ባዳለሙ ባረየሲ ኣባ ናኒቢሻቻ መሞከለ ሱኖ ባረየ ኤንኬ፡፡ ወይናሙ ባረየ ኣውራ ናቲኬ ኣባ ናሱሱጓ ኣውራ ኮሺያ ኤና ኣተረባ ሙጀ ሳተ ኒባልፋኑኬ ኤና ቢሺባባ ኣልፊ ባሮኬ ሾኑኬ ወይናሙ ኤናደ አለፊ ሳተ ኣይኒያ አለፊ ሳተ ሾሱማ ኳ ዬሙ ካቢኒናታ ጋደ ኣ ኣለፊ ባረየ ኤኘመማ ኤናዳ ቢሺባበ ኣልፊ ባረ ክባል ፋሱማ ኳ ዬናታ ሾዳየ ኤናተ ጎን ከሺሲ ኢቢሸቻ ኣማማ ጋሙሱኖ ኢኻታ ሰዳ ኣተረቦማ ሾዲያንደ ኣለፊ ባረየና ዳውሲ ኢጋሰሰ፡፡

(ኡቶ ሳህለ ገራሪ 20/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ አንድ

ኣሺ ላጋላ ኣቢና ሺጊደ ባና ጎኪናከ፡፡ ኦማንኪሙ ውየላ ሺጊዳየ ቡቢየሲ ኪቻቻ ላዋሰ፡፡ ኦማንኪሙ ቶካ ካቶካሲ ኢቲያላ ኒሺሱኖ ኪዳ ኮሲማየሲ ጋ ኪቻካ፡፡ ኦማንኪሙ ሳላንጋ ኣቢና ቶካ ኪቶኮዳ ካቲከ ኪዳንኪ ኦዋኮሊመ ኦደቲያ ኦለ ላካንከ፡፡ ሃላታ አይናሻ ሊካሙሙ ኣባናይኪ ናታላሊቻማ ሲ ሻ ገራ ኪኪ ኢኪ ኢለንከሚኖ ኢምቦነ ሱኖ ቶካካቶከማ ኡዋ ካውኪ ኣንቲ ሱኖ ሳላንጋ ገራሲሙ ላካሲ ሸማሙ ቱሲ ኣማ ኡላ ኣንደ ኣውዋ ሱቲ ሲ ኢደጋሰ፡፡

(ኡቶ ገብረሚካኤል ገራሬ፣ 17/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ሁለት

አመላላ ኣዳ ሰሰነ ቡቢየ ኦኮቡቡረኪ ባና ሞርካ ኮላኬ፡፡ ኣላ ሳላንጋሲ ኣንዳ ኮኬ፡፡ ኢያፋሙቻ ሰንኬ፡፡ ዋ ሳላንጋሲ ኣንዳ ኮኩማ ሰሰናየንኪ ጋበላተ ቶጊላተ ደያ፡፡ ኣመለላ ጋበላተ ቶጊላተ ባርየ ጎማቶንኪ ሞርካሲ ሚኪዳኪ ኣሳላጋማ ሳና ኣንዳ ኪታኬ ደያ ኤና ኣማ ቡቢያ ታጋማኖ ዊን ከዊ ደራሱማማ ማይዳምበ ኢከነኪ ሚኬላኬ፡፡ ሞርካ ኢካሚሊ

ሳኒ ኪታኪ ኣዊ ጎሲኖሲ ኮኬሎሲ ኮኬለሙ ኪኪሺኬ፡፡ ጋብላተ ቶጊላታ ኣ ሳላንገማ ኣሱን ኣንጻ ኪለና ዲያ ኤናሲ ገበደያ ኒሻማ ዋሙ ኮንቲጎሱ ዊን ከዊኖ ኦታ ኤለ ጎሶ ንኪ ሚሳሳኬ ሞርካ ማይዳ ካሳሳኬማ ለካሙሙ ኦለሲ ኣሰንጋ ቶኮቶኮሲ ጋሰ፡፡ ሳላንጋ ኢሮን ኮሲማ ዮማ ሞርካ አኪዳከ ኣዋሰ፡፡ ሳላንጋ ኣጃሙ ኪማ ኣሚኖ ኤና ኣሱን ሱሳ ኒተከሚያ ኣሚና ኣዊኖ ኦታ ኣለ ጎሱኖሲ ኮኬላከ፡፡ ሳላንጋ ማሊሙ ኮዳኬ ኣባ ኣሱጋ ኣንዳ ናለና ለኪን ዳታ ናይመ ኣሱጎማ ናለና ኣጋለተ ኪረተ ናይናመሰ፡፡ ሞርካ ኢኪሺኪ ኣጋላተ ኪረተ ኢካንኪ ኒኮ ኑሱ ኒናኖሲ ኮኬላኬ፡፡ ሳላንጋ ኣውሮማ ናኪመ መዳማ ኢተኬቲኖ ኣከሴ ኣባ ኣሱን ነሱኖማ ቶጊላ ኣጋለሙና ጋባላ ሳርታሙና ደያ አሱን ናለና ወይናሙ ኣየ ኒኮካሰያ ኣታሙ ናሱ ናሰናሴ፡፡ ወይናሙ ሞርካ ኣማ ታጋማ ኮሺመሲ ጋባሎተ ቶጊሎተሲ ኢያፋሲ ኣጋላተ ሳርታተ ኮኪሰኬ፡፡ ሳላንጋ ኣንዳ ጎጎሲ ኢጋሎተ ሳረቶረ ኣካኪ .... ኪኪኩኙ ማኪ አደኮኪ ሞርካሲ አሱን ናሱቻ ናኪ ናይኖ ዋ ኣደኮላ ኳከ ኤናሻኒ ቢያ ኮላ ጎሲ ቢያ ኒኪኒሳ ከላኖ ናውኬሲ ኢሳሳ ሞርካ ናኖ ኤናስኮ አከሲ ኮላናሻ ኣረሙ ካሚ ሲ ሚማማ ላ ሞርካሲ ካሚያ ባታ ከበታ ከበኒናማ ሰለካዶካ ሰለካ ኑያ አቢኒ ሴ ጎማቶሰ፡፡ ሞርካ ማሊሙ ኪፋኪ ዋካ ሚሚማ ኣደኮታ ሰለካ ሱማ ሰሊያ ኪንቲኪ አበን ዱሱኖ አላ ኪያፋሲ ጋሴ፡፡

(አቶ ገብረሚካኤል ገራሬ፣ 17/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ሶስት

ውየላላ ሞካተ ኣውንተ ታቢላላ ሚለኖ ሞካ ኣውንሲ ናኖ ኪደያ ሲ ኮከላከ፡፡ ኣውን ኣባ ኪዳቻ ኣውንን  ደያ ሲ ኢኪሺኪሶከ፡፡ ሞካ ኢደ ኮኮሻሙ ከሸራሻደ ኖኮሚነከ ዳኮ ኢኪታና ኢከዳሙና ወይንዮኑ? አኮሲ ኮከላከ፡፡ አውን ኣባ ወይኖዳቻ ኳ ዳሙ ኮተከማ ኮሺታ ኣዳማተ ወይንናናሲ ኢኪሺ ኪሾከ፡፡ ሞካ ኣዳሙሲ ዋይያ ፊሪ ሲ ኣባ ሞካንኪ ዲኪሚኒናዳታተ ኣለካ? ሱኖ ታቢሊያ ሚኪ ኣኒጋንከ፡፡ አውን ታቢሊያ ኣያ ኣባመ ኳንደያ ኣዳማ፡፡ ኪ....ጋ ሙዳሞኮሺኖ ኳተ ጋጂባሙ ኮኮለከ፡፡ ኦማንኪ ሞካ ሳካማሙ ኪታቢኪ ኖ አውን ሊዳ ኣባ ሞካ ኣምሲ ላጋሲ ናፋኪ ናፋንፋራቻማ ሲ ኣበዳሙ ኪከ፡፡ ኳ ታጊማ ኣዮኮማሙ ዳጊያላ ኮሺማ አላላ አጂኪ ኣጉሰ፡፡ ሞካ አላ አጉዳ ኢካይሎኖ ኣላ ኦኮማላ ጎ ኪፋራከ፡፡ ኮፋራ ፋው ኪያማለሙ ኮፋኪ ኮታቢያሙ ኣቶዳ ኢያከ፡፡ ኳታጊማ ሾዳሙ ኪራ ሺሻዳዲና መናላ ኩቱኪ አሎተ ኪለከ፡፡ ኣማንኪ ሞካ ኣቶዲያንኪ ታርጋሲ ፊሱማለሙ ኪራንዳ መኒያላ ኮሺሞማ ኒሻሲ ኢካላከ፡፡ ኣማንኪሙ ሞካ ኣውን! ኣውን! ኣውን! ኣዳዳ! ኣዳዳ! ሲ ኣውሰ፡፡ ኣውን ኣዳናኒ ሰ፡፡ ኣውን ኣታሙበ ኣውን! ዳ ኪዳ? ኣሺድያ ናውዳምበ ኳ ታጊማ ናምበ ሲ ኳታ ኪደ ጋሰ፡፡

(መምህርት አስመረት ሰለሞን፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ አራት

ዳዳላ ኪኪሽ ሻተ ዳኮ ኪመኬ። ዶዶማ ቡቡየሲ ኪመና። አተማ ኪኪሽሎተ ሰላሲ ኣባርሞተ ዋማ ደቡሪ ዋ ኣሰቶተ ጋሲ ቡቢየሲ ደኒሰላ ኪመና። አኬዳሙ ወየ ኪኪ ቴራ ኪካማለሙ ሱኳ አጋረ ማላ ኩቴኬ። ዳደማ ሃለታ አይኖዳ ፋካራና አውረያ ኟዳና አ ሚኒ ካሚኒኖ ሻ ኣረሙ ካሊኪ ካኬላ ኪመላ ና ኒመኖ ዳኪ ካኬላንኪ ጎማቶንኬ ጎማቲያ ኮካለ ኦሊኪ ዳዳሲ ኦኮዳኪ ኤና ቡበሻሲ ካመከዳ ማቲኬ። ወይናሙ ታማ ሃደራ ኮኬላ ማኬለኟማ ኢኪሺ ካሰንኬ። ዳደ ኤደሳ ኪሰኬ። ጎማቲያ ኮከላ ኣመዳ ሳታያንኪ ና ኒመኖንኪ ኦኬላኬ። ኡኑ ካሺደያ ኪሾናሲ ኣኒሙ ኪሚን ኮሺማ ዳታ ኤኪሲ ዋማሙ ኪኮሺ ኮሳኬ። ዳቶማ ኣናላ ቡቢያሲ ሳሳ ጀንሰላ ኪታ ኪሽ ኪሽኬ ወይናሙ ካሺደያ አኬሰ። ኣባ አንዳ ናመሞማ ዋ ኣሚላላ ሱሳ ቢባ ናታናሶሞማ ዲያ ሱኖ ኪኪሻንዳ ሳታየ ኡፊያላ ኣበ ኪታካሰከኖ ኣበ ካመከ ኣባ ከመከ ዳሙ ጋንኬሰ።

(ሚኪኤሎ ጆቦ፣ 19/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ አምስት

ኦማንኪሙ ሳላንጋ ኟ ኪኮ ኪዶኪ ጋሰ። ኦማንኪሙ ኢታ ባዲያሊሙ ኮኪ ሻሎማ ጋኪኪ ጋሲ ኢኮይሎከ። ሳላንጋ አንዳ አዱሙሲ ወየላ ሳላንጋ አማሲ ኢኪዳሙ ናቢኒ ሲ ላዋሰ። ኦማንኪሙ ኟ ኢከኪዶኪ ለይሰ። ኤታ ኣሺ ኮካላሲ ኟ ኪካኟ ኮኪ ኡዋኖ ሳላንጋ ኢቢኒከ። ኦማንኪሙ ሳላንጋ አቶሊ ኢኪዳሙ ናየሙ ሹ ስካሰሲ ኮከለከ። ኤታ ሳላንጋሲ ፎፎጋለሙኮ ኣፊታመ ዲታ ቶማላ ኪሻያና ካቱ ሲ ደጋሰ። ኦማንኪሙ ሳላንጋ ማሊድያ ኪፊከኪኡኑ ኢኪሞማ ኩዳከሲ ኢኪኪ ቶላ/ፎፎጋሰሙ/ ኪፊታኖ ኤታ ኣካካኪ ኢዋሊ ፊተተ ጋሰ።

(አቶ ግደይ ዮሐንስ፣ 23/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ስድስት

ፋነካላለ ቡተ ሳተ ሳማሙ ወይኖኮይነከ ቡታየ ሻኪተየ ኣራ፣ ቢባ፣ ኡማና ዳያ ኢና በቡታናየ ስማሪየማሙ ኣባያሾሲ ዳረሱታ ፋናከ ገራ ወይኖከ። ዉለላ አውንጋ ላዋሲ አ ቡተየሲ ኣከዳሙ ናሚንኪ ናያናኟሲ ላውሱማላ ቡታየታ ኪኪ ኢኒቲማ ስመረየሙ ባይሲ ዳረሰሙ ኮይለኪፋናካ ገራ ኮፋራማ ባዳለሙ ውየላላ ኢኪ ቡታ ቢቦተ ኡመቶሲ ኢኪዳኪ

አመመ ገሪሱመ ሞኮንቲኒ ለኪነ ኣባበታ ኣራንደ ኮዳያማ ገራሲሙ ጋንኮንቲኪማ ኣመሙ ዶረ ኣነኪሙ ዳሙ ዲታ ባያሻሙ ቻማ ሱማለ በተኡመተ ቢበተ ማሲድያ ሚፋኪ ቡታ ኣሮሲ ሚኪዳኪ ኣመ ኣናሙ ባያሸማቻማ ኣማመንኪ ዳዳ ኢኮማላ ቡታ ኣሮማ ሃይ ዳዲመ አኮሲ ዳጋሰ ዲታ ኮዳዮማመ መከኖ ቡታ ኣሮማ ዳሲ ኢንጋሌያ ወይኖዳ ኪቢማ አውነጎማ ኢኪ ኣያኪኚከ፡፡ አማንኪ ኢዳ ዳማደ ጎንኮሺማ አኑመ ቡታ ኣሞሲ ኢኪዳኪ ኣና ኩሉደንደ ንኮማንከ ኖኮንቲነ ላኪን ኮዳያንደ ቢባማ ገረሰሙ ጋንኮንቲ ኖ ኣባና ኣኑ ናንቲኪ ናውከማ ኣኑመ ባያ ሸኑ ቻማ ዶረ ኣኑኪሙ ዳዳ ሱማለ ቡታ ቢቦማ ማሊዶያ ኪፋኪ ኮዲያሲ ኢኪዲኪ ኣባ ኣነሙ ባያ ሸኖ ቻማ ኣናና ውለያሙ ኪተከ ኣባና ኩለቻ ናተከ ቻማስማለሙ በታ ኡሞማ ሃይዳዲመ ኢኮሳ ኣታሙና ቡታ ኣሮሙዳ ዳጋ ሱማ ቡታ ቢቦማ ኡኩኖ ዳሙኖ ቡታ ቢቦሲ ኣያኪነኪንኪ እዶ ውየ ባረ ጎሱማ ቡታ ኡሞሲና ኪያኪኻኪ እደ ኢመንደ፡፡

(አቶ ግደይ ዮሐንስ፣ 23/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ሰባት

ኳ ኡማሎኮ ኮንታለ ማሳ ባቻ ኮሊኪ ጋንኪ ኦሉማ ውያ እንዳ ኮላኖ ኣረ ስላላ ዳማዳ ጎዲሙ ሺሱሙ ፈንካቢቼንኪ አሉኪ ኣሳ ስላላ ኒኚኮኮሺማ ሺማላንዲታ ኩቱኪ ኣሳ ከለኖዱሲ ኢያማ ፈሙ ኦሎከማኪ ፈንኪ ጋንኮቢቼ ኮኮሺማ ኢመንኪ ኣሳሲ ዋ ኩንዳሲ ከያኖ ዋቾሊ ዲና ሉሲማ ኢመቢላለ ጋንኮቢችኖ ኢንቲከ ኣቦከ ላካሙ ኪመቢላላ ጋንካበቼከማ ለካሙ ኣኮሱማ ጋዳ ኣና ኣይላኖ ካይሎከማ ኦኮሙኖ ዋ ሉሱሞማ ኢዊከጇኪጋስስ፡፡

(ወ.ሮ አብርሀት ቱላ፣ 22/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ስምንት

ጎሞኮሺማ ዳካ ላይዳ ኣቢሻ ኮቶንኮንኪ ዱማ ኩከሰ ማኣቢሻ ኣዳካቻማኮ ኣይኢሚኖ ዱማ ኡኩኖ ሲ ኣኪሱ ኖ ኣኩኖ ናሹላ ፋዳታ ናይካ ኳ ኢተማባ ኣይኢሚኖሻሲ ሹላፋደታ ኪከ፡፡ ሹላፋደ ኣይኢሚኖ ኖኖ? ኣኮሱማ ኣይያ ዳርካኮ ዱማ ኢሳና ኮሺሚያ ኣቢሻ ካስላታ ሉሱቦሻ ዱማ ኩከሱማለ ሹላ ፋደማ ዶሪኮ ኣዱበታ ፋጊዳ ኪናኪ ፋገሲ ኮተ ሱኖ ኮተከ፣ ኮፍቻ ሱኖ ኮፋቻከ፣ ወይዳ ኮቱ ሱኖ ወይንኮቱከ፣ ሱጉዳ ካዋሱኖ ስጉ ኮኑ ሚቻኖ ዮ ኣዶራማ ኣኪኪ ዳከያተ ጎሙሙ አከዳ ኩዳሙ አተከቻሙ ታማ ኣና ሳነያታ ጋደ ኣይኒያከ ኳ ከናያ አቢኒናማሲ ሹለ ፋደማ ኢሲሳኖ ኢኪ ዳኪያተ ጎሙ ፋገሲ ኮተ ሱኖ ኮተከ፣ ኮፍቻስኖ ኮፊቻከ፣ ዋይዳ ኮቱ ሱኖ ወይነከቱከ፣ ስጉዳ ካዋ ሱኖ ስጉንኪ ሚቻኖ አቢሻ ኢዊኪ ሳኒያጋሰ፡፡

አቢሻ ሳና ጋሱማ ላይዳ አቢሻ ኢኖ ዳካተ ኒኺኪ ሰዱያምኮሚ ካኖ ኡጉንጉየ ጎያሚ ዳኮማ ፋገሲ ኮተሱኖ ኮተከ፣ ኮፍቻሱኖ ኮፍቻከ፣ ወይዳኮቱሱኖ ወይንኮቱከ፡፡ ሱጉዳካዋ ሱማ ኡከ፡፡ አኩኖ ዳካ አጉንጉያ ኪኪ ስጉናኝሲ ቲሞዳታ ካፋሱማ ዳካሲ ኦሲ ኪብንጎኻሳ ኣቢሻና አጉንጉያ ኪኪ ዳኮታ ኪማ ኣኑሱና ኪበንጎንኻሱኖ አሰጋሙ ላካሞኮሺማ ዳኪሻላ ቶማናካኝሲ ኢማ ማሎካ ኩቱኖ ናኖላኝሲ ኢማ ዳኪሽሲና ኪቢንጎኻሱኖ ኦሲጋሙ ላካንኮኮሺኖ አቢሽያ ሻዲያ ሳና ዮኪ ሉሱማ ዳካተ አቢሻ ኡጉንጉየ ጋሙ ላካኖሺኖ ዮኪ አንቲኪ ኣዳ ኪዳ ኪኪ ቢቢላ ታይታ ኪተኪኮ ዳካላዉ ኩቱኖ ቶፌሲ አጃጋሱኖ ኣቢሻ ላውኩቱኖ ቶፌሲ ኣጁ ጋሱኖ ዳኪሽሲ ፋጊሲ ሳካዳ ሱኖ ሳካሱኖ ዳካተ ኣቢሻ ኦማንኪ ጋባላ ምኮፈገደሞማ ኦማንኪከ፡፡

(አቶ ኮንታለ ሊጋ፣ 11/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት አስራ ዘጠኝ

ሊላ ኩዋኖ አቢሻ ቢሻ ኪኪ
ቢሻ ኪቦኮሺኖ ዳካ ኣቢሺታ ኪኪ
ካውንቲጊና ካኖ ኦኮሱኖ
ኣቢሻና ኮሻኮሺያ ካኖ ኣኮስኖ
ካው ቲጊኪኪኖ ሚኖከሰ፡፡

(አቶ ኮንታለ ሊጋ፣ 11/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ

ቢሻ ሚሚኪ ኣኮታ ስና ሚማሞኮሺማ ላሽ ኢኪ ኣኮታ ጋንኪኝኖ ኦኮማ ኢንቲኪ ኣባሲ ላሻ ኣኮታ ኝደላ ሱኖ ኢያዶ ኣኮሱኖ ኣሰ አክሱማ ላሾማ ኣሱኑ መሙ ናኝ አኮሱኖ ኣሰ አኮሱኖ ኣሳኑመሙ ናኝ አኮሱኖ ኣባሲ ላሻ አከሱ ኢዋና ኣሰ ኣይላሺኖ ኣከሱማ ኣሰትመሙ ናኝ አኮሱኖ ታይታ ኪኪ ኝሽ አኮሱኖ አኩኖ ኝሽ ሱኖ ኣኩኖ ዋመንዲ ኒሚኪኪ ሚተማኻኪ ኣጋሊያሙ ኣፋራተ ሚለሚኪ ኮዲያተ ሚሚና ኣዳ ከሉኪ ኡጋባላ ላይንከ ዲታ ኳ ባየ አሉ ሻሙኖ ኒፉራቶማ ኣመ ኣለማ ኣወ ካያፊሙ ሱኖ ኢሊኪ ኢያፊንከ፡፡

(አቶ ኮንታለ ሊጋ፣ 11/05/2009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ አንድ

ዳካየ ፊላ፣ ቲቲኪሻና ፉላና ሰሰ

ኦማንኪ ኣቢና ኮዲየሲ ኣኪዳኪ ኣረ ኣዳ ጋዲ ኣኮሱኖ ኮዲየተ ኮኮቢንኪ ኣዳ ኮሊኪ ኣዳንኪ ኣደኪ ኢታ ጋንኮሎማ ኢታ ዳጋሲ ዳጋኮሊማ ና ኣባኣሲ ላይናኝማ ኣሊኪ ዳካኝ ሲ ኣቢሺያ ኦታ ኩኙኖ ማዊማሎከ ኣኮንኪ ኣሰሳካ ኢመላ ኢካኖ ማይዳኪምቢ ካስኒሻሲ ኢሳመኖ ኦሊኪ ቲቲኪሻ ኮሳስኖ ኣቢሻኟ ሚንደሊ ኡቹማ ለጋሮሰሰ፣ ፊላ ኮሊ ኮሳሶኖ ሚሚንቸከ ካሳላላ ሚሚንቾካ ካሳላላ ሚ…ሚ ካታካሚሚ ኣኮሱኖ ፉሉ ኮሊ ኮሳሳኖ፣ ኒቦ ካሶኖ ናኟኖ፣ ናሊ ናሶ ኒኟኖ ኢቢሻኟ ሚንዳሊ በላስላለበ ኩካ ስላላበ ኩ…ኩ…ሱኖ ኣቢሺያ ፋያንኮሲ የኪ ቲቲኪሻተ ፊላተሲ ኢሚኪያፋሲ ፉላ ኪከሰ፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ሁለት

ኳየ ኣላ ካሳንዳ፣ ኣላ ሚንዳ ተተራ፣ ኣላ ማካላ ቲራ ስ ጋንኪ ኣደ ኮሊማ ካሳንዶማ ኣላዋ ናላዋናኟኟ ሲ ኣላላ ኣጉሲ ኮፊታኪ ካስሙ ኮያኖ ካሰቱጉሳኖ፣ ሚንደ ተተሮማ ኰ ናሳሳ ኟሲ ኣቺኪኪ ፋጉሲ ኮያኪ ሚናዳ ኮተኖ፣ ማካላ ቲሮማ ቢያ ናኖኟሲ ኢኪ ቢያ ኪኖኖ ማካላ ኢ ፋከኖ ሰቲየ ኣደዳ ኳ ሽሙታ ኮቾኮሰ፡፡

(ወ.ሮ ጅኔ ሃይለስላሴ፣ 23//052009 ዓ.ም)

## ተረት ሃያ ሶስት

